


© መብቱ በሕግ የተከበረ ነው

0912007335

የሽፋን ስዕል ጥበበ ተረፈ

# ምዕራፍ አንድ

1969 ሰኔ ረፋዱ ላይ ሸራቸው የተገለጠ ሁለት የወታደር ማርቸዲስ ካሚዮኖች በቆራሄ አሸዋማ ሜዳ ላይ በመካከለኛ ፍጥነት ይሽከረከራሉ። ካሚዮኖቹ ጀርባ ላይ ያሉት ወታደሮች ሸራ መወጠሪያ ብረቶች ላይ በመደገፍ ፊታቸውን በየአቅጣጫው ዞረው ቆመዋል። የጠመንጃዎቻቸውን አፈሙዞችና አይኖቻቸውን ፊት ለፊት አትኩረው በንቃት ይመለከታሉ።

በአካባቢው የጠላት እንቅስቃሴ እየከፋ በመምጣቱ ማንኛውም ነገር ትኩረትን ይጠይቃል፤ የሞትና የሽረት ወቅትና አካባቢ ነውና። ሜዳው፣ ቁጥቋጦው፣ ሸለቆው፣ ቦዩ . . . በጥንቃቄ እየተፈተሸ መታለፍ አለበት። ከጠላት በድንገት አደጋ ቢጣል ቅጽበታዊ እርምጃ ለመውሰድ ቀልጣፋነት ፣ በቂ ወታደራዊ ትምህርትና መሣሪያ እንደሁም አካባቢውን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። በዚህ ሞያ የተካኑት የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አባሎች በኦጋዴንና በሌላውም አካባቢ ጠላት እያሰረገ የሚልካቸውን ወንበዴዎች አባሮ በመምታት የሰለጠኑ ናቸው። ይህን ሞያቸውን እንኳን ወገን ጠላትም ያምንላቸዋል።

በካሚዮኖቹ ላይ ተሳፍረው የሚጓዙት ወታደሮች እንዲህ ባለው ተግባር ተሰማርተው የቆዩ ናቸው። በተለይ በቆራሄ፣ መረራሌ፣ ሺላቦ፣ ደበወይንና በሌቹም የጠላት እንቅስቃሴ አለ በተባለባቸው አካባቢዎች ሁሉ እየተዘዋወሩ ተልእኮዋቸውን በመፈጸም ላይ ነበሩ። የባሰና አስጊ መስሎ የተገመተ ሌላ ግዳጅ ስላጋጠመ፣ ጠቅላይ ሰፈሩ ቀብሪ ደሃር

የነበረው የ12ኛ ሻለቃ ፈጥኖ ደራሽ መምሪያቸው በአስቸኳይ እንዲመጡ በቴሌግራም ትእዛዝ ያስተላለፈላቸው።

ካሚዮኖቹ በአሸዋማው ሜዳ ላይ እየተምዘገዘጉ፣ ውሃ በቦረቦረው ቦይ ላይ እየዘለሉ፣ ዳገቱን እየቡዋጠጡና ቆንጥሩን እየጣሱ ይሽከረከራሉ። አጋዴን በረሃ ውስጥ በአብዛኛው ቦታ ዝናብ ካልዘነበ የመንገድ ችግር የለም። ስለዚህም በአጫጭር የግራር ዛፎች ፣ እጅብ እጅብ ባሉ የቆንጥር ቁጥቋጦዎች እየተሽሎከለኩ ይጓዛሉ። ለጥ ባለው ሜዳ ላይ በያለበት ተበታትነውና የሚታዩት ኩይሳዎች (የምስጥ ጎጆዎች)፣ ልዩ ልዩ ቅርጾች አሉዋቸው። ቀረብ ተብሎ ምንነታቸው እስኪረጋገጥ ዛፍ፣ ሰው፣ ሌላም ለዓይን እንግዳ የሆነ አውሬ እየመሰሉ ያሳስታሉ።

ካሚዮኖቹ እየሰነጠቁ በሚያልፉባቸው መንገዶች ላይ የሚትጎለጎለው አቡዋራ ከሩቁ ሲታይ ጠሮ ንፋስ (ሽምልምል ነፋስ)፣ ከሚያነሳው አቡዋራ ጋር ይፎካከራል። እየተሽመለመሉ የሚነሱት የአሸዋ አመልማሎዎች በየቦታው ቀጥ ብለው ሲታዩ፣ በጭጋግ የተጋረደውን ሰማይ የደገፉ ምሰሶዎች ይመስላሉ። ወታደሮቹ የሚጉዋዙት እንደ አካባቢው ፣ እንደ መንገዱ አመቺነትና ሁኔታ ነው። አንዳንዴ በአቡዋራው ምክንያት ካሚዮኖቹ ተከታትለው መጉዋዝ ያቅታቸውና በመሃላቸው መጠነኛ ክፍተት በመተው ግራና ቀኝ ጎን ለጎን ይሽከረከራሉ። አንዳንዴ ደሞ አካባቢው አጠራጣሪና ጫካ ሲሆን፣ ወታደሮቹ ከካሚዮኖቹ ላይ ይወርዱና ግራና ቀኙን እያሰሱ ወይም እየፈተሹ በእግራቸው ሲጓዙ ካሚዮኖቹ መንገዱን ይዘው በዝግታ ያልፋሉ።

በአካባቢው ጠላት ካጋጠመ ተኩስ ይከፈትና፣ በጥይት ተጠዛጥዞ

በሳንጃ ተዘናጥሎ፣ በቦምብ ተሰናጥሮ ማለፍ ነው፡፡ የሞቱት ተቀብረውና ቁስለኞች ተጭነው ጉዞው ይቀጥላል፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ ሰርጎ ገቦቹ አደጋ ጥለው መሸሽ እንጂ፣ ፊት ለፊት ስለማይታኮሱ እንዲህ ያለ ሁኔታ አዘውትሮ አይገጥምም ነበር፡፡ አሁን ግን እየተጠናከሩ በመምጣታቸው የሚያደርሱት ጉዳት ቀላል አልሆነም፡፡

ካሚዮኖቹ በፍጥነት ሲበሩ፣ ዝግ ሲሉና ሲቆሙ ውለው ፀሃይ ወደ መጥለቂያዋ ስታዘቀዝቅ ቀብሪደሃር ከተማ ደረሱ፡፡ ፈጥኖ ደራሹ ፖሊስ ካምፕ አካባቢ ብቅ ሲሉ፣ እንደ ወትሮው ቤተሰቦቻቸውና ጉዋደኞቻቸው እጆቻቸውን እያወዛወዙና እያጨበጨቡ ከብሩህ ፈገግታ ጋር አልተቀበሉዋቸውም፡፡ አንዳንዶቹ እነበሩበት ቆመው እጆቻቸውን ወደላይ ብድግ በማረግ ቀዝቀዝ ያለ ሰላምታ ከሰጡዋቸው በሁዋላ አይኖቻቸውን ቡዝዝ አርገው ወደ መሬት ይመልሳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደሞ፣ በተለይም ሴቶችና ህፃናት፣ ወሬ ለመጠየቅና የሆነውን ነገር ለማወቅ እየተሩዋሯጡ ካሚዮኖቹን ይከተላሉ፡፡ ካሚዮኖቹ ካምፕ ውስጥ ሲገቡና የውጭ ሰዎች እንዳይገቡ ሲከለከል ነው ገታ ያሉት፡፡

የነማን አባት፣ የማን ባል፣ የነማን ወንድም ሳይመለስ ቀርቶ ይሆን? ሁሉም አሰፍስፎ ይጠባበቃል፡፡ አባቶቻቸውን በሩቁ ያዩ ህጻናት እቆሙበት በደስታ ይዘላሉ፡፡ ባሎቻቸውን ያዩ የቤት እመቤቶችም ‹‹ተመስገን አምላኬ ፣ የቀብሪ ደሃር ማርያም ምስጋና ይገባሽ!. . .›› እያሉ ባሻገራቸው ወደሚታየው ቤተክርስቲያን እጅ ይነሳሉ፤ ልባቸው በደስታ ይዘላል፡፡ ዘግይተው የመጡ ሕፃናትና ሴቶች ደሞ ‹‹አባዬ የታል? ባሌ አልመጣም?...›› እያሉ እስፍራው የቆዩትን ሰዎች በጥያቄ ይወተውቱዋቸዋል፡፡

ቀደም ብለው ቢመጡም ባሎቻቸውን ካሚዮኖቹ ላይ ያላዩ ሚስቶች

በድንጋጤ ፈዘውና እጆቻቸውን ደረቶቻቸው ላይ አጣምረው ቆመዋል
ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ ወይም በሚቀጥለው ማለዳ ተረኛ መርዶ
ሰሚዎች እንደሚሆኑ በመገመት ትንፋሽ አጥርዋቸዋል። ከካሚዮኖቹ
የወረዱት ወታደሮች ለቁጥጥር ሠልፍ ሲዘጋጁ፣ ቁስለኞች
ለመጀመሪያ እርዳታ ህክምና በቃሬዛ ወደ ክሊኒክ ተወሰዱ።

ትንሽ እንደቆዩ፣ የፈጥኖ ደራሹ ፖሊስ አዛዥ የሆነው ሻለቃ፣
በወታደራዊ ትጥቁ እንደሆነ መጣ። የመቶ መሪው የተሠለፉ
ወታደሮቹን አስጠንቅቆ ለአዛገፉ የሚገባውን ወታደራዊ ሰላምታ ሰጠ።

‹‹አሳርፍ በል! ፣ እንኳዋን በደህና መጣችሁ›› አለ አዛገፉ ቡጢውን
እየጨበጠና አቡዋራ የለበሱትን ወታደሮችት እያየ። ለጥቂት ሰከንዶች
አሰብ አረገና፣

‹‹ሰብሰብ በሉ! ዛሬ ሌሊት ወደ ሌላ ግዳጅ ትሄዳላችሁ፤ አሁን
ወደየቤታችሁ ሄዳችሁ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ጥቂት እረፉ። ጊዜ
እንዳይባክን ነው በቀጥታ ያነጋገርኩዋችሁ፤ ሌላው ትእዛዝ
በአዛገርችሁ በኩል ይደርሳችሁዋል። የሙዋች አባሎች ቤተሰቦች ሃዘን
እንዳያበዙ ምክሩዋቸው›› አለና የተሰለፈውን ጦር የመቶ መሪ
አስከትሎ ወደ ቢሮው አመራ።

የአስር አለቃ በርሁን ጋሻውና ወታደር አስግድ ሙሉነህ
እንደሌሎቹ አባሎች ሁሉ መኖሪያቸው ካምቡ ውስጥ ስለሆነ ቤታቸው
ለመድረስ ጊዜ አልወሰደባቸውም።

የበሪሁን ሚስት- ለምለም፣ እጆችዋን ግራና ቀኝ ዘርግታ እየበረረች
መጣችና ባልዋ አንገት ላይ ተጠመጠመች። ጥብቅ አርጋ እንዳቀፈችው
ፊትዋን አንገቱ ሥር ሸጉጣ ናፍቆት፣ ስቀቀንና ደስታ የተቀላቀለበት
ለቅሶ አለቀሰች። ልጆችዋ ፣ በተለይም ትልቁ ልጅዋ አለም፣ አባቱን

የመሳም ተራ እንዲደርሰው ከሁዋላዋ ቀሚስዋን ይጎትታል። ሌሎች ከሩቅና ከቅርብ የተሰበሰቡ ሰዎች አንዳንዶቹ ‹‹ እንኳዋን በደህና መጣችሁ›› ለማለት፣ ሌሎቹ ደግሞ የራሳቸውን መርዶ ለመጠየቅ ተራ ይጠብቃሉ።

መርዶ ዝግጅት ተደርጎ፣ ቤት ድረስ ተሂዶ እንደማይነገር ሁሉ፣ ተረጂዎች አርጂዎች ዘንድ እየሄዱ እሚጠይቁበት ደረጃ ተደርሰዋል።እንዲያ ይሁን እንጂ ሌላማ ምን ሲደረግ? ማን ለማን ንፍሮ ሲቀቅል? ማን ሊያስተዛዝን? ቶሎ ቁርጥን አውቆና የተረፈውን ይዞ እየገፉ ከሚመጣው አደጋ ለመሸሽ ካልሆነ በቀር። በርይሁንና እስግድ፣ እንኩዋን ደህና መጣጥሁ፣ ሊሉዋቸው የመጡ ወዳጆቻቸውን እያሰናበቱ ወደየቤታቸው ሲያመሩ፣ ጥቂቶቹ ተከተሉዋቸው።

አቡዋራቸውን ተጣጥበው ምግብ ከበሉ በሁዋላ፣ ቡና ሲጠጡ፣ እዚያ ከነበሩት አንድዋ ስቅስቅ እያለች ድምጽ የለሽ ለቅሶ ታለቅስ ጀመር። ህፃን ልጅዋ በሁኔታዋ ተደናግጦ አይን አይንዋን ይመለከታል። ሴትዮይቱ የነበሪሁን የቅርብ ጉዋደኛና የሥራ ባልደረባ የነበረ ወታደር ሚስት ናት። ባልዋ ከጥቂት ቀናት በፊት ሽላቦ ላይ ከጠላት ጋር ሲተናነቅ ነው የሞተው።

በርሁን ፀጉርዋን ተላጭታና፣ አንገትዋ ለይ ነጭ ክር አስሩ፣ ሃዘን ጨርቅ ውስጥ የተኮራመተችውን የጉዋደኛውን ሚስት እያየ ሲተክዝ ቆየና፣

‹‹አይዞሽ ፤ ጠንክር በይ። የአንቺ ልቅሶና ሃዘን ባልሽን አይመልሰውም. . .›› እያለ ሲናገር፣ እልፍ ብሎ የተቀመጠ ጉዋደኛው ቀበል አረገና፣

‹‹ትሰማህ እንደሆን ተቆጣት በሪሁን። አስቸግራናለች። ስራዋ

ማልቀስ፣ ማንባት ሆንዋል። በተለይ የባልዋን ጉዋደኞች ባዩች ቁጥር ለቅሶዋ ይከፋል። በመርዶ በተጥለቀለቀችው የቀብሪደሃር ከተማ እስዋን ሊያጥናና የሚችል የለም። ሁሉም የራሱ መርዶ ፣ የራሱ ሃዘን አለው። አንድ አዲስ መርዶ በመጣ ቁጥር፣ ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሚስቶችና አባቶቻቸውን ያጡ ልጆችን እየሰበሰበች ሙሾ ስታወርድና ደረትዋን ስትደልቅ ነው የምትውለው››አለ በንዴት።

አሰግድ ‹‹መርዶ በመጣ ቁጥር›› የሚለውን ቃል ሲሰማ ይወያዩበት የነበረውን ርእስ ለወጥ አረገና፣

‹‹በሌላ አካባቢ ያሉት አባሎቻችን እንዴት ናቸው? እንዴት ነው የጠላት እንቅስቃሴ?›› አለ ጉዋዳኞቹን እየተመለከተ።

‹‹ምን ይነገራል ! ጦርነቱ ተባብስዋል። ብዙ የጠረፍ ፖሊስ ጣቢያዎች ተደምስሰዋል። በቀላፎ ፣ በዋርዴር፣ በጎዴ… ወረዳዎችና ደረቅ ጣቢያዎች የነበሩት የፈጥኖ ደረሽና ሌሎች የፖሊስ አባላት ካቅማቸው በላይ በሆነ ጦር እየተከበቡ ተጨፈጨፉ። በነበራቸው የነፍስ ወከፍ መሣሪያ የተቻላቸውን ያህል ተከላክለው እዚያው ወደቁ። የተረፉት የጦር አባሎችና ሰላማዊው ህዝብ ወደሁዋላ አፈግፍገው ከወገን ጋር እንዳይቀላቀሉ የጠላት ጦር መንገድ ላይ እያደፈጠ አላሳልፍ አላቸው። በመሆኑም፣ በረሃ ውስጥ ተበትነው በርሃብና በውሃ ጥም አለቁ። ሁኔታው በጣም ያሳዝናል. . .›› አለ አንዱ እንደመተከዝ እያለ። ሌላው ቀበል አርጎ፣

‹‹በአካባቢው የደረሰው ጉዳት በኛም ሳይደረስ የበላዮቻችን በነገሩ አስበውበት ቤተሰቦቻችንንና ሌላውንም ሰላማዊ ህዝብ በጊዜ ከዚህ ባስወጡልን፤ እኛስ ግዳጃችን ነው፤ የምንችለውን አርገን እንደጉደኞቻችን እንሞታለን›› አለ በብስጭት።

"እኔ የሚገርመኝ ይህን ያህል እልቂት መድረሱን እየሰሙ፣ እኛምረዳት ጦርና የተሻለ መሳሪያ ይላክልን እያልን ስንወተውት፣ ከላይ ያሉት አለቆቻችን ዝም ማለታችው ነው" አለ አሰግድ። ይህ ብዙ ጊዜ የተጠየቀና መልስ ያጣ ነገር ስለሆነ፣ ማንም መልስ ወይም አስተያየት ሊሰጥበት አለፈለገም። ለትንሽ ጊዜ ቤቱ ውስጥ ዝምታ ነገሰ። ሁሉም በአካባቢው እያደገ የመጣውን የጠላት እንቅስቃሴ፣ ጦርነቱ ያደረሰውን ጉዳትና ሊያስከትል የሚችለውን እልቂት ያሰላስሉ ጀምር።

በሪሁን ከባዱን ዝምታ ለመስበርና፣ በየሰዉ ላይ የነገሰውን ፍርሀት ለጊዜውም ቢሆን ለማቅለል አስቦ ወደ ሙዋች ጉዋደኛው ሚስት ዞር አለና፣

‹‹ እንግዲህ ጠንከር በይ፤ ማንኛችንም ሙዋቾች ነን፤ የመሞቻችን ምክንያቶቸ የተያዩ ቢሆኑም። የባልሽ አሙዋሙዋት የጀግና ነው፤ የሚያኮራ። አባቶቻችን ድንበራቸውን ሳለማስደፈር ከጠላት ጋር እየተናነቁ በወደቁበት ስፍራ ነው የሞተው። እሱና እንደሱ የተሰዉ ሁሉ ሞቱ አይባሉም፤ በታሪክ ይኖራሉ። እኛም እርእያነታቸውን በመከተል፣ ጠላትን እንበቀልላቸዋለን ፤ የወደቁለትንም አላማ እናስከብራለን፤ ስለዚህ አታልቅሺ›አለ።

‹‹ሰሞኑን በሚንቀሳቀሰው ኮንቮይ ወደ መሃል አገር ትሂድ፤ እዚህ ምንታረጋለች?›› አለ አሰግድ።

‹‹ምን እስዋ ብቻ! ሰላማዊው ህዝብ በሙሉ ከአካባቢው ይወጣል ይባል ነበር፤ ዘገየ እንጂ። ብቻ ይሄ ህዝብ በጊዜ ከአካባቢው ሲወጣ ሲችል ለእልቂት ቢዳረግ የዘላለም ጸጸት ይሆናል›› አለ ሌላው ጉዋደኛቸው በሰፊው ተንፍሶ።

እንዲህ ሲወያዩ ቆዩና፣ ቀስ በቀስ ሰዎቹ ወደየቤታቸው ሄዱ።

‹‹በል እንግዲህ አንተም በጊዜ ወደ ቤትህ ሂድና እረፍ፤ ሌሊት መጥቼ ቀሰቅስሃለሁ›› አለ በሪሁን አሰግድን እያየ።

‹‹ግዴየለም፤ እኔ ቀሰቅስሃለሁ። በዘጠኝ ሰዓት አይደለም?››

‹‹አዎ ፣ብቻ የቀደመ ይቀስቀስ››

በርይሁን አሰግድን ወደ ቤቱ ከሸኘ በሁዋላ ትጥቁን እያዘገጃጀና፣ ለጉዞ የሚይዛቸውን እቃዎች እያሳሰረ ከልጆቹ ጋር ሲጫወት አመሸ። እንቅልፋቸው ሲመጣም ተራ በተራ ወደ መኝዋታቸው እየወሰደ አስተኛቸው። ትልቁ ልጁ አለም፣ ከእንቅልፉ ጋር እየታገለ ከአንገቱ ቀና አለና፤

‹‹አባዬ? ፣ሁለተኛ የትም አትሄድብንም?፣ ከኛ ጋር እዚሁ ትኖያለህ?›› አለ የአባቱን አንገት እቅፍ አርጎ።

‹‹የትም አልሄድም፤ ብሄድም ቶሎ መጣለሁ›› ብሎ ሳም አረገና መልሶ አስተኛው።

አልጋው አጠገብ ቆሞ የተኛው ልጁን ቁልቁል እየተመለከተ፣ ከቦታ ቦታ ሲንከራተት፣ ቀበሮ ጉድጉዋድና ድንኩዋን ውስጥ ያሳለፈውን ህይወት፣ ቤተሰቦቹ ሳይጠግቡት፣ እሱ ሳይጠግባቸው ያሳለፈውን ጊዜ አስቦ በስጨት አለና፣

‹‹ዘወትር በሰላምና በጸጥታ ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖር ሰው ምንኛ እድለኛ ነው? ተሳቆና የቤተሰብ ሰቀቀን ሆኖ መኖር እንዴት...በሆንም፣ ቢሆንም...›› እያለ ዘወር ሲል፣ የጠዋት ቁርሱን አዘገጃጅታ ከመጣችው ባለቤቱ ጋር ተያዩ።

‹‹ምነው በርዬ? ›› አለች እርጥብ እጆችዋን በቀሚስዋ ጫፍ እያዳረቀችና ቅሬታ ያረበበበትን የባልዋን ፊት እየተመለከተች።

‹‹ምነው? ምን እየሸብኝ?›› ቅሬታውን በፈገግታ ለመሸፈን ሞከረ፡፡ ቀረብ እያለች ትኩርብላ አየችው፡፡ ቀይ ዳማ ፊቱ ጠቁሮ፣ ሉጫ ጸጉሩ በረዶ እንደመታው የገብስ ቡቃያ ተመሰቃቅሎ፣ በጸሀይ የነደደውና ምጥጥ ያለው ፊቱ ገርጥቶ፣ በስፖርትና በወታደራዊ ትምህርት ዳብሮ የነበረው ሰውነቱ ጥምጥም ብሎ ታያት፡፡ በሪሁን አንድ ጊዜ ከግዳጅ ወደቤቱ ብቅ ያለ እንደሆን፣ በቤተሰቦቹ የሚናፈቅ ትዝታ ትቶ የመሄድ ችሎታ አለው፡፡ ለልጆቹ ደግ አባት፣ የሚስቱ አፍቃሪ ባል ነው፡፡ እጆቹን ለምለም ትከሻ ላይ ጣል አረገና፣

‹‹አየሽ ለምለምዬ የአንቺ እዚህ መቆየት እኔን ከሞት አይጋርደኝም፡፡ እንደውም ስጋትና ሃሳብ ነው የሚሆንብኝ ፡ እንደምታውቂው በአባባቢው ሰላም የለም፡፡ የጠላት እንቅስቃሴ አይልዋል፡፡ እቅዱ ወደ መሃል አገር የሚያመሩትን መንገዶች ሁሉ በመዝጋት መሃሉና ዳሩ አገር እንደይገናኙ ማረግ ነው፡፡ ለዚህም ነው ወታደሮቹ በጎን አሳብረው በማለፍ ወደ መሃል አገር በሚወስደው መንገድ ላይ የምትገኘውን የሼኮሽ ጣቢያ የሚያጠቁት፡፡ ስለዚህ መንገድ ሳይዘጋና የባሰ ሁኔታ ሳይመጣ ሰሞኑን በሚንቀሳቀሰው ኮንቦይ ከነ ልጆችሽ ወደ መሃል አገር መሄድ አለብሽ፣ እሺ? የኔ መቤት›› አለ፡፡

ፈገግ አለችና ‹‹በል ብቻ በጊዜ ተኛ፡፡ በጠዋት ለመንቃት እንድትችል፤ ለሱ ግድየለህም ››አለች፡፡

በሪሁን፤ ቀደም ሲል የጀመረውን ጉትጎታ ወደ መኝታቸው ከሄዱ በሁዋላም አልተወም፣

‹‹ለምለምዬ ባክሽ እሺ በይኝ፣ ባክሽ በጊዜ ወደ መሃል አገር ሂጁ›› አለ ጸጉርዋን እያሻሸና ጉንጯን እየሳመ፡፡

‹‹አልሄድም በርዬ፤ እውነቱን ልንገርህ አልሄድም፤ ላንተ የሚመጣው ሞት እኔንም ይዞኝ እንዲሄድ ፈልጋለሁ›› አለች የልቅሶ በሚመስል ድምጽ።

‹‹እነዚህ ልጆችሽ አያሳዝኑሽም? እነሱ እንኳዋን ከዘመድ ቢቀላቀሉ. . .››

‹‹እነሱን ልካቸዋለሁ በርዬ ። ምናለበት አሁን ይህን ብትተወው? እሱን ለኔ ተወው። ለኛ አትጨነቅ። ሰዉ እንደሚሆነው እንሆናለን›› ብላ እቅፍ አረገችው። እሱም አቀፋት፣ ጣቶቹ ሰውነትዋ ላየ ቢርመሰመሱም ሃባቡ አልተሰበሰበም።ይህን ስለተረዳች፣

‹‹እቀፈኝ በሪዬ፣ ጠበቅ አርገህ አቅፈኝ›› አለች ጉንጩን በከንፈሮችዋ እየዳሰሰች። እቅፍ አረጋት። በዙሪያቸው የነበረውን የስጋት ቆፈን አስወግደው ለዚጌውም ቢሆን የራሳቸውን የፍቅር ሙቀት በሥፍራው ተኩ። አንገቱን፣ ጉንጩን፣ ከንፈሩን ፣ ሁለመናውን በከንፈሮችዋ ዳሰሰቻቸው። እሱም እንዲሁ። እርስ በርሳቸውን በርሀብ ወቅት እደተገኘ ምግብ ተሻሙ።

‹‹በሪሁንዬ አትልቀቀኝ፣ አትተወኝ፣ እንደሱ ቆይልኝ. . .›› እያለች በደስታ አቃሰተች። ለዘላለም እንዲያ ቢኖሩ፣ ሌሊቱ ባይነጋ... የሁለቱም ምኞት ነበር። የበሪሁን እቅፍ ለለምለም ሰላም ፣ ፀጥታና ፍቅር የሞላበት ገነት ነው።

‹‹እፎይ! ፣ ይብላኝላት ለዚያች ለሂሩት›› አለች ለምለም ሁለመናዋ ባልዋ ላይ ወድቆ፣ ትንፋሽዋ እጥር እጥር እያለ።

‹‹እንዴት ምን ታስበሽ?››

‹‹አሰግድን ያጣች እለት፣ እሱ ሞተ ያልዋት እለት፣ ሰው አትሆንም››

‹‹ምንም አይሆን፣ ግዳጅ የሄደ ሁሉ ይሞታል ያለሽ ማነው? ቢሞትም የሞተለት አላማ ምን መሆኑን የምትረዳ ስለሆነች፣ ብታዝንም በጀግናነቱ ትጽናናለች"

ሂሩት የሰምለም ታናሽ እህት ናት፡፡ የምትኖረው ከቤተሰቦችዋ ጋር አዲስ አበባ ነው፡፡ ከአሰግድ ጋር አንድ ሰፈር አድገው፣ አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ይማሩ ነበር፡፡ እስከ ዘጠነኛ ክፍል አብረው ከተማሩ በሁዋላ፣ ቤተሰቦችዋ ከዚያ በላይ ሊረዱዋት እንደማይችሉ ይነግሩዋታል፡፡ ያኔ ነው አሰግድ፣

‹‹አንቺ ትምህርትሽን ግፊበት፣ እኔ ሥራ ይገፍ ረዳሻለሁ››ብሎ በወታደርነት የተቀጠረው፡፡ ወታደር ሆኖ ወደ ኦጋዴን ሲመጣ፣ እነ በሪሁንን ያገኛቸዋል፡፡ በሪሁን ከስምንት ዓመታት በፊት በፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ኃይል ውስጥ ተቀጥሮ የአገልግሎት ዘመኑን በሙሉ ኡጋዴን ነው የኖረው፡፡ አካባቢውን በደንብ አውቆታል፣ ቁዋንቁዋውንም በሚገባ ያቀላጥፊዋል፡፡

አሰግድ የሚባል ወጣት በወታደርነት ተቀጥሮ ወደ አካባቢው መምጣቱን ሂሩት እንደጻፈችለትና፣ እንዲያላምዱትም አደራ እንዳለቻቸው ሁሉንም የሚያውቃቸው ሰው ለሰመለም ይነግራታል፡፡ እስዋም በሪሁን ከግዳጅ ሲመለስ ይህንኑ ታሳውቀዋለች፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ አሰግድ በሪሁን አለበት ሻምበልና መቶ ውስጥ ስለተመደበ፣ በግዳጅ ስፍራዎች ሁሉ አብረው በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው

አሰግድ ኦጋዴን ከመጣ ከአንድ ዓመት በሁዋላ ወደ አዲስ አበባ ሄደና በሂሩትና በሱ መሀል የነበረው ፍቅር በቃል ኪዳን በቀለበት ታሰረ፡፡ ሂሩትም ትምህርትዋን ቀጠለች፡፡ ትግሉ በመሃልና በዳር በተፋፋመበት ወቅትት፣ አሰግድ ከወራሪዎች ጋር የሚያረገውን

ፍልሚያ እያበረታታች እስዋም በመሃል በሚደረገው ትግል ውስጥ ገባች።

በዚህ ምሽት አስግድ ከበሪሁን ተሰናብቶ ወደ ቤቱ ቢመጣም አልተኛም። ለወጉ ያህል ልብሱን ሳያወላልቅ አልጋው ላይ ጋደም በማለት እራስጌው የተሰቀለውን የሂሩት ፎቶግራፍ ትኩር ብሎ ሲመለከት ቆየ። ፎቶግራፉም ፈገግ እንዳለ በአጸፋው አትኩሮ ተመለከተው።

‹‹ሂሩት እኮ የውቦች ውብ ነች፣ የኔ ቆንጆ . . .›› እያለ ሲመለከተው፣ ፎቶግራፉ ድብዝዝ እያለ፣ እየራቀ፣ እየጠፋ ሄዶ፣ ሂሩት እየሣቀችና እያሩዋሩዋጠች ስታሳስቀው. . .ቀይ ዳማ ፊትዋ ላይ የሚደምቀው ፈገግታ አካባቢውን ሲያበራለት፣ ንፋስ እያመሰቃቀለ ፊትዋ ላይ የሚበትነውን ጸጉር ወደ ሁዋላ እያለች ወደሱ ስትሮጥ፣ በእቅፉ ሲቀበላት . . . ። ከህሳብ አለም ድንገት ብንን አለ። ብቻውን መሆኑን አላመነም። ከሂሩት ወደ ሺህ ኪሎ ሜትሮች በሚቆጠር እርቀት እንደ ተለየ ማስታወስ አቃተው። ቆሞ ዙሪያውን እያየ ራሱን ነቀነቀና ጎንበስ ብሎ አልጋው ሥር ያለውን የእንጨት ሳጥን ሳበው። ለጉዞው የሚሆኑ የውስጥ ልቦሶች ለመያዝ ነበር ያሰበው፣ እጆቹ ሌላ ነገር ላይ አረፉ እንጂ ። ሂሩት በየጊዜው የጻፈችለትን ደብዳቤዎች አጠራቀመበት ፖስታ ላይ። እንደሚሰበር እቃ ቀስ በሎ አነሳው።

‹‹...አስግዬ፣ብትርቀኝም፣ ናፈቆትህ ቢያስጨንቀኝም፣ ነጻነታችንን ላለማስደፈር ድንበራችን ላይ ከሚፋለሙት ጀግኖች ጎን መሰለፍህን ሳስበው እጽናናለሁ። የምትከፍሉትን መስዋእትነት ለማገዝ እዚህ ያለነው በደጀንነት ቆመናል። አይዞህ በርታ፣ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ የህዝባዊ ሰራዊት አባላት (ሚሊሽያዎች) ዝግጅታቸውንና ትጥቃቸውን

አሙዋልተው ጎናችሁ ለመቆም በቅርብ ጊዜ ወደዚያው ይመጣሉ። እኛም ለእናንተ ስንቅ በማዘጋጀትና በመሃል ካሉት ፀረ-አብዮተኞች ጋር በመታገል ላይ ነን። ትግላችንን በአሸናፊነት በአጠናቀቅን በመግስቱ ትዳራችንን እንደምንመሰርት ተስፋዬ የጸና ነው። በተቻለህ መጠን ቶሎ ቶሎ ጻፍልኝ. . .›› ይላል። ፈገግ አለና ደብዳቤውን ስፍራው መለሶ አሰም ጻፈላት። እቃዎቹን ወደ ሻንጣው እየመለሰ ሰአቱን ቢመለከት፣ ለጉዞ የቀረው ጊዜ አንድ ሰዓት ነው። ያን በርይሁን ቤት ማሳለፉ እደሚሻለው አስቦ፣ ወታደራዊ ትጥቁን ታጥቆና ቤቱን ዘግቶ ወደ ወደዚው አመራ።

‹‹አሰግድ መጣህ እንዴ ?›› አለ በሪሁን መኝታው ውስጥ እንዳለ። ለመነሳት ቢሞክር ለምለም ከእቅፍዋ አላስወጣ አለችው። ጉንጭዋን ሳም አረገና፣

‹‹አሰግድ ውጭ ቆምዋል ልክፈትለት። አንቺ ተኚ ልጆቹ ሳይነቁ መሄድ አለብኝ ›› አላት። ፊትዋን ጉያው ቀብራና እቅፍዋን እንደብረት አጠንክራ ዝም አለችው። እንደምንም እጁንና አንገቱን አላቆ ተነሳና በሩን ከፈተ።

‹‹አልተዘጋጀህም እንዴ? ሰአቱኮ ደርስዋል›› አለ አሰግድ በር ላይ ቆሞ።

ለምለም ማታ ያዘጋጀችውን ቁርስ ቀማምሰው ለመሄድ ሲነሱ፣ ሁለቱንም አቅፋ ክፉኛ አለቀሰች። በሪሁን እጅዋን ገፋ አርጎ፣

‹‹ምነው ለምለምዬ ያለወትሮሽ ለቅሶ ለቅሶ አለሽ? ወደ መቃብር የምትሸኚን ይመስል፣ ከትናንት ጀምረሽ እንዲህ የምታነቢው ለምንድነው? ከዚህ ቀደም ለግዳጅ ሄደን አናውቅም እንዴ?›› አለ እንደመቆጣት ብሎ።

‹‹ልክ አይደለሽም ለምለም፣ ግዳጃችሁን ፈጽማችሁ በደህና ተመለሱልኝ ብለሽ በመሸኘት ፈንታ ታለቅሻለሽ? በይ እንቺ ይህን ደብዳቤ ለሂሩት ላኪልኝ›› አለ አሰግድ በሁኔታዋ እየባባ፡፡

‹‹በሉ ደህና ሁኑ፣ በደህና ተመለሱ›› ብላ የአሰግድን ጉንጭ፣ የባልዋን ከንፈሮች ሳመችና እንባዋ እንዳይታይባት ፈትዋን በመዳፎችዋ ጋረደችው፡፡ ጥቂት ቆይታ መዳፎችዋን ብታነሳ እነበረሁን የሉም፡፡ ከአይኖችዋ የሰወራቸው ጭለማ ራሱ ሞት መሰላት፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

በሪሁንና አሰግድ ለግዳጅ ወደ ሄዱባት የሼኮሽ መንደር ከደረሱበት እለት ጀምሮ እንደተለመደው ከሌሎቹ አባሎቻቸው ጋር ምሽጋቸው ውስጥ ናቸው፡፡ የሼኮሽ መንደር በደገሃቡርና በቀብሪደሀር መካከል ትገኛለች፡፡ መንደርዋን አቋርጦ ከሚያልፈው አውራ ጎዳና ባሻገር፣ በስተደቡብ ሲል እልፎ እልፎ ጉች ጉች ያሉ ቁጥቋጦዎች ያሉበት ጭው ያለ ሜዳ አለ፡፡ በስተሰሜን ደሞ እንደ ሰንሰለት ተያይዘው፣ በእጣንና በደሬ ዛፎች የተሸፈኑ ኮረብታዎች ይታያሉ፡፡ በምሥራቅና በምዕራብ አቅጣጫ፣ ከርቀት እይታ በሚከለክሉና እልፎ እልፎ ጉብ ጉብ ባሉ ኮረብታዎች የተከበበች ናት፣ መንደሪቱ፡፡ ባካባቢዋ በቁጥቋጦዎች ፣ በሰበርባራ መሬቶችና በኮረብታዎች የተሸፈኑና ከየአቅጣጫው ወደ መንደሪቱ የሚያስገቡ የእግር መንገዶች ስላሉ ወንበዴዎች በነዚያ ሰርገው እየገቡ ነው መንደሪቱን የሚያጠቁዋት፡፡

የአካባቢው ብሄረሰብ አባሎች ከብት አርቢዎች ስለሆኑ፣ ኑሮዋቸው በደሳ፣ (ተንቀሳቃሽና ተገጣጣሚ ጎጆዎች ) ውስጥ ነው፡፡ ለተወሰኑ ቀናት ወደ መንደሪቱ ተጠግተው ደሳዎቻቸውን ይተክሉና ይቀመጣሉ፡፡ ግመሎቻቸውን፣ ፍየሎቻቸውን፣ በጎቻቸውን እና ሌሎቹን የቤት እንስሳዎቻቸውን ቀን በአካባቢው ባለው ቁጥቋጦ ውስጥ ሲያግዱ እየዋሉ፣ ሌሊት በእሾህ በሚከልሉት ጊዜያዊ በረት ውስጥ ያጉርዋቸዋል፡፡

ከብት አርቢዎቹ በርከት ብለው በመጡ ጊዜ፣ መንደሪቱና ይደምቃሉ፡፡ አቡዋራውን እያነሳ ከየአቅጣጫው የሚተመው የከብት

መንጋ ለቁጥር ይታክታል፡፡ ነጭ፣ ጥቁርና ዝጉርጉር መልክ ያላቸው ላሞች ፣ በጎችና ፍየሎች በአሸዋማው ሜዳ ላይ ፈሰው ሲሩዋሩዋጡ በሩቁ ለሚያያቸው፣ እጋለ ምጣድ ላይ የሚፈካ ማሽላ ይመስላሉ፡፡ በመንደሬው እንቅዋንቅዋርም ሰውጥ ይታያል፡፡ ወተቱና ቅቤው ይረከሳል! ጠቦቶች በቀላል ዋጋ ይገኛሉ፡፡ አንድ ሰሞን ደሞ እንስሳቱ ውሃና የተሻለ ግጦሽ ፍለጋ ርቀው ሲሄዱ አካባቢው ጭር ይላል፡፡

ሌሎቹ የመንደሪቱ ነዋሪዎች፣ የፖሊስ አባላትና በአነስተኛ ንግድ የሚተዳሩ ሰዎች ናቸው፡፡ እነሱም ቢሆኑ ግድግዳቸው ከጨፈቃ በተሰራና ጣራቸው በአሸዋ በተከደነ ጎጆዎች ውስጥ ነው የሚኖሩት ፡፡

የሼኮሽ መንደር እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ገጠር መንደሮች በሳምንት ውስጥ በተወሰነ ቀን የሚቆም ሰፊ ገበያ የላትም፡፡ ወጣ ብሎ «መጋላ» የሚባል መገበያያ ቦታ አለ፡፡ የሚሸጠው ነገር ያለው ሰው ረፋዱ ላይ በማንኛውም ሰአት መጋላ ይወጣል፡፡ ሸማቹም ይከተላል፡፡ ማሽላ፣ በቆሎ፣ ወተት፣ ቅቤ፣ ፍየል. . . ዘወትር ከመጋላው አይጠፉም፡፡ በጣም አነስተኛ ይሁን እንጂ፣ አልፎ አልፎ ጥቃቅን የኮንትሮባንድ እቃዎችም ብቅ ይላሉ፡፡

ባለፉት ሁለትና ሶስት ወራት ጠላት የሚልካቸው ሰርጎ ገብ ወንበዴዎች መንደሪቱን ለመውረርና ለመዘረፍ የተደጋገሙ ሙከራዎች ቢያረጉም፣ ነዋሪውና የፖሊሱ ሃይል ባረጉት መከላከል ወደኋላ ተመልሰዋል፡፡ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ ሃይላቸውን እያጠናከሩ መምጣታቸው አልቀረም፡፡ በሰውና በንብረት ላይ የሚያደርሱት ጉዳት እየከፋ መጥትዋል፡፡ በመሆኑም በርከት ያሉ ሰዎች ከመንደሪቱ ሲወጡ፣ የቀሩት ወደ ፖሊሶች ምሽግ አካባቢ መሰብሰብ ጀምረዋል፡፡

በዚህ ወቅት ነበር ተጨባጩን ሁኔታ ለአካባቢው ነዋሪ በዝርዝር

ማስረዳት አስፈላጊ የሆነው። በዚሁ መሰረት ፍርሀትና ግራ መጋባታቸውን ትተው እንዲረጋጉ ለማረግና፣ ድጋፋቸውንም ለመጠየቅ የፈጥኖ ደራሹ ፖሊስ አዛዥ፣ ሙቶ አለቃ ሲሳይ ረጋሳ ሕዝቡንና በቦታው የነበረውን ጦር ሰብስቦ ሰፊ ገለጻ አረገ፣

‹‹ በአካባቢያችን ያለው የጠላት እንቅስቃሴ ከምንጊዜውም ይበልጥ እየጠነከረና እየከፋ መጥቷል። ጠላት ከኛ የተሻለ ትጥቅ ያለውን ጦሩን ወደኛ በማንቀሳቀስ ላይ ነው፣ እንደውም ሰሞኑን በደረሰን መረጃ እንዳረጋገጥነው በተጠናከረ መደበኛ ጦሩ አማካይነት ግልጽ ወረራ ሊሰነዝርብን ተዘጋጅቷዋል። አላማው ይህችን የሼኮሽ ጣቢያ ደምስሶ እዚሁ በመመሸግ አካባቢውን ለመቆጣጠር ነው። ይህን በማረግም ከዳር ያለው ሰላማዊ ህዝብና ጦራችን መተላለፊያ እንዲያጣ፣ እንዲሁም እርዳታና ስንቅ እንዳያገኝ ለማረግ ነው። በዚህ ዘዴው ተጠቅሞ በአንዳንድ ስፍራዎች በህይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርስዋል። የጠላት ጦር በርዳታ ስም ከውጭ በገፍ ያገኘውን ዘመነዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀና ከእኛ በተሻለ ሁኔታ የተደራጀ ነው። ሀገራችን ያላት አነስተኛ ጦር፣ ሥልጣንና ጥቅማቸውን የተቀሙ የገዥ መደብ አባላት፣ እንዲሁም አስተባባሪያቸው ኢምፔሪያሊዝም በመሃል ሀገርና በዙሪያችን ባስነሱብን ርነቶች ተጠምድዋል ...።

"ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የረዥም ጊዜ ህልማቸውን እውን ለማረግ ነው በዚህ ግንባር ያሉ ጠላቶቻችን የሚጣደፉት። ባንዳንድ ቦታዎች ያገኙዋቸው ጊዜያዊ ድሎች ሊያደናግጡን አይገባም። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ከጀርባችን አሉ፣ ከጎናችን ለመቆምም በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ናቸው። ሰሞኑን እንደሰማችሁት የህልውናችንና የአብዮታችን አለኝታ የሆነው አዲሱ የሚሊሺያ

ሰራዊት ወደኛ በመገስገስ ላይ ነው። ህባዊ መሠረት ካለውና በአይነቱ አዲስ ከሆነው ሰራዊታችን ጋር ሆነን ለጠላቶቻችን የማያዳግም ትምህርት እንሰጣቸዋለን። እስከዚያ ከኛ የሚጠበቀው ነገር፣ ባለን ሃይል እስከ መጨረሻው መከላከልነው። ስንቅና ጥይት በከፍተኛ ጥንቃቄ መቆጠብ አለብን፣ በህይወት እያለን ጠላት የጥበቃ ወረዳችንን አይረግጣትም. . . ››አለ።

ስብሰባው መበተን እንደጀመረ፣ መቶ አለቃ ሲሳይ ወደ ሬዲዮ ኦፕርተሩ ሄዶ ‹‹እስቲ ቀብሪደሃርን ጥራ!›› አለው ። ወታደሩ ምሽግ ውስጥ ሆኖ  ከሬድዮው ጋር ይታገል ጀመር። ሬድዮው እምቢ ብሎት ሳይሆን፣ ከቀብሪደሃር ለጥሪው መልስ አጣ። ድምጹ እስቲዘጋ ሲጮህ ቆይቶ ወደ አለቃው ዞር አለና

‹‹ከጠዋት ጀምሬ ጠራለሁ፣ መልስ የለም። ሌሎች ጣቢያዎችንም ጠራሁ ፣ ላገኛቸው አልቻልኩም››  አለ የመነጋገሪያውን መያገ በራሱ አውልቆ የግንባሩን ላብ እየጠራረገ። መቶ አለቃ ሲሳይ ከንፈሩን ነከሰ፣ የቀብሪደሃር ከተማ በጠላት ጦር  ሳትደመሰስ አትቀርም የሚል ጥርጣሬ አደረበት።

"ቢሆን ነው እንጂ ..." አለና አይኖቹን ፊትለፊት ቡዝዝ አረገ።

ጸሐይ አደመጥለቂያዋ ስትቃረብ አካባቢውን በሩቅ መመልከቻ መንጽር ለመቃኘት በስተሰሜን አለው ኮረብታ ላይ ወጣ። በርቀት ይታዩ የነበሩት ኮረብታዎችና ሸለቆዎች በጭጋግ ተጋርደዋል። አልፎ አልፎ ጉችጉች ያሉት ቁጥቋጦዎች ጸጥ ብለው በጨለማው እየጠቆሩ ለአንድ ተንኮል የሚያደፍጡ አራዊት በመምሰል ላይ ናቸው።

ቀን ከንፋስ ጋር ይላፋ የነበረው አሸዋ አስፈሪውን ሌሊት በጸጥታ ለማሳለፍ በጊዜ አንቀላፍቶአል። አእዋፍ በጊዜ በየጎጆዋቸው

ተከተዋል፡፡ የሜዳ ፍየሎች እንደወትሮው በመንጋ እየሆኑ አይታዩም፡፡ የጫካው ንጉስ አንበሳ እንኳዋን አስፈሪ ድምፁን ከጠፋ ውሎ አድርዋል...፡፡

መቶ አለቃ ሲሳይ ባየው ለውጥ እየተገረመና አካባቢውን እንደ ብርድ ልብስ በመሸፈን ላይ ያለው ጭለማ እየቀፈፈው ወደምሽጉ ሄደ፡፡ ጊዜው ከረምት ነው፡፡ ሌላው የኢትዮጵያ ክፍል በዝናብ ጠል ርስዋል፡፡ አጋዴን ግን በተገላቢጦሹ እንደ እቶን እሳት ያነፍራል፡፡

ለዐይን ያዝ ሲያረግ አካባቢው በከፍተኛ ጸጥታ ተዋጠ፡፡ ወታደሩ ሁሉ በየምሽጉ ሆኖና ጣቱን ጠመንጃው ምላጭ ላይ አርጎ በንቃት ይጠባበቅ ጀመር፡፡ ዘግየት ብላ የወጣችው ግማሽ ጨረቃ ደብዘዝ ፈካ ነው የምትለው፣ ለብርጉንዋ የሰስተች ትመስላለች፡፡

ፍጡር ሁሉ በፍርሃት መዳፍ የተያዘ በመሰለበት በዚያ ምሽት፣ ድንገት ዐይን የሚያስጨፍን ብልጭታ ታየና፣ የጆሮ ከበሮ የሚበሳ ድምጽ በአቅራቢያው ተሰማ! መብረት ከሰማይ የወረደ መሰለ፡፡ ባንዴ አላበቃም፤ እየደጋገመ ይፈነዳ ጀመር፡፡

‹‹ጠላት በመድፍ ድብደባ ጀመረ! እስቲ ጥራ! ሞክር!›› አለ መቶ አለቃ ሲሳይ፣ ወደ ሬድዮ ኦፕሬተሩ ዞር ብሎ፣ የሬዲዮ ግንኙቱ ግን ከማለዳው ጀምሮ እንደተቋረጠ ነው፡፡ አካበቢው የሚወድቀው የመድፍ ጥይት አፈር እያነሳ ያለብሳቸው ጀመር፡፡ የመድፍ ጥይት ያረፈባቸው አዳንድ ምሽጎች ውስጣቸው የነበሩትን ሰዎች እየዋጡ አፎቻቸውን ዘጉ፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን፣ መቶ አለቃ ሲሳይ ወታደሮቹ ተኩስ እንዳይጀምሩ ይከለክል ነበር፡፡ ትንሽ ቆይቶ የመድፉ ተኩስ ቆመና ከሚነድ ደመራ እንደሚወጣ የእሳት ፍንጥርጣሪ የሚያበሩ የጠመንጃ

ጥይቶች ሰማይ ላይ ይንጣጡ ጀመር። እያለፉም ቤቶች ላይ በማረፋቸውና ነበልባል በመፍጠራቸው፣ አካባቢው በከፍተኛ ብርሃን ተጥለቀለቀ።

የጠላት ጦር እየቀረበ ሲመጣ በእሳቱ ብርሃን ወለል ብሎ ይታይ ጀመር። የመቶ አለቃ ሲሳይ ጦር መተኮስ ጀመረ፣ የነበረው አንድ ሞርተር ትነሽ አጉዋራና ጥይቱ ስላለቀ ጸጥ አለ። ከሁለት መትረየሶች አንዱም እንዲሁ አፉን ዘጋ። ማስ ጠመንጃዎችና አንዱ መትረየስ ዋይ ዋይ ይሉ ጀመር። እየሮጠና ከመጣው የጠላትት ጦር አብዘኛው ከመሬት እየተላተመ እዚያው ቀረ። የተረፈው በመጣበት ሁኔታ ተመለሰ።

ትንሽ ቆይቶ የመድፉ ድብዳባ እንደገና ከቀድሞው ይበልጥ ያገሳ ጀመር። ምሽጎች ተደረመሱ፣ ብዙ የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ጀግኖች የእሳት ጎራዴ በሆነው የመድፍ ጥይት እየተመተሩ ወደቁ። በከለላ የተደበቁት ሁለት ማርቸዲስ ካሚዮኖችና አንድ አነስተኛ የሬዲዮ ጀኔሬተር፣ ነደዱ። ግመሎች፣ ፍየሎች፣የቀንድ ከብቶች ከየበረታቸው እየወጡ ተራወጡ።

የጦሩ አባላት የነፍስ ወከፍ መሣሪያዎች ይዘው፣ ከመድፍና ከሮኬት ጋር መዋጋቱ እጅግ አስቸጋሪ ሆነባቸው። ቁጥራቸውም እጅግ እየቀነሰው መጣ። ቢሆንም ምሽጋቸውን አልለቀቁም፣ ጀርባቸውን ለጠላት አልሰጡም። በቆራጥነት ተከላከሉ።

ከጥቂት ደቂቃዎች ፋታ በሁዋላ በከባድ መትረየሶች የሚረዳ ሌላ የጠላት እግረኛ ጦር ከምእራብ አቅጣጫ ብቅ አለ። በዚህ ጊዜ መቶ አለቃ ሲሳይ በቅጽበት የተረፉትን ወታደሮች ይዞ ቀኙን ረድፍ፣ አስር አለቃ በሪሁን የግራውን ረድፍ፣ አስግድ ደግሞ በመሃል ያለውን የወገን

ጦር በመምራት ውጊያውን አጧጧጡፉት። ከፊት ለፊት የሚመጣው የጠላት ጦት እንደቅጠል ሲረግፍ፣ ከሁዋላ ሌላ ይመጣል። ቢጨልፉት የማያልቅ ጅረት መሰለ። አሁንም ከወገን ጦር ብዙ ጀግኖች ወደቁ፤ የተረፉትም ቢሆኑ ተዳከሙ፤ ጥይታቸውም ወደማለቁ ተቃረበ። ወድቀው የሚያጉዋሩትን ቁስለኞች የሚያነሳ ጠፋ። ጥይት የሚያቀብልም ሆነ ከሁላ ወይም ከጎን ብቅ የሚል የወገን ጦር አልደርስ አለ። ሁሉም ወደፍጻሜው የተቃረበ መሰለ።

‹‹ወደፊት!!›› አለ መቶ አለቃ ሲሳይ ቆሞና ድምጹን ከፍ አርጎ፣ በሕይወት የነበሩና የተከተሉት ከአምስት አይበልጡም። በረድፈ ሆነው እየተኮሱ ወደፊት ገሰገሱ። እልህና ሲቃ እየተናነቃቸው ፣ እየተሳደቡ፣ እየፎከሩ...። የእሳት ውስጥ ገብ ሆነ። አካባቢው በቃጠሎ፣ በባሩድና በሚቃጠል የሰው ስጋ ሽታ ታፈነ።

መቶ አለቃ ሲሳይ እሬሣ እየረገጠና እየተራመደ ድምጹን ከፍ አርጎ "አብዮታዊት እናት አገር ወይም. . . ›› ሲል ድንገት ድምጹ ቁርጥ አለ። በሪሁን ዞር ብሎ ቢመለከት ወድቋል። ወደሱ ሲሮጥ ጎኑ የነበረው አሰግድ ‹‹ተመታሁ›› ብሎ በርከክ አለ። አጎንብሶ እስየተኮሰ ሄዶ መቶ አለቃ ሲሳይን ቢያየው ከአንገቱ በላይ የለም። አሰግድ አጎንብሶ መጣና፣

‹‹ደህና ነኝ! እጄን ነው የተመታሁት! ያዘው! ያዘው!›› አለ፣ ደህና እጁን መቶ አለቃ ሲሳይ ብብት ሥር አስገብቶ። ተረዳድተው መሬት ለመሬት እይተጎተቱት ሮጡ። በፈራረሱ ቤቶች መሃል እየተሹለከለኩ ከተኩሱ መሃል ወጡ።

ትንሽ ራቅ እንዳሉ ከለላ ይዘው የአሰግድን ቁስል በጨረቅ አሰሩ። የአለቃቸውን የማዕረግ ምልክቶች ካወለቁና መታወቂያውን ከወሰዱ በሁዋላ አሸዋውን በሳንጃቸው ማስ ማስ አርገው ቀበሩት።

‹‹እንሂድ፣ ጠላት አቅራቢያችን ነው ያለው›› አለ በራሁን የአሰግድን ደህነኛ እጅ ይዞ።

‹‹ወዴት? በየት በኩል?›› አለ አሰግድ በእሳት የምትጋየውን የሼኮሽ ከተማ በሩቁ አያየ።

# ምዕራፍ ሦስት

‹‹ከማን ጋር ነው የሚዋጉት?›› አለ አሰግድ ከሁዋላው በሚሰማው የጥይት ተኩስ እየተገረመ።

‹‹እርስ በርሳቸው ይሆናል፤ ከሁለት አቅጣጫ የመጣው የጠላት ጦር በስህተት እርስ በርሱ ሳይገጥም አልቀረም›› ፡

በሪሁንና አሰግድ ከተኩሱ መሃል ወጥተው አለቃቸውን ከቀበሩ በሁዋላ፣ ረባዳ መሬት እየመረጡ ጉዞዋቸውን ወደ ምሥራቅ አቀኑ። ቀዝቃዛ ንፋስ ሽውሽው ይላል። የአሰግደ ቁስል ለጊዜው በጨርቅ ታስረ እንጂ ደሙ ሙሉ በሙሉ አልቆመም።

‹‹ያዘኝ፤ ያዘኝ ›› አለ አሰግድ ትንሽ እንደተጉዋዙ እየተንገዳገደ። በሪሁን ቀልጠፍ ብሎ ብብቱ ስር ገብቶ ሲደግፈው ዝልፍልፍ አለና መሬት ተቀመጠ። በሪሁን ጠማንጃውን አኑሮ በቀስታ በጀርባው ካስተኛው በሁዋላ የልብሱን ቁልፎችና ቀበቶውን አላላለት። ትንሽ ጠብቆ የልቡን አመታት አደመጠ፣ ነቀነቀው፣ በስሙ ጠራው፣ አሰግድ አልነቃ አለ።

ያረገው ሙከራ ሁሉ ውጤት አልባ ቢሆንበት ጠመንጃውን ታፋው ላይ አጋድሞ አጠገቡ ቁጭ አለና ከዳውን ውጥቶ ነቀነቃት። በጣም ትንሽ ውሃ ነው ያላት። ግማሽ ጉንጭ  ፉት አለና ተጉመጥምጦ ተፋው። ጀብርናውን (ዝናሩን) ዳበሰ፣ አስር ጥይቶች ብቻ ቀርተውታል። የጥይት፣ ካርታውን ከጠመንጃው አወለቀና ጥይት ባለበት በኩል በጣቱ ጫን፣ ጫን አረገው ጉደሎ ነው። ከጀበርናው ጥይት እያወጣ ሞላና ካርታውን ሥፍራው መልሶ ጠመንጃውን አቀባበለ።

ራሱን በእጆቹ ደግፎ በማቀርቀር ትንሽ ሲያስብ ቆየና፣ ዞር ብሎ አሰግድን አየው፣ ቁስሉን በቀኝ አመልካች ጣቱ ነካ ነካ አረገው፣ ደሙ መፍሰሱን አቁሟል። እንደገና የልቡን ምት አዳመጠና፣

‹‹ብዙ ደም ስለ ፈሰሰው አዙሮት ይሆናል። ምን ይሻለል? ››እራሱን ይዞ አቀረቀረ። በደብዛዛው የጨረቃ ብርሃን ትኩር ብሎ ቢመለከተው የአሰግድ ጠይም ፊት ጠቆረበት። ጎላ ጎላ ያሉት አይኖቹ ቆባቸውን ደፍተው ተደበቁበት። ድካሙ ፣ ርሃቡ፣ ውሃ ጥሙ እሱንም ቁልቁል ሳበው። እንደ አሰግድ መጋደም አሰኘው። ግን ጊዜውና ቦታው ከሞት የሚሸሹበት እንጂ፣ የሚያርፉበት ስለ አይደለ ብድግ ብሎ ወደ ሼኮሽ መንደር ተመለከተ። አሁንም ጭስዋ ሽቅብ ይትጎለጎላል።

‹‹ በእብሪት ተነሳስቶ በሰው ምድርና ህይወት ላይ ይህን ያህል ጥፋት ማድረስ?›› አለና በሰፊው ተነፈሰ። ከጎኑ የወደቁት ጉዋደኞቹ፣ የተራመደው እሬሣ ብዛት፣ ከነህይወታቸው የተቃጠሉት የቤት እንስሳት፣ ህፃናት፣ ነፍሰጡሮች...፣ ላንድ አፍታ በአእምሮው ብልጭ አሉበትና ዘገነነው።

ከመንጋቱ በፊት ካካባቢው መራቅ ስላለባቸው፣ አሰግድን ሊቀሰቅሰው ሞከረ። የሚነቃ አልሆነም። ጠመንጃውን በደረቱ በኩል አነገተና ቀና አርጎ ሊሸከመው ሲታገል፣

‹‹ ውሃ ፣ ውሃ አጠጣኝ ›› አለ አሰግድ ድክም ባለ ድምጽ። ከአንገቱ ቀና አርጎ አስቀመጠውና፣ በደንብ መንቃቱን ካረጋገጠ በሁዋላ፤

‹‹ያንተ ኮዳ ባዶ ነው፣ ያለችን ይህች ናት›› ብሎ በኮዳው ክዳን እየቀዳ ሁለቴ አስጎነጨው። አሰግድ ውሃውን ውጦ ራሱን ሲነቀንቅና አይኖቹን ጭፍን ክፍት ሲያርግቆይቶ፤

‹‹ብዙ ተኛህ እንዴ?›› አለ በሪሁንን እያየ።

‹‹አልተኛህም። እንደምንም በርታና ትንሽ ራቅ ብለን የተሻለ ሰዋራ ሥፍራ እንፈልግ፣ ሳየነጋ›› አለ እጁን ወደሱ እየዘረጋ። እንደምንም ብሎ ተነሳና የበሪሁንን ትከሻ ተምርኩዞ ቀስ እያሉ ያዘግሙ ጀመር። ነግቶ አካባቢው ወለል ማለት ሲጀምር እጅብ አለ ቁጥቋጦ ውስጥ ገቡና አረፍ አሉ።

‹‹በጣም ጠዘጠዘኝ ምን ይሻላል?›› አለ አስግድ በጀርባው እንደተኛ የቆሰለ እጁን ወደ ላይ አርጎ። ሰውነቱ ይበልጥ ገረጣ፣ ከንፈሮቹ ደረቁ።

‹‹ጭሮሽ (በክረምት ጎርፍ ከሚወርድበት፤ ወይም ከረባዳ ስፍራ አሸዋው ማስ ማስ ሲደረግ የሚወጣ ውሃ) ልፈልግ፣ ውሃ አግኝተን ቁስሉን ብናጥበው ሻል ይልሃል ››

‹‹በአካባቢው የጭሮሽ ውሃ የሚገኝ አይመስለኝም››

‹‹ግድ የለህም ልፈልግ››

‹‹እሽሽሽሽ ድምጽ አይሰማህም?›› አለ አስግድ ቀና በማለት ድምጹ ወደ መጣበት አቅጣጫ ራሱን ዘንበል አርጎ። በሪሁን ጠመንጃውን ትከሻው ላይ ደግኖ ድምጹ ወደ ሚመጣበት አቅጣጫ ፈጠጠ። አስግድም በደህነኛ እጁ ቦንቡን ጨበጠ።

የጫካው ቅጠል ይንሹዋሹዋል። የሰው ወይም የሌላ ነገር ድምጽ ግን የለም። ትንፋሻቸውን ውጠው በጸጥታ ሲያዳምጡ፣ ጫካው በሰዎች የተሞላ ይመስል በዙሪያቸው ያለው ቅጠል ጠሰሰሰስ ይል ጀመር።

‹‹የጠላት ወታደሮች አካባቢውን በማሰስ ላይ ናቸው መሰለኝ›› አለ አስግድ በሹክሹክታ።

‹‹የያዝከውን ቦምብ እንዳትወረውር፤ ጥይታችን ሲያልቅ ለኛ ይሆናል›› አለ በሪሁን ድምጹ ወደ ሚመጣበት አፍጦ፡፡ ግመሎች ናቸው፡፡ ፍርሃታቸው ትንሽ መለስ አለ፡፡

‹‹ግመሎቹም ሆኑ እረኛዎቻቸው እንዳያዩን ጸጥ ብለን ባለንበት እንቆይ፡፡ እረኞች ጠመንጃ ይይዛሉ፡፡ ብዙም ሊሆኑ ይችላሉ›› አለ በሪሁን፣

ከፊት የቀደሙት ግመሎች ቅጠል እየቀነጣጠሱ ሲያልፉ፣ ከሁዋላ የነበሩት ሲከተሉ፣ እየራቁ ሄዱና አካባቢው እንደገና ጸጥ አለ››

ትንሽ ቆይቶ አንዲት ትንሽ ልጅ ቅልና በትንሽ የአንገት ልብስ መሳይ ጨርቅ የተቋዋጠረ ነገር ይዛ እያንጎራጎረች ባጠገባቸው አለፈች፡፡ በሪሁንና አስግድ በፍርሃታቸው ራሳቸውን ታዝበው ተያዩና ፈገግ አሉ፡፡

‹‹መጣሁ፤ ከዚህ እንዳትነቃነቅ›› አለ በሪሁን ብድግ ብሎ ፡፡

‹‹የት ትሄድ?››

‹‹ልጅቱን ውሃ ልለምናት››

‹‹አትሰጥህም ፤ እንደውም ካየችህ ትጮሃለች››

‹‹ግድ የለህም የማረገውን አውቃለሁ››

‹‹ልትገላት?››

‹‹ግድ የለህም ጠብቀኝ አልኩህ›› አለና ጠመንጃውንውን ዘቅዝቆ እንደያዘ ከቁጥቋጦው ወጣ፡፡ ልጅቱ ከአካባቢው ርቃለች፡፡ እየተገላመጠ እሮጥ እሮጥ አለ፡፡ ግመሎቹን በሩቁ አያቸው፡፡

‹‹ልጅቱ ውሃውን አልሰጥህም ብትለኝስ? አስግድ እንዳለው ስታየኝ ብትጮህስ? በአካባቢው ሰዎች መኖራቸው የማይጠረጠር ነው፡፡ እንዴት ባረግ ይሻላል?›› እያለ ሲያደባ ድንገት አንድ ሰው አየ፣

ምርኩዝ ይዛ የምታዘግም ባልቴት:: እርጅና አጉብጥዋታል፣ ግራ ጡትዋና ግራ እጅዋ ከትከሻዋ ጀምሮ ራቁታቸውን ናቸው:: በሪሁንን ስታየው፤ «እህህ! ሃህ" ብላ የመውደቅ ያህል ቁጭ አለች:: ፈጠን ብሎ ተጠጋትና፣ «ቢዮ ፣ ቢዮ (ውሃ ውሃ ) ፈልጋለሁ» አላት በቀኝ አውራ ጣቱ ወደ አፉ እያመለከተ::

«አሼ! አሼ!» እያለች ተጣራች:: ቀደም ብሎ እነበሪሁን ያዩዋት ትንሽ ልጅ እየሮጠች መጣችና፣ በሪሁንን ስታየው ቀጥ ብላ ቆመች::

«አምጪ ውሃውን» አለች ባልቴትዋ እጅዋን ወደ ልጅቱ ዘርግታ:: ልጅቱ አይኖችዋን ከበሪሁን ላይ ሳታነሳ ቅሉን ለባልቴትዋ ሰጠቻት:: ባልቴትዋ በሚንቀጠቀጥ እጅዋ ለበሪሁን ሰጠችው:: «የሚበላ ነገር!» አለ በሪሁን ውሃውን በእጁ ይዞ ልጅቱ ወደ ያዘችው ቁዋጠሮ እየተመለከተ:: ልጅቱ እያንገራገረች፤ የያዘችውን ቁዋጠሮ ወደ በሪሁን ወረወረችና፣ በቁጥቋጦው ውስጥ እየተሹለከለከች ሮጠች፣ ሊከተላት ፈልጎ ሮጥ ቢል፣ እንኩዋን ሊይዛት በአይኖቹም ሊያያት አልቻለም:: የጣለችውን ቁዋጠሮና ውሃውን ይዞ ወደ አስግድ ተመለሰ::

«ውሃ አገኘህ? ሰጠችህ?» አለ አስግድ በሪሁን የያዘውን ቅል እየተመለከተ::

«አዎ፤ መጀመሪያ ግን እንደምንም ብለን ከዚህ መራቅ አለብን:: ልጅትዋ ሮጣ ነው የሄደችው፣ ሰዎች ለመጥራት ሳይሆን አይቀርም» አለ በሪሁን ወደሁዋላ እየተገላመጠ::

እየተሹለከለኩና እየተገላመጡ ልጅቱ ከሄደችበት አቅጣጫ በተቃራኒ ሮጡ:: እየራቁ በሄዱ መጠን ቁጥቋጦዎቹ እየሳሱ፣ ሜዳው እየሰፋ የታይ ጀመር:: ውሃ በሸረሸረው ቦይ ውስጥ ለግማሽ ሰዓት ያህል ተጉዋዙና ቆም አሉ:: የተከተላቸው ሰው የለም:: አካባቢው ጸጥ ያለ

ነው።

አንድ ግርራር ዛፍ ስር አረፍ ብለው፣ ከቅሉ ውሃ ትንሽ ተጎነጩና፣ ርሃባቸውን ለማስታገስ እየተጣደፉ ቁዋጠሮውን ቢፈቱት፣ ጥሬ ማሽላ ሆኖ አገኙት። ተያዩና የንዴት ፈገግታ ተለዋወጡ። በምሬት የራሰው አፋቸው መልሶ ደረቀ፤ በምግብ ፍላጎት የተላወሰው አንጀታቸው የፈለገውን ስለ አጣ እን ደ ሐምሌ ሰማይ በቁጣ አስገመገመ።

በሪሁን የቅሉን ውሀ በሁለቱም ኮዳዎች ሞልቶ፣ በተረፈው የአሰግድን ቁስል ሙልጭ አርጎ ካጠበለት በሁዋል፣

‹‹የረጋው ደም መወገዱ ጥሩ ነው፤ ቁስሉ አያቂምም›› አለ። ከዚያ የራሱን ሸሚዝ ቀዶ ቁስሉን ደህና አርጎ አሰረለትና፤

‹‹ትንሽ ተኛ፤ ይሻልሃል፤ ጥላ በረድ ሲል ጉዞዋችንን እንቀጥላለን›› አለ እጆቹን እያደራረቀ።

አሰግድ ጋደም እንዳለ እንቅልፍ ሸለብ አረገው። በሪሁን ይህን ሲያይ ጠመንጃውን ይዞ አካባቢውን ሊቃኝ ከቁጥቋጦው ውስጥ ወጣ። ትንሽ እልፍ አለና ጉብታ ላይ አለ ግራር ዛፍ ላይ ወጣ። አካባቢው ወለል ብሎ ታየው።

‹‹የት ነው ያለነው? የቀብሪደሃር አቅጣጫ በየት የሆን?›› አለ ዙሪያ ገባውን እየተመለከተ። በሩቁ ከሚያያቸው ጉብታዎች የሚያውቃቸውን በምልክት ለማስታወስ ሞከረ። ሙቀቱ እያጥበረበረው አጥርቶ ለማየት አልቻለም።ብቻ አንድ ነገር ልብ አረገ፣ ወደ ቀብሪደሃር ከሚወስደው የመኪና መንገድ ርቀው ወደ ሰሜን አቅጣጫ መጉዋዛቸውን። ወደ መንገዱ ለመጠጋት ቢያንስ የግማሽ ቀን ጉዞ እንደሚጠብቃቸውም ገመተ።

ከሼኮሽ ወደ ቀብሪደሃር በመኪና ከሁለት ሰዓት በላይ ያስኬዳል።

ርቀቱም ከመቶ ኪሎ ሜትር በላይ ነው።

«በእግር ጉዞ በስንት ሰዓት እንደርስ ይሆን? ምን እየበላንና እየጠጣን? መንገዱስ ከወላት ጦር ነፃ ይሆን? ግድ የለም ፣ የሆነው ይሁን፣ እንሞክራለን። ብቻ አሰግድ በበረታልኝ ፣ ህክምና ካላገኘ ቁስሉ ይመረቅዛል...። ለምለምና ልጆቼስ እንዴት ሆነው ይሆን? ምናልባት የወገን ጦር ሸክሽ ደርሶ ሙዋቾቹ ሁሉ ታውቀው፣ አስከሬናቸው ተቀብሮ መርዶው ለቤተሰቦቻቸው ቢነገር፣ ለለምለም ምን ይሉዋት ይሆን? ሞቶ ብላና ቁርጥዋን አውቃ እንድታለቅስ አትሆን፣ ወይ አለ ብላ አትጠብቀኝ፣ አንድ ቀን እንኳዋን ሳይደላት...» አለና ራሱን የነቀነቀ። አይኖቹ እንባ አቀረሩ። «ማን ያውቃል፣ በሁሬያችን ካለው ሞት አምልጠን አንድ ቀን ያገናኘን ብቅ ስንል ‹አልል ባሌ ከመቃብር ወጥቶ መጣልኝ› ብላ ትቀበለኝ ይሆናል፣ ብቻ እስቲ አሰዋም ደህና ትሁን» እያለ ከባሩ ላይ ወረደ። ወደ ነበረበት ሲመለስ አሰግድ ሲያቃስት አገኘው።

«በረሀን አልቻልኩም፣ በጣም አመመኝ፣ ሰውነቴ ነደደ፣ እራሴ ዞረ» አለ አሰግድ ቁስለኛ እጁን በሌላው ደግፎ። ልብሱ በላብ ርስዋል፣ አይኖቹ ቀልተዋል።

«አይዞህ ፣ ሙቀቱ ስለ አየለ ነው።ጥላ በረድ ሲል ይተውሃል» አለ በርይሁን የአሰግድን ቁስል እያየ

"ጨርቁን ፍታው" አለ አሰግድ እየተወራጨ።

«አይዞህ ጠንክር በል፣ ምንም አይልህ። ስጋ ለስጋ የሄደ ጥይት አይደለም እንዴ? መግል ሲይዝ ነው» ቆጣ አለ።

አሰግድ የቁስሉን ስቃይ አልቻለውም። በእንብርኩ እየዳኸ ጥርሱን ነክሶ ያቃስት ጀመር። በሪሁን በጣም ጨነቀው፣ የጉዋደኛውን ስቃይ

ሲያይ እሱም ህመም ተሰማው። ሲያበረታታው ኮስተር ቢልም ውስጡ ተጨነቀበትና፡

‹‹ቁጭ ብለህ ስለ ምታሰላስለው ነው ህመሙ የሚሰማህ፡ጨከን በልና እናዝግም›› አለ።

‹‹በየት በኩል፤ ወዴት? እስካሁን ወዴት እንደምንሄድ አውቀሀል?››

‹‹አዎ፤ ያለንበትን አውቄዋለሁ። ወደ መኪናው መንገድ ጠጋ ብለን ዳንዳርን እየተጓዝን ቀብሪደሃር እንገባለን››

‹‹ቀብሪደሃር? እህእ፣ እህህህ›› ደረቅ ሳቅ ሳቀ።

‹‹ምነው?"

‹‹ምንም፤ እሺ ተነስ እንሂድ›› በሪሁን ቀበቶውን ፈቶ አሰግድ አንገት ላይ አጠለቀለትና ለቁስለኛ እጁ መደገፊያ ካበጀለት በሁዋላ

"ጠመንጃህን ስጠኝና ቅደም" አለው።

‹‹ግድ የለም እኔ ይዘዋለሁ››

‹‹ቦምቡን የዝና ጠመንጃውን ስጠኝ፣ አይመችህም››

በጥንቃቄ እየተመለከቱና ቦታ እየመረጡ አቅጫጫቸውን ወደ መኪናው መንገድ በማቅናት ጉዞውን ተያያዙት። ጸሃይ ዘቅዘቅ እስክትል ረጅም መንገድ ተጓዙ። በሪሁን የአሰግድን ድካም አይቶ ከአንድም ሁለት ጊዜ ‹‹እዚህ እንረፍ›› ብሎት ነበር። ‹‹ ደህና ነኝ፣ እንቀጥል›› እያለ እምቢ አለው። በሁዋላ ግን እግሮቹ ሲጋጩና ሲንገዳገድ ስላየው አንድ ምቹ ቦታ መርጦ፣

‹‹እዚህ ማረፍ አለብን›› አለው ። ሌሊቱን እዚያው አደሩ። አሰግድ ጥርሱን ነክሶ ሲያቃስት፣ ሲቃዥ፣ ሲወራጭ፣ በሪሁን አጠገቡ ተቀምጦ ሲጨነቅ ነጋላቸው።

ማለዳ አስግድ ከተጋደመበት ቀና አለና፣

‹‹ለኔ ብለህ የምትሰቃይበት ምክንያት የለም፣ ሂድ ፣ መንገድህን ቀጥል›› አለ በተዳከመ ድምጽ፡፡

‹‹ምንም ስቃይ የለብኝ፤ አብረን ነው የምንሄደው፡፡ እንዴት ጥዬህ ሄዳለሁ›› እያለ ሲናገር አቋረጠውና፣

‹‹ መሄድ አለብህ፡፡ መትረፍ ስትችል ለኔ ብለህ የምትሞትበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ እኔ በየቀኑ በመሞት ላይ ነኝ፡፡ የሞት መጋዝ ይገዘግዘኛል፤ ቆርጦ ሊጥለኝ ትንሽ ነው የቀረው፡፡ በዚህ ሁኔታዬ ያን ሁሉ መንገድ ልጉዋዝ አልችልም፡፡ ይህን አንተም ታውቀዋለህ...ሂድ፣ ቀብራዳሃር ለመድረስ የምትችለውን ሁሉ ሞክር፡፡ እኔ ግን የምመክርህ ወደ ቀብሪደሃር ከምትመለስ በዚሁ ወደ ደገሃቡር እንድትሄድ ነው፡፡ ከዳር ያለው ሕዝብ ወደ መሃል ሲሸሽ አንተ ወደ ዳር የምትሄድበት ምክንያት አልገባኝም፡፡ እህ እህ፣ ብቻ ወደምትሄድበት ሂድ፣ ለኔ ካዘንክልኝና ከወደድከኝ ግን ስቃዬን ቀንስልኝ፡፡ መሞቴ ላይቀር ስቃዬ ለምን ይብዛ? አንድ ጥይት አትንፈገኝ፣ ይህን ነው በዚህ ጊዜ እንደትልቅ ውለታ የምቆጥረው ››

‹‹አላረገውም አስግድ፣ አላደረገውም፡፡ አብረን እንደወጣን አብረን እንመለሳለን፡፡ ካልሆነም የሚመጣውን ነገር አብረን እቀበለዋለን፡፡ ሞት እንደሆነ የጠላት ጉዋደዋኛችን ነው፤ አብሮን ነው የኖረው፡፡ ስንታገለው እስከ ዛሬ ኖረናል፤ ወደ ፊትም የምንችለውን ያህል ታግለነው ይውሰደን እንጂ በቀላሉ አንንበረከክለትም፡፡ እውነተኛ ባልንጀራ ጉዋደኛውን ከሞት ይከላከላል፤ ካልሆነለትም አብሮት ይሞታል እንጂ፣ አይገለውም፡፡ ወደ ቀብሪደሃር ለምን ትመለሳለህ ላልከኝ ደሞ፣ ሁለት ዋና ዋና ምክያቶች አሉ፡፡ አንደኛ የበላይ አካላችን ማለት የፊጥኖ

ደራሹ ፖሊስ መምሪያ ያለው እዚያ ስለሆነ ሄደን ሪፖርት ማረግ አለብን። ሁለተኛ፣ እነ ለምለምንም ትተናቸው የመጣነው እዚያ ነው። ስለዚህ እዚያ ደርሰን ሁኔታውን ማየት አለን፤ ጠሩና ሕዝቡ የሚሆነውን መሆን ይኖርብናል››

"እኔ እዛም ስለማልደርስ ያለኩህን አርግልኝ"

"ኢሆንም፣ አላረገውም አልኩህኮ"

‹‹ተወው፤ እኔ አረገዋለሁ። ያኔ አንተም ነፃ ትሆናለ››አለና በጀርባው ተኛ። ለጥቂት ጊዜ ዝም ተባባሉ። በሪሁን የአሰግድን ንግግር ያሰላስል ጀመር፣ ‹‹ራስን ለገድል?›› አለና ጠጋ ብሎ፣

‹‹እየሀ አሰግድ፣ ችግርና ስቃይ እንዳይደርስ አስቀድሞ መከላከሉ ብልህነት ነው። ይህ ሳይቻል ቀርቶ ችግሩ ከመጣ ግን፣ እንዳመጣጡ መቀበልና ፊት ለፊት የተጋረደውን የችግር ተራራ ሰርስሮም ቢሆን፣ ለማለፍ መሞከር እንጂ፣ መሸሽ ተገቢ አይደለም። ብልህነትና ቆራጥነት የሚፈለገውም እንዲህ ባለው ጊዜ ነው። እስከ ዛሬ የምንችለውን ሁሉ አርገናል። ወደፊትም የበለጠ መስዋእትነት ይጠብቀናል። ጠንክሮና ሌላ መስዋዕትነት ከፍሎ መሞት ጀግንነት ነው። ለዚያ ሳይደርሱ እራስን ማጥፋት ግን ሽሽት ይሆናል›› አለ።

አሰግድ በጀርባው እንደተጋደመ ወደ ላይ አፈጠጠ። እንባው በጎደጎዱ አይኖቹ ጠርዝ ቁልቁል ወደ ጆሮዎቹ ወረደ። የተሰነጣጠቁ ከንፈሮቹን ነከሰ። በሪሁን ከአንገቱ ቀና አረገና ትኩር ብሎ አየው።

‹‹ውሃ አጠጣኝ›› አለ በሹክሹክታ፣ የቀራቸው ውሃ ከኮዳ ግማሽ ያነሰ ነው። በኮዳው ክዳን እየቀዳ ካጠጣው በሁዋላ፣ በጨርቅ የታሰረውን ጥሬ ማሽላ እየፈታ፣

‹‹ይረዳናል፤ ትንሽ እንቆርጥም›› አለ። ዝም ብሎ አየው፣ አሰግድ።

እሱ እየቆረጠመ፣ ለአስግድም አቃመው። መቆርጠም አቃተውና ተፋው።

በሪሁን ጠመንጃውን ዘቅዝቶ እንደያዘ ከቁጥቋጦው ወጣ። አስግድ ይሄኔ ቦምቡን ከኪሱ አውጥቶ አየና፣

‹‹እራሴን ስገድልለት ነፃ ይሆንና የማምለጫ እርምጃው ይፈጥንለታል›› እያለ ቦመቡን ልቡ ላይ ይዞ ሊያፈነዳ ሲዘጋጅ፣

‹‹ጀግንነት የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሳይከፍሉ እራስን ማጥፋት ሽሽት ነው!!›› የሚለው የበሪሁን ንግግር በጆሮው አስተጋባ።

‹‹የቦምቡን ድምጽ በአካባቢው ያለ የጠላት ጦር፣ ወይም ነዋሪው ቢሰማ፣ በሪሁንን ለአደጋ የሚዳርግ ሁኔታም ይፈጠራል›› እያለ ሲያመነታ በሪሁን ሁለት ጠፍጣፋ ድንጋዮች ይዞ መጣ።

‹‹ምን ልታረግ ነው አንተ!›› እያለ የያዛቸውን ድንጋዮች በቁመ ለቀቃቸውና ቦምቡን ነጥቆት ራሱን ሲነቀንቅ ቀየና፣

‹‹በጣም አዝናለሁ አስግድ፣ ኃበዝ ጉዋደኛ አለኝ እያልኩ እመካብህ ነበር። እንዲህ በአጭሩ ተስፋ የምትቆርጥና ለቀላል ፈተና የምትንበረከክ ነህ ለካ›› ብሎ፣ እንደተደጋሞው ሲቆጣውና ሲመክረው ከቆየ በሁዋላ፣ ያመጣቸውን ድንጋዮች አመቻችቶ አንዱን ወፍጮ ፣ ሌላውን መጅ በማረግ ማሽላውን ይፈጭ ጀመር። አስግድ ባረገው ሙከራ በጣም ተጸጸተ፣ በሪሁንን እንዳሳዘነው ተሰማውና፣

‹‹በሪሁን›› አለ በደካማ ድምጹ። በሪሁን ወፍጮው ላይ እንዳጎነበሰ ዝም ብሎ አየው።

‹‹ይቅርታ አርግልኝ ፣ በጣም አሳዘንኩህ፣ የሁለታችንንም ስቃይ የምቀንስ መስሎኝ ነው››

‹‹የኔን ስቃይ የምትቀንስልኝ በምልህ ነገር ስትተባበረኝ ነው።

ያንተ ስቃይ የሚቀንሰው፣ በራስህ ጥንካሬ ቢሆንም፣ እየተመካከርን የሚበጀንን ስናረግም ነው››፡፡

‹‹እሺ፣ ላለፈው ይቅርታ፤ ወደፊት አልደግመውም››

በሪሁን የፈጨውን የማሽላ ዱቄት ውሃ ባለበት ኮዳ ውስጥ ጨምሮ በመበጥበጥ፣ እራሱ ፉት ካረገ በሁዋላ፣ አሰግድን ካንገቱ ቀና አርጎ፣

‹‹ውተት ውተት ነው የሚለው፤ ይህን ስትጠጣ ትበረታለህ፡፡ ምንም ቢሆን የእህል ዘር ነው፣ በሽታውም ሻል ይልልሃል ›› አለ፡፡ አሰግድ የተሰጠውን እየደጋገመ ተጎነጨና፣

‹‹አንተ ደሞ ጠጣ›› አለ፡፡ ኮዳውን መልሶ እየገፋለት፡፡

‹‹እኔ በቃኝ አንተ ጠጣ››

በሪሁን ኮዳውን ከድኖ አስቀመጠው፡፡

‹‹አትጠጣም እንዴ?››

‹‹ግድ የለም፣ የተረፈው ይቀመጥልን››

በሪሁን ለቁስለኛ ጉዋደኛው አዝኖ ቆጠበለት እንጂ፣ እሱንም እቡና ሆነ ጥሙ ጎድቶታል፡፡ ለሁለት ቀናት ተከታል ያህል እህል አልቀመሱም፣ ጦር ሰፈራቸው በነበሩ ጊዜም ቢሆን ቀለብ አልቆባቸው ስለ ነበር፣ በግማሽ ርሃብ ነው የሰነበቱት፡፡

‹‹እንዴት ነው ቁስልህ? ትንሽ አልተሻለህም?›› አለ በሪሁን የአሰግድን ቁስል እየተመለከተ፡፡

‹‹አታየውም፣ እብጠቱ ትከሻዬ ደርሶ›› አለና ገለጥ አርጎ አሳየው፡፡ የግራ እጁ ሽሚዝ እጅጌ እሁለት ላይ ተሰንጥቅዋል፡፡ የቁስሉ እብጠት እየገፋ በመሄዱ ነበር የተረተሩት፡፡

‹‹ቀስ እያልን ብናዘግምስ?›› አለ በሪሁን ጭንቅ እያለው፡፡

‹‹እንሞክር›› አለና የበሪሁንን ትከሻ ተሞርክዞ ብድግ አለ፡፡

ከነበሩበት ቁጥቋጦ ወጥተው ትንሽ እንደተጓዋዙ ቀጭን የእግር መንገድ አገኙ። በዚያ ሲጓዋዙ ቆይተው ጥቅጥቅ ካለ ጫካ አካባቢ ሲደርሱ የሰዎች ድምጽ ሰሙና ቆሙ። በርይሁን ቦምቡን ለአሰግድ ሰጠው። ጠመንጃ የያዙ ሁለት ሰዎች ድንገት ከፊትለፊታች ብቅ አሉ። በሪሁን ጠመንጃውን ደገነ። አሰግድም ቦምቡን አመቻቸ። ሁለቱ ሰዎች አሮጌ ጠመንጃቻቸውን በጀርባቸው በኩል ትከሻቸው ላይ አግድም እንደ ዱላ እንደያዙ ዝም ብለው ቆሙ።

አንደኛው ረዘም ያለና ወደ ጥቁረቱ የሚያደላ ጠይም ነው። ከወገቡ በታች በእርጅናና በእድፍ የገረጣ ቫርጉርጉር ሽርጥ አገልድሞ፣ ከወገቡ በላይ በላብ የጠቆረች አሮጌ ሸሚዝ ለብሶዋል። ትልቅ ቢላዎ ታጥቆአል። እንደ ፍየል ጢም የሾለ ጢሙን በቀጭኑ እየላጨ ጆሮው አካባቢ ካለው ጸጉሩ ጋር አገናኝቶታል። ከግንባሩ ገለጥ ያለ ጎፈሬው በመጠኑ ተከርክሞ ስር ስሩ ተላጭትዋል። የአካባቢውን ጎልማሶች የሚወክል ቁመናና መልክ ነው ያለው።

ሌላው ሰውዬ አጠር፣ ፈርጠም ያለ ሆኖ፣ የራስም ሆነ የጺም ጸጉር የለውም፤ ተላጭቶታል። አለባበሱና ሌላ ሁኔታው እንደጓዋደኛው ሆኖ፣ ከወገቡ በላይ እራቁቱን ነው። የደረቱ አጋማሽ በጸጉር ተሸፍንዋል። በኮስታራ ግንባሩ ስር ጭልጭል የሚሉት ትንንሽ ዐይኖቹ ተንኮለኛ አስምለውታል።

በሪሁን ጠመንጃውን መለስ አረገና በሱማሌኛ፣

‹‹እንደምናችሁ ፤ ከየት ነው የምትመጡት?›› አለ ሰዎቹ የአካባቢው ከብት አርቢዎች መሆናቸውን በመገመት። ሰዎቹ ድንጋጤያቸው መለስ አለላቸውና፣

‹‹ የአካባቢው ነዋሪዎች ነን›› አለ ረዘም ያለው ሰውዬ።

‹‹ለስራ ጉዳይ በአካባቢው ስንዘዋወር ይህን ጉዋደኛዬን አንበሳ ነከሰው›› አለ በሪሁን ወደ አሰግድ ቁስል እያመለከተ፡፡ ሰዎቹ ቁስሉን ሲመለከቱ ዘገነናቸው፡፡

‹‹ታዲያ ከመኪናው መንገድ ርቃችሁ ወዲህ ለምን መጣችሁ?›› አለ አጭሩ ሰውዬ አይኖቹን አሰግድ ቁስል ላይ እንደተከለ፡፡

‹‹አንበሳውን አቁስለነው ስለ አመለጠን እሱን ፍለጋ ነበር ›› አለ በሪሁን ፣ የፈጠረው ምክንያት ምን ያህል እንዳሳመናቸው ለማወቅ ሰዎቹን እያየ፡፡ ሰዎቹ ዝም ብለው እነበሪሁንን በአይኖቻቸው ይመረምሩዋቸው ጀመር፡፡

‹‹ውሃና ምግብ ብትፈልጉልን ትልቅ እርዳታ ነው፡፡ ገንዘብ እንከፍላለን›› አለ በሪሁን፡፡ ሁለቱ ሰዎች ተያዩና፣

‹‹ተከተሉን›› ብለው ወደ መጡበት አቅጣጫ ተመለሱ፡፡ እነበሪሁን ቀረት ብለው በዝምታ ተያዮና ተከተሉዋቸው፡፡

‹‹እነዚህ ሰዎች ወዴት ነው የሚወስዱን? በርግጥ ዘላኖች ናቸው? በአካባቢው የጠላት ጦር እንቅስቃሴ መኖሩን ሳያውቁ አይቀሩም፣ የነሱ ደጋፊዎች እንደሆኑስ? ጠቁመው አደጋ ቢያስጥሉብንስ?" ተባባሉ በሹክሹታ፡፡

# ምዕራፍ አራት

እነ በሪሁንን ያስከተሉዋቸው ሰዎች ግማሽ ሰዓት ያህል ከተጉዋዙ በሁዋላ ገላጣ ስፍራ ላይ የተተከሉ ሶስት ደሳዎች (ጎጆዎች) አሉበት ሲደርሱ ቆሙ፡፡ ሁለቱ ደሳዎች ጐን ለጐን ሲሆኑ፣ በሮቻቸው ትይዩ ናቸው፡፡ አንደኛው ደሳ ደሞ አስር እርምጃ ያህል እልፍ ብሎ ጀርባውን ለሁለቱ ደሳዎች በመስጠት ተተክልዋል፡፡ ሁለቱ ደሳዎች አጠገብ በእሾህና በደረቀ ጭራሮ የተከለለ የከብቶች በረት አለ፡፡ እልፍ ብሎ ለማገዶ የሚሆን ደረቅ እንጨት ተከምርዋል፡፡ አንዲት ህጻን እተቀራረቡት ደሳዎች መሃል አለ ሜዳ ላይ እራቁትዋን ተቀምጣለች፡፡ ከአፍንጫዋና ከአፍዋ በሚወጣው ፈሳሽ የራሰውን የማሽላ ቂጣ የሚሻማት የገነብ መንጋ ቀፎው ላይ የሰፈረ ንብ ይመስላል፡፡

እነበሪሁንን ይዘዋቸው ከሄዱት ሁለት ሰዎች ረዘም ያለው ቀየው ሲደርስ፣ ድምጹን ከፍ አርጎ ተጣራ፤ አንዲት ልጅ እግር ሴትዮ ከወደ ጉዋሮ ብቅ አለች፡፡

‹‹ምንጣፍ አምጪልን›› አለ ረጅሙ ሰውዬ ሴትዮየቱን እየተመለከተ፡፡ ከቁጠማ የተሰራ ምንጣፍ ሜዳ ላይ ከተነጠፈ በሁዋላ፣

‹‹ተቀመጡ፣ ውሃ አመጣላቸሁዋለሁ›› አለ ረጅሙ ሰውዬ፡፡

አሰግድ ምንጣፉ ላይ ጋደም እንዳለ ቀና ብሎ በሪሁንን አየው፡፡ ቃላት የሌለው ጥያቄ ተለዋወጡ፡፡

‹‹አቡዋራችሁን ታጠቡ›› አለ ረጅሙ ሰውዬ በትልቅ ቅል ውሃ አመምጥቶ፡፡

‹‹ይጠጣል?›› አለ በሪሁን ቅሉን ከሰውዬው እየተቀበለ፡፡

‹‹አዎ፤ ይጠጣል›› አለ ሰውዬው ሳቅ ብሎ፡፡

አስግድ ውሃውን ከበሪሁን ተቀብሎ ትንሽ እንደተጎነጨ ፤ በሪሁን ቅሉን ከአፉ ላይ ያዘበትና፤

‹‹በባዶ ሆድህ ብዙ አትጠጣ›› ብሎ ከውሀው እየተጎነጨ ሁለቱ ተጉመጥምጦ ተፋ፡፡

ምሽት ቢሆንም ወበቁ እንዳለ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ለብ ያለ የበረሃ ንፋስ ሽው ይላል፡፡ አሰግድ፤ በሪሁንና አስተናጋጆቻቸው ውጭ ተቀምጠው ያወሩ ጀመር፡፡ የአስግድን ቁስል የሚያክምለት መድሀኒት አዋቂ እንደሚያያመጡለት ሰዎቹ ገለጡላቸው፡፡ የነ አሰግድን አመጣጥ ለማጣራትም አሰግድን በጥያቄ ያዋክቡት ጀመር፡፡ አሰግድ በአካባቢው ያለውን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ይመለከታል፡፡ ጠመንጃውን ጠበቅ አርጎ እደያዘ ነው፤ የእጁ ህመም ሻል ብሎታል፡፡

ጨረቃ የምትወጣው ዘግይታ በመሆኑ፤ ገና ጸሃይ ከመጥለቅዋ አካባቢው በጭለማ ተጋረደ፡፡ በጭስ የጠቆረና ደብዛዛ ብርሀን የሚረጭ ፋኖስ ትነሽ ልጅ አንጠልጥሎት፤ በወተት የተቀቀለ ሩዝ ዳርዳሩ ላይ የማሽላ ቂጣ ተደርጎበት በእርጌ ሳህን፤ አንዲት ሴት ይዛ ከአንደኛው ደሳ ውስጥ ብቅ አለ፡፡ ሁለቱ ወንዶችና፤ እነ በሪሁን በሳህኑ ዙሪያ ተሰብስበው ይመገቡ ጀመር፡፡ በሪሁንና አስግድ ያለሃፍረት እየተሻሙ በሉ፡፡

‹‹ጠላኸው እንዴ? የግመል ወተትኮ መድሃኒት ነው፡፡ ቁስልህን ቶሎ ያድንልሀል ›› አለ አንደኛው ሰውዬ አስግድ በኩባያ የተሰጠውን ወተት እንዳልወደደው ተረድቶ፡፡

‹‹የግመል ወተት ሲጠጣ ያስቀምጠዋል፤ ይቅርበት›› አለ በሪሁን

በርሃብ የተጎዳው የአሰግድ ሆድ በወተቱ ተቆጥቶ እንዳያመው በማሰብ፡፡

‹‹የላም ወተት ይምጣለት?›› አለ አጭሩ ሰውዬ ለልጆች ትእዛዝ ለመስጠት ዞር እያለ፣

‹‹ይቅርብኝ፣ ለአሁኑ ውሃ እጠጣለሁ›› አለ አሰግድ በተሰባበረ ሁማሌኛ፡፡

ከእራት በሁዋላ፣ አጭሩ ሰውዬ ብድግ ብሎ እየተንጠራራ፣

‹‹እንግዲህ እንደተነጋገርነው መድሃኒት አዋቂውን ሰውዬ ልጆች ሌሊት ሄደው ያመጡታል፡፡ ሰውዬው የታወቀ ነው፡፡ በአንዴ ነው ቁስሉን የሚያሽረው፡፡ አሁን መኝታችሁን እናሳያችሁና እረፉ፤ ደክምዋችሁዋል››አለ፡፡ በዚሁ መሰረት፣ እነበረሁንን አስከትሎ ለብቻው ወዳለው ደሳ ሄደና፣

‹‹ይሄ የኔ ቤት ነው፡፡ እዚህ ታድራችሁ›› አለ ፋኖሱን ይዞ ደሳው ውስጥ እየገባ፡፡ እነበርይሁን አልተከተሉትም፡፡

"ግቡና ተኙ ተነጥፎላችሁዋል" አለ ሰውዬው ከድሳው እየወጣ፡፡

‹‹እሺ እንገባለን፣ እናንተ ሂዱ ደህና እደሩ›› አለ በረሁን በአክብሮት፡፡

ሰዎቹ ከሄዱ በሁዋላ እነበረሁን ደሳው ውስጥ ገቡ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ ፋኖሱን አጥፍተው ከደሳው ወጡና፣ ወደ ጉዋሮ በመዞር እልፍ ብሎ ያለው ቁጥቋጦ ውስጥ ገቡ፡፡ እዚያ ከተጸዳዱ በሁዋላ እልፍ ብለው ምቹ ቦታ መረጡና አደፈጡ፡፡

‹‹አንተ ትንሽ ጋደም በል እኔ ጠብቃለሁ ›› አለ በረሁን በሹክሹክታ፡፡ እስከ እኩለ ሌሊት አሰግድ ካንቀላፋ በሁዋላ፣ በረሁንን ሰወጠው፡፡ ስለተጠራጠሩ ደሳው ውስጥ ለማደር አልደፈሩም፡፡ ፡

አንድ ቀን እንዳደሩ መድሃኒት አዋቂው ሰውዬ መጥቶ የአስግድን ቁስል አጥቦ ከቅጠላቅጠል የተቀመመ መድሃኒት አሰረበት፡፡ ቁስሉ ከባድ ስለሆነ በተደጋጋሚ መታከም የሚኖርበት መሆኑንም ነግረዋቸው ሄደ፡፡

በሶስተኛው ቀን ማታ እራታቸውን በልተው፣ ከአስተናጋጆቻቸው ጋር ሲያወሩ አንድ ሰውዬ መጣ፡፡ እነበሪሁን ሰውዬውን በጥርጣሬ ይመለከቱት ጀመር፡፡ ረጅሙ ሰውዬ ሁኔታቸው ስለገባው፣

‹‹ይህ ሌላ ስፍራ የሚገኝ ዘመዳችን ነው፣ ሊጠይቀን ነው የመጣው›› አለ፡፡ እንግዳውም አብሮዋቸው ሲጫወት አመሸ፡፡ እነበሪሁን ወደ ጎጆዋቸው ከተመለሱ በሁዋላ፣ ቀስ ብለው ወደ ውጭ በመውጣት፣ አካባቢውን ሲቃኙ አመሹ፡፡ የጨረቃዩቱ ብርሃንዋን ድብዝዝ ያለ ነው፡፡ አካባቢውን ሲቃኙ ቆዩና አንድ ሰዋራ ቦታ አረፍ አሉ፡፡ ጭር ብልዋል፡፡ ከሩቅ የአንበሳ ግሳት ይሰማል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጥቂት እንደቆዩ፣ በሪሁን ድንገት አስግድን ያዝ አረገውና ‹‹ጎንበስ በል›› አለው በሹክሹክታ፡፡ ወዲያው አንድ ነገር በአጠገባች ውልብ ብሎ አለፈ፡፡ አሉበት ሆነው በፀጥታ ሲመለከቱ፣ አንድ ሰው አጠገባቸው ያለው ጉብታ ላይ ወጥቶ መቆሙን አዩ፡፡ ሰውዬው ማታ የመጣው እንግዳ መሆኑንም አረጋገጡ፡፡

‹‹እናፍነው›› አለ አሰግድ በሹክሹክታ፡፡ በሪሁን "ዝም በል" የሚል ምልክት እያሳየው ወደሰውየው አፈጠጠ፡፡ ትንፋሻቸውን ውጠው ይመለከቱ ጀመር፡፡ ሰውዬው ለረጅም ጊዜ ከቆየ በሁዋላ ግራና ቀኝ መልከት መልከት አረገና፣ በቀስታ አፍዋጨ፡፡ ጠመንጃ የያዙ አራት ሰዎች ተከታትለው መጡ፡፡ ሰዎቹ የያዙዋቸውን መሣሪያዎች አይነት ለመለየት በይቻልም፣ አለባበሳቸው ከአካባቢው ነዋሪዎች

የተለየ አይደለም። ከእንግዳው ሰውዬ ጋር በሹክሹክታ ከተነጋገሩ በሁዋላ፣ እነበረሁን ወደ ነበሩበት ደሳ አመሩ፤ እነበረሁንም ቀስ እያሉ ሰዎቹን ተከተሉዋቸውና እንቅስቃሴያቸውን በግልጽ ሊያዩ እሚችሉበት ስፍራ ከለላ ይዘው ቆሙ።

ሰዎቹ እነበረሁን ጎጆ አጠገብ ሲደርሱ ፈንጠርጠር ብለው ጠመንጃዎቻቸውን ወደ ደሳው በር ደግነው ቆሙ። እነሱን እየመራ ያመጣቸው እንግዳ ሰውዬ እነበሪሁንን የሚያስተናግዱዋቸውን ሰዎች አመጣቸው። ሰዎቹ የሚሉት አይሰማ እንጂ፣ ከጎጆዋቸው አንስተው እነበሪሁን ደሳ አጠገብ እስኪደርሱ ከእንግዳው ሰውዬ ጋር ይጨቀጨቁ ነበር። ስፍራው ከደረሱ በሁዋላም እንኩንዋን፣ ሰውዬው የሚያዛቸውን ነገር እንፈጽምም እያሉ አስቸገሩት።

ጠመንጃ ይዘው ደሳው ፊተለፊት ከቆሙት ሰዎች አንዱ፣ በንዴት እርምጃ መጣና ጠመንጃውን ሁለቱ ሰዎች ላይ ደገነባቸው። አንደኛው ሰውዬ በድንጋጤ እየተርበተበተና ወደ ነበሪሁን ጎጆ እያየ፣

‹‹እንግዶች! የመንግሥት ወታደሮች!›› ብሎ ተጣራ። ከውስጥ ምንም መልስ የለም።

‹‹የመንግሥት ወታደሮች ፣ እናንተን ነው፣ እስቲ አንዴ ብቅ በሉ፣ መድሃኒት የሚያረግላችሁ ሰውዬ ይፈልጋችሁዋል። ከነገ ጀምሮ ወደ ሩቅ አገር መሄዴ ስለሆነ፣ አታገኙኝምና መድሃኒቱን አሁን ልስጣችሁ ይላችሁዋል›› አለ ደገመና። አሁንም ከደሳው ውስጥ መልስ የለም።

መሣሪያውን በነበርየሁን አስተናገጆች ላይ ደግኖ የነበረው ሰውዬ አጠገቡ የነበሩትን ሰዎች ወደ ሁዋላ ገለል እንዲሉ በእጁ ምልክት አሳያቸውና የደሳውን በር በርገጫ በረገደው። ቀጠለና ከገያው ቦምብ አውጥቶ ወደ ውስጥ በመወርወር በደረቱ ተኛ። በዚያው ቅጽበት

ከፍተኛ ብልጭታ ታየና ደሳው ብትንትን አለ። ጠመንጃ የያዙት ሁሉ ጥይቶቻቸውን በመጋየት ላይ ባለችው ደሳ ላይ አርከፈከፉባት።

በሪሁንና አሰግድ በእሳቱ ውጋገን እርስ ተያዩ። ሊደርስባቸው የነበረውን አደጋ አይተው ዘገነናቸው። እሳቱ ወደ መጥፋቱ ሲቃረብ ጠመንጃ የያዙት ሰዎችና መሪያቸው፣ አመዱን በእንጨት እየጫሩ መረመሩት፤ ምንም የለም። ከዚያ መለስ ብለው እነ በርይሁንን ያስተናገዱዋቸውን ሰዎች ከነቤተሰቦቻቸው እያቆራኙ በገመድ አሰሩዋቸውና፡

‹‹እዚህ ደሳ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ወዴት ሄዱ?›› እያሉ በዱላ ይደበድቡዋቸው ጀመር።

‹‹እንበላቸው›› አለ አሰግድ ቦምቡን እየመዠረ። የሰዎቹን ስቃይ ሲመለከት በጣም አዘነ።

‹‹ቆይ፤ ሌሎቹንም እብረን እንዳንፈጃቸው››

‹‹ታዲያ ሰዎቹን እኮ ገደሉዋቸው. . .››

‹‹ቆይ እስቲ›› አለ በሪሁን ቆጣ ብሎ።

የህፃናቱ ወይታ፣ የሴቶች ለቅሶ፣ የወንዶቹ ማቃሰት ያሳዝን ነበር። በዚህ ሁኔታ ከቆዩ በሁዋላ ገሪፊዎቹ ደከማቸውና፣ እልፍ ብለው ቀጥሎ ስለሚያረጉት ነገር ይመካከሩ ጀመር።

‹‹የሚመካከሩት ሊፈጁዋቸው ሳይሆን አይቀርም፤ የነዚህን ሰዎች ህይወት ማትረፍ አለብን። እነዚህን ነፍሰ ገዳዮች አሁኑኑ ልንቀድማቸው ይገባል። እኔ በግራ በኩል ተጠግቼ ቦምብ ልጣልባቸው፣ አንተ እዚሁ ሆነህ ልቀማቸው›› አለ አሰግድ ለመሮጥ እየተዘጋጀ።

‹‹ትችላለህ?››

‹‹አው››

‹‹ቀጥል››

እንበሪሁን በሰከንድ በሚቆጠር ጊዜ ሁሉን ፈጽመው የታሰሩትን ሰዎች ይፈቱዋቸው ጀመር፡፡ የፊጥኝ ታስረው ሞታቸውን ይጠባበቁ የነበሩት ሰዎች እንበሪሁንን ሲያዩ፣ በሞት ላይ ስልጣን ያላቸውና አላህ የላከላቸው መላእክት መሰሉዋቸው፡፡ አንገታቸው ላይ እየተጠመጠሙ በደስታ አነቡ፡፡

ከዚያም እንበሪሁን የተደበደቡ አስተናጋጆቻቸውን መክረውና አበረታትተው ሊነጋጋ ሲል ሰገሁ ተነሱ፡፡

‹‹ወዴት ነው የምትሄዱት አሁን? እዚህ መጥተው የሞቱ አባሎቻቸውን የሚፈልጉ የጠላት ወታደሮች ድንገት ካገኙዋችሁ...›› አለ አነደኛው ሰውዬ የምተለቅስ ህጻን ልጁን አቅፎ፡፡

‹‹ወደ ሼኮሽ ነው የምንመለሰው፤ አያገኙንም፣ ተጠንቅቀን እንጉዋዛለን›› አለ በሪሁን ትጥቁን እያጠባበቀ፡፡ እውነቱን አልነገራቸውም፤ ምናልባት የጠላት ጦር መጥቶ የመረመራቸው እንደሆን፣ ከስቃይ የተነሳ ሰዎቹ የነ በርይሁንን አቅጣጫ መናገራቸው ስለማይቀር የመሄጃ አቅጣጫቸው መደበቅ ነበረበት፡፡

‹‹እኛም እዚህ አንቆይም፤ እንሄደለን፡፡ በዚህ ሁኔታማ ምኑን ኖርነው?›› አለ አጭሩ ሰውዬ ክንዱ ላይ የተጋደመውን ሰንበር እያሻሸ፡፡

‹‹ወራሪ ጦር የሚያረገው ይህን ነው፡፡ ሰላም ማሳጣት፣ ህዝቡን ማሰቃየትና መጨፍጨፍ፣ መዝረፍ፡፡ ተባብሮ ጠላትን በቆራጥነት መከላከል ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ሰዎች መሀላችሁ ያሉ ጠላቶቻችሁ ናቸው...››አለ አሰግድ ሰዎቹን እየተሰናበተ፡፡

ሰዎቹ የማሽላ ቂጣ በአሮጌ ሸርጥ ቁዋጥረው፣ ውሃም

በኮዳዎቻቸው ሞልተው ለነበሪሁን አስያዙዋቸው። እነሱም ከሙዋቾቹ ካገኙዋቸው መሣሪያዎች ሁለት አውቶማቲክ የክላሽ ጠመንጃዎች፣ እንዲሁም በምቦችና ጥይቶች ወስደው፣ የራሳቸውን ጠመንጃዎችና ሌሎች መሣሪይዎች ለሰዎቹ ተዉላቸው። አነበርይሁን የመሣሪያውን አጠቃቀም ቢያውቁም ክላሽ ጠመንጃ ሲታጠቁ የመጀመሪያ ጊዜያቸው ነበር።

# ምዕራፍ አምስት

እነበሪሁን ካስታመሙዋቸውና ካስተናገዱዋቸው ሰዎች ተለይተው ጉዞ ከጀመሩ ሶስት ቀናት አልፍዋቸዋል፣ ቀን ከጸሃዩ ሙቀት፣ ከአሸዋው ግለት፣ ከውሃ ጥሙ፤ ሌሊት ከአውሬ እየታገሉ። የአሰግድ ቁስል እልፎ አልፎ ቢያመረቅዝም እብጠቱና ስቃዩ ቀንሶለታል።

ወደ ቀብሪደሃር የሚወስደውን አውራ ጎዳና በሩቁ እያዩ፣ ሜዳውን እያቋዋረጡና በየቁጥቋጦው እየተሹለከለኩ ገሰገሱ። አልፎ አልፎ በብዛት የሚርመሰመሰው የጠላት ጦር ሲያጋጥማቸው እየተሸሸጉ ያሳልፉት ነበር።

‹‹ቀብሪደሃር ደህና አትመስለኝም›› አለ በሪሁን በሰፊው ተንፍሶ

‹‹ምን ትሆናለች?›› አለ አሰግድ።

‹‹ይሄ ሁሉ ጦር በዚያ እያለፈ አይደለም የሚመጣው?››

‹‹የጦሩ ዓላማ መንገድ ለመዝጋት ስለሆነ፣ በሌላ አቅጣጫም ሊመጣ ይችላል››

‹‹ይሆናል››

ጉዞ በጀመሩ በአምስተኛው ቀን ለአይን ያዝ ሲያረግ ወደ ቀብሪደሃር ተቃረቡ። መሽትሽት እንዲልላቸው ከለላ ይዘው አረፍ አሉ። የተሽከረካሪዎች ድምጽ ከሩቁ ይሰማቸዋል። ከአውራ ጎዳናው ላይ አቡዋራ ወደላይ ይነሳል። ቀደም ብለው ካዩዋቸው የበለጡ የጠላት ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች እየተከታተሉ አለፉ።

‹‹ያለ ጥርጥር ቀብሪደሃር ተደምስሳለች ›› አለ በሪሁን አይኖቹን ወደ ከተመይቱ አቅጣጫ በጉዝጉዝ እርጎ። አስግድ በበሪሁን ንግግር ያመነበት ቢሆንም፣ ጉዋደኛውን ለማጽናናት በማሰብ፣

‹‹አይመስለኝም፤ እስቲ እናያለን። የለምለምንና የልጆቼን እራሳቸውን እንኳዋን ማየቱ አንድ ነገር ነው፣ ቁርጡን ማወቁ›› የነበረው የተስፋ ብርታት የሳሳበት መሰለ።

ምሽቱ ገፋ ሲያረግ፣ በጭለማው በመከለል በዘጠነኛ ብርጌድ ጦር ሰፈር አልፈው ከተማዋ መዳረሻ ላይ አለው አፋፍ ላይ ብቅ አሉ። ለወትሮው እዚህ ተሁኖ ቁልቁል ሲመለከቱዋት ከተማይቱ በኤሌክትሪክ ብርሃን ደምቃ ትታይ ነበር። ዛሬ ግን ጭለማ ውጥዋታል። ጦር ሰፈሩ ውስጥ ጭስ ይታያል። ወደዚያ መሄዳቸውን ትተው ወደ ቀኝ ታጠፉ። በከተማይቱ ዙሪያ አልፎ አልፎ ብልጭ ድርግም የሚል ብርሃን ይታያል፣ የተሽከርካሪዎች ድምጽም ይሰማል። ተሽከረካሪዎቹ ታንኮች መሆናቸውን በድምጻቸውና በመብራታቸው መለየት ይቻላል።

ከኮረብታው ወርደውና በአይሮኘላን ማረፊያው አቋርጠው ገነት ካምኘ ይባል ከነበረው የፊጥኖ ደራሽ ፖሊስ ጦር ሰፈራቸው ደረሱ። ለጥቂት ጊዜ ገዝም ብለው በአትራቢያው ተሸሸጉ፤ አካባቢው ጭር ብልዋል። የሚንቀሳቀስ ፍጡር ያለበት አይመስልም። ቀስ እያሉ በሪሁን ወደ ነበረበት ቤት ተጠጉ፤ የቤቱ አንድ ጎን ተደርምስዋል። እንዳሊሉት ቤቶች ውጪ ላይ ብዙ እቃዎችና ልብሶች ተበታትነዋል። እቃዎቹ መሃል የአንድ ሰው እሬሣ ተጋድምዋል። በሪሁን ፈጠን አለና እሬሣውን ገለበጥ አርጎ ደሰሰው ፤ ፊቱ በደም የተሸፈነ የአንድ አባውንት እሬሣ ነው። ጭለማ ስለሆነ ማንነቱን ለማወቅ አይቻልም።

በሪሁን ፈረሰው ቤቱ ውስጥ ገባ፡፡ ጭለማው ከውጩ ይብሳል፡፡ በዳባሳ ወደ ጉዋዳ ገባና ጨለማው ላይ አፈጠጠ፡፡ የሚስቱ ጠረን ሸተተው፣ የልጆቹን ትንፋሽ የሰማ መሰለው፡፡ እየኼዳኽ አልጋዎቹንና ወለሉን ዳሰሳቸው፣ ከቤቱ ፍርስራሽ አፈር በቀር ምንም የለም፡፡ የጠላት ጦር ክተማይቱን እንዳጠቃና እንደያዛትም አረጋገጠ፡፡

በርይሁን ሲቃ ይዞት ከግድግዳ ግድግዳ ሲላጋ በተደረመሰው ጣራ በኩል ሃይለኛ ብርሃን ታየው፡፡ በር ላይ ቆሞ የነበረው አሰግድ ድምጹን ዝቅ ድርጎ ‹‹ባውዛ በማብራት ላይ ናቸው›› እያለ ወደ ውስጥ ገባ፡፡ ከተማዋ መግቢያ ላይ የሚበራው ባውዛ ጨረሩን እያዙዋዙዋረ ከተማይቱን  በብርሃኑ ከዳር እስከ ዳር ከዳሰሳት በሁዋላ ድርግም አለና ጥቁሩ ጭለማ በቦታው ተመለሰ፡፡ በአካባቢው ከሚርመሰመሱት ታንኮች አንዱ ወደ ከተማይቱ እንብርት መጣ፡፡

ባሉበት ቢቆዩ የሚጠብቃቸውን አደጋ በመረዳት ቀስ ብለው በመጡበት አኩዋሁዋን ከከተማየቱ ወጥተው ኮረብታው ላይ ቁጭ አሉ፡፡

‹‹ከተማይቱ በከባድ መሣሪያ ትድብድብ እንጂ ብዙ ህዝብ የተጎዳ አይመስለኝም›› አለ አሰግድ በሹክሹክታ፡፡

‹‹ሕዝቡ ወዴትና እንዴት ሄደ? ለምለምና ልጆቼ እንዴት ሆነው ይሆን?›› አለ በሪሁን ጨለማው ላይ አፍጦ፡፡

‹‹ሕዝቡ እንደሆነ ይሆናሉዋ፤ በተገኘው ነገር፣ በተሽከርካሪም በእግርም  እየሆኑ ጠላት ከመምጣቱ በፊት ጉዞ ጀምረው ይሆናል፡፡ ክፉው ነገር በየመንገዱ የሚገጥማቸው አደጋ ነው፡፡ ሕዝቡ ክተሰባሰበና እየተረዳዳ ከተጉዋዘ፣ ግን መንገዱን በሰላም ሊዘልቀው ይችላል››

‹‹ያን ሁሉ የጠላት ጦር እንዴት ያልፉታል? ›› አለ በሪሁን

የሚሰቱና የልጆቹ ስቃይ እየታየው። ለምለም ትንሹን ልጅዋን አዝላ፣ ትልቁን ይዛ በኦጋዴን በረሃ ስትንከራተት፣ ውሃ ጥሙ፣ ርሃቡ፣ መንገዱ፣ አድከምዋቸው ተዝለፍልፈው ሲወድቁ፣ ጨካኙ የጠላት ወታደር በታንክ ሲወጣባቸው...ለአንድ አፍታ አእምሮው ብልጭ አለበትና ዘገነነው፣ ራሱን አዞረው፣ አጥወለወለው።

‹‹ምንድነው የምናረገው?›› አለ  አሰግድ ተስፋው ሙትት ባለ አነጋገር።

‹‹እ? ኡፍ፣ ምን አልከኝ››?

‹‹ምንድነው የምናረገው? ወዴት ነው የምንሄደው?››

‹‹ወደ መጣንበት እንመለሳለን››

‹‹የመጣንበትኮ ተደምስዋል፣ መንገዱ ሁሉ በጠላት ተይዝዋል››

‹‹በመንገዱ አንሄድም። ወደዚህ በመጣንበት ሁኔታ እንመለሳለን። ደሞም አገሩ ሁሉ በጠላት አልተያዘም። እስካልተያዘው ሰፍራ ተጉዘን እዚያ ካለው የወገን ጦር ጋር በመቀላቀል የምናረገውን እናረጋለን›› አለ በሪሁን በእልህ።

በከተማይቱ ዙሪያ የሚርመሰመሱት ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ብዛት እየጨመረ መጣ። መብራቶቻቸውን አብርተው፣ በረደፍ እየሆኑ ሲሽከረከሩ በሩቁ ለሚያያቸው፣ አካባቢው የአሸዋ ሜዳ ሳይሆን፣ ትልቅ ከተማ፣ ተሽከርካሪዎቹም የትራፊክን ስርዓት እየጠበቁ የሚጉዋዙ ተሽከርካሪዎች ይመስሉ ነበረ። ድምጻቸው እንደንብ መንጋ ‹‹እምም›› ይላል።

ጉብታው ላይ ያለው ባውዛ እንደገና በራና ብርሃኑን ወደ ላይ ሰደደው። ይሄኔ ተሽከርካሪዎቹ በሙሉ መብራቶቻቸውን አጠፉ፣ ድምጻቸውም ጸጥ አለ። የሌሊቱን ጭጋግ እየሰነጠቀ ቀጥ ብሎ

የወጣው የባውዛ ጨረር ጫፉ የማይታይ ምሰሶ ይመስላል።

‹‹የወገን አይሮፕላን ሳይመጣ አይቀርም፣ የቦምብ ድብደባ ከጀመረ ሁኔታው አስከፊ ይሆናል፣ እንሂድ›› አለ በሪሁን ብድግ ብሎ።

ሁለቱም ተነስተው ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ከተማዪቱ ተመለከቱ። ጥቁሩ ጭለማ ውጥዋታል። መለስ ብለው በሞት ጥላ ውስጥ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

# ምዕራፍ ስድስት

‹‹አሁን ያለንበት ሁኔታ በቀላሉ የማንወጣው ሊሆን ይችላል። ቢሆንም እጃችንን ጠላት አይዘውም። ጥለን መውደቅ አያቅተንም፣ ሌላው ቢቀር. . .›› አለ በሪሁን አንድ ረባዳ ሥፍራ በደረታቸው ተኝተው ለተኩስ ሲዘጋጁ። የጠመንጃዎቻቸውን መጠበቂያዎች ለቀው፣ ጣቶቻቸውን ምላጩ ላይ በማሳረፍ ወደ አንድ አቅጣጫ አነጣጥረው ይጠባበቃሉ።

መንገድ ላይ አደጋ ሲያጋጥማቸው ይህ የመጀመሪያቸው ባይሆንም፣ የአሁኑ ጠንከር ማይል አይቀርም። ከቀብሪደሃር ተነስተው፣ እንደሰዶም እሣት የቃላትን የሺኮሽ ከተማ አመድ በሩቁ እያዩ አልፈው በስድስት ቀናቸው ብርቆት ከተባለ አካባቢ ደረሱ። ከርሃብ ይልቅ የጎዳቸው ውሃ ጥሙ ነው። ለምግባቸው ሚርሚር የሚባል ዛፍ ፍሬና አንዳንድ ቅጠሎች በመመገብ ረሃባቸውን ሊያስታግሱ ችለዋል። የነበራቸው ውሃ እስከ መንገዳቸው አጋማሽ ሸኝትዋቸው አለቀ። በየደረሱበት የጭሮሽ ውሃ ፈለጉ፤ አልተሳካላቸውም። በየሜዳው ካጋጠሙዋቸው የዱር አራዊት ገድለው መመገብ ሲችሉ፣ አካባቢው የጠላት ጦር ያለ በመሆኑ የሚተኩሱት የጥይት ድምጽ የሚያስከትለውን ጉዳት በገመት ተዉት።

በጉዝዋቸው ሁሉ አንድ ቀን ብቻ ነበር የተሳካላቸው። ቁጥቋጦ ውስጥ ተሸሽገው፣ የአካባቢው እረኞች ከሚነድዋቸው ብዙ ፍየሎች

አንድዋን አፍነው ለማስቀረት በቻሉበት እለት፡፡ ፍየልን፣ በተለይም የአጋዴንን ፍየል ይዞ ዝም ማሰኘት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን የተረዳው በሪሁን ባስገራሚ ፍጥነት የፍየሊቱን ጉሮሮ በሳንጃ በመበጠስ ጸጥ አሰኛት፡፡ ሌሎቹ ፍየሎችና እረኞቹ ከአካባቢው ሲርቁላቸው፣ ጨጉዋራዋን አወጡና ፈርሱን ጨምቀው ጠጡት፤ ጥሬውን ሊበሉት የሚችሉትን ስጋ በሉ፡፡ ያ አጋጣሚ ትንሽ ብርታት ሰጣቸው፡፡

ካደፈጡበት ቁጥቋጦ እልፍ ብሎ በሚታየው ሰፊ ሜዳ ላይ ነበር የጠላት ጦር እየመጣ መከማቸት የጀመረው፡፡ ዋናውን መንገድ ይዞ ከቀብሪደሃር አቅጣጫ ይመጣና፣ ብርቆት አቅራቢያ ሲደርስ ወደ ግራ እየታጠፈ ወደ ሜዳው ይገባል፡፡ ካሚዮኖች፣ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች፣ ታንኮች ...እየመጡ ተደረደሩ፡፡ ወታደሩ ከየካሚዮኖቹ እየወረደ ሜዳው ላይ ይርመሰመስ ጀመር፡፡ ጦሩ ለእረፍት እንጂ እነሱን ለመክበብ ያልመጣ መሆኑን ሲገነዘቡ ነው ትንሽ የተረጋጉትና በጠላት እንዳይታዩ ይበልጥ የተጠነቀቁት፡፡ አጋጣሚው የጠላትን ጦር ሁኔታ ለማጥናት አመቺ ሆነላቸው፡፡

ጀንበር ዘቅዘቅ ስትል የጠላት ጦር እንደገና ጉዞ ጀመረ፡፡ እንዳመጣጡ ቅደም ተከተል ተንቀሳቅሶ ሲያበቃ አካባቢው ፀጥ አለ፡፡ እነበሪሁንም ከተደበቁበት በጥንቃቄ ወጡ፡፡ የተለቀለቀ ውድማ ይመስል የነበረው አሸዋማ ሜዳ፣ በምግብ ትርፍራፊ ፣ በነዳጅና በዘይት ነጠብጣብ፣ በብጥስጣሽ ወረቀቶችና በምግብ ቆርቆሮዎች ተሸፍኖ፣ የገጠር ገበያ የዋለበት መስልዋል፡፡

እነ በርይሁን በገላጣው ስፍራ እልፍ ብለው ሲመለከቱ፣ አንድ አነስተኛ የወታደር ጂፕ መኪና ከዋናው መንገድ ወጣ ብላ ቆማለች፡፡ ቁጥቋዋጦውን ከለላ አርገው ወደ መኪናይቱ ተጠጉ፡፡ ሁለት

ወታደሮችየመኪናይቱን ሞተር ለማስነሳት ይታገላሉ።

‹‹እንበላቸው›› አስግድ ወደሰዎቹ አፈጠጠ።

‹‹ቆይ!›› ቆጣ አለ በሪሁን።

ቀደም ብለው ከስፍራው የተንቀሣቀሱት ተሽከርካሪዎች ድምጽ ለጆሮ እየራቀ ቢሄድም፣ የሚያነሱት አቡዋራ አፈርማ ደመና እየሰራ ከሩቅ ይታያል። ሁለቱ የጠላት ወታደሮች የመኪናይቱን ሞተር ለማስነሳት ታግለው ስላልሆነላቸው፣ አንደኛው ወታደር የሬድዮ መነጋገሪያውን አነሳና እጁን እያወራጨ ከሌላ ስፍራ ከሚያነጋግረው ሰው ጋር ሲጨቃጨቅ ቆየና፣ መነጋገሪያውን በንዴት ወረወረው። መሀረቡን ከኪሱ አውጥቶ የፊቱንና የአንገቱን ላብ እየጠራረገ እነበሪሃን ወደነበሩበት ቁጥቁዋጦ መጣ።

‹‹ልበለው?›› አለ አስግድ ተቁነጠነጠ።

‹‹ቆይ›› አለ በሪሁን የወታደሩን እንቅስቃሴ በትኩረት እየተመለከተ።

ወታደሩ ከኪሱ ሲጃራ አውጥቶ ለኩሶ እያጨሰ በቀጥታ ወደነሱ መጣ። በሪሁን ቀስ ብሎ ጠመንጃውን አስቀመጠና ጎንበስ ብሎ ድኩላ እንደየ ነብር አደባና ወታደሩ አጠገባቸው ሲደርስ፣ ቀልጠፍ ብሎ ሳንጃውን ጉሮሮው ላይ ሰካበትና ወዱዋላ ዘረጠጠው።

‹‹ያኛውን ልበለው?›› አለ አስግድ ወደ ሌላኛው ወታደር እያነጣጠረ።

‹‹በለው?››

ወታደሩ እንደኩዋስ ወደ ላይ ጉኖ መኪናዋ ስር ተዘረጋ። ሁለቱንም ወታደሮች በርብረው ጠቃሚ ነው የሚሉትን ነገር ሁሉ ወሰዱ። መኪናይቱ ውስጥ ያገኙትን ምግብና ውሃ፣...ከያዙ በኋላ የመገናኛ

ሬድዮኑን ከመኪናው ለማላቀቅ ቢሞክሩ አልሆን ስለአላቸው አበላሹትና ጉዞዋቸውን ቀጠሉ፡፡

ጸሐይ ከምእራብ አድማስ ጉዋሮ ዞራ፣ ሙቀቱ በርዶ መንገዳቸውም እየቀና ሲጉዋዙ፣ ሁለት የጦር አይሮኘላኖች ከበላያቸው እያፉዋጩ አለፉ፡፡ በድንገጤ ተያኢተው የተሻለ መሸሸጊያ ሲፈልጉ፣ ሩቅ ሰማይ ላይ እንደሚያስገመግም መብረቅ ያለ ድምጽ ሰሙ፡፡ በሪሁን ቆመና፣

‹‹የወገን አይሮኘላኖች ናቸው፤ ቀደም ብሎ ከዚህ የተንቀሣቀሰውን የጠላት ጦር አፈር አበሉት፣ ይሄ ነው!›› አለ እሩቅ እያየ፡፡ ሁለቱም ቆመው በሩቁ የሚትጉላጉለውን ጥቁር ጭስ ሲመለከቱ፣ አይሮኘላኖቹ እንደገና መጡና በመንደድ ላይ በነበረው የጠላት ጦር ላይ የቦንብና የመትረየስ ተኩስ አወረዱበት፡፡ የቃጠሎው ነበልባል ከጥቁሩ ጭስ ጋር እየተጯካከረና እያሸነፈ ሰማይን ለመላስ የሚንጠራራ መሰለ፡፡

እነ በሪሁን ባዩትና እነሱም ባደረሱት ጥቃት ተደሰቱ፤ ሃይላቸው ታደሰ፣ ብርታት ተሰማቸው፡፡

‹‹ከአደጋው የተረፉና የሸሹ የጠላት ወታደሮች ከፊታችን ያጋጥሙን ይሆናል፡፡ ከዚህም ሌላ ጠላት የደረሰበትን ጥቃት ሲረዳ፣ ረዳት ጦር ወደ ስፍራው ይልክ ይሆናል፡፡ ስለዚህ፣ የሚቀጥለው ጉዞዋችን ዝግ ያለና ጥንቃቄ ያልተለየው መሆን አለበት››አለ በሪሁን፡፡

ቀን ዝም ያለው ንፋስ በጸሃይ መራቅ እንደፈነደቀ ሁሉ እንዳሻው ይጋልብ ጀመር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደሞ አሸዋውን እየሸመለለ ጫፉ የማይታይ የአሸዋ ምሰሶ ይሰራል፡፡

‹‹ነገ ደገሐቡር እንደርሣለን፤ እስዋም በጠላት ጦር መያዝዋ

ማይጠረጠር ነው›› አለ በሪሁን ሌሊቱን ካረፉበት ተነስተው በንጋት ጨረቃ ሲጉዋዙ።

‹‹እንዲያ ከሆነ፣ በከተማይቱና በአካባቢዋ የጠላት ጦር ኖራል›› አለ አሰግድ።

‹‹ይህ አይቀርም፤ ጠላት ያጋዘውን ሠራዊትና ዘመናዊ የጦር ሣሪያዎች የሚያከማቸው በሚይዛቸው ቁልፍ ቦታዎችና ከተማው ካባቢ ነው። እስካሁን ካለፍንባቸው አካባበዎች ይልቅ የጠላት ጦር ሚበዛው ከፊታችን ነው›› አለ በሪሁን።

# ምዕራፍ ሰባት

እነበሪሁን እንደገመቱት ወደ ፊት እየገፉ በሄዱ ቁጥር፣ በአካባቢው የሚርመሰመሰው የጠላት ጦር ብዛት ጨመረ። በተለይ ወደ ደገሃቡር ሲቃረቡ ጉዞዋቸው አስቸጋሪ ይሆን ጀመር። ቢሆንም ከተማይቱ ውስጥ ሳይገቡ ለማለፍ አልፈለጉም። ቀኑን እንደተለመደው ቁጥቋጦ ውስጥ ተሸሽገው ዋሉና ለአይን የገዘ ሲያረግ ጉዞ ጀምረው፣ ሲነጋጋ ከተማይቱ አቅራቢያ ደረሱ። ከተማይቱን መሀል ለመሀል ሰንጥቆ በሚያልፈው ጨረር ወንዝ አቅራቢያ ምቹ የመደበቂያ ስፍራ መርጠው ቀኑን ለማሳለፍና እዚያው ለመቆየት ወሰኑ።
ጸሐይ ምሥራቅ አድማስ ላይ የጋለ አለሎ ስትመስል አካባቢው ወለል አለ።

‹‹እስቲ ዙሪያውን ልቃኝና ልምጣ። አንተ እዚሁ ቆይ›› አለ በሪሁን ብድግ ብሎ።

‹‹የከተማ አካባቢ ስለሆነ በቀላሉ ትጋለጣለህ!››

‹‹ግዴለህም አልጋለጥም። እዚሁ ቆየኝ መጣሁ ››ብሎ ከቁጥቋጦው ወጣ።

አሰግድ በጀርባው ተንጋሎ ስለ ደረሰበት አደጋ፣ ከሞት ጋር እየታገለ ስለተጉዋዘው ረጅም ጎዳና፣ ወደ ፊት ስለሚገጥሙት ችግሮች ሲያሰላስል፣ በአቅራቢያው የሰዎች ንግግር ሰማ። ጠመንጃውን በተጠንቀቅ ይዞ ሲመለከት፣ አራት ሰዎች ፍየሎች እየነዱ አለፉ። እነሱ አልፈው ጥቂት እንደቆዩ በሪሁን በሌላ አቅጣጫ ብቅ አለ።

‹‹እንዴት ነው አካባቢው?›› ትኩር ብሎ አየው፡፡ በረሁን ቁጭ ብሎ በሰፊው ተነፈሰና፣

‹‹ከተማይቱ በጠላት ጦር ተይዛለች›› አለ፡፡

‹‹በአቅራቢያው ብዙ ወታደሮች አሉ?››

‹‹የወታደር ተሽከርካሪዎች ከሩቅ ይታያሉ፡፡ ብዙ አይደሉም እንጂ፣ ሰላማዊው ሕዝብም ከተማይቱ ውስጥ ውርውር ይላል፡፡ ከተማይቱን ይበልጥ ተመልክቼ መምጣት አለብኝ››

‹‹የማያስፈልግ መስዋእትነት ከምትከፍል ለምን አንድ ነገር አርገን አንሞትም?›› ቆጣ አለ ሰግድ፡፡

‹‹ምንም አልሆንም፣ ይህን ያልኩት ሁኔታው ምቹ መሆኑን ስለተረዳሁ ነው፡፡ ሰላማዊው ህዝብ ከየአቅጣጫው ወደ ከተማይቱ በመግባት ላይ መሆኑን ለመገመት ችያለው፡፡ የንግድ ልውውጥም የተጀመረ ይመስለኛል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ተጠቅሜ አንዳንድ ሁኔታዎችን ለማጣራት ችላለሁ፡፡ የጠላት ጦር ወደ መሀል ባረገው ጉዞ የደረሰበትን ስፍራ ማወቁ ይጠቅመናል፡፡ ምናልባት ከወገን ጦር ጋር ብንቀላቀል ሊጠቅም የሚችል መረጃ ማጠናቀርም ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ አንተ እዚሁ ቆይ፡፡ እኔ ደርሼ መጣለሁ›› እያለ ብድግ አለና ማሰኖዳውን (የጦር ሜዳ ሻንጣ) ይከፋፍት ጀመር፡፡

‹‹እኔም ሄዳለሁ›› ብድግ አለ፣ ሰግድ፡፡

‹‹አይሆንም፣ አንተ እዚሁ ቆይ፡፡ ቀደም ሲል የኖርኩበት ስለሆነ፣ ከተማውን በሚገባ አውቀዋለሁ፡፡ አካባቢውን መስዬ ቋንቋዋውን እየተናገርኩ የምችለውን ለማረግ ሞክራለሁ፡፡ አንተ ቋንቋዋውን በደንብ ስለ ማትችል በቀላሉ ትጋለጥ ይሆናል፡፡ ከዚህም ሌላ ያለን ሽርጥ አንድ ብቻ ነው፡፡ እሱን እኔ ለብሼ ሄዳለው ላንተ የሚሆን የለም

ከዚያ በራሁን የለበሰውን የወታደር ልብስ አውልቆ፣ ቀደም ብሎ አስግድን ያስታመሙት ሰዎች ምግብ ቁዋጥረውበት የሰጡዋቸውን አሮጌ ሸርጥ አገለደመ። ከላይ በላብ የጠቆርች ካኔቴራውን ብቻ ለበሰ። ጫማውን አወለቀ። አንድ ቦምብ ጉያው ደበቀና፦

‹‹በል እንግዲና ከዚህ ንቅንቅ እንዳትል ፣ራስህን ደብቅ። በአስር ሰአት እመለሳለሁ። ከዚያ ከዘገየሁ እስከ አስራሁለት ሰዓት ጠብቀኝ። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ካልመጣሁ፣ ቦታህን ለውጥና ለጥቂት ጊዜ ሁኔታውን አረጋግጠህ ጉዞህን በመጣንበት ሁኔታ መቀጠል ትችላለህ። ቻዎ!›› ብሎት ዙሪያ ገባውን እየቃኘ ከቁጥቋጦው ወጣ። ከአካባቢው እልፍ እንዳለ፣ ከብቶች የሚነዱ ሰዎች አገኘና ቀልቀል አለ። ከተማው መግቢያ ላይ ሲደርስ ወታደሮች አየና ደንገጥ ብሎ ቦምቡን ዳበሰ።

"በፍተሻ ያገኙብኝ ይሆን?›› ብሎ ሰጋ።

ወታደሮቹ አጠገብ ሲደርስ አብረውት የነበሩት ሰዎች አንድ በንድ እየተፈተሹ አለፉ። የወታደሮቹ አፈታተሽ መሰላቸት የሚታይበትና ጥንቃቄ የጎደለው ነበር። እየሣቀና ዘና እያለና አብረውት የነበሩትን ሰዎች እየመሰለ ፍተሻውን በሰላም አለፈ። ትንሽ እንደ ሄደ ሌሎች ወታደሮች አቆሙዋቸው። እነዚህኞቹ ቀረጥ አስከፋዮች ናቸው። እሱ የያዘው ከብትም ሆነ ሌላ የሚሸጥ እቃ ስላልነበረው አልፎ ሄደ። ወደ ከተማው እንብርት ሲቃረብ፣ ከርምጃው ዝግ ብሎ አካባቢውን ይቃኝ ጀመር። ደገሃቡርን ቀደም ብሎ የሚያውቃትና የኖረባት ስለሆነ የሚዘዋወርበትን አቅጣጫ ለመምረጥ አልተቸገረም። አልፎ አልፎ የወታደር መኪናዎች ውር ውር ይላሉ። በየቦታው ወታደሮች ቆመዋል። ቀደም ብለው ቡና ቤቶች የነበሩና ሌሎች ጥሩ ጥሩ ቤቶች

የወታደሮቹ መገልገያ ቢሮዎችና ማረፊያዎች ሆነዋል።

የጠላት ጦር ከተማይቱን በወረረ ጊዜ ወደ ገጠር የሸሹት የአካባቢው ብሄረሰብ አባላት በመመለስ ላይ ናቸው። ቢሆንም አብዛኛዎቹ መኖሪያ ቤቶች አሁንም ዝግ። በጦርነቱ ወቅት የነደዱ የጠላት ታንኮችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ከሰል መስለው በየመንገድ ዳር ተገትረዋል።

ከተማይቱ ውስጥ እየተዘዋወረ እነዚህን ሁሉ በጥንቃቄ በማጥናት ላይ እንዳለ፣ ድንገት አይኖቹ በአጠገቡ በማለፍ ላይ በነበረ አንድ ሰውዬ ላይ አተኩሩ። ሰውዬውም በአጸፋው ትኩር ብሎ አየው። ከተላለፋ በሁዋላ ሰውዬው ዞር እያለ በረሁንን ይመለከተው ጀመር።በረሁን ሰውዬውን የት እንደሚያውቀው ለማስታወስ እየሞከረ ከርምጃው ፈጠን አለ። በጉዞው ላይ እንዳለ በሃሣቡ ብልጭ አለበትና ሰውዬው ቀደም ብሎ አዚያው ደገሃቡር ከተማ ውስጥ የሚኖርና እስማኤል የሚባል ነጋዴ መሆኑን አስተወሰ።

‹‹ባናግረው ምን ነበረበት? እሱስ ለምን አላናገረኝም? ቢያውቀኝ ነው ልብ አርጎ ያየኝ" እያለ በፍርሀት ጉዞውን ወደ ሌላ አቅጣጫ ሲያቀና እስማኤል ተከተለው።

‹‹ይሄዋ! ሊያስይዘኝ ነው›› አለ፣ የልቡ ምት እየፈጠነ፣ ቦምቡን ዳበስ አረገና እንደገና ወደቀኝ እጥፍ በማለት ስረቅ እያደረገ ወደ ሁዋላ ቢመለከት እስማኤል የሚከተለው መሆኑን ተረዳ። ለመሮጥ አሰበ። በአካባቢው ብዙ ሰዎች ውርውር ስለሚሉና ወታደሮችም ስለሚበዙ ድርጊቱ ለባሰ አደጋ እደሚዳርገው አስቦ ፍርሀቱን ዋጥ በማረግ ረጋ አለ።

ሰዎች ከሚበዙበት አካባቢ እልፍ እንዳለ፣ እስማኤል ከበረሁን

ሁዋላ ሮጥ እያለ፡፡

‹‹ቤሩን! ! ቤሩን!›› ብሎ ተጣራ፡፡ በርሀን እንዳልሰማ ሆኖ እርምጃውን አፈጠነ፡፡

‹‹ቤሩን አትፍራኝ፣ አይዞህ ቆየኝ፣ እናግረኝ›› አለ እስማኤል ድምጹን ዝቅ አርጎ፡፡ በርይሁን እስማኤልን ሌላ ሰው ያልተከተለው መሆኑን ተረድቶ ከመንገድ ወጣ አለና አንድ ቤት ጥግ ቆመ፡፡

‹‹ቆሞ መነጋገር ክልክል ነው፡፡ ዝም ብለህ ተከተለኝ›› አለ እስማኤል ጨብጦት እያለፈ፡፡ እየተጠራጠረ ተከተለው፡፡ ትንሽ እልፍ እንዳሉ እጥፍ አሉና አንድ ቤት ውስጥ ገቡ፡፡ ቤቱ ከጨፈቃ ተሰርቶ ጣራው በአሸዋ የተከደነ ነው፡፡ ክፍሉ ውስጥ ሁለት አግዳሚዎችና አንድ ትንሽ ጠረጴዛ አሉ፡፡ እስማኤል በቀጥታ ወደ ውስጠኛው ክፍል ሲገባ በርይሁን ቆም አለ፡፡

እስማኤል ደገሃቡር ከተማ ውስጥ አሉ ከሚባሉት የሸቀጣ ሸቀጥ ነጋዴዎች አንዱ ነበር፡፡ በርይሁንና አንዳንድ ጉዋደኞቹ፣ ሲኖራቸው እጅ በእጅ በመክፈል፣ ሳይኖራቸው በዱቤ የሚፈልጉዋቸውን እቃዎች በመውሰድ የረጅም ጊዜ ማሚላቸው(ደንበኛቸው) አርገውት ነበር፡፡ ወዳጅነታቸው ከዚያም አልፎ አንዳንድ ውስታዎች እስከመለዋወጥ ከፍ ብሎ ነበር፡፡

‹‹ግባ ወደ ውስጥ አትፍራ፣ እመነኝ፡፡ እኔ አንተን ለማስያዝ ብፈልግ ምንም ጊዜ አይወስድብኝም፡፡ ግን አላረገውም፡፡ ወላሂ እመነኝ ቤሩን›› አለ እስማኤል ወደ ሁዋላ መለስ ብሎ እየሣቀ፡፡ ተከታትላው ወደ ጉዋዳ እንደገቡም፣

‹‹ተቀመጥ፣ ሻይ ይምጣልህ›› እያለ ወደ ውስጠኛው ክፍል ለሲገባ ሲል፣

‹‹የለም፣ ግድ የለም፣ አልቀይም ሄዳለሁ፡፡ ይልቅስ የምንነጋገረውን እንነጋገር›› አለ በሪሁን የእስማኤልን እጅ ያዝ አርጎ፡፡

እስማኤል አበሪሁን ጐን ቁጭ አለና አንድ እጁን ትከሻው ላይ ጣል አርጎ አይን አይኑን እያየ፣

‹‹ቤቱን አይዞህ እመነኝ፡፡ አብረን ኖረናል፡፡ ምንም ሣትጠራጠርና ሳትፈራ ማንኛውንም ነገር ንገረኝ›› አለ፡፡

‹‹ስለምን?›› ትኩር ብሎ አየው፡፡

‹‹ስለማንኛውም ነገር- ለመሆኑ ከየት መጣህ?››

‹‹ከሴኮሽ››

‹‹ጣቢያው ተደምስዋል፣ ብዙ ሰው ተጎድትዋል ሲባል አልሰማህም?››

‹‹እኔ ተረፍኩ››

‹‹እንኩዋን አላህ አተረፈህ፡፡ ከጦርነቱ የተረፈው ህዝብ ሁሉ ቀደም ብሎ ሲያልፍ አንተ እስከዛሬ የት ቆየህ?››

‹‹በእግር ጉዞ ከመንገድ ውጭ በመጉዋዜና ትንሽ ስለ አመመኝ ነው እስከ ዛሬ የቆየሁት፡፡ ለመሆኑ የደገሃቡር ህዝብ እንዴት ሆነ?››

‹‹ህዝቡና ጦሩ ለረጅም ጊዜ በታላቅ ጀግንነት ከጠላት ጋር ተዋግቶ፣ በየስፍራው ተገትረው ያየሀቸውን ታንኮችና ተሽከርካሪዎች አውድሞ ፣ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ የጠላት ወታደሮች ደምስሶ ነው ከተማይቱን የለቀቀው፡፡ ጦራችንም ከአቅሙ በላይ ሆነበት፡፡ መጠነኛ ከባድ መሣሪያና የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች ይዞ በመቶ የሚቆጠሩ ታንኮችና መድፎች አንጋግቶ ከመጣ ጠላት ጋር መዋጋት አስቸጋሪ ነው፡፡ በህይወቴ ያላየሁትና ምንጊዜም ከህሊናዬ የማይጠፋ ከባድ ጦርነት ነበር፡፡ ከፊት ያለው የጠለት ጦር ሲረግፍ፣ ከሁዋላ እንደውሀ

ሙላት ይመጣል፡፡ ከፊት ያለው ታንክ ሲነድ፣ ሌላው ከሁዋላ እሣት እየተፋ ወዲህ ይገሰግሳል፡፡ በእለቱ የሞቱት የጠላት ወታደሮች አሬሣ እስከ ዛሬ ተቀብሮ አላለቀም፤ ስሞኑን በትእዛዝ በመቅበር ላይ ነን. . .›› እያለ ሲናገር አቋረጠውና፡-

‹‹ከቀበሪ ደሃርስ? ብዙ ህዝብ ተጎድትዋል?››

እስማኤል ግንባሩን እንደማሻሸት አለና፣

‹‹አ - ዎ ህጻናትና ደካማ ሴቶች ተጎድተዋል፡፡ ከተማ ውስጥ ሣይሆን መንገድ ላይ፤ ረሃቡና ውሃ ጥሙ ጭምር ነው የጎዳቸው፡፡ የተረፉት በደህና አልፈዋል፡፡ ብቻ አሳዛኝ ትርኢት ነበር፡፡ ወላጆቹን ያጣ ህጻን ፣ የልጅዋን አሬሳ ቁጥቋጦ ስር ጥላ የመጣች እናት፣ ሚስቱ ሞታበት ህጻናቱን ያዘለ አባት፣ በአጠቃለይ ቤተሰቡንና ንብረቱን አጥቶ በደመነፍስ የሚሸሽን ሰው ማየት እጅግ ይዘገንናል...››እያለ ሲደር፣ ከተቀመጡበት ቀጥሎ ያለው ክፍል ሰዎች ገቡ፡፡ እስማኤል ወደ ማድቤት እያሰገገ ተጣራ፡፡ አዳፋ ሽርጥ ያገለደመ ልጅ እግር ሰውዬ እየሮጠ ሄደና ሰዎቹን አነጋገራቸው፡፡

‹‹አይዞህ ሻይ ፍለጋ የመጡ ሰዎች ናቸው፡፡ ሻይ ነጋዴ ሁኛለሁ፡፡ የምታውቀው መደብሬ ስለ ተደመሰሰና በወራሪው ጦር ስለተዘረፈ ቶሎ ለመቋወቋዋም አልቻልኩም››

እነሱም ሻይ መጥቶላቸው ሲጠጡ በሪሁን ጆሮዎቹን ሌላኛው ክፍል ውስጥ ወዳሉት ሰዎች ንግግር ጣለ አርጎ፤

‹‹በአካባቢው ያለው የጠላት ጦር እንቅስቃሴ እንዴት ነው?›› አለ

‹‹በጣም አስከፊ ነው፡፡ በየእለቱ ወደ መሀል አገር የሚጉቋዘው የጠላት ወታደርና መሣሪያ ብዛት ለቁጥር ይታክታል፡፡ የመሣሪያው አይነት ታይቶ አይታወቅም፡፡ ወራሪው መንግሥት ይህን ሁሉ

መሣሪያ ለማጠራቀም ስንት አመት እንደፈጀበት አላህ ይወቀው›› ሱጫ ጸጉሩን ወደ ሁዋላ አለ፡፡

‹‹ከተማው ውስጥስ ያለው ሁኔታ እንዴት ነው? የጦሩ ጥበቃና ቁጥጥር ማለቴ ነው››

‹‹ጥብቅ ነው፣ ጥብቅ ነው፣ ብቻ ከተማው ውስጥ ህዝብ እንዲገባላቸው ስለሚፈልጉ በነዋሪዎቹ ላይ የሚያረጉት ቁጥጥር ለጊዜው ትንሽ ላላ ብልዋል፡፡ በሁዋላ ግን ቁጥጥሩን እንደሚያጠብቁት እርግጠኛ ነኝ፡፡ ደሞ ወታደሮቹ ጉበኞችና ዘራፊዎች ስለሆኑ፣ ገንዘብ ካለ የነሱ ቁጥጥር ብዙም አስቸጋሪ አይሆንም››አለና ሻዩን ፉት እያለ፣

‹‹ለመሆኑ ምን አቅደሀል?›› አለ

‹‹እንዴት? ስለምኑ?››

‹‹ወዴት ለመሄድ አስበሃል?››

በሰፊው ተንፈሶ ሻዩን ፉት ይል ጀመር፡፡

‹‹ወደፊት የሄደው የጠላት ጦር እጅግ ብዙ ነው፡፡ እርምጃው ግን እንዳለፈው ጊዜ ፈጣን አይመስልም፡፡ በየእለቱ ብዙ እስረኞችንና ቁስለኞችን ወደሁዋላ ያግዛሉ፡፡ ጉዞህን ወደፊት ለመቀጠል ብትፈልግ ከፍተኛ ፍልሚያ እሚደረግበት ክልል ውስጥ ትገባና ከሁለቱም አቅጣጫ ለሚተኮስ ጥይት ትጋለጣለህ››

‹‹ታዲያ ምን ላርግ?›› አለ በሪሁን ወደ እስማኤል ዞር ብሎ፡፡

‹‹ጦርነቱ እስኪለይለት እዚሁ ቆይ››

‹‹ይቻላል?››

‹‹አዎ ይቻላል››

‹‹የለም፣ አይሆንም፡፡ ፍልሚያው አለበት ግንባር ድረስ እንደምንም ሄጄ ከወገን ጦር ጋር በመቀላቀል ጠላትን መደምሰስ፣ ወይም

በመጣበት እግሩ እንዲመለስ ማረግ አለብኝ››

‹‹እኛም እኮ እዚህ ያለነው ህዝቦች የወገን ጦር ነን። ምንም እንኳዋን በቂ ትጥቅ ኖርን የጠላትን ግስጋሴ ልንገታው ባንችል፣ ያቅማችንን ያህል ተዋግተናል። አሁንም ባሙችን መንገድ ሁሉ እንዋጋለን። ጠላትን ወደንና አቅፈን አላስቅጠመጥነውም። እርግጥ በጠላት ፕሮፖጋንዳ ተወናብደው፣ ወይም ተገደው ከጠላት ጎን የተሰለፉ ወገኖች መካከላችን አሉ። በአንጻሩ ደሞ አስተባባሪና መሪ ካገኙ እንደተደመሙት አባቶቻችን ጠላትን ፋታ ለመንሣት የተዘጋጁ ቆራጦች አሉን።

"የጠላት የግፍና የእብሪት ወረራ ያንገበገባቸው፣ የንብረታቸው መዘረፍ፣ የሴቶቻቸው መደፈር፣ ከአቅም በላይ የሆነ ቀረጥ መገፍገፍ፣ ከቦታ ቦታ የመዘዋወርን መብት መገፈፍ፣ በጠቅላላው የነጻነት ማጣት ያንገበገባቸው ጥቂት አይደሉም። እነዚህን አስተባብሮ ከፍተኛ ጀብዱ መፈጸም ይቻላል። ይኼ ከዋናው ግንባር ያላነሰ ገድል ሊፈጸምበት የሚችል ስፍራ ነው። እዚሁ ቅርና በሁኔታው እንመካከርበት››

በሪሁን እስማኤል ያለውን በማሰላሰል ላይ እንዳለ ፣ ራቅ አለ ስፍራ ተኩስ ተሰማ።

‹‹በየት አቅጣጫ ነው?፣ ምንድነው?›› አለ በሪሁን መነሳት እየቃጣው።

‹‹የተለመደ ነገር ነው። የጦርነት ክልል መሆኑን አጣኸው? አይዞህ ፣ ጠላት በግድ የመለመለውን ጦር ከተማው አካባቢ ተኩስ ሲያለማምድ ይሆናል›› ፈገግ አለ እስማኤል።

‹‹ልሂድ ብችል ማታ፣ ያለዚያም ነገ ብቅ እልና፣ አሁን ስለ አነሳኸው ሃሳብ እንመካከራለን›› ብድግ አለ።

‹‹ወዴት ልትሄድ ነው?›› ትኩር ብሎ አየው፡፡

‹‹አየህ እስማኤል ከኔ ጋር የመጣ አንድ ጉዋዳኛዬ አለ፣ ከተማው መግቢያ ላይ ነው ትቼው የመጣሁት፡፡››

‹‹ለምን እስከአሁን አልነገርከኝም? ቆይ አብረን እንሄድና እናመጣዋለን››

በሪሁን ከእስማኤል ጋር አሰግድ ወዳለበት ሲገሰግስ፣ ቀደም ብሎ ስለ ሰማው ተኩስ ነበር የሚያሰላስለው፡፡ ተኩሱ አሰግድ አለበት ስፍራ ይሆናል ብሎ ሰግትዋል፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

በርይሁንና እስማኤል ከቤት ሲወጡ ጀንበር ዘቅዘቅ ብላ ሙቀቱ በረድ ብሎ ነበር፡፡ ለአስግድ የሚሆን ሸርጥና ሌላም ልብስ ይዘዋል፡፡

‹‹በጣም ትገርመኛለህ!›› አለ እስማኤል በርይሁንን እየተመለከተ፡፡

‹‹አለባበሴ ነው? የገረመህ?››

‹‹አለባበስህ ፣ አነጋገርህ፣ ሁኔታህ ሁሉ አይነተኛውን ሱማሌ ነው የምትመስለው››

‹‹ነኝና! ከዚህ ሌላ የምታውቀው ነገር አለ እንዴ?›› አለ በቀልድ ወደ እስማኤል አፍጦ፡፡

‹‹ነህ፣ ስምህም ኡስማን ነው፤ አይደለም እንዴ?›› አለ እስማኤል ጥያቄውን በጥቄ እየመለሰና እየቀለደ፡፡ እየተሳሳቁ ሲሄዱ፣ ባጠገባቸው የሚያልፍ ሰው ሁሉ ዞር እያለ ያያቸው ነበር፡፡

‹‹ጉዋደኛህ ሱማሌኛ ይችላል?›› አለ እስማኤል፡፡

‹‹በመጠኑ፣ በደንብ አይችልም፡፡ ቋንቋዋ አለመቻሉ ችግር ሳይፈጥርብን አይቀርም?››

‹‹ግዴለም፣ ዘዴ እንፈልግለታለን፡፡ ከቤት ሳይወጣ ለመኖር ፍቃደኛ መሆን አለበት፣ ቋንቋዋውን በደንብ እስኪችል ማለቴ ነው፡፡ ያለዚያ ስላዩ ብዙ ነው››

‹‹እኔስ ብሆን እንዴት ሆናለሁ፣ ማለቴ መታወቂያና መኖሪያዬን ፣ ጎሳዬን ቢጠይቁኝ እንዴት ሆናለሁ?››

‹‹ቀላል ነው፣ በአሁኑ ጊዜ ይህን በተመለከተ ከባድ አይደለም፡፡

በነገው እለት በኛ ቀጣና ወዳለው የመመዝገቢያ ጣቢያ ሄደን ትመዘገበለህ። የሚጠይቁህ ነገር ቢኖር፣ የሚያውቅህ ሰው አቅርብ የሚል ነው። እኔ አውቀዋለሁ፣ ዘመዴ ነው፣ ከኔ ጋር ሲሰራ ከገጠር መጥትዋል፣ እላቸዋለሁ። ከዚህ ሌላ እድሜህን፣ የመጣህበትን ቦታና የመሳሰለውን ። ትነግራቸዋለህ። ጉዋደኛህ ግን ቁዋንቁዋችንን በደንብ ካልቻለ በቀላሉ ሊለዩት ይችላሉ። ለዚህ ነው ከቤት ሳይወጣ መኖር አለበት ያልኩት››

‹‹እንዳልክ እናረጋለን፣ ይህ ችግር የለውም። ለኔ መታወቂያ ይሰጡኛል ማለት ነው?››

‹‹እስካሁን ምዝገባ እንጂ፣ መታወቂየ መስጠት አልጀመሩም። ከተመዘገብክበት ቀን አንስቶ በከተማው ነዋሪነት ትታወቃለህ። ሻይ ቤቱን ለማሻሻልና ምግብ ለመሥራት ስለ አሰብኩ፣ ሃላፊነቱን ተረክበህ ትሰራለህ። ተራው ሰውም ባለስልጣኖችም በኔ ሰራተኛነት ያውቁሀል። ጉዋደኛህ ማድቤት ውስጥ ይሠራል። እዚያ ያሉት ሰራቶች እንዳይጠረጥሩት ዘዴ እንፈጥራለን። በተቻለ መጠን ከሰዎች ጋር ንግግር የሚለዋወጥበት ሁኔታ እንደይፈጠር መጠንቀቅ አለበት››

‹‹አሁን ያለህን ሻይ አፍይ ምን ያህል ታምነዋለህ?››

‹‹እሱ ይሄዳል ፣ ግድ የለም። በነገው እለት ይሄዳል›› እንዲህ እያወሩ አሰገድ አለበት ስፍራ ተቃረቡ። ዙሪያውን እየቃኙና በአካባቢው ተመልካች እንደሌለ እያረጋገጡ ወደ ቦታው ደረሱ። አሰግድ ግን የለም። በጥያቄ ተያዩ።

‹‹እዚህ ነበር የተውከው?›› አለ እስማኤል አካባቢውን እየቃኘ።

‹‹እም፤ ስንት ሰዓት ይሆናል?›› አለ በሪሁን የራሱን ሰዓት ማመን አቅቶት

‹‹ዘጠኝ ሰዓት ተኩል››

እየተዘዋወሩ ቢፈልጉ አጡት፡፡ በአካባቢው ሌላ ተልካች ይኖር የሆናል በማለት ጥርጣሬን ለማስወገድ ማገዶ የሚለቅሙ መሰሉ፡፡ በርይሁን መጀመሪያ ድምጹን ዝቅ አርጎ፣ ቀጥሎ ጉላ በማረግ እየደጋገመ ‹‹አስግድ! አስግድ!›› እያለ ተጣራ፤ መልስ የለም፡፡

‹‹ቅድም የሰማሁት ተኩስ እዚህ ይሆን እንዴ? አስግድን ይዘውት ይሆን? የቀጠሮ ሰዓታችን ገና ነው፣ ወዴት ሄደ?››

አለ አይኖቹን ፊትለፊት ቡዝዝ አርጎ፡፡

‹‹እጅ ወደላይ! ፤ እንዳትነቅነቁ!!›› አለ አንድ ድምጽ በተሰባበረ ሱማሌኛ ከሁዋላቸው፡፡ እንደታዘዙት አረጉ፡፡

ሰውዬው ጠመንጃውን እንደ ደገነ ከፊት ለፊታቸው ቦረ፣ አዩት፡፡ በሪሁን አወቀው ፣ አስግድነው፡፡

‹‹አስግድ ሰላም ነው፣ ምንም የለም?›› አለበርይሁን እጆቹን እንደሰቀለ፡፡ የእስማኤል ልብ ደረቱ ውስጥ ዘለለች፣ መላ ሰውነቱ በላብ ተነከረ፡፡

‹‹ባላችሁበት ተንበርከኩ›› አለ አስግድ ጠመንጃውን ወደነሱ እንደደገነ፡፡

‹‹ሰላም ነው አልኩህ! ፣ ይሄም ጉዋደኛዬ ነው!›› አለ በሪሁን በትእዛዙ መሠረት እየተንበረከከ፡፡

‹‹በሉ ተነሱ›› አለ አስግድ ሁኔታውን ከተረዳ በሁዋላ የጠመንጃውን አፈሙዝ መለስ አርጎ፡፡

‹‹ምነው ተጫወትክብን፤ በዚህ ሰዓት እንደምመጣ ነግሬህ የለም እንዴ?›› አለ በሪሁን ሳቅ ብሎ እስማኤልን እያየ፡፡

‹‹ሰው አስከትዬ መጣለሁ አላልከኝም›› አለ እስማኤልን በጥርጣሬ

እየተመለከተ።

‹‹ከነበረክበት ቦታ ሳጣህ ጊዜ ደንግጬ ነበር" አለ በርይሁን በጉደኛው ጠንቃቃነት ደስ እያለው።

ጊዜ ሳያባክኑ ጠመንጃዎቻቸውን በጨርቅ ጠቅለው አሳቻ ቦታ ቀበሩ። አሰግድም ልብሱን ለውጦ ከጉደኞቹ ጋር ተመሳሰለና ወደ ከተማ ተመለሱ። በጉዞዋቸው ወቅት በርይሁን ከተማው ውስጥ ያየውን ጠቅላላ ሁኔታና ከእስማኤል ጋር የተመካከሩትን ሁሉ ዘርዝሮ ለአሰግድ ነገረው። ጀንበር ወደ መጥለቂያዋ ተቃርባ የስአት አላፊው ጊዜ ስለ ደረሰ የፍተሻ ጣቢያዎችን በጊዜ ለማለፍ በመለስተኛ ሩጫ ገሰገሱ።

እስማኤል ቤት አቅራቢያ ሲደርሱ ጠመንጃ የያዙ ሁለት ወታደሮች አስቆሙዋቸው።

‹‹የትነው የምትኖሩት ?...›› እያሉ በጥያቄ ያዋከዋቸው ጀመር። በሪሁንና እስማኤል ልዩ ልዩ ምክንያቶች እየሰጡ በልምምጥ አስረዱዋቸው። አሰግድ ዝም ብሎ ቆመ፡

‹‹ኤህ አንተስ?›› አለ አንደኛው ወታደር ወደ አሰግድ ጠጋ ብሎ።

‹‹በሽተኛ ነው፣ መስማትም ሆነ መናገር አይችልም›› አለ በርይሁን ፈጠን ብሎ። አሰግድ አይኖቹን አፍጦ የተባለውን ለመምሰል ወታደሮቹን በዝምታ ተመለከታቸው። ወታደሮቹ በቀላሉ የማይተውዋቸው መሆናቸውን ስለገመተ እስማኤል አንደኛውን ወታደር ለብቻው አነጋግረውና በእጁ አንዳች ነገር አስጨብጠው።

‹‹ነከሂ፣ ነመሪ፣ ነመሪ (እንሂድ፣ እንሂድ ) ተዋቸው›› አለ ወታደሩ ወደ ጉዋደኛው ዘወር ብሎና ከእስማኤል የተቀበለውን ነገር ኪሱ እየከተተ።

እነበሪሁን ድንጋጤውና ጭንቀቱ መለስ ብሎላቸው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። እሚሄዱብት ሲደረሱ ኢስማኤል በር ላይ አንድ ረጅም ሰውዬ ቆሞ ጠበቃቸው።

‹‹ከየት ነው የምትመጣው?፣ ሶስት ጊዜ መጥቼ አጣሁህ። ለጥብቅ ጉዳይ ፈልጌህ ነበር›› አለ ሰውዬው ወደነሱ እየተራመደና እስማኤልን እየተመለከተ።

‹‹እንደምንዋሉ፣ ለሻይ ቤቴ የሚሆን እቃና ሰራተኛ ለመፈለግ ሄጀ ነው። ምነው በደህና ፈለጉኝ?›› አለ እስማኤል ሰውዬውን ጨብጦና እጁን በሁለት እጆቹ ይዞ።

‹‹ለብቻህ አነጋግሬኝ›› አለ ሰውዬው አይኖቹን እነ በሪሁን ላይ ተክሎ። እስማኤል ወደ ነበሪሁን ዞር አለና፣

‹‹ቤት ግቡና ቆዩኝ መጣሁ።›› ብሎ ከሰውዬው ጋር እልፍ አለ። እነበሪሁን እንደታዘዙት ቤት ውስጥ በመግባት ፈንታ፣ እልፍ ብለው እስማኤልና ሰውዬው የሚያረጉትን ይመለከቱ ጀመር።

እስማኤልና ሰውዬው ለረጅም ደቂቃዎች አወሩ።ሰውዬው ከእስማኤል ጋር በሚያወራበት ጊዜ እነበሪሁንን በጥርጣሬ ይመለከታቸው ነበር።

‹‹ግቡ! ግቡ! ወደቤት እንግባ፣ ሰአት እላፊው ደርሰዋል!›› አለ እስማኤል ከሰውዬው ተሰናብቶ ወደነበሪሁን እየመጣ። ተከታትለው ቤት ገቡና በሩ ተዘጋ።

‹‹ሰአት እላፊው የሚጀምረው በአስራ ሁለት ሰአት ነው?›› አለ በረሁን ጉዋዳ ገብተው ሲቀመጡ።

‹‹አዎ እንደውም ግማሽ ሰአት አልፍዋል።›› አለ እስማኤል ሰአቱን እያየ።

‹‹የአሁኑ ሰውዬ በስእት አላፊ ተያዙ በለኛ›› አለ በሪሁን

‹‹እሳቸው በስእት አላፊ የሚያዙ ሰው አይደሉም›› ሳቅ አለ።

አስግድና በሪሁን በጥያቄ ተያዩ።

እስማኤል የተለኰሰ ፋኖስ አምጥቶ ሁሉቱን ከፋኖሶች ከሚለየው በር ላይ ከንጠለጠለው በሁዋላ ወደ ነበሪሁን ዞር አለና፤

‹‹ሶላት፣ (ስግደት) አላደርስኩም። የመክሪብ(የምሽት) ሶላት ሰግጄ መጣለሁ። ተጫውቱ፣ እራትም ይዘጋጃል›› ብሎ ወጣ።

‹‹ይሄን ሰውዬ ምን ያህል አመንከው?›› በርይሁንን ትኩር ብሎ አየው አስግድ።

‹‹የቱን?››

‹‹ይሄን ወዳጅህን››

‹‹አንድ ወዳጅ ሊታመን በሚችልበት ደረጃ አምነዋለሁ ግን.. .››

‹‹እ፣ ግን ምን?››

‹‹የቅድሙ ሰውዬ ሁኔታ ትንሽ አጠራጠረኝ። ብቻ እስቲ እናያለን››

ትንሽ ቆይቶ እስማኤል ፊቱን በእጆቹ እያሻሸና ድምጽ የለሽ ጸሎት እያነበነበ ገባና፣

‹‹ተጫውቱ፤ እራትና ሻይ አሁን ይመጣል›› አለና ወደ አስግድ ዞር ብሎ፡-

‹‹እንዴት ነው ቁስልህ?›› አለ

‹‹ደህና ነው፣ አለፎ አለፎ ህመሙ ቢኖርም ቁስሉ በመድረቅ ላይ ነው››

‹‹ግድ የለም ወዳጄ የሆነ ሐኪም አለ ከነገ ጀምሮ እሱ ያክምሃል››

‹‹መድሃኒቱ ከተገኘ እኛው ብንረዳው ይሻላል›› አለ በርይሁን ፈጠን ብሎ።

‹‹ግድ የለም ሰውዬው የሚታመን ነው። ቤሩን አሁንም ትጠረጥረኛለህ፣ አታምነኝም? ግድ የለህም እመነኝ፣ በአንተም ሆነ በጉዋደኛህ ላይ አንዳች ክፉ ነገር አይደርስባችሁም። እንተማመን፣ ካልተማመንን ምንም ማረግ አንችልም›› አለ እስማኤል ትንሽ ፈርጠም ብሎ።

‹‹አንተን ባለማመን አይደለም እስማኤል። በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት ሊደርስ የሚችልን አደጋ ለመከላከልና አንዳች ቁም ነገር ሳንሰራ በሁሪያችን ከሚያገሳው ሞት መንጋጋ ውስጥ እንዳንገባ በማለት ነው›› አለ በርሀን።

‹‹ብዙ ቁም ነገር ትሰራላችሁ፣ አብረን ከፍተኛ ቁም ነገር እንሰራለን። ከዚህ ቀደምም የፈጸማችሁ ቁም ነገርና ጀብዱ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። የአገርን ህልውና ለማስከበር ከሚደረግ መጋደል የበለጠ ቁም ነገር ያለ አይመስለኝም።››

‹‹ነው፣ እብሪተኛ ወራሪዎች በመሬታችን ላይ እስካሉ ድረስ ግን ፈጽምን የምንለው ቁም ነገር አይኖርም›› ከንፈሩን ነክሶ፣ በርይሁን።

አስግድ፣ ቀደም ብሎ እስማኤል ‹‹እሳቸው በሰአት እላፊ የሚያዙ ሰው አይደሉም›› ስላላቸው ሰውዬ ማንነት ሊጠይቅ አሰበና ‹‹አትጠርጥሩኝ›› የሚለውን የእስማኤል አነጋገር ስለ ፈራ ተወው።

የእስማኤል ሰራተኛ ያዘጋጀውን እራት አቀረበ። በርይሁንና አስግድ በጎድጉዋዳ ሳህን የቀረበውን ሩዝ ያለ ምንም ይሉኝታ ተመገቡ፣ ከሻዩም ደጋግመው ጠጡ። አብርዋቸው የቆየውን ረሃብ ለማባረር በጸጥታ ሲመገቡ፣ እስማኤል መመገቡን ቆም እያረገ በአዘኔታ ይመለከታቸው ነበር።

‹‹ቅድም ፈታሾቹ በያዙን ጊዜ የፈጠርከው ዘዴ እስካሁን

ይደንቀኛል›› አለ እስማኤል በረሁንን እያየ፡፡

‹‹ችግር ብልሃትን ይወልዳል፣ ምን ላርግ? ተጋሰጥን ብዬ ፈርቼ ነበር››

‹‹ያ ሀዴ ባይፈጠር ኑሮ ምን ታረግ ነበር?››አለ እስማኤል ፈገግ ብሎ አሰግድን እያየ፡፡

‹‹በአነጋገሬ ይጠረጠሩኛ እንደሆነ እንጂ ለጥያቄዎቻቸው መልስ መስጠቱ አያቅተኝም ነበር፡፡ ብቻ በርይሁን ገላገለኝ ››

‹‹ እኔ ሳልሆን የእስማኤል ጉቦ ነው የገላገለህ››

‹‹አዎ በጉቦ ብዙ ነገር ይሰራል፡፡ የጦሩ አባሎች ከላይ እስከታች የጉቦ ሱሰኞች ናቸው›› አለ እስማእል አይኖቹን በሰፊው ከፍቶ፡፡

‹‹የተለያየ አለባበስና ትጥቅ ያላቸው ብዙ ወታደሮች ከተማው ውስጥ አይቻለሁ፤ እንዴት ነው?›› አለ በረሁን ድንገት

‹‹አዎ፣ የተለያዩ ወታደሮች አሉ፡፡ የሚኖሩትና የሚሰለጥኑት በተለያዩ የጦር ሰፈሮች ነው፡፡ የአንዱ የጦር ክፍል አባል ከሌላው ጋር አይገናኝም፣ ለጦርነት ሲሰማሩም በተለያዩ አቅጣጫዎች ነው፡፡ በጠቅላላው ጦሩ በሶስት ዋናዋና ክፍሎች ይመደባል፡፡ የመጀመሪያው እብሪተኛው ወራሪ መንግሥት ያዘመተው መደበኛ ጦር ነው፡፡ ይህ ጦር በእግረኛ፣ በአየር መቃወሚያ፣ በብረት ለበስ፣ በማድፈኛና በሌሎች ልዩ ልዩ ምድቦች የተከፋፈለ ነው፡፡ የጦሩ ዋና ሰፈር በቀድሞው የሃያ ሁለተኛ እግረኛ ሻለቃ ጦር ሰፈር ውስጥ ሆኖ፣ በከተማዋና በአከባቢዋ ብዙ ቦታዎችም ሰፍርዋል፡፡

"ከዚህ ጦር ትንሽ ለየት ያለው ‹ጥቁር ለባሽ› የሚባልና የነብር አርማ ያለበት መለዮ የሚያረግ ጦር ነው፡፡ ይህ ጦር በሌሎቹ ዘንድ‹‹አፋኝ ጉዋድ ›› በመባል ይታወቃል፡፡ ዋና ስራው ከጦሩም ሆነ

ከህዝቡ መሀል በማንኛውም ነገር በሚጠረጠሩ ሰዎች ላይ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ነው፡፡ ይህ የጦር በአሁኑ ጊዜ በከተማው መሃል አሰው ትልቅ መስጊድ አጠገብ ሰፍርዋል፡፡

"ሌላው የጦር ክፍል ደሞ፣ ዶፉን (የመብረቁ ጦር) በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ከኦጋዴን ብሄረሰቦች መሃል በውድም ሆነ በግድ የተመለመሉ ወጣቶች አሉበት፡፡

"ሰስተኛው የጦር ክፍል፣ አህመድ ጉሬ (ግራኝ መሐመድ) ይባላል፡፡ ጦሩ ከሐረርጌ የደጋው ክፍል በጠላት ኘሮፓ ጋንዳ በመታለል፣ በመገደድና በመታፈንም ጭምር እየመጡ አጭር ጊዜ የውጊያ ትምህርት የሚሰጣቸው ሲሆኑ፣ ተመልማዮቹ ወደ ጦሩ ሰፈር እንደመጡ ጸጉራቸው ስለሚላጭ በአካባቢው ህዝብ ሂረን(መላጣዎቹ) በመባል ይታወቃሉ፡፡ ወራሪው ጦር የጦሩ አባሎች እንዲላጩ የሚያረግበት ምክንያት፣ እየጠፉ ስለሚሄዱ በምልክታቸው እያደኑ ለመያዝ ነው፡፡

"ይህ ክፍል ጥሩ ይዞታ የሌለውና በሌሎቹ የጦር ክፍሎች የተናቀ ነው፡፡ የውጊያ ተልእኮው ወደ ደፈጣው ያዘነብላል፡፡ ማንኛውም የጦሩ አባል ወደ ከተማ እንዲገባ አይፈቀድለትም፡፡ ታፍኖ ይመጣና እየተጠበቀ ሰልጥኖ ታፍኖ ይዘምታል፡፡ ሶስቱንም ክፍሎች አጠቃሎ በከተማይቱና በአካባቢዋ ያለው ጦር ከአሥራ አምስት እስከ ሃያ ሺህ ይገመታል››

‹‹የጦሩ ሞራልና የውጊያ ብቃቱስ እንዴት ነው?›› አለ አሰግድ እስማኤልን እየተመለከተ፡፡

"እውነቱን ለመናገር፣ በመጀመሪያው ሰሞን የጦሩ ሞራል በእብሪት የተሞላ ከመሆኑም በላይ፣ እንቅስቃሴው የሚገታ

አይመስልም ነበር። አሁን ግን ተስፋ መቁረጥና ፍርሃት ይታይበታል። እንደውም ሰሞኑን ጦሩ እርስ በርሱ መጋደልና ለአለቆቹም አልታዘዝም ማለት ጀምሯል"

‹‹ጦሩ በሕዝቡ ዘንድ ያለው ተወዳጅነትና ተቀባይነት ምን ያህል ነው?›› አለ በርይሁን በክርኖቹ ጠረጴዛወው ላይ ተመርኩዞና አገጩን በመዳፎቹ ደግፎ።

‹‹ወራሪ ጦር ምንጊዜም በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትና ተቀባይነት አይኖረውም። እርግጥ በጠላት ፕሮፓጋንዳ የተታለሉና ለጊዜው ከጎኑ የተሰለፉ ጎሳዎችና ግለሰቦች ነበሩ። አሁን ግን ሀቁን እየተረዱት ወጥተዋል። ጠመንጃ የያዘን ሃይል በባዶ እጅ ፊት ለፊት መቃወም አይቻልም። የሚረዳው ካገኘ ግን ከጎኑ ተሰልፎ ክንዱን ለማንሳት ህዝቡ ዝግጁ ነው።

"ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ጦሩ የፈጸመበት ድርጊት ‹ወይ ነጻነት› አስኝቶታል። በዙ ሰው ንብረቱ ተዘርፍዋል፤ ሚስቱና ሴቶች ልጆቹ ተደፍረውበታል። በየምክንያቱ እንደ በግ እየተጎተተ ይታሰራል፣ ያለፍርድ ይረሸናል›› አለና በሰፊው ተነፈሰ።

‹‹ወራሪው መንግስት በውጭ ሀይል እርዳታ ለረጅም ጊዜ ነው የተዘጋጀው። እጅግ ብዙ ዘመናዊ መሳሪያ ታጥቅዋል። ለዚህ ነው ጦሩ ብዙ ጉዳት ያደረሰውና ሰፊ መሬት የያዘው" አለ በሪሁን በሰፊው ተንልፍሶ።

‹‹በመጣበት እግሩ ይመለሳታል፣ ይህ ግብስብስ ጦር" አለ እስማኤል ጥርሱን ነክሶ።

"እንደሱማ አይመለስም፣ እዚሁ መቅረት አለበት!" አለግድ ተቆጣ።

"ጦራችን ከተጠናከረና እኛም ከበረታን፣ ይህን ማረግ እንችላለን፣

ወላፈ እንችላለን!" እስማኤል እጁን ጨበጠ።

"ህዝቡን ለማነሳሳትና ለፍልሚያ ለማዘጋጀት ያረጋችሁት ጥረት አለ?" አለ አስግድ።

‹‹ሙከራም፣ ዝግጅትም አላረግንም። አሳቡን ግን ጥቂት ሰዎች ተወያይተናል። እናንተን ካገኘን ደሞ ብዙ እንሰራለን ››

በሪሁንና አስግድ እስማኤል ያቀረበውን ኃሳብ ያሰላስሉ ጀመር።

‹‹ለስራችን እንዲያመቸን ንግዴን አስፋፋለሁ። ሻል ያለ ቤት እንዲሰጠኝ ጠይቄ ‹የፈለከውን መርጠህ ልትገባበት ትችላለህ› ተብያለሁ። በነገው እለት አንዱን ይዛለሁ። ቀደም ብዬ እንደነገርኩዋችሁ እናንተ በኔ ሰራተኝነት ትታወቃላችሁ፣ በተለይ ቤሩን..." እያለ ሲናገር፣ ከውጭ የሩምታ ተኩስ ተሰማ።

‹‹እንተኛ! እንተኛ! ተኙ!›› መብራቱን አጠፋ፣ እስማኤል።

# ምዕራፍ ዘጠኝ

‹‹እመንንም አላመንን፣ ወደድንም ጠላን፣ የውርደትና የሞት ተጠቂዎች ሆነናል። ማታ ታይተው ጠዋት የማይገኙ ሰዎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ መጥቷል። የሚስቶቻችን ባሎች፣ የልጆቻችን አባቶች፣ የንብረታችን ጌቶች ለመሆን አልቻልንም። እስከመቼ ነው ይህን ሁሉ የምንታገሰው? እነዴት በገዛ አገራችን እንደበሬ እየተጎተትን ቃርደን እንለቅ ...?" አሉ ሃጂ ጎደኔ የተባሉ የአካባቢው ታዋቂ ሰው፣ ሌሊት በመስኪድ ላይ በነበረው ምስጢራዊ ስብሰባ ላይ ።

እስማኤል ነው፣ ቀደም ብሎ ለነበሪሁን ባማከራቸው ሃሳብ መሠረት ለእቅዳቸው ተባባሪ ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውን ሰዎች በምስጢር የሰበሰባቸው። ስብሰባው ለመጀመሪያ ጊዜ በመስኪድ ላይ ነው፣ አሲ.ሃሽ በተባለ ግለሰብ ቤት ውስጥ። አሲ.ሃሽ የከተማው ነዋሪ ሲሆን፣ በወራሪው ጦር መሪዎች ተመርጦ የቀጣና ሃላፊነት ስለጣን ተሰጥቶታል። መኖሪያ ቤቱ ከቀጠናው ጽህፈት ቤት ጋር የተያያዘ በመሆኑና የማይጠረጠር ስለሆነ ነው ለስብሰባ ስፍራነት የተመረጠው።

ለአይን ያዝ አርጐ የሰአት እላፊው ከመድረሱ በፊት እስማኤል፣ በሪሁንንና አሰግድን አስከትሎ ወደ አሲ.ሃሽ መኖሪያ ቤት አመሩ። ስፍራው ሲደርሱ፣ አሲ.ሃሽ እንደ ባለጉዳዮች እያነጋገረ ለስብሰባ ወደ አዘጋጀው ክፍል ወሰዳቸው። ክፍሉ መጠነኛ ሲሆን፣ ኅርንጉርጉር

ምንጣፎች የተደጉባቸው ፍራሾች ዙሪያውን ተነጥፈውበታል።
በየማእዘኑ የሰንደል ጭስ ይተናል። በሪሁን፣ አስግድና እስማኤል
ባካባቢው ልማድ መሰረት እግሮቻቸውን አያጠፉ ምንጣፉ ላይ
ተቀመጡ። አሊሃሽ ፈገግ እያለ፡-

‹‹ተጫወቱ ሌሎቹ እንግዶች አሁን ይመጣሉ›› አለና በሩን መለስ
አርጎ ወጣ

‹‹ሃጂ ኢብራሂም ሰሞኑን ስለሞቱ እዚያ ዱአ (ጸሎት) ሲያረጉ
ይሆናል የቆዩት›› አለ እስማኤል በስብሰባው ላይ የሚካፈሉት ሰዎች
በጊዜው ባለመምጣታቸው እነበሪሁን የተሰማቸውን ጥርጣሬ አይቶ።

‹‹ምን ሆነው ነው የሞቱት?›› አለ አሰግድ ትኩር ብሎ እያየው።

‹‹ወታደሮች ቤታቸው ድረስ መጥተው ይዘዋቸው ሲሄዱ
ለማምለጥ በመሞከራቸው ገደሉዋቸው ነው የሚባለው›› አለ
እስማኤል በሰፊው ተንፍሶ። በዚህ ጊዜ፣ የቤቱ ጌታ አሊሃሽ ሶስት
ሰዎች አስከትሎ ገባ። እነበሪሁን ብድግ አሉ።

‹‹አሰላም አሌይኩም ተቀመጡ›› አሉ ረዘም ያሉና በቀኝ እጃቸው
ጥቁር መቁጠሪያ ያንጠለጠሉ ሰውዬ። ሁሉም ቦታ ቦታቸውን ይዘው
ቁጭ አሉ። መቁጠሪያ የያዙት ሰውዬ ድምጻቸውን ዝቅ አርገው
የጸጥታ ጸሎት ያነበንቡ ጀመር።

‹‹የሚፀልዩት ሰውዬ ሃጂ ሳደኜ ይባላሉ፤ ምናልባት ቤሩን
ታውቃቸው ይሆናል። የታወቁ የባህል ሃኪም ናቸው፣ ችግረኞችን
የሚረዱና በህዝቡ የተወደዱ። ሶስት ልጆቻቸው በሰሞኑ ጦርነት
ሞተውባቸዋል። አራቱ ደሞ በወራሪው ጦር ታፍነው ተወስደዋል።
የት እንደደረሱ አይታወቅም። ሰውዬው በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ
የመሆናቸውን ያህል፣ በጠላት ይፈራሉ" አለ እስማኤል ወደነበሪሁን

ጎንበስ ብሎ በሹክሹክታ። አነበራሁን እንዳጎነበሱ የሃጂን ሹል ጺም፣ የደፋፋዋትን ሾጣጣ ኮፊያ፣ ከኮፊያቸው ሥር የሚብረቀርቀውን ሸበት ትኩር ብለው ተመለከቱ።

እስማኤል አሁንም ድምጹን ዝቅ አርጎ፣

‹‹ከሳቸው ጎን የተቀመጠው ደሞ ሐሚድ ጣሂር ይባላል። በአካቢያችን የጠላት እንቅስቃሴ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ፣ የተቃውሞ ድምጹን እንዳሰማ ነው። አንድ ጊዜ በጠላት ሰርጎ ገቦች ተገዶ ከተወሰደ በሁዋላ፣ ለአመት ያህል በደፈጣ ውጊያ ሰልጥኖ አመለጣቸው። አሁንም በድብቅ ነው የሚኖረው። ህዝቡ ስለሚወደውና ስለ ሚፈልገው ሸሽጎታል። መሀል የተቀመጠው ልጅ እግር ሰውዬ አብዱ ኑር ይባላል። እሱም በሰርጎ ገቦች ታፍኖ ከተወሰደ በሁዋላ አምልጦ ነው የመጣው። አስተናጋጃችንን ሊሊሃሽን ከዚህ በፊት አስተዋውቄያችኋለሁ። ቀደም ብሎ በጫት ንግድ ይተዳደር ነበር። እርግጥ መጀመሪያ በጠላት ፕሮፓጋንዳ ተታሎ አብርዋቸው ቆይትዋል። ለደፈጣ ውጊያና ለመረጃ ትምህርት ወደ አንድ የአረብ አገር ልከውትም ነበር። ከዚያ እንደተመለሰ የአላማቸውን ከንቱነት በመረዳት ኮብልሎ ወደ ተውልድ አገሩ ተመለሰ። አሁን የጠላት ጦር በመጣ ጊዜ ከተማይቱን ለመከላከል ከተዋደቁት ጀግኖች ጋር ከፍተኛ ተጋድሎ አርግዋል። ዛሬ ደሞ ወዳጅ መስሎ ከጠላት ጋር በመስራት ላይ ስለሆነ፣ ለቡድናችን በጣም የሚጠቅም ሰው ነው።

ሃጂ ጎደኒ ጸሎታቸውን እንዳበቁ በሁለቱም መዳፎቻቸው ፊታቸውን ቁልቁል እያሹ ወደነ በሪሁን ዞር ብለው፣

‹‹እንደምናችሁ ወንድሞቼ ››አሉ። አነበሪሁን ብድግ ብለው በድጋሚ እጅ ነሱ። ቤቱ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ወደ ነበሪሁን

ተመለከቱ። እስተናጋጁ አሊሃሽ ድምጹን ዝቅ አርጎ፣

«ዛሬ ከኛ ጋር ዱአ (ጸሎት) የሚያደርጉ ወዳጆች መካከለችን አሉ።

ስለነሱ እስማኤል ያስረዳናል›› አለ።

በዚሁ መሰረት እስማኤል ስለነበሩሁን በአጭሩ አስረዳ። ሃጂ ጎደኔ

ፈገግ ብለው ሁሉን በትኩረት ከቃኙ በዋላ፣ አሊሃሽን ጠቀሱት። ብድግ

ብሎ ሁለት ዙርባ (ጥቅል) ጫት አመጣና ፊታቸው አጋደመ። ሃጂ

ጥቅሉን ፈቱና ለምለሙን ጫት በጭብጣቸው እየለኩ ለታዳሚዎቹ

አደሉ። ጫት የሚታደላቸው ሰዎች እየተነሱ በአክብሮት ከተቀበሉ

በሁዋላ የሃጂን እጅ እየሳሙ ወደየቦታቸው ተመለሱ።

የጫት አደላው ሲያበቃ፣ እነበርይሁንን ጨምሮ፣ ሁሉም በጫት

ቃንበጥ ጉንጫቸውን እየሞሉ ያኝኩ ጀመር። ጎን ለጎን የተቀመጡት

እየተዋወቁ የየራሳቸውን ወሬ ጀመሩ። ትንሽ እንደተቆዩ፣ ሃጂ ጎደኔ

ጉሮሮዋቸውን ሞረዱና፣

«አልሃምድሊላሂ፣ የተሰበሰብነው ለቁምነገር ነውና ስብሰባችንን

እንጀምር" ብለው ወደ ነበርይሁን ዞር አሉና፣

"ስለነዚህ ወንድሞቻችን እስማኤል ከሞላ ጎደል ነግሮናል። እስቲ

ይበልጥ ከነሱ እንስማ›› አሉ። በርይሁን ሁሉን አየና፣

«ወንድሞቼና አባቶቼ ሆይ፣ ለአንድ አላማ እንዲህ ለመሰባሰብ

በመቻላችን እኔና ጉደኞዬ በጣም ደስ ብሎናል። አገራችንን ለመውረር

በየጊዜው የተነሱብን ጠላቶች ከመጡባቸው በሮች አንዱ፣ ኦጋዴን

ነው። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ድንበራችንን ለማስከበር

ከወራሪ ጠላት ጋር እየተናነቁ ሉአላዊነታችንን አስከብረው ህላፊነቱን

በእጃችን አኑረዋል። ይህን የታሪክ ሀላፊነት፣ ባለንበት አስቸጋሪ ጊዜ

ምንና እንዴት እናርግ ለመባባል ነው እንግዲህ የተሰበሰብነው..."አለ።

"ወራሪው ጦር ከቅርብና ከሩቅ ያሉ ጠላቶቻችን በገፍ ስላስታጠቁትና አገራችንም በውስጥና በዙሪያዋ ባሉ ችግሮች በመወጠርዋ በአጋጣሚው በመጠቀም ወረውናል። ይህ ድፍረታቸው ባጭር ጊዜ ይቀለበሳል፣ በህዝቦችዋ የተባበረ ክንድ..." አለ አሰግድ ክንፈሩን እየነከሰ።

አሊሃሽ የያዘውን የጫት እንጨት እሰባበረ፣

"የሚገርመው፣ ጠላቶቻችን የምንዋጋው ነጻ ልናወጣችሁ ነው ማለታቸው ነው" አለ። በርይሁን ሳቀና፣

"እነማንን ነው ነጻ የሚያወጡት? እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝብ፣ የኦጋዴን ጭቁን ህዝብም በአድሃሪው ስርአት ሲመዘበርና መብቱ ሲረገጥ ነው የኖረው። ይህ ጭቆናና ብዝበዛ ያንገሸገሸው የኢትዮጵያ ህዝብ ሃይሉን አስተባብሮ በመነሳት ጨቋኞችን የገባር መደብ ገርስሶታል። ስርአቱንም በማፈራረስ እኩልነትና ፍትህ የሰፈነባት፣ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት በመታገል ላይ ነው። በዚህ መላውን ጭቁን ህዝብ በሚያቅፍ ትግል ውስጥ ያለውን የኦጋዴን ጭቁን ህዝብ ነው እንግዲህ በነጻነት ስም ሊሸነግሉት የሚሩዋሩዋጡት። የኦጋዴን ህዝብ፣ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዘቦች ጋር ነው ነጻ የሚወጣው..." አለ።

"ይህን እውነት ለተወናበደው ሕዝባችን ማስገንዘቡ ነው ከዋነኞች ትግሎቻችን አንዱ። ይህ ሲሆን ህዝቡ በጠላቶቹ ላይ ይነሳል" አለ እስማኤል በእልህ።

ሃጂ ጎደኔ የያዙትን የጫት ዘለላ ቀንበጥ በጣታቸው መታ መታ እያረጉ፣

‹‹ወንድሞቻችን የተናገራችሁት በልባችን ያለውን ነው። ሁሉም

ይገባናል፣ የነጻነትን ምንነት ያወቅነው አሁን አይደለም። የአንድ ነገር ጥቅሙ ይበልጥ የሚታወቀው፣ ያ ነገር ከታጣ በሁዋላ ነው፣ የሚባለው ነገር ከምንጊዜውም ይበልጥ ዛሬ ነው የገባን። የውርደት ቡትቶ ተከናንቦ ለዛላለም ከመኖር፣ ለአንድ ቀን ብሩህ የነጻነት ሸማ ለብሶ መሞት ይመረጣል። እንዳልከውም አባቶቻችን የአገራቸውን መሬት ጠላት በእብሪት እንዳይረግጣት ሲከላከሉ ኑረዋል። ዛሬም ጀግኖች አሉን። የዛሬው ወራሪም ይህን ያውቀዋል፣ ያገኘውን ድል ጨብጦት እንደማይቆይ። ለዚህ ነው ወታደሮቹ ቤቶች እያፈረሱ ቆርቆሮዎችን፣ የቤት እቃዎችን፣ የመኪና ሞተሮችንና ሌሎችንም የህዝብ ሀብቶች በጥድፊያ ወደ ሃገራቸው የሚያግዙት። ለመስረቅ የመጡ ሌቦች ናቸው። ወላሂ ውነቴን ነው›› አሉ በንዴት ፊታቸው ቀልቶ።

ሃጂ የጀመሩት የጫት ጥቅል ስለ አለቀ ሁለተኛውን ጥቅል ፈተው እንደቀድሞው አደሉ። ተሰብሳቢው ሁሉ የጠላትን የግፍ ድርጊት እና ቁጭቱን በተለያየ ሁኔታ ሲገልጥ ቆየ። በጨረሻም ወደ ፊት በሕብረት መደረግ ስላለበት ነገር የየግሉን አስተያየት ሰጠ።

በቀረቡት ሃሳቦች ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ከተደረገ በሁዋላ፣ ለጊዜው ከተማው ውስጥና ባካባቢው ሁኔታዎችን እየገመገመ አስፈላጊውን የሚያረግ አደጋ ጣይ ቡድን እንዲቁዋቁዋም ተወሰነ። ለቡድኑም አስተባባሪነትና ሊቀ መንበርነት ሃጂ ጎደኔ ባንድ ድምጽ ተመረጡ። ለጊዜው ብቁ የሰው ኃይልና መሣሪያ ባይኖርም፣ በአጭር ጊዜ ሊሙዋላ እንደሚችል በማመን በየአቅጣጫው አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት የሚያረጉና በኃለፊነት የሚመሩ ሰዎች ተመረጡ።

በዚሁ መሠረት ሃሚድ ጣሂር ከከተማው ውጭ የሚደረገውን

የደፈጣ ውጊያ እንዲመራ፣ ኡስማን ጣሃ (በሪሁን ጋሹው) ዩኑስ ጅብሪል(አሰግድ አስሙ)ን እና እስማኤልን ይዞ የከተማውን ውስጥ የደፈጣ ውጊያ እንዲመራ፣ በተጨማሪም የሃጂ ጎደኔ ረዳት ሆኖ በምክትል አስተባባሪነት እንዲሰራ ተወሰነ።

ከዚህም ሌላ አሊሃሽ፣ አብዲ ኑርን ጨምሮ መረጃዎችን በማጠናቀር ምስጢራዊ ፕሮፓ ጋንዳና ቅስቀሳ በማረግ እንዲሁም ለቡድኑ ሰዎችን በመመልመልና እርዳታ በማስገኘት እንዲሰሩ ስምምነት ተደረገ።

በመጨረሻም ሃሚድ ጣሂር በቀኝ እጁ በያዘው የጫት እንጨት የግራ መዳፉን መታመታ እያረገ።

‹‹ወንድሞቼ ከተባበርን፣ በአንድ ልብና በቆራጥነት ከተነሳን፣ እንደተአምር የሚቆጠር ስራ እንሰራለን። ጥርጣሬ፣ ዘረኛነትና ፍርሃት በመካከላችን ካለ ግን ሀሳባችን አይሳካም፣ ምንም ሳንሰራ እንጠፋለን። በደጋፊዎቻችንም ላይ ስቃይ እናበዛባቸዋለን። ስራችንን የሚሰለፍ የሰው ሃይልና በእጆቻችን የምንጨብጣቸው የጦር መሳሪያዎች ለማግኘት ችግር ያለብን አይመስለኝም። ህዝቡ ዛሬ እጠላት የሚሰነዘርበት መጥፎ ድርጊት ሁሉ አንገሽግሾታል ‹ነጻነት ወይም ሞት?› ብልዋል። የሚመራው ካገኘ በቆራጥነት ይቆጋል። የጠላቶቻችን ቤት በእጃችን ነው። ብር የማይከፍተው የመሳሪያ ግምጃ ቤትና የሚስጢር ካዝና የላቸውም›› አለ ገንዘብ እንደሚቆጥር የቀኝ እጅ ጣቶቹን እያፍተለተለ።

ወንድማማችነትና የአላማ አንድነት የሰፈነበት ይህ ስብሰባ ከተራራ የገዘፈ ግዳጁን ለመጀመር በጋለ ስሜትና ወኔ ወሰነ። አባሎቹ በሙሉ ሃጂ ጎደኔ ዘንድ ቀርበው እጆቻቸውን በማነባበር እስከሞት

ላይነጣጠሉና ላይከዳዱ ሚስጥርም ሲጠብቁ በመሃላ ቃል ገቡ።

ስብሰባው እንዲህ ቆይቶ፣ ሲነጋጋ ሲል ሃጂ ጎደኔ ጉሮሮዋቸውን አጠሩና፣

"ሃሳባችንን አሳህ ያቅናልን ወንድሞቼ ። የወደፊት ግንኙነታችን ሁሉ በአሊሃሽ በኩል በሚስጢር ይሆናል። ሁላችሁም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማረግ አለባችሁ። ጠላቶቻችችን የሚጠረጥሩዋቸውን ሰዎች ለመግደል የማያመነቱ መሆናቸውን እንዳትረሱ። ማንንም ቶሎ ማመን የለባችሁም...›› እያሉ ሲናገሩ እስማኤል አንድ ነገር በሃሳቡ ብልጭ አለበት። አሰናብተዋለው ያለው የሻይ ቤቱ ሠራተኛ ጉዳይ። ካንዴም ሁለት ሶስቴ፣ "ሂድልኝ፣ ሰራተኛ አግኝቻለሁ" ብሎታል።

‹‹ታዲያ ለምንድነው ያልሄደው?፣ እንደደረስኩ እቃውን አሸክሜ አባርረዋለሁ። ዛሬም እሱን ቤት ትቼው መምጣ አልነበረብኝም›› አለ ለራሱ፡

የስብሰባው ተካፋዮች አንድ በአንድ እየወጡ ሄዱ። እነበሪሁንም ወደ ሁዋላ ቀረት ብለው ከአሊሃሽ ጋር ትንሽ ከተመካከሩ በሁዋላ ወጡ።

ቤታቸው ሲደርሱ የእስማኤልን ሰራተኛ አላገኙትም። ቀኑን ሙሉ ጠበቁት፤ አልተመለሰም። በአቅራቢያቸው ያሉትን ሰዎች ሁሉ ጠየቁ፣ አላየነውም አሉዋቸው።

‹‹ሂድ ሌላ ሰራተኛ አግኝቻለሁ ብዬዋለሁ፣ ብዙ ጊዜ...ለምን በስውር መሄድን መረጠ?" አለ እስማኤል አይኖቹን ቡዝዝ አርጎ።

‹‹ያለፍላጎቱና ከአቅሙ በላይ በሆነ ኃይል ተወስዶ እንደሆነስ?›› አለ አሰግድ

‹‹ታፍኖ እንደሆነ ማለትህ ነው?›› አለ በሪሁን አይኖቹን በሰፊው

ገልቦ።

‹‹አው››

‹‹ለምን ይታፈናል?›› ጠየቀ አሰግድ።

‹‹ከሱ የሚፈልጉትን ምስጢር ለማግኘት፣ ቀደም ብሎ ስለነሱ የሚያውቀው ምስጢር ካለ እንዳያወጣ፣ በተለየ ግዳጅና ተልእኮ ለማሰማራት... ሊሆን ይችላል›› አለ በርደሀን የስጋት ፈገግታ እያሳየ።

# ምዕራፍ አሥር

በሪሁንና አሰግድ ደገሃቡር ከተማ ከገቡ አንድ ወር አልፏቸዋል። ቀደም ብለው ከተማው መግቢያ ላይ የቀበሩትን መሳሪያ በአሳቻ ጊዜ በመውሰድ ቤት ውስጥ ሸሽገው እስማኤል በከፈተው አዲስ ሆቴል ውስጥ ስራቸውን በትጋት ያካሂዳሉ። ሆቴሉ ከገጠር አነስተኛ ምግብ ቤቶች ያልተለየ ቢሆንም በከተማዋ ታወቂ ሆኖ ብዙ ደንበኞችን አፍርቷል።

በሪሁን በአስተናጋጅነት፣ አሰግድ በምግብ አብሳይነት፣ እስማኤል ደሞ ስራው ከበድ ያለበትን ወገን እየረዳ በገንዘብ ተቀባይነት ይሰራሉ።

በርከት ያሉ የጠላት ጦር አባላት፣ ከተራ ወታደር እስከ ከፍተኛ መኮንኖች የእስማኤል ምግብ ቤት ደንበኞች ሆኑ። እንዲያውም አንዳንዶቹ፣ በተለይም ከአጋድን ተመለመሉት ሚሊሺያዎች፣ ሆቴሉ ውስጥ ልዩ ስፍራ እየተዘጋጀላቸው ጫት ይቅሙ ጀመር። በሪሁን ባስታናጋጅነት ችሎታውና በታዛኝነቱ «ትሁት ሰራተኛ» ተባለ። እስማኤል ደሞ ለደንበኞቹ የተለየ ክብር በመስጠቱና በችግራቸው ጊዜ በገንዘብ ጭምር ስለረዳቸው፣ «ታማኝ የልብ ወዳጃቸው» ሆነ። ደንበኞቹ የሆኑ የጠላት ጦር አባላት እርስ በርሳቸው ሲጣሉና በመካከላቸው አለመግባባት ሲፈጠር የሚያስታርቃቸው እሱ ሆነ። መኮንኖች ደንበኞቹም ቢሆኑ ብሶትና ብስጭታቸውን ያዋዩታል፣ ምክርም ይጠያይቁታል።

አንድ ቀን የዶፋን ጦር አባላት የሆኑ ሁለት ወታደሮች ጉዋዳ

ውስጥ ተንጥፎላቸው ጫት ሲቅሙ፣ እስማኤልም ሻይና ውተት አፍልቶ፣ ሰንደልም አጭሶ አብሮዋቸው ተቀመጠ፡፡

‹‹እኔኮ በጣም የሚገርመኝ›› አለ ረዘም ጠቆር ያለው ወታደር የጫቱን ቀንበጥ እየቀነጣጠሰ ‹‹እኔኮ በጣም የሚገርመኝ ከፊት የምንቀድመውና በጦር [illegible] እሳት የምንማገደው እኛ ስንሆን፣ ተጠቃሚዎቹና ፍላጎታቸው ሁሉ የሚሙዋላላቸው የመደበኛው ጦር አባላት መሆናቸው ነው፡፡ አለቆቻችን ለነሱ ከሚያደርጉት ክብካቤ እሩቡን ያህል እንኳዋን ለኛ አያስቡም፡፡ የራሳቸውን ጦር እንደልዩና የተቀደሰ ዘር ይቆጥሩታል፡፡ ሞት በፊቱ እንዲያልፍ አይፈልጉም፡፡›› አለ ምርር ባለ አነጋገር፡፡

‹‹ምናለበት አሁን ይህን ባታነሳብን? አርፈን ጫታችንን እንቃምበት፡፡ ወደን የገባንበት ስለሆነ ይበሰን፣›› አለ አጠር ቀላ ያለው ወታደር፡፡

‹‹ወደን አትበል! ፤ ወድጄ በል፡፡ እኔ ወድጄ አልገባሁበትም›› አለ ረዘም ያለው ወታደር ድምፁን ከፍ አርጎና አይኖቹን አፍጦ፡፡

‹‹እህ፣ እህእ ፤ ነገሩ ጫን እያለ ሲመጣና እቅዱ ሁሉ ህልም ሲሆን፣ ተገደ[illegible] ነው ማለት ምን ይጠቅማል፡፡ በቆረጥከው ለትር ዝም ብለህ ተጨስ[illegible] አለ [illegible]ጭሩ ወታደር እየሳቀ፡፡

‹‹አዎ [illegible] ሞንግሥት ሰማያት እንደሚወሰድ መልአክ ስለቀረቡን እጆቻችንን ስ[illegible]ታናች[illegible]ር፣ ሲኦል በር ላይ ሲጥሉን ነው ሰይጣኖች መሆናቸውን [illegible]ወቅነው›› አለና በስፊው ተነፈሰ ሌላው፡፡ ለጥቂት ጊዜ ሁሉቱም ዝም ብለው ጫታቸውን ይቀነጣጥሱ ጀመር፡፡ እስማኤል ሻይና ውተቱን እየቀዳ ከማቅረብ በቀር በንግግራቸው መሐል ጣልቃ ሲገባ አልፈለገም፡፡

ረጅሙ ወታደር በጫት እንጨት ራሱን መታመታ አረገና፣

‹‹እህእ ፣ ደሞኮ የሚገርመው››ብሎ ወደ እስማኤል ዞር አለና

‹‹የመደበኛው ጦር አባላት በኛ ላይ ያላቸው ንቀትና ተጽእኖ ነው።

ፃህ!፣ ዲንቲ አባሃወስ›› አለ።

‹‹ይህ ማንኛውም ወራሪ ጦር የሚያሳየው የቅኝ ገዥነት ምልክት ነው›› አለ ሌላው ወታደር በተስፋ መቁረጥ ፈገግ ብሎ።

‹‹ለችግሩ መፍትሄ መፈለግ ነው እንጂ፣ መሳጨቱ ምን ፋይዳ አለው?። ሰው አንዳንዴ ይሳሳታል፣ይሄ ያለ ነው። ይህ ይቅርታ የለሽ በደል አይደለም። ዋናው በደል፣ ከገቡበት ክፉ ተግባር ለመውጣት ነው። ነገሩን ካነሳችሁት ሰሞኑን የተፈጸመ አንድ ነገር ላጫውታችሁ ›› አለ እስማኤል ሻይ ሲቀዳላቸው እየተንጠራራ፣ ‹‹በከር ቁራህን ምናልባት ታውቁት ይሆናል። በከተማችን የታወቀ የሸቀጣሸቀጥ ነጋዴ ነበር። በጦርነቱ ጊዜ የት እንደደረሰ አይታወቅም፣ ከተማችን ስትያዝ ማለቴ ነው። ከዚያ በሁዋላ አልታየም። በቀደም ጠዋት የዚሁ ሰው የወንድም ልጅ የሆነ አንድ የናንተው ክፍል አባል፣ እየተበሳጨ መጣና፣ ‹የአጎቴን ንብረት በሙሉ፣ ማቀዝቀዣዎች ፣ አልጋዎች፣ ቁም ሳጥኖች፣ የህጻናት ልብሶች... እንኳዋን ሳይቀሩ በሶስት ትልልቅ ካሚዮኖች እየጫኑ አጋዙዋቸው› አለኝ። እነማናቸው ይህን የሚረጉት?፣ ወዴትስ ነው የሚወስዱት? አልኩት። ‹አለቆቻችን ናቸዋ ፣ ወደ ሀርጌሳና ሞቃዲሾ ላኩት› አለኝ። ነገሩ ትንሽ ነደድ አደረገኝና ‹የአጎትህ ንብረት ስለተነካ ነው የቆጨህ? ፣ የከተማው ሕዝብ ንብረት ሲጋዝ፣ የትምህርት ቤቶችና የክሊኒኮች ቆርቆርዎች እየተነቀሉ ሲወሰዱ፣ እርዳታ ማስተባበሪይና ማቋዋቋዋሚያ ኮሚሽን ያሰራው ተገጣጣሚ ቤት እንኳዋን ሳይቀር እየተፈታታ ሲወሰድ የት ነበርክ?›

አልኩት፣ ‹እም ህዝባችንን ለወራሪና ለዘራፊ አሳልፈን የሰጡን እኒኖ እንደኔ ያሉት ነን› እያለ ሲበሳጭ ውሎ ሄደ፡፡ በማግስቱ በንዴት ጊዶ ከአለቆቹ አንዱን ገደለና ራሱም ሞተ፡፡ በሁዋላ እንደሰማነው ወታደሩ ሰፋ ያለ ኑዛዜ በጽሁፍ ትቶዋል ይባላል››

‹‹ሰምተናል፣ ለኛ የተነገረን ‹ወታደሩ የጠላት ሰላይ ነው፣ አለቃውን በድርጊቱ ስለደረሰበት ገደለው› ተብሎ ነው›› አለ ረጅሙ ወታደር በሰፊው ተንፍሶ፡፡ ሌላው ወታደር አቀርቅሮ የጫት እንጨት እየሰነጣጠረ ዝም አለ፡፡

እስማኤል ውይይቱን በዚሁ ጉዳይ ለመቀጠል በመፈለግ፣

‹‹ወታደሩ በተወው የዛዜ ቃል፣ ‹ወገኖቼ ተነሱ! በወራሪው ጦር ላይ ክንዳችሁን አንሱ፣ ነጻ አወጣችሁዋለሁ የሚለን ጦር ሃሰተኛ ነው፣ በተለይ ጠመንጃ ጨብጠህ ከጦሩ ጎን የተሰለፍከው ወገኔ ከስህተትህ ተመለስ፣ አላማ በሌለው የጦርነት እሳት ውስጥ ራስህን አትማግድ፣ ሌላው ወገንህ አልቅሶብሃል ፣ አዝኖብሀል... ይህ ጦር ነገ በኢትዮጵያ ጦር ሲባረር፣ በታላቅ ትዝብት ላይ ትወድቃለህ፣ ከወንጀለኛነትም አታመልጥም...ብልዋል እየተባለ ይወራል›› አለ፡፡

ወታደሮቹ ዐይኖቻቸውን ቡዝዝ አርገው ጫታቸውን እያኘኩ ዝም አሉ፡፡ እስማኤል የወታደሮቹን ውስጣዊ ስሜት በፊታቸው ላይ የሚያነብ ይመስል ትኩር ብሎ ሲመለከታቸው ቆየና፣

‹‹በውጊያውም ቢሆን አልቀናንም ይላሉ ከየግንባሩ የሚመጡ ቁስለኞች" አለ፡፡ ረጅሙ ወታደር፣ በሰፊው ተንፈሰና፣

‹‹ከእንግዲህ ወደ ሁዋላ እንጂ ወደ ፊት የለ? መሞት፣ ማለቅ እንጂ፣ መግደል የለ? ከሁዋላችን በሞት እየተገፋን ወደ ሞት እንሄዳለን፡፡ በመትረየስ እየተነዳን፣ ከፊታችን አለ እሳት ውስጥ

እየገበን እናልቃለን›› አለ፡ ወታደሩ፡፡ ድምጹን እንዲቀንስ እስማኤል ምልክት ቢያሳየው እጆቹን አወናጨፈና ፣‹‹አባ ሃወስ! የፈለጉትን ያርጉ!›› አለ፡፡

የአጭሩን ወታደር ዝምታ እስማኤል አልወደደውም፡፡ እሱን ውይይቱ ውስጥ ለማስገባት በማሰብ ዞር አለና፣

‹‹ከማዶ የመጡ ብዙ መደበኛ ወታደሮች ከጦር ግንባር ሸሻችሁ ተብለው ታስረዋል፡፡ የራሳቸውን ወታደሮች አስርን እያሉ ወደ ሁዋላ ያሸሹዋቸዋል፡፡ የኛ ሰዎች ቢሆኑ ግን እዚያው ነበር የሚረሽንዋቸው እያሉ አንዳንድ ወታደሮች ይናደዳሉ›› አለ በጥያቄ እያየው፡፡

‹‹ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ ይባላል፡፡ አየህ እስማኤል እንዲህ ተደረግን፣ በደል ደረሰብን…እያሉ የሚወራጩ ሰዎችን ሳይ በጣም ይነደኛ፣ ይገርመኛልም፡፡ መጀመሪያ የወሰኑትን ሲወስኑ የሚደርስባቸውንም መገመት እንዴት ተሳናቸው?›› እያለ ሲናገር ሌላው ወታደር አቋረጠውና፣

‹‹እንዴት ተሳነን? በል፤ ወይስ አንተ አሁንም በድረገቱ እምነህበት ነው የምትሳተፈው›› አለና አፈጠጠበት፡፡

‹‹እምነበት እንኳዋን አይደለ… ››

‹‹ታዲያ እንዴ ከተነከርኩ በዚያው ልዝቅጥ ነው? ›› አለ ረጅሙ ወታደር አይኖቹን እያጉረጠረጠ፡፡

‹‹ታዲያ ምን መውጫ አለን?›› አለ፡፡

እስማኤል ጣልቃ ገባና ‹‹ይህ ሲደርስ እንደሚችል እንዴት ማወቅ ተሳናቸው ባልከው ላይ ብንነጋገርበት ደስ ይለኛል፡፡ እውነቱን ለመናገር፣ ብዙ ሰዎች ያኔ የአሁኑ ሃቅ አለተከሰተላቸውም፡፡ አንተም ምናልባት ከነሱ አንዱ ትሆናለህ፡፡ እርግጥ ምንም እንኳዋን

ምኞታቸው ህልም ቢሆን፣ ከወራሪው ጦር ጋር የአላማ አንድነት ኖርዋቸው እስከ አሁን የሚወጉንም አሉ። በሁዋለኞቹና በፊተኞቹ መካከል ብዙ ልዩነት አለ። የፊተኞቹ ስህተታቸውን በተገነዘቡ ጊዜ ወደ ሃቁ ተመልሰው ጠላቶቻቸውን ሊታገሉ የሚችሉ ናቸው። የሁዋለኞቹ ግን የሚፈልጉትን ለማግኘት በሚያርጉት ጉዞ ማንኛውንም በደልና ግፍ ያለርህራሄ ይፈጽማሉ። ስለ ሌላው ሰው ንብረትና ሕይወት ደንታ የላቸውም። እንዲህ ያሉትን በማንበርከክና በመደምሰስ ካልሆነ በቀላሉ መመለስ አይቻልም። ታዲያ ከፊተኞቹ ሃቁን የተረዱና የተጸጸቱ ካሉ በሁዋለኞቹ ላይ ጠመንጃዎቻቸውን ማዞር አለባቸው እንጂ፣ አንዴ ተታለናልና በጀመርነው መቀጠል አለብን ማለት የለባቸውም። እንዲህ የሚሉ በኔ ግምት ከሁዋለኞቹ ጠላቶች ተለይተው አይታዩም›› አለ አጭሩን ወታደር እያየ። ረጅሙ ወታደር በእስማኤል ንግግር በጣም ረክቶ ጉዋደኛውን ቢያየው ጥርሱን በስንጥር እየጎረጎረ አይኖቹን ፊትለፊት ቡዝዝ አርግዋል። ሶስቱም ጸጥ ብለው ጫታቸውን ሲቀነጣጥሱ፣ በሪሁን ብቅ አለና እስማኤልን ጠቅሶት ተመለሰ። ፈጠን ብሎ ቢወጣ፣ ዋናው ቤት በር ላይ ቆሞ ወደ ውጭ ይመለከታል።

‹‹ ምነው ቤሩን?›› አለ በሹክሹክታ፣ ከሁዋላው እየቀረበና በርይሁን ወዳፈጠጠበት እየተመለከተ።

‹‹ቤቱን ተመልከት፡መጣሁ›› ብሎት እየተጣደፈ መንገዱን አቋርጦ ሄደ። እስማኤል በር ላይ ቆሞ ሲመለከተው በሪሁን ከዋናው መንገድ ባሻገር ያለው መንደር ውስጥ እጥፍ ብሎ ተሰወረበት።

ቆየት ብሎ ጉዋዳ የነበሩት ወታደሮች እስማኤልን እያመሰገኑ ሄዱ። በተለይ አጭሩ ወታደር ከእስማኤል ባገኘው ምክር የረካ መሆኑን ገለጸ እየደጋገመ አመሰገነው።

እስማኤል ወደ ማድ ቤት ሄደና‹‹ቤሩን ምን አጋጠመው?›› ብሎ አስግድን ጠየቀው፡፡

‹‹ምን አጋጠመው?›› አለ ጥያቂውን በጥያቂ እየደገመ፡፡

‹‹አይ ተወው፡፡ የነገረህ ነገር ካለ ብዬ ነው›› ብሎ መለስ ሲል፣ አስግድ ያዝ አረገና፣

‹‹ንገረኝ እንጂ! ምንድነው የሆነው?›› ብሎ አፈጠጠበት፡፡

‹‹ምንም አልሆነም ‹ቤቱን ጠብቅ መጣሁ› ብሎኝ ስለ ወጣ፣ ምናልባት የሚሄድበትን ነግሮህ እንደሆን ብዬ ነው›› ብሎት ወደ ነበረበት ተመለሰ፡፡ አስግድ ጭንቅ አለውና፣

‹‹እስኪ ሆኔታ ቢኖር ሳይነግረኝ አይሄድም ነበር፡፡ ምን ሆኖ ይሆን? የትስ ነው የሄደው?›› አለ እርጥብ እጆቹን ሽርጡ ላይ እየጠራረገ፡፡ አላስችል ቢለው፣ ከማድ ቤት ወጥቶ ተመለከተ፡፡ ምግብ ቤቱ ተመጋቢ ለበትም፡፡ ገባ ቢል፣ እስማኤልና በርይሁን በሩ ላይ ቆመው ሲነጋገሩ አያቸው፡፡

በርይሁን ዞር ብሎ፣

‹‹አይዞህ አስግድ ሰላምነው›› አለና ወደ እስማል ጆሮ ጠጋ ብሎ፣

‹‹የጠፋውን አሽከርህን አየሁት›› አለ ከንፈሩን ነክሶ፡፡

‹‹የት?›› አለ አሽከሩን በሪሁን አይን ውጥስ ይፈልገው ይመስል አፍጦ፡፡

‹‹እዚህ ድረስ መጥቶ አየኝና ተመለሰ፡፡ ያኔ ነው የጠራሁህ፡፡ ተከትዬው በሩቁ እያደባሁ ስመለከት፣ በቀጥታ ሄዶ፣ መንደር ውስጥ ጥግ ይዘው ከቆሙ ሁለት ባለጠቁር መለዮ ወታደሮች ጋር ሲነጋገር ቆየና እየተገላመጠ ተለያቸው››

ሰውነቱን አንዳች ነገር ውርር አረገው፣ እስማኤል፡፡ ከንፈሮቹ

ደረቁ። ቀደም ሲል እንደገመቱት፣ ሠራተኛው ከጠላት አንዳች ተልእኮ ተሰጥቶት የሚከታተላቸው መሆኑን ተረዱ። በቅርብ ጊዜ ሊደርስባቸው የሚችለውን አደጋ እያሰላሰሉ ሲተክዙ፣ በርከት ያሉ ምግብ ፈላጊዎች ስለገቡ ስጋት ባጠላበት ስሜት ወደ የስራቸው ተሰማሩ።

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

‹‹በሪሁን››

‹‹ወይ›› አሰግድና በርይሁን ብቻቸውን ይወያያሉ።

‹‹የዚህ የእስማኤል ሰራተኛ ነገር ምን ይመስልሃል?››

‹‹ከአንድ ወር በፊት አንተ እንዳልከው ጠላቶቻችን በስላይነት ሳይመድቡት አልቀሩም››

‹‹ማንን እንዲሰልል፣ እኛን?››

‹‹እኛንም ሌሎችንም››

‹‹ሰውዬውን ባየኸው እለት ስለ ሁኔታው ስትነግረው እስማኤል ምን አለ?››

‹‹ምንም››

‹‹ታዲያ ይሄን ነገር እንዴት ታየዋለህ? ታስታውስ እንደሁ፣ እዚህ ቤት የገባን እለት፣ በሰዓት እላፊ የማይያዝ ሰው ማየታችን ትዝ ይለኛል። እስማል ስለ ሰውየው ምንም አልነገረን። አሁን ደሞ፣ ጠፋ የተባለው ሰራተኛው ቤት ድረስ መምጣቱን ሲሰማ ምንም አስተያየት አለመስንዘሩ ገርሞኛል። በዙሪያችን የሚደራ የተንኮል ድር አለ ብዬ ስጋሁ››

‹‹በሰዓት እላፊ ስለማይያዘው ሰውዬ እንኳዋን እኛም በጊዜው አልጠየቅነው። እኔ እንደሚገባኝ ሰውዬው የወራሪው ጦር የመረጃ ሰራተኛ ነው። እስማኤል ሰውዬውን የሚቀርበው ለተለየ አላማ

ይመስለኛል፡ አሁን ለጀመርነው ስራ ቀና ሁኔታ ለመፍጠር።

በቀደምለት ከተማው ውስጥ ስለ ምንጀምረው እንቅስቃሴ ስንነጋገር ትዝ ይልህ እንደሁ ይህን ነገር ነካክቶታል። ስለ ሰራተኛውም ስነግረው በጣም ከመደንገጡ የተነሣ ምንም አስተያየት ለመሰንዘር አልቻለም። ደሞስ ምን ይበል? ቀደም ብለን የገመትነው ሁኔታ ነው የደረሰው። ዛሬ ጠዋት ያለውን ሰምተህ የለም? ‹በቅርብ ቀን እርምጃዎች መውሰድ ካልጀመርን መቀደማችን እርግጥ ነው› ሲል ይህንኑ ስጋቱን መግለጡ ነው። እስከ አሁን በተግባር እንዳየነው ከሆነ፣ እስማኤል የሚታመን ሰው ነው። ራሱ እንዳለው እኛን ማጋለጥ ቢፈልግ የሚችግረው ነገር አለነበረም። እና ግድየለህም አትስጋ ›› አለ በሪሁን የአስግድን ትከሻ መታ መታ እያረገ።

ይህን የሚወያዩት በእለቱ በሚደረገው ሌላ ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደ ስጋ ነጋዴው አብዲ ኑር ቤት በመሄድ ላይ ሳሉ ነበር። በዚያን እለት ስብሰባ ላይ እስማኤል አልተገኘም፣ ቤት ቀርትዋል። ይህ የሆነው ማሟሻውን የሚመጡ ሰዎች ስለነበሩና ከነሱ ጋር የሚሠራው ሥራ ስላለ ነው።

ስብሰባው ሥፍራ ሲደርሱ አባሉቹ ሁሉ ቦታ ቦታቸውን ይዘው አገኙዋቸው። በመዘግየታቸው ይቅርታ እየጠየቁና ሰላምታ እየሰጡ አልፈው በተዘጋጀላቸው ሥፍራ ተቀመጡ።

እንደ ተለመደው እጣን ጭሶ፣ ምርቃቱ ወርዶ ፣ የስብሰባው ስርዓት ተጀመረ። በስብሰባዎች ወቅት አዘውትረው ይህን ስርዓት የሚያረጉት፣ በአካባቢው ልማድ መሰረት ዱአ (ጸሎት) በየቤቱ ስለ ሚደረግ ስርአቱን ሽፋን በማረግ ተግባራቸውን ለማከናወን ነው። ስርአቱ ጋብ ብሎ ወደ ውይይቱ ሲገቡ፣ ሃጂ ጎደኔ ጉረሮዋቸውን

ስሉና፦

‹‹እስቲ እስከዛሬ ስለተከናወኑትና ወደፊትም ስለሚከናወኑት ስራዎች ከየሃላፊዎቹ እንስማ›› አሉ በዙሪያቸው ያሉትን ሁሉ እየተመለከቱ፡፡ ሁሉም ለውይይቱ በሚቀናቸው ሁኔታ እየተመቻቹ ተቀመጡ፡፡

‹‹አንተ ጀምርልን›› አሉ ሃጂ የመረጃና የፕሮፓጋንዳ ክፍሉ ኃላፊ ወደ ሆነው ወደ አሊሃሽ ዞር ብለው፡፡ አሊሃሽ መዳፎቹን አሻሸና፦

‹‹ተግባራችንን በጥሩ ሁኔታ በማከናወን ላይ ነን፡፡ ማንኛውም ነገር ከሞላ ጎደል ተሳክቶልናል፡፡ ከተማው ውስጥና ባካባቢው አደጋ በመጣል ተግባር ለሚሰማሩት አባሎቻችን የሚረዱ ልዩ ልዩ መሳሪያዎች ተገኝተው ቃድለዋል፡፡ በተጠየቅን ጊዜም እንደ አስፈላጊነቱ ለማቅረብ እንችላለን፡፡ ህዝቡን በምስጢር ለማንሳሳት የምናረገውን የቅስቀሳ ተግባር በከፍተኛ ጥንቃቄና በዘዴ ተያይዘነዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ በጣም የምናቸውንና ፍላጎቱ ያላቸውን አደጋ ለሚጥለው ቡድን ልከናቸዋል፡፡ ገንዘብና ልዩ ልዩ ትጥቆች በማሰባሰቡ ስራ የምንፈልገውን ያህልም ባይሆን፣ አጀማመራችን ደህና ነው፡፡ እንደምታውቁት መሳሪያ፣ ጥትቅና ጠቃሚ ወሬ (መረጃ) ፣ ለማግኘት ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ገንዘብ መሰብሰብ ትጋትን ይጠይጠይቃል፣ አደገኛም ነው፡፡ ከፍተኛ ጥንቃቄንና ብልህነትን ይፈልጋል፡፡ በመረጃ አሰባሳቡ በኩል በርከት ያሉና የሚያስደስቱ፣ የሚየስፈሩም ወሬዎች ይደርሱናል፡፡ ከሚያስደስቱት ወሬዎች መሃል በሁለተኛው ቀን ስብሰባችን ላይ እንደገለጽኩት በጠላት ጦር አበሎች መሃል ያለው መቃቃር እየሰፋ በመሄድ ላይ ነው፡፡ ልዩ ልዩ ጎሳዎች በጦሩ ውስጥ ያሉትን ያመራር ስፍራዎች ለመያዝ በሚያረጉት ትግል ከፍተኛ

ተቃርኖ ተፍፕርዋል፡፡

"ሁሉም የራሱን ጎሳ በስልጣን ለማሳደግ ይጥራል፡፡ የጎሳው አባል ወደ ግንባር እንዳይሄድበት ይከላከላል፡፡ ግንባር ያለውም ጦር እየሸሸ ስለ አስቸገራቸው፣ መፍትሄ መስልዋቸው የጦሩ አዛገሮች በየቀኑ ብዙ ወታደርችና መኰንኖችን ይረሽናሉ፡፡ እስር ቤቶቻቸውም ተጣበዋል፡፡ ከፍተኛ መኰንኖቻቸውም የግል ጥቅማቸውን ያሳድዳሉ፡፡ በደጋው አካባቢ የሚያስማሩዋቸውን ወታደሮች ወደ ዘረፋው እንዲያተኩሩ ያረጉዋቸዋል፡፡ ልዩ ልዩ እቃዎች፣ በተለይም ጫት እየዘረፉ ወደ ሞቃድሾ የሚልኩ አሉ፡፡ እዚህ ከተማችን ውስጥም ለሕዝቡ የሚቀርበውን ጫት በተዘዋዋሪ የሚያስቸረችሩት እነሱው ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ከፍተኛ መኰንኖች በዚህና ይህን በማሳሰሉ ወራዳ ተግባሮች ተሰማርተዋል፡፡

"አንድ ከፍተኛ መኰንናቸው በወረራው ወቅት ከማረካቸው ሰላማዊ ሰዎች መካከል የመረጣትን የመሃል አገር ሴት፣ እንደሰማሁት ስምዋ ኤስቴር ይባላል፤ በሄደበት ሁሉ የወታደር ልብስ አልብሶ በድብቅ ይዝዋት ይዞራል፤ ወድዋታል፡፡ ከሁለት ቀናት በፊት ደሞ ሌላ ከፍተኛ መኰንን ይህችን ሴት ሲያበልጋት ወዳጅዋ ስላየው በጥይት አቁስሎታል፡፡ ይህ ሁኔታ በበታች አባሎችና ባለቆች መካከል ያለውን ቅራኔም አባብሶታል፡፡

"በሌላ በኩል በትናንትናው እለት ፊቅ መንገድ ላይ ይጉዋዝ በነበረ የጠላት ጦር ላይ ከባድ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ጉዳቱን ያደረሱት የአዲሱ ሚሊሺያ ጦር አባሎቻችን ናቸው፡፡ እነዚህ ሚሊሺያዎች ከወራት በፊት ወደ ኦጋዴን ጫፍ ዘለቆ የነበረው ጦር አካል ናቸው ይባላል፡፡ የጠላት ጦር ምቹ ቦታዎችን አስቀድሞ በመያዙና በመሳሪያም አይነትና

ብሃት፣ በሰውም ቁጥር ብልጫ ስለ ነበረው ጊዜያዊ የበላይነትን አግኝቶ ይሆን ጦራችንን ወደ ሁዋሁዋላ እንደያፈፍግ አርጎታል።

"ከተማው ውስጥም እንደምታዩት ሕዝቡ ከጥላቻው የተነሳ ከጦሩ አባላት የሚሰጡትን ትእዛዞች አልፈጽምም በማለት ላይ ነው። ከላይ የገለጽኩዋቸውና ሌሎቹም ሁኔታዎች በጦሩ መካከል ያሉትን አለመግባባቶች ይበልጥ ለማክረር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው። አስፈሪ ናቸው ያልኩዋቸውን ወሬዎች ሌሎቹ ጉዋደኞቼ የሚሉትን ከሰማን በሁዋላ ገልጻለሁ›› አለና አበቃ።

‹‹አንተስ ምን ትላለህ›› አሉ ሃጂ ከከተማው ውጭ የሚካሄደውን የደፈጣ ውጊያ ወደ ሚመራው ሃሚድ ጣሂር ዞር ብለው

‹‹እኛ አስፈላጊውን ሁሉ አጠናቀናል፣ የምንጠብቀው አደጋ መጣል ጀምሩ የሚለውን ትእዛዝ ብቻ ነው። ›› አለ ፈገግ ብሎ።

‹‹ሃዬ (እሺ)፡አንተስ ኡስማን?›› አሉ ሀጂ በሪሁንን እያዩ። በሪሁን የያዛትን ብጣሽ ወረቀት መልከት አረገና፤

‹‹እኛም ዝግጅታችንን ከሞላ ጎደል አጠናቀናል፣ የሚያስፈልጉን መሣሪይዎችም ደርሰውናል። የተላኩልን ሁለት ሰዎች ለከተማ ውስጥ አደጋ መጣልና የአፈና ተግባር ብቁ ሁነው ስለ አላገኘናቸው ወደ ሃሚድ ቡድን እንዲሄዱ አርገናል። በመሠረቱ ለኛ ሥራ ብዙ ሰው አያስፈልግም። ለጊዜው ሶስታችን እንበቃለን። የከተማ ውስጥ ስውር እንቅስቃሴ ከሌላው ትንሽ ለየት ይላል። ጠላት ጉያ ሁኖ ጠላትን የማጥቃት ተልእኮ ስለሆነ፣ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይጠይቃል...."

ሃጂ ጫታቸውን ተጉመጥምጠው ዋጡና፣

‹‹ወንድሞቼ ፤ ከየክፍሉ ኃላፊዎች የቀረበውን ሪፖርት አደመጥን። እንደኛ ያለውን ቡድን ማቁዋቁዋምና ተግባሩን

እንዲቀጥል ማረግ ቀላል ሥራ አደለም፡፡ እንዳላችሁት ከፍተኛ ጥንቃቄና በልህነትን ይጠይቃል፡፡ የሚተማመኑና ሕብረት ያለቸውን ቀራጥ ሰዎች ይፈልጋል፡፡ እስከዛሬ በነበረው የዝግጅት ጊዜ የታየው ፍለጎት፣ ታታሪነትና ፍቅር፣ ለተሰለፋችሁበት ከፍተኛ ግዳጅ፣ ዝግጁዎች መሆናችሁን ያመለክታል፡፡ ይህ መተማመንና በቂ ዝግጅት ካለ፣ ከተማው ውስጥም ሆነ በዙሪያው የሚደረገው አደጋ የመጣል ተግባር መጀመር ያለበት ይመስለኛል››አለ፡፡

የስብሰባው ተካፋዮች ሁሉ የየበኩላቸውን ሃሳብ ከሰጡና ሰፋ ያለ ውይይት ከተደረገ በሁዋላ፡-

ሀ. እንደ አመቺነቱ እየታየ በከተማው ውስጥም ሆነ ባካባቢው አደጋ የመጣሉ ተግባር እንዲጀመር፡፡

ለ. የሁሉቱ አደጋ ጣይ ቡድኖች እንቅስቃሴ የተቀናጀ እንዲሆን በበሪሁን መሪነት እንደካሄድ፡፡

ሐ. አስጊ ሁኔታዎች ቢፈጠሩ ለመሸሸጊያነት የሚያገለግሉና በጥቂት ኃላፊዎች ብቻ የሚታወቁ ስፍራዎች ከተማው ውስጥ እንዲዘጋጅ፡፡

ሰ. የርስ በርሱ ግንኙነት ከአሁኑ ለየት ባለና በረቀቀ ዘዴ እንዲሆን፣ ለዚህም የሚረዱ ባሞያዎችና ታማኝ ሰዎች እንዲመደቡ የሚሉ ውሳኔዎችን አስተላለፉ፡፡

በውይይቱ መጨረሻ በሪሁን ድምጹን ትንሽ ጎላ አርጎ፡-

‹‹አባቶቼና ወንድሞቼ፣ እስከዛሬ እቅዶችን ስናወጣና ዝግጅት ስናረግ ቆይተናል፡፡ እንግዲህ ወደ ተግባር መሸጋገራችን ነው፡፡ ባንድ ልብ፣ በተቀነባበረና ብልህነት ባልተለየው አሰራር ከተንቀሳቀስን ብዙ ልንሰራ እንችላለን፡፡ ህብረት የድል መጨበጫ ዋነኛ መሳሪያ ስለሆነ፣

እንደ አንድ ሰው ሆነን እንነሳ፡፡ እስከ ሞት እንተማመንና ታሪክ ሰርተን እንለፍ፡፡›› አለ፡፡

አሊሃሽ ቀጠል አርጎ ‹‹ቅድም ሪፖርቴን ሳቀርብ የደረሱኝን የሚያስፈሩ ዜናዎች በመጨረሻ አቀርባለሁ ማለቴን ታስታውሳላችሁ›› ብሎ መዳፎቹን እያሻሸ ‹‹ደስ የሚያሰኙ ወሬዎችን የመስማታችንን ያህል አስፈሪ ዜናዎችም ይደርሱናል፡፡ ጠላት የጸጥታ አስከባሪ ናቸው የሚላቸውን ጥቁር ለባሽ ወይም ‹ባለጥቁር መለዮ› ወታደሮቹን ቁጥር ከእጥፍ በላይ ለመጨመር አቅድዋል፡፡ በዚህ ሳምንት ሁለት ከሚዮኖች ሙሉ ጥቁር ለባሽ ወታደሮች ወደ ከተማይቱ ገብተዋል፡፡ እቅዳቸው ከተማይቱ ውስጥ ከምን ጊዜውም የበለጠ ጥብቅ ቁጥጥርና አሰሳ ለማረግ ነው፡፡ ይህን የሚያረጉበትም ምክንያት፣ ሰሞኑን የወገን አይሮኘላኖች የጦር ሰፈሮቻቸውንና የስንቅ ክምችቶቻቸውን እየደጋገሙ ስለ መቱባቸው ተበሳጭተው ነው፡፡ ‹አይሮኘላኖቹ ቁልፍ የሆኑ ቦታዎችን ሊያጠቁ የሚችሉት በከተማይቱ ውስጥ መገናኛ ሬድዮ ያላቸው ጠቋዋማዎችና አስተኩዋሾች ቢኖራቸዋው ነው፡፡ በዚህ ነገር የሚጠረጠሩ ሁሉ እየተያዙ እርምጃ እንዲወሰድባቸው› ብለው ወስነዋል፡፡ በዚህ ወር ብቻ አስራ አምስት ሰዎች ከቤታቸው እየተወሰዱ ሳይመለሱ ቀርተዋል፡፡ ሰሞኑንም በጉዋደኞችን በሃጂ ኢብራሂም ላይ የተፈጸመው ድርጊት ይህ ነው፡፡ ነገሩ በቀስታ ወደኛም በማዝገም ላይ ነው" አለና ሃጂ ጎደኜን ትኩር ብሎ እያየ፡

‹‹ዛሬ ጠዋት እንደነገርኩዎት እርስዎም እንዲያዙ ትእዛዝ ተሰጥዋል፡፡ በመፈለግ ላዩ ነዎት፣ መሰወር አለብዎት›› አለ፡፡

ስፍራው ያሉት በድንጋጤ ተያዩ፡፡

‹‹እንዲህ ከሆነማ በፍጥነት መሰወር አልብዎ፡፡ በስውር ሆነው

ብዙ መሥራት ይችላሉ›› አለ በሪሁን ሃጂን እየተመለከተ። ሁሉም የበሪሁንን ሃሳብ በመደገፍ፣ ሊታወቅ ወደ ማይችል ስፍራ እንደውም ከከተማው ውጭ ሄደው ይሸሸጉ አሉ።

ሃጂ ይህን ሲሰሙ በስፊው ተነፈሱና፣

‹‹አላህ እንኩዋን ከተዛተ ከተወረወረም ይሰውራል፣ አትሩጥ አንጋጥ ያለው እሱ ያውቃል›› አሉ ፈገግ ብለው።

"ይሄ እንኩዋን ትክክል አይመስለኝም ሃጂ! አላህ ያውቃል እያሉ ማረግ የሚችሉትን ሳያደርጉ ቢቀሩና የተፈራው ነገር ቢደረስ፣ አላህን መውቀስና ማማረር ይመጣል። ይህ እንደሚሆንም እርግጠኛ ነኝ። ከገገርዎቻችን ጋር የጥቅም ተከፋዮች የነበሩት የሃይማኖት መሪዎቻችን ‹አላህ ያውቃል እሱኑ ጠብቁ› እያሉ እኛ ስናንጋጥጥ እነሱና የጥቅም ጉዋደኞቻቸው ያለውን ሁሉ ተሻምተው ለእግራችን እንኳን መቆሚያ አሳጡን። ተበደልን ስንል ‹አላህ ያረገው ነው› ይሉናል። ለአመጽ ስንነሳ ‹ይህ የአላህን ፍቃድ መቃወም ነው ይሉናል። በዚህ ሁኔታ ስንታለል ኖረናል፣ ዛሬ ደሞ በዚያው አስተሳሰብ መኖር የለብንም። የምንችለውን ማድረግ እንጂ፣ ገደል ስር ቆሞ ናዳ ሲመጣ እጅን አጣምሮ አላህ ያውቃል እያሉ መጠበቅ ሞኝነት ነው። ሁሉንም ነገር አላህ እንዲያረግልን የምንጠብቅ ከሆነማ፣ ያቀድነው ሁሉ አያስፈልግም›› ፈርጠም ያለ አነጋገሩ የፈጠረውን ስሜት ለማወቅ ሃጂንና ሌሎችንም እያየ።

ሃጂ ባንድ እጃቸው ሹል ጺማቸውን ወደ ታች እየላጉና በሌላው መቁጠሪያቸውን እቆጠሩ ዝም አሉ።

‹‹አስፈላጊውን ነገርና ስፍራ እኔ አዘጋጃለሁ። በቶሎ ወደ ሚዘጋጅልዎ ስፍራ ይሄዳሉ›› አለ አሊ.ሃሽ፣ ሃጂን እየተመለከተ።

እሱም እምቢም ሳይሉ ፊታቸውን ወደሌላ መለሱ።

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

እነበሪሁን ካደሩበት የስብሰባ ስፍራ ሲመለሱ፣ የቤታቸው በር ገርበብ ብሎ አገኙት። ከፍተው ቢገቡ እስማኤል የለም። ጉዋዳም ማድቤትም አጡት። ‹‹ወዴት ሄዶ ይሆን?›› እያሉ ወጣ ገባ ሲሉ፣ አስጊ አደጋ፣ በተለይም የኢትዮጵ ጦር አይሮፕላኖች ሲመጡ የሚሰማው የማስጠንቀቂያ ድምጽ (ሳይረን) ጠላት ጦር ሰፈር ውስጥ ጮኸ። ይህ ድምጽ በሚሰማበት ጊዜ ሰው ሁሉ በየበሩ በቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ በግባት ከአይሮፕላኖች የቦምብ  አደጋ ራሱን መሸሸግ አለበት። ማስጠንቀቂያው በቀን ቢያንስ አምስትና ስድስት ጊዜ ይጮሃል። አብዛኛውን ጊዜ አይሮፕላኖች አይመጡም። ቢመጡም የጦር ሰፈሮችን እንጂ ከተማውን አይደበድቡም። በመሆኑም ህዝቡ ማስጠንቀቂያውን ችላ ይለው ጀመር።

እነበሪሁንም በማስጠንቀቂያው አልተሸበሩም። በከተማዋ ዙሪያ ያለው ያየር መቀወሚያ ተኩስ ግን ከወትሮው ለየት አለባቸው። ለሌላው ጊዜ ተኩሱ ላንድ  አፍታ ዋይ ዋይ ይልና ዝም ይል ነበር። ያንለት ግን ጅብ እንደመጣባቸው ውሻዎች የጣር ጩኸቱን አምባረቀው።

ወዲያው ያን ሁሉ እሩምታ የዋጠና ከተማይቱን ከመሰረትዋ ያናጋ ወፍራም ድምጽ በተከታታይ ተሰማ። እነበሪሁን ሮጠው ወደ ውጭ

ወጡ። የአየር መቃወሚያው ጥይት ከተማይቱ ሰማይ ላይ እንደእሳት ጉመራ ይፈላል። ሁለት አይሮፕላኖች በጥይቱ ፍላት ውስጥ እየተሽከረከሩ ውልብ አሉና ጠፉ። ጠላት ጦር ሰፈር ውስጥ ጥቁር ጭስ ትጉልል፣ እያለ እየተሽከረከረና ጃንጥላ እየመሰለ ሽቅብ ወጣ።

ትንሽ ቆይቶ ተኩሱ ቀነሰ። የአደጋ ምልክቱ ሳይረን ግን ኡኡ በማለት ላይ ነው። ወታደሮችና ባለስልጣኖች መብራቶቻቸውን ባበሩ መኪናዎች እየተሩዋሩዋጡ፣

‹‹ሰው ሁሉ እሳት ሊያጠፋ የሚችል ነገር እየያዘ፣ ወደ አደጋው ስፍራ ይሄድና እርዳታ ያርግ!!›› ይሉ ጀመር። በሪሁንና አሰግድ የተደሰቱበትን አደጋ ሂደው ለማየት ፈለጉ። በሌላ ወገን የእስማኤል ከቤት መታጣት ክፉኛ አሳሰባቸው። የጠላት ወታደሮች እንዲህ ያለውን ግርግር ለዘረፋ ስለሚጠቀሙበት ቤቱን መጠበቅም አለባቸው። ማረግ የሚገባቸውን ሲያሰላስሉ፣ እስማኤልሮጠ መጣ።

‹‹የት ሄደህ ነበር?›› ሁለቱም ጠየቁት።

‹‹እዚሁ ቅርብ ነበርኩ፣ እናንተ ደህና ናች?›› አለ ቶሎቶሎ እየተነፈሰ፣

‹‹አደጋው ቦታ ብንሄድስ?›› አለ አሰግድ መሮጥ እያቃጣው፣

‹‹አያስፈፈልግም፣ አንሄድም፣ ኑ ወደ ቤት እንግባ›› አለ እስማኤል ቀደም ብሎ። ቤት ገብተው በየስራቸው ላይ ተፍ ተፍ ይሉ ጀመር።

‹‹ምን ውሳኔ ላይ ደረሳችሁ›› አለ እስማኤል በሪሁንን እያየ።

‹‹አደጋ የመጣሉ ተግባር እንዲጀመር ወስነናል››

‹‹ወካስ፣ (እንዲያ ነው) ››

‹‹የት ነበር የሄድከው?››

‹‹የግመል ሥጋ ሳያልቅ ለመግዛት በጠዋት ቄራ ሄድኩና፣ አንድ

አስደንጋጭ ወሬ ሰማሁና ሁኔታውን ይበልጥ ሳጣራ ቆየሁ፡፡››

‹‹የምን ወሬ?››

‹‹ባክህ ያን ሰውዬ ሊያስሩት ነው››

‹‹የቱን?››

‹‹ያን ደህና ወሬ ይሰጠን የነበረ የመረጃ ክፍል ሰራተኛ››

‹‹የቱ ነው እሱ አላውቀውም››በርይሁን ትኩር ብሎ አየው፣

‹‹አዎ፣ ከናንተ ጋር እንኳዋን አላስተዋወቅሁትም፡፡ ከአሊሃሽ ጋር ነበር ያገናኘሁትና የሚሠራው፡፡ ረዘም ወፈር ያለ ነው፡፡ መጀመሪያ እናንተን ይገናያችሁ የመጣሁ እለት እዚህ አግኝተነው በሰዓት እላፊ አይያዝም ያልኩዋችሁ ሰውዬ››

‹‹አወቅሁት ፣ ለምንድነው የሚያስሩት?››

‹‹በድርጊቱ ደርሰውበት ይሆናላ!››

‹‹እንዲህ ከሆነማ አሊሃሽ ፣አንተ፣ ሁላችንም በአደጋ ላይ ነን በለኛ!›› አለ በሪሁን አፍጦ፡፡

‹‹ሰውዬው ስለኛ ፣በተለይም ስለ ቡድናችን ጠለቅ ያለ ምስጢር አያውቅም፡፡ ምናልባት ምርመራ ከበዛበት አሊሃሽን ያጋልጠው ይሆናል፡፡ ይህንኑ ለአሊሃሽ ነግረነው በጋራ አንድ ዘዴ እንፈልጋለን›› በለሬው ተነፈሰ፡፡

‹‹ዝም ብሎ ከሚያዝ ለምን አይሸሽም?››

‹‹ይህንኑ ጠይቄውነበር፡፡ እንዲያውም እኔ ሃላፊነቱን ወስጄ ልደብቅህ ብየው ነበር፡፡››

‹‹ታዲያስ?››

‹‹እምቢ አለኝ››

‹‹ተነስ እንሂድ››አለ በርይሁን ፈጠን ብሎ፡፡

‹‹የት?››

‹‹እስውዬው ዘንድ››

‹‹ለምን?››

‹‹ምን ቸገረህ ተነስ››

ውጩን ያጨለመው የጭስና ያቡዋራ ደመና ትንሽ ገፍዋል። ለእርዳታ የወጡ ሰዎች ይሩዋሩዋጣሉ። አበዛኞዎቹ የመገደድ እንጂ፣ የፍላጎት ተግባራዊ ተሳትፎ አይታይባቸውም። የወታደር መኪናዎች ውሃና እርዳታ ሰጪ ሰዎችን ወደ አደጋው ስፍራ ያግዛሉ።

በሪሁንና እስማኤል ከቤታቸው ወጥተው ግርግሩ መሐል ተቀላቀሉ። ወደ ሚሄዱበት እየሮጡ ስፍራ ሲቃረቡ፣ ወደ መንደር መንገድ ገቡ ገቡ። እስማኤል እየመራ፣ በሪሁን እየተከተለ ትንሽ ሄደው አንድ እተዘጋ ቤት አጠገብ ደረሱና ቆሙ።

‹‹ብቻውን ነው?›› አለ በሪሁን በሹክሹክታ

‹‹አዎ›› በሩን አንኩዋኩዋ፣ እስማኤል።

‹‹ማነህ?›› አለ አንድ ጉርናና ድምጽ ከውስጥ

‹‹እኔ እስማኤል ነኝ››

በሩን የከፈተው ሰውዬ አንገቱን ብቻ ብቅ አርጎ ተመለከተና አይኖቹን በሪሁን ላይ እንደተከለ

‹‹ምነው እስማኤል፣ ምን ፈለግህ?›› አለ

‹‹ልናነጋርርህ ፈልገን ነበር። እዚህ ከምንቆም ቤት ብንገባስ?››

ሰውዬው እነ እስማኤልን ካስገባ በሁዋላ በሩን ሊዘጋ መለስ ሲል፣ በሪሁን ቀልጠፍ ብሎ የቀኝ እጁን ክርን ውዬው አንገት ላይ በመጠምጠም ወደ ሁዋላ ዘርጥጦ ጣለው። ሰውዬው ግዙፍና ጠንካራ ስለነበር ክፉኛ ታገለው።

‹‹ እርዳኝ እንጂ፣ ቆመህ ታየኛለህ እንዴ?›› አለ በረሀን የሰውዬውን አንገት ቆልምሞ እንደያዘ እስማኤል ላይ አፍጦ።

እስማኤል እየተርበተበተ፣ ባር ይዘዋቸው የበረሀንን ፊት ለመቡዋጠጥ የሚወራጩትን የሰውዬን እጆች ያዘለት።

በረሀን ባለ ሃይሉ የሰውየውን አንገት ቆልምሞ ቆየና ለቀቀው። ተዝለፍልፎ በጀርባው ተዘረጋ። መሞቱን አረጋግጠው በሩን መለስ አረጉና በመጡበት ሁኔታ ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

ጦር ሰፈሩ ውስጥ የሚነደውን እሳት ለማጥፋት የከተማው ህዝብና ጦሩ ውሃ በማፋሰስ፣ አሸዋ በመበተን... ያረገው ሙከራ ሁሉ ከንቱ ሆነ። ምንም ሳይበግረው ሲነድ ዋለና አውቶ ጠፋ። ቀን ብቅ ሳይሉ የዋሉት የእስማኤል ምግብ ቤት ደንበኞች ማምሻውን በብዛት መምጣት ስለጀመሩ፣ እነበረሀን ሥራ በዛባቸው። እያዘገዩ የሚመጡትን ደንበኞቻቸውን፣

‹‹በዛሬው እለት በደረሰው አደጋ ምክንያት ለእርዳታ ሄደን ስለነበር፣ በቂ ምግብ አላዘጋጀንም። ያዘጋጀነውም አለቀ፣ ይቅርታ አርጉልን›› እያሉ መለሱዋቸው።

ትንሽ ቆየት ብሎ ወዳጃቸትን እያሉ የሚያግባቡት የጠላት ጦር ሙቶ አለቃ መጥቶ፣

‹‹ዛሬ ያለውን ነገር ስጡኝ፣ በጣም ርቦኛል›› እያለ ስለ ለመናቸው፣ ጎዋዳ ገብተው ድስቱንም መጥበሻውንም እየጠራረጉ ያገኙትን አቀረቡለት።

‹‹በዛሬው አደጋ ብዙ ንብረት ተጎዳ እንዴ?›› አለ በረሀን ለሙቶ አለቃው ሻይ እየቀዳለት።

‹‹አስራ ሰባት ከባድ መኪናዎች ነዳጅ እንደጫኑ ነደዱ›› አለ

እያለመጠ፡፡

‹‹አሥራ ሰባት መኪናዎች!!››አሉ በሪሁንና እስማኤለ የውሸታቸውን ደንግጠው፡፡

‹‹መቼ ይሄ ብቻ ፡ የስንቅ እጥረት ባለበት በአሁኑ ጊዜ ለቁጠባ እያሉ ያሸጉት አንድ መጋዘን ሙሉ ስንቅ አብሮ ከስለላቸው፡፡ጠራቸውን ምን ያበሉት ይሆን? ››

‹‹እንዴት መኪናዎቹን ግልጽ ቦታ ያቆሙዋቸዋል ባለስልጣኖቻችን?›› አለ በሪሁን የዘነ በመምሰል፡፡

‹‹የኛ ከፍተኛ መኮንኖች ስህተቶቻቸውን በበታቾቻቸው ጫንቃ ላይ መጫናቸው ነው የሚገርመው፡፡ ከሣያ የሚበልጡ የበታች (የመስመር) መኮንኖችን አስረዋል፡፡ ››

‹‹ወቀሳውም ሆነ ምስጋናው ለሁሉም ነው፣. . .›› እያለ በሪሁን ሲናገር ሙቶ አለቃው አቁዋረጠውና፣

‹‹አደለም፣ እንደሱ አደለም፡፡ ወቀሳው፣ ቅጣቱ፣ ሞቱ፣ ችግሩ ለኛ፤ ምስጋናውና ሹመቱ ለነሱ ነው›› አለ፣ መመገቡን አብቅቶ ለመሄድ እየቸኮለ፤

‹‹አላህ ይስጣችሁ፣ በሉ ደህና እደሩ ፣ ምናልባትም አንገናኝ ይሆናል፡፡ አለቆቻችን ሲደናገጡ የሚይዙትን የሚጨበጡትን ነው የሚያጡት፡፡ የበታቾቻቸውን በማሰርና በመግደል ሃላፊነታቸውን የተወጡ ይመስላቸዋል፡፡ እና እንደጉዋደኞቼ የመታሰር ወይም የመሞት እድል ይገጥመኝ ደርሰኝ ይሆናልና፣ ደህና ሁኑ፡፡ እድል ከጋረደችኝ እንገናኛለን››እያለ ሄደ ወጣ፡፡

ሰዓት እላፊው ደርሶ፣ እነ አሰግድ በራቸውን ዘግተው ቤቱን ሲያጸዳዱ፣

‹‹የትኛው አለቃቸው ነው እንዲህ የሚያስመርራቸው? ኮሎኔል ሳላህ ቤሪ የሚሉት ይሆን እንዴ?›› አለ በሪሁን ሲሸጥ የዋለውን የምግብ ሂሳብ እየቆጠረ፡፡

‹‹እሱ አይደለም፤ እሱንማ ጦሩ በጣም ነው የሚወደው፡፡ ኮሎኔል አደም ፋራህ የሚባለውን ነው፡፡ እሱ ነው የሚያሰቃያቸው፡፡ እዚህ ያለው ብርጌድ አዛዥና የከተማውም የበላይ አስተዳዳሪ እሱ ነው፡፡ ጦሩ የሚፈልገው እሱ እንዲነሳለትና ‹ደግ ነው› የሚባለው ኮሎኔል ሳላህ ቤሪ በቦታው እንዲተካለት ነው፡፡›› አለ እስማኤል የታጠቡ ሳህኖችን እያስተካከለ፡፡

‹‹ኮሎኔል ሳላህ ቤሪ መገደል አለበት››

‹‹ኮሎኔል አደም ፋራህ ማለትህ ነው?››

‹‹አይደለም ፤ ደግነው የሚባለው ሳላህ ቤሪ››

‹‹አደም ፋራህስ?›› አለ እስማኤል ግራ ተጋብቶ፡፡

‹‹እሱ ይቀመጥ›› አለ በሪሁን ፈገግ ብሎ፡፡

‹‹እንዴት ክፋውንና በጦሩ የተጠላውን ትተን፣ ደጉንና በጦሩ የተወደደውን እንገለዋለን?››

‹‹ለኛ ሁለቱም ጠላቶቻችን ናቸው፡፡ እርምጃ ስንወስድ ግን ለአላማችን መሳካት የሚረዱንን ሁኔታዎች እየመረጥንና እየመረመርን መሆን አለበት፡፡ አየህ እስማእል፣ ክፋው አዛዥ ከነክፋቱ ሲቆይና በሕዝቡና በጦሩ ላይ የሚፈጽመው ግፍ እየበዛ ሲሄድ፣ አንደኛ ህዝቡ ተመሮ ለነጻነቱ የሚያረገውን ትግል እንዲያፋጥን ይገፋፋዋል፡፡ ሁለተኛ የጦሩ ሞራል ይወድቃል፣ በአዛገሮችና በወታደሮች መሀል የለው አለመግባባት ይከርራል፡፡ ይሄ ጠቃሚና የምንፈልገው ነገር ነው፡፡››

‹‹ታደያ ደጉ አዛዥ ለምንድነው የሚገደለው?›› አለ እስማኤል

‹‹በእሳት ላይ ቤንዚን ለመጨመር›› ሳቀ፣ አሰግድ፡፡

" ልክ ነህ፣ በእሳትላይ ቤንዚን ለመጨመር ነው፡፡ ጠሩ የሚወደውን አዛዥ ሲያጣ ቁጣው ይጨምራል፡፡ ‹ሌሎቹ አዛገሮቹ አውቀው ነው ደጉን አዛገሮችንን ያስገድሉት› ብሎ በአዛገሮቹ ላይ ያምጻል፤ ገባህ?›› እስማኤልን ትኩር ብሎ አየው፡፡

‹‹ገባኝ›› እስማኤል እራሱን እየነቀነቀ፡፡

‹‹ያን የመረጃ ሰራተኛ ዛሬ የገደላችሁት ለምንድነው?›› አለ አሰግድ በሪሁንንና እስማኤልን እያየ፡፡ እስማኤል ከትከሻው ነጠር አለና፡-

‹‹ ወላሂ፣ እኔም እስከ አሁን ነገሩ ግልጽ አልሆነኝም፡፡ በርይሁን እንሂድ ሲለኝ አንድ ዘዴ ልናማክረው መስለኝ እንጂ፣ እንደዚያ ያለ ሁኔታ እንፈጽማለን የሚል ግምት አልነበረኝም››

‹‹ለምን እንዳደረግነው አልገባህም?››

‹‹አው››

‹‹ይቅርታ አርግልኝ፣ የተግባባን መስሎኝ ነበር፡፡ በግልጽ ሳላስረዳህ በመቅረቴ ጥፋተኛ ነኝ፡፡ ወደፊት አላረገውም፡፡ የሙዋቹን መገደል አስፈላጊ ሆኖ ያገኘሁበት ምክንያት ይህ ነው፡፡ ሰውዬው በአንድ ነገር በመጠርጠር ሊያዝ እንደሚፈለግ ተረድቶ ለጊዜውም ቢሆን ተሸሽግዋል፡፡ ይህን ያረገው ቢያገ፣፣ የተጠረጠረበትን ነገር ካላወጣ እስከ ሞት የሚያደርስ ስቃይ እንደሚደርስበት ተረድቶ ነው፡፡ ግን ለዘለቄታው ለመሰወር አይፈለገም፡፡ ታዲያ በፍቃዱ እጁን ከሰጠ፣ ወይም ከተያዘና ምርመራው ከቀጠለ፣ የሚያው ቀውን ምስጢር ማውጣቱ አይቀርም፡፡ ምናልባትም ከሚጠረጠርባቸው ነገሮች አንዱ

ከአሊሃሽ ጋር ያለው ግንኙነት ሲሆን ስለሚችል፣ ከስቃዩ የትነሣ አሊሃሽን ያስይዘው ይሆናል፡፡ የአሊሃሽ መያዝ ደሞ የሁላችንም መያዝና ፣ የቡድናችን መጥፋት ነው፡፡ ይህ ሁሉ ከመድረሱ በፊት ነገሩን በአጭሩ መቅጨቱ አስፈላጊ ሆነ፣ ጊዜውና ስፍራውም አመቺ ነበር፣ ያ አጋጣሚ ሳያመልጠን ልንጠቀምበት ተገባ፡፡ ማንኛውንም ለእንቅስቃሴያችን እንቅፋት የሚሆን አደገኛ የግንኙነት ሰንሰለት ቶሎ መበጠስ አለብን፡፡ ለዚህ ነው ያን እርምጃ የወሰድነው›› አለ በሪሁን ፈገግ ብሎ፡፡

‹‹መልካም አርጋችሁዋል፡፡ እኔ እንኩዋን ምክንያቱን በትክክል ገምቻለው፡፡ እስማእል እንደኔ እንዳልገባው ስለተረዳሁ ነው ነግሩን ያነሳሁት"አለ አሰግድ፡፡

ኢስማኤል ፈገግ ብሎ እጁን ወደ በሪሁን ዘረጋና፡፡

‹‹ወገሬናያ›› (ገባኝ) ብሎ ጨበጠው፡፡

የምሽት ስራቸውን ጨርሰው ሰሞኑን ከተማው ውስጥ ስለሚፈጽሙዋቸው አደጋዎችና ስለሚገደሉ ሰዎች ተነጋግረው፣ ‹‹መቼ? እንዴት ?›› በሚለው ሃሳብ ሲወያዩ፣ ራቅ አለ ስፍራ ከባድ የፈንጂ ድምጽ ተሰማና የእሩምታ ተኩስ ተከታተለ፡፡ ተኩሱ ቀዝቀዝ፣ደመቅ ሲል ቆየቶ ወደ ከተማው መሃል እየቀረበ መጣ፡፡

ከተማይቱ በሌላ ጦር የተወረረች መሰለ፡፡

‹‹ደሞ ምን ተፈጠረ?›› አለ እስማኤል ጭንቅ እያለው፡፡

‹‹ቅድም መቶ አለቃው እንዳለው ጦሩ ዕርስ በርሱ መተላለቅ ጀምሮ ይሆን?›› አለ በሪሁን፡፡ ሶስቱም መሳሪያዎቻቸውን በመያዝ መብራቱን አጥፍተው የሚመጣውን ነገር በተጠንቀቅ ይጠብቁ ጀመር፡፡

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

‹‹ባለፈው ሌሊት ያን ሁሉ ተኩስ ስሰማ ጠዋት አንድም ሰው በህይወት የሚገኝ አልመሰለኝም ነበር፤ ለምን ነበር ተኩሱ? ›› አለ አሊ ሃሽ ወዳጁ ከሆነ የጠላት ጦር አምሳ አለቃ ጋር ጉዋዳ ውስጥ ለብቻቸው ጫት ሲቅሙ::

‹‹የኢትዮጵያ ጦር የላከብን አደጋ ጣይ ቡድን ከተማዋን ሊያጋያት ነበር:: እንደምንም ተሩዋሩጠን መለስነው››

‹‹እንዴት ባክህ›› አለ የውሸት ወደንገጥ ደንግጦ

‹‹ልክ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሲሆን መጥተው ወደ ፊት መውጫ መንገድ ላይ ባለው የጦር መሳሪያ ግምጃ ቤታችን ላይ አደጋ በመጣል አቃጠሉት፤ ያን ስንከላከል፣ በጎን አሳብረው ወደ ከተማይቱ መሃል ገቡ:: እነሱን ለማስወጣት ነበር ተኩሱ››

አሊ ሃሽ ይህን ሲሰማ ድርጊቱ በከተማይቱ ዙሪያ አደጋ እንዲጥል በተመደበው ቡድናቸው የተፈጸመ መሆኑን ተረዳ:: እቅዱን ቀደም ብሎ ያወቀው ቢሆንም፣ በጠላት ጦር በኩል የተፈጠረውን ሁኔታ ለማወቅ ፈለገና፣

‹‹ታዲያ አስቀራችሁዋቸው አመለጡ?››

‹‹አመለጡ ባክህ፣ ለከተማይቱና ለአካባቢዋ ጥበቃ ኃላፊ የነበረው ሻለቃና ወታደሮቹ ታስረዋል::››

‹‹መሆን አለበት፣ መታሰር አለባቸው››

የአምሳ አለቃው የጦሩ የመረጃ ክፍል ሰራተኛ ሲሆን፣ አሊ ሃሽ

ወዳጅ በመምሰል ብዙ ጠቃሚ መረጃዎች ከሚያገኝባቸው ሰዎች አንዱ ነው፡፡

‹‹ሃይላችሁን እያጠናከራችሁ ጥብቅ ቁጥጥር አርጉ፣ እንዳታስጨርሱን››

‹‹ሃይላችን ላልቶ አይደለም አደጋው የተፈፀመው፡፡ ከተማው ውስጥ የኢትዮጵያ ጦር በድል አድራጊነት እንዲመጣላቸው የሚጠበቁ አሉ፡፡ እነሱ ናቸው የሚያስጠቁን፡፡ መጀመሪያ እነሱን በመጠራረግ ከተማይቱን ማጽዳት አለብን ››

‹‹እንዲህ የሚያረጉ ካሉማ በእርግጥ ሊጠራረጉ ይገባል፡፡››

‹‹አሉ ፣ ብዙዎች አሉ፡፡ በትናንትናው እለት ትንሽ ቀንሰናል፡፡ ሰሞኑንም ይቀጥላል››

‹‹በየግንባሩ ያለው ጦራችንስ እንዴት ነው?››

‹‹ደህና ነው፡፡ አንዳንድ ፈሪዎች ወደ ፊት በመሄድ ፈንታ ወደ ሁዋላ እየተመለሱ ስለ አስቸገሩን በቀደም ሌሊት

ቀጋቸውን ሰጥተናቸዋል፣ እርምጃው የቀጥላል››

ከወሬዎቹ ብዙዎቹ ለአሊሻሽ እንግዳ አልነበሩም፡፡ ቀደም ብሎ ከመደበኛ ወሬ አቀባዩ ሰምቶዋቸዋል፡፡ እውነተኛነታቸውን ለማረጋገጥ ስለፈለገ ነው ምንጩ ድረስ ሄዶ የሚቆፍረው፡፡ አምሳ አለቃው ሲጃራውን ሳብ ቡልቅ አረገና፡-

‹‹አንድ ልክስክስ ሠራተኛችን ራሱን ገደለ›› አለ

‹‹ማነው እሱ?፣ ለምን?››

‹‹የኛ ክፍል ባልደረባ ነበር፣ ተከታታይ፡፡ ከተማይቱ ውስጥ ካሉና ከአንዳንድ ከማይታመኑ ሰዎች ጋር እየተገናኘ ምስጢር የሚያባክን መሆኑ ተደረሰበት ሊያዝ ሲል የመርዝ ክኒን ውጦ ራሱን ገደለ፡፡ ከሱ

የምንፈልገው ብዙ ነገር ነበር፡፡ ምን ያደርጋል ቀደመን፡፡››

አሊሃሽ ሰውየው በነበርይሁን እንደተገደለ ቢያውቅም፣ በህይወት ቢያገዘ ኑሮ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ገምቶ ዘገነነው፡፡ ብቻ ድንጋጤው የተቆርቋዋሪነት መሰለ፡፡ ‹‹የሚገናኛቸው ሰዎች እነማን እንደነበሩ ታውቀዋል?›› ሲል አሰበና ከአፉ መለሰው፡፡

‹‹ቀደመን፣ ቀደመን›› አለ አምሳ አለቃ በቁጭት ራሱን እየነቀነቀ

‹‹ከፍተኛ ሚስጢሮችን ይበልጥ ሳያባክንና ለአደጋ ሳይዳርገን መሞቱ ጥሩ ነው፡፡ ብቻ እንደነዚህ ባሉ ልክስክሶች እንጻር ቆራጥና ጀግኖች አባሎች ስለአሉን ደስ ይለኛል፣ እጽናናለሁ፣ እንደኮሎኔል ሳለህ ቤሪ የተወደዱና የተመሰገኑ አዛገሮች አሉን››አለ አሉሃሽ የፈለገውን ምስጢር ለማግኘት ወደ ሚረዳው አቅጣጫ ነገሩን በመለወጥ፡፡

‹‹አዎ፣ ሳላህ ቤሪ በጣም ግሩም አዛዥ ነው፡፡ በቅርብ ቀን የዋና አዛዥነቱን ስፍራ ይጨብጣል፡፡ ትእዛዙ ከሞቃድሾ እስኪመጣ ነው የሚጠብቀው፡፡ በመንግሥቱ ስልጣን አካባቢ ያሉት የሱ ጎሳ ሰዎች ደካሞች ስለሆኑ ነው እስከ አሁንም የቆየው››

‹‹በከተማው አለ እንዴ? ሰሞኑን አላየሁትም››

‹‹ወደ ግንባር ሄዶ ነበር፣ ትናንት መጥቷል፡፡ በቅርብ ቀን አንድ የሙዚቀኞች ቡድን ከሞቃድሾ ስለሚመጣ በዚህ አካባቢ የሚደረገውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያሙዋላ ታዝዋል"

‹‹በከተማ ውስጥ ያለው ሁኔታ እንደሰሞኑ ከቀጠለ የሙዚቃ ቡድኑ የሚመጣ ይመስልሃል? ትርኢታቸውንስ የት ያሳያሉ ብለህ ነው?››

‹‹ለነገሩማ የሰዓት እላፊውን ለሁለተኛ ጊዜ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት

ወደ አራት፣ ወይም ስድስት ሰዓት ገፋ ልናረገው ነበር። የሚቀጥሉትን ሁለት ቀናት አይተን ሁኔታው ከተሻሻለ፣ ባይሆን እስከ አራት ሰዓት ገፋ እናረገዋለን። ይህ ከተቻለ የሙዚቀኞቹ ቡድን ይመጣና ቢቻል ከተማው መሃል፣ባለው የመውሲድ ሜዳ ለህዝቡ፣ በየጦር ሰፈሩ ደሞ ለጦሩ ያሳያል። ካልተቻለ ግን ያው ለመኰንኖቹና ለሌሎች ባለስልጣኖች ብቻ አንድ አዳራሽ ውስጥ አቅርቦ ወደ መጣበት ይመለሳል ››

‹‹የሙዚቃውን ትርኢት ለማየት ብንችል መቼም ደስ ይለናል››

‹‹ይሞከራል፣ እንሞክራለን›› አለ በባለስልጣን አነጋገር።

‹‹ህዝቡ እስከዛሬ እንዳረገው ሁሉ በጉልበት ሥራ ይተባበራል። ያው ዱርበናችሁን(ነጋሪታችሁን) ስትጎስሙት ወጥተን እንሰራለን››አለ አሊሃሽ ሳቅ እያለ።

ዱርበን (ነጋሪት) ከተማው መሃል ረጅም ማማ ላይ የተሰቀለ ታምቡር መሳይ ከበሮ ነው። ይህ ከበሮ ወይም ነጋሪት ከአርብ በቀር በየእለቱ ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ይጎሰማል። ያኔ አቅሙ ለሥራ የደረሰ ማንኛውም ሰው ይወጣና በቀጣና ኃላፊዎች አማካይነት እየተሰለፈ ለልዩ ልዩ የጉልበት ስራዎች ይሰማራል። ድንጋይ ሲሸከም፣ መሬት ሲቆፍር፣ ቆሻሻ ሲጠርግና ሲያግዝ እስከ ጠዋቱ አንድ ሰዓት ድረስ ይቆያል። በተለይ ቀደም ብሎ ለሌላ ስራ አገለግሎት ተከምሮ የነበረውን ብሎኬት ጠላት የገበያ አዳራሽ እስራበታለሁ ብሎ ወደ አስጀመረው ስፍራ ለማጉዋጓዝ ሕዝቡ በከፊተኛ የጉልበት ሥራ ተጠምዶ ያረፍድ ነበር። ብሎኬቱ ካለበት፡ አዳራሹ እስከሚሰራበት ስፍራ ድረስ ህዝቡ ጎን ለጎን ይሰለፋል። ከቦታው ርቀትና ከሰው ብዛት የተነሳ አንዱ ጫፍ ቆሞ ሌላውን ለማየት አይቻልም። በዚህ ሁኔታ

ሰዉ ባለበት ቆሞ፣ ድንጋዩን በመቀባበል ብቻ እሚፈለግበት ስፍራ ያደርስ ነበር። ያለበቂ ምክንያት ለሥራ ያልወጣ ሰው በገንዘብ ወይም በእስራት ይቀጣል።

‹‹እየህ ክቡር እሃምሳ አለቃ›› አለ አሊሃሽ ሻዩን እየቀዳለት፣

‹‹እየህ ፣ እውነተኛ ወዳጆቻችሁን ከአስመሳዮች በጥንቃቄ ለይታችሁ ማወቅ አለባችሁ። እናንተን መስለው የተጠጉዋችሁ ብዙ ተንኰለኞች አሉ››

‹‹ካሉ መጋለጥና መመንጠራቸው እርግጥ ነው››

‹‹እኔ እንከዋን ይህን ያነሳሁት ለሃያሉ ጦራችንና በግልም ላንተ ለወንድሜ በማሰብ ነው። ከዚህም ሌላ የማውቀውን ክፉ ነገር የማሳወቅ ኃላፊነት አለብኝ። የማውቀውን መግለጥ የኔ ኃላፊነት፣ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ የናንተ የባለስልጣኖች ፋንታ ነው።››

‹‹ምን የምታውቀው ነገር አለ?››

‹‹ያን ሸህ መሐመድ አህመድን ምን ያህል ታውቀዋለህ?››

‹‹ሼህ መሐመድ እንዳንተው ረዳታችንና ወዳጃችን መሆኑን ነው የማውቀው›› አይኖቹን በሰፊው ከፈተና አየው። አሊሃሽ እየሳቀና ራሱን እየነቀነቀ፣

‹‹አይመስለኝም፣ በደንብ አታውቀውም። እኔን የምታውቀኝ በሱ ደረጃ ከሆነ፣ ባልታወቅ ይሻለኛል። ‹ዘመዶቼን ጠይቃለሁ› እያለ አስፈላጊውን መረጃ ሁሉ ከዚህ ወስዶ ለኢትዮጵ ጦር እያቀበለ ነው የሚመጣው። ትንሽ የካርታ ትምህርት ስለ አለው፣ የኛ ጦር ያለበትንና የድርጅት ማከማቻ ስፍራዎችን ሁሉ እነሱ በሚሰጡት ካርታ ላይ ምልክት እያረገላቸው አይደለም እንዴ በአይሮኘላን የሚደበድቡን? ትላንት የተቃጠሉትን መኪናዎች ጠቁዋሚ ባይኖር

እንክርዋን በሩቅ ያለ ጠላት፣ እኛስ እናውቃቸው ነበር፡፡ ታማኝ እየመሰለ እውነተኛ ወዳጆቻችንን የጠላት ጠቋሚዎች ናቸው እያለ የሚያስፈፈጅና በጠላት ብቻ ተከበን፣ ተቃዋሚዎች እንዲበዙብን የሚያረግ ሰው ነው፡፡ ብዙ ነገር ስታውቂ እንዴት ይህን መረዳት አቃታችሁ? ›› እጆቹን በብስጭት አወራጨ፡፡

በጉንጩ የሞላውን ጫት ማኘኩን አቁሞ በጥሞና ሲያደምጠው ቆየና፡-

‹‹ነው?›› አለ አምሳ አለቃ፡፡

‹‹ልንመልሰው ለማንችለው አደጋ ተጋልጠን ሲቆጨን እንዳይኖር ብዬ ነው›› አለ አሊሃሽ ንግግሩን ጫን አርጎ፡፡

የአምሳ አለቃው የያዘውን የጫት እንጨት እየሰነጣጠረ ትንሽ ሲያስብ ቆየና፣

"በዛሬው ሌሊት ዋጋውን እንሰጠዋለን›› አለ ለመሄድ እየተነሳ፡፡

ሼህ መሐመድ አህመድ፣ የጠላት ጦር ታማኝ ወዳጅ ነው፡፡ ነጻነት ፈላጊ የሆኑ ብዙ ሰዎችን እየጠቆመ አሳስርዋል፤ አስገድልዋል፡፡ አሊሃሽ የሰውዬውን ድርጊት ሲከታተል ከቆየ በሁዋላ፣ የነሱም የቅርብ ቀን ጠላት እንሚሆን ገመተ፡፡ በመሆኑም ሳይቀደማቸውና በቡድናቸው አባላት ላይ አደጋ ሳያደርስ የሚጠፋበትን ወጥመድ በየአቅጣጫው ማስቀመጥ አስፈላጊ መሆኑን ተረዳ፡፡ ለዚህ ነው ከሚያምነው ጦር ጋር በማቃቃር እሾህን በእሾህ ለማውጣት የተነሳው፡፡

# አሥራ አራት

‹‹ያ ሰውዬ መጣ!›› አለ በሪሁን ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለ።

‹‹የቱ?›› አለ ኢስማኤል አይኖቹን አፍጦ።

‹‹ያ ያንተ ሠራተኛ››

‹‹ከሰላ ይዞ ብቅ ወዲህ ሲመለከት አየሁት። እኔና አሰግድ እንከተለዋለን፣ አንተ እዚሁ ቆይ›› ብሎ አሰግድን ትከሻው ላይ መታ አረገውና ተከታትለው ወጡ። እስማኤል ሊያናግራቸው ሲሞክር፣ በፍጥነት ዋናውን መንገድ አቋርጠው ራቁት። እሱን በግማሽ እንደከፈተ፣ በር ላይ ቆሞ ሲመለከታቸው መንደር ውስጥ እጥፍ አሉና ተሰወሩ።

‹‹ምን ሊያረጉት ነው የሚከተሉት?›› እያለ ጉዋዳ ውስጥ ወዳለው አንግዳ ሄደ። ሰውዬው በደፋን ጦር ውስጥ በሹፌርነት የሚያገለግል ወታደር ነው። ረሺድ ሙስጠፋ ይባላል። ከነ እስማኤል ጋር እየተገናኘ እንዲሰራ በአሊሃሽ በኩል ከተላከ አንስቶ ጦሩ ውስጥ ቡድኑን የሚመለከቱ ብዙ ጠቃሚ ስራዎች አከናውኗል።

‹‹ብዙ መሥራት ይቻላል። ዋናው ነገር ሚስጢር መጠበቁ ነው። የጦሩ የስለላ ድርጅት በጣም ብዙ አባላት ስላሉት ምስጢር ለማግኘት ብዙ ጊዜ አይወስድበትም። ከዚህም ሌላ እንኩዋን አንድ ፍንጭ አግኝቶ ‹በይሆናል› ብቻ የፈለገውን እርምጃ መውሰድ መሆኑን መርሳት የለብንም››አለ ረሺድ ረጅም አፍንጫውን እያሻሸ ፡፡

‹‹ቀደም ብዬ እንደገለጥኩልህ የዛሬው ተልእኮህ ከበፊቱ ለየት ያለና ትንሽ ከበድ ያለ ይሆናል፡፡ ይሄውም ኮሎኔል ሳላህ ቤሪን መግደል ነው፡፡  ባጭር ጊዜ ውስጥ መፈፀም አለበት፡፡ ኮሎኔሉ በቅርቡ ከሞቃዲሾ ለሚመጣው የመቀዘቀኞች ቡድን አንዳንድ ነገሮችን ለማዘጋጀት ከተማው ውስጥ ስለሚገኝ  ለማገኛውም አደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ ይህን እድል ወደ ፊት አናገኘው ይሆናል፡፡ ሲሩዋሩዋጥ ስለምታገኘው በሚቀጥሉት ሶስት ቀናት  ግዳጅህን መፈጸም አለብህ፡፡ ማንኛውም ነገር ተጠንቶ ነው ትእዛዙ የተሰጠህ፡፡ አስቸጋር ነገር ያለ አይመስለኝም፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ካልተፈጠረ ትእዛዙ መፈፀም አለበት፡፡ ገባህ?››

‹‹ገባኝ፡፡››

‹‹የወታደሮች የደንብ ልብስ ፈልግ ተብለህ ነበር››

‹‹አዎ፣ ተብዬ ነበር፡፡››

‹‹ታዲያስ?››

‹‹ነገሩን አንተ ቀድመህ አነሳኸው እንጂ የእኔም አመጣጥ ስለዚሁ ልነግርህ ጭምር ነበር፡፡ ትጥቁ በቀላሉ የሚገኝ አልሆነም፡፡ ምክንያቱም ለደፋን ጦር አባሎች የተሰጣቸው የደንብ ልብስ አንዳንድ ብቻ በመሆኑ፣ በግገርም ሆነ በሌላ ዘዴ ብሞክር ላገኝ አልቻልኩም፡፡ አንድ የደፋን አባል መለወጫ የሌላትን አንድ ልብስ ቢሸጥና ነገሩ ቢደረስበት ቅጣቱ እስከሞት ሊሆን ይችላል፡፡ የሌሎቹን የጦር ክፍሎች የደንብ ልብስ ግን በመጠኑም ቢሆን አግኝቻለሁ፡፡››

‹‹ያገኘኸውን አምጣ፣ ሌላው በኛ በኩል ይፈለጋል፡፡ ሰሞኑን በአየር መቃወሚያ ክፍል አባላትና በናንተ መካከል የተደረገው የተኩስ ልውውጥ በጠና ዘንድ ምን ዓይነት ስሜት ፈጥርዋል?››

‹‹ውጥረቱ አሁንም አልበረደም። ባለሥልጣኖች ከጦር ሰፈር ወደ ጦር ሰፈር በመሩዋሩዋጥ ላይ ናቻው። እኛም ነገሩ እንዳይበርድና፣ ግጭቱ እንዲከር በማነሳሳት ላይ ነን። እንደውም ትላንት አንድገና ተኩስ ሊጀምር ትንሽ ሲቀረው ነው ከሀሉቱም ወገን ባለስልጣኖች መጥተው ያበረዱብን››

‹‹አየር መቃወሚያዎች በጣም ፈርተዋችሁዋል›› አለ ኢስማኤል እየሳቀ።

‹‹ለምን አይፈሩንም ፣ ብዙ ሰዎች ናቸው ከ የተጎዱባቸው። ከኛ አራት ሰዎች ብቻ ናቸው የሞቱብን።››

‹‹ባለስልጣኖቻችሁ መንስኤውን በደንብ ተረዱት?››

‹‹መፍትሔ ባላገኙለትም እንጂ ተረድተውታል። በጦርነት እሳት ውስጥ እየገባን የምንማገደው እኛ መሆናችንን፣ ጥሩ ጥሩ ቀለብ፣ ልብስና ደሞዝ የሚያገኙት ግን ሌሎች መሆናቸውን፣ በጦሩም ሆነ በባለ ስልጣኖች ዘንድ የተናቅን መሆናችንን አስረድተናል። ለተኩሱ ልውውጥና ለብዙ ሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የሰርዲን ስንቅ ጉዳይ መሆኑንም አስረድተናል። ስንቁ ራሽን ባለቀብን ጊዜ የተትረፈረፈ ስንቅ ከነበረው የአየር መቃወሚያ ጦር ዘንድ በምጽዋት መልክ የመጣልን ነበር። ምጽዋቱን ከምስጋና ጋር ተቀብለን እየቆጠብን በመመገብ ላይ ሳለን፣ አየር መቃወሚያዎቹ መጥተው ራሽን ስላለቀብን የሰጠናችሁን ሰርዲን መልሱልን አሉን፣ እኛ ሌላ ስለሌለን አንሰጥም ብንላቸው፣ በግድ እንወስዳለን ብለው ተኩስ ከፈቱብን ብለን ገልጠናል››

‹‹ምርመራው ገና በረጅሙ ሳይቀጥል አይቀርም›› አለ እስማኤል።

‹‹ይህ እንዳይሆን ነው የኛ ጥረት። ምርመራው መቆም አለበት።

ያለዚያ ቀስቃሾች ናቸው የሚሉዋቸውን ሰዎቻችንን አንድ በአንድ እየለቀሙ ነው የሚፈጁዋቸው፡፡ እስከ አሁንም ባልታወቀ ምክንያት ሁለት ሰዎች ከመካከላችን ጠፍተውብናል፡፡ ያለን አማራጭ ውጥረቱ ይበልጥ እንዲከር መገፋፋት፣ ካልተቻለም ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ ማረግ ነው››

‹‹ጥሩ ነው፣ ብቻ ጠንቀቅ በል፡፡ በአፋኞች እጅ እንዳትወድቅ፡፡ በዙሪያህ ያሉትን ደጋፊዎቻችንንም አስጠንቅቃቸው፡፡ ሰሞኑን አንድ ጽሁፍ ይሰጥህና በሚስጢር ትበትናለህ፡፡ ከሁሉ በፊት ግን በኰሎኔሉ ላይ የተሰጠህን ግደጅ መፈጸም አለብህ፡፡›› አለና ብድግ ብሎ ለስንብት ጨበጠው፡፡

ወታደሩን ሸኝቶ በር ላይ እንደቆመ፣ በሪሁን ቶሎ ቶሎ እየተራመደ መጣ፡፡

‹‹አሰግድስ?›› አለ እስማኤል በርይሁንን ሁዋላ እያየ፡፡

‹‹ይመጣል፣ የተከተለኝ ሰው መኖሩን ተመልከት›› አለውና ወደ ውስጥ ገባ፡፡ ትንሽ ቆይቶ አሰግድ መጣ፡፡ እሱም እንደበሪሁን ‹ ‹የተከተለኝ ሰው መኖሩን ተመልከት›› ብሎት ገባ፡፡

እስማኤል በር ላይ ቆሞ እንደታዘዘው አካባቢውን ሲቃኝ፣

‹‹እንዴት ነው? ›› አለ በሪሁን ከውስጥ፡፡

‹‹ምንም የለም›› መለሰ አለሃሽ፣

‹‹የምሳ ሰዓት ደርሷል ፤ ደንበኞቻችን አሁን ይመጣሉ፣ ሲደርስ የሚችለውን ምግብ ቶሎ ቶሎ እናዘጋጅ›› አለ በሪሁን ሸርጡን እየታጠቀ፡፡

‹‹ምን አርጋችሁ መጣችሁ?›› አለ እስማኤል፣ ምግብ ለማብሰል በሚዘጋጁበት ጊዜ በርየሁንን እና አሰግድን እያየ ፡፡

‹‹በሁዋላ እንነጋገራለን፣ አሁን ወደ ስራው›› አለ በሪሁን ተፍ ተፍ እያለ፡፡

በሪሁን እንዳለው ቶሎ ቶሎ ብለውና ተረዳድተው ለምሳ የሚሆን ምግብ አደረሱ፡፡ ገበያው ደርቶ የበላው ሲወጣ፣ ያልበላው ሲገባ ቆየ፡፡ ዘግየት ብሎ አንድ አጠር፣ ፈርጠም ያለ ሰውዬ መጣ፡፡ ከዚያ ቀደም እነ እስማኤል ቤት ተመግቦ አያውቅም፡፡ ሸርጥ አገልድሞ ከላይ እጀ ጉርድ ሸሚዝ ለብሰዋል፡፡ በልብሱና በሰውነቱ ንጽህና ሰውዬው ከከተማው ነዋሪዎች፣ በተለይም ከአዲስ መጦቹ አንዱ መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡

በሪሁን ሰውዬውን ሲያየው አንዳች ነገር ውርር አረገው፡፡ የታዘዘውን ምግብ ለማምጣት ማድቤት ገባና፣

‹‹አሰግድ ያ ሰውዬኮ መጣ! ››አለ፡፡

‹‹ የቱ? ›› አይኖቹን አፈጠጠ፡፡

‹‹ የአፋኞች ሙቶ አለቃ፡፡ ጠዋት የእስማኤል ሰራተኛ ካነጋገራቸው ሰዎች አንዱና፣ አጠር ያለው››

‹‹የታል?››

‹‹ምግብ ቤት ውስጥ ተቀምጥዋል፣ ልብሱን በመለወጥ ሸርጥ አገልድሞ ነው የመጣው፡፡ ምግቡን ይዘህለት ሂድና እየው››

አሰግድ እንደ ታዘዘው አርጎ ተመለሰና፣

‹‹አየሁት ፣ እሱ ነው›› አለ በሪሁንና እስማኤል ወደሚነጋገሩበት ጉዋዳ ገብቶ፡፡

‹‹አንተ ወደ ሰውዬው ሂድና አጫውተው›› አለ በሪሁን እስማኤልን ገፋ እያረገ፡፡

‹‹ሊሰልል፣ ወይም አንድ ነገር ሊያረግ ነው የመጣው›› አለ አሰግድ

ዘንፈሩን ነከሱ።

በሪሁን በሁለት እጆቹ ወገቡን ይዞ ፊት ለፊት እያየ፣

«ማታ ሲመጡብን አስበዋል ማለት ነው፣ ምን ይሻላል?» አለ

«እንበለው፣ እናስቀረው» አለ አሰግድ ቡጢውን ጨብጦ። በሪሁን ሰውዬው ወደ ነበረበት ሄደና አካባቢውን ቃኘ። ምግብ ቤቱ ውስጥ ሌላ ተመጋቢ የለም። እስማኤልና ሰውዬው ብቻ ያወራሉ። ቀልጠፍ ብሎ ወደ ማድቤት ተመለሰና አጥንት የሚክሰክሱበትን መጥረቢያ በሸርጡ ከልሎ ያዘና፣

« አሰግድ ተከተለኝ» አለው። ተከታትለው ሲወጡ አሰግድ ወደ ሁዋላ ቀረት አለ።

«መረቅ ልጨምርልዎት?» አለ በርይሁን ወደ ሰውዬው እየተጠጋ። ሰውዬው ከእስማኤል ጋር የሚያረገውን ውይይት ለማቋዋረጥ ስለአልፈለገ ያልሰማ መሰለ።

በሪሁን ተመቻቸና ባለ ሃይሉ ተንጠራርቶ መጥረቢያውን በዘቢያው በኩል ሰውዬው ማጅራት ላይ አሳረፍው። ሰውዬው ብድግ አለ። አሰግድ ሮጦ ግብግቡ ውስጥ ሲገባ እስማኤል ወደ ዋናው በር ሄደ። በሰከንዶች በሚቆጠር ጊዜ ውስጥ እነ በሪሁን ሰውዬውን አዳክመው እየጎተቱት ማድ ቤት ገቡ።

ጥቃቱ ድንገት ባይሆንና ለሁለት ባይረባረቡበት ኑሮ፣ ሰውዬው በቀላሉ የሚበገር አልነበረም። እሰማኤል በስጋት እየተሸማቀቀ ምግብ ፍለጋ የሚመጡትን ሁሉ በር ላይ ቆሞ፣

«ምግብ የለም፣ አልቅዋል » እያለ መለሳቸው።

«አሬሳውን ለጊዜው የት እንደብቀው?» አለ አሰግድ ወደ እስማኤለ መጥቶ።

በሪሁን፣ አሰግድና እስማኤል ማንኛውንም ነገር ካከናወኑ በሁዋላ ምሳ ይመገቡ ጀመር።

‹‹ሰውዬው ‹የጥቁር ለባሽ › ጦር አባል መሆኑን በምን አወቃችሁ?›› አለ እስማኤል ሁለቱን በመገረም እያየ።

‹‹ከዚህ ቀደምም አይቼዋለሁ። ዛሬ ደግሞ ያንተን አሽከር እየተከተልን ስናደባ በቀጥታ ሄዶ ከአሁኑ ሙዋችና ከአንድ ሌላ ሰው ጋር ተገናኘ። ሰስቱ አንድ ቤ[illegible] ነግ ቆመው ለረጅም ጊዜ አወሩ። ከለላ ይዘን እንመለከታቸው ነበር። አሁን የገደልነው ሰውዬ ሙቶ አለቃ እንደነበር በለበሰው የደንብ ልብስ ተረድቻለሁ። አሽከርህ ከነሱ ተሰይቶ እየተገላመጠ ቁልቁል ወደ ቆረአሲ (የከተማው የቆሻሻ መጣያ ) አመራና አንድ ጎጆ ውስጥ ገባ። አንዲት ባልቴት ከጎጆይቱ ወጣ ገባ ስትል ቆየችና እቃ ብጤ ይዛ ወደ ከተማው መሃል አመራች። ቀልጠፍ ብለን ወደ ጎጆይቱ ብንገባ፣ አሽከርህ ጠመንጃ ሲፈታታ አገኘነው። ከተቀመጠበት ሳይነቃነቅ ሥራችንን ሰርተን መጣን" እያለ በርየሁን ሲናገር፣

"ገደላችሁት?" አቋዋረጠው እስማኤል።

"አው፣ ያኔ ነው በደንብ ያየሁት። ከሱ ያገኘነው ሽጉጥ፣ ገመድና አውቶማቲክ ሴንጢ የጥርጣሬያችንን ትክክለኛነት ያረጋግጣል››

‹‹ይህን በማረጋችን በላያችን ያንጀበበው የስጋት ደመና ለጊዜውም ቢሆን ተነዋል›› አለ አሰግድ ቀበል አርጎ።

‹‹ድንቅ ስራ ነው የሰራችሁት። ጉዋዳችን ያለውን ሬሳ ምን እናርገው? የመረጃ ክፍሉ ሠራተኞች የሙዋቹን እዚህ መግባት አውቀው ከሆነ ጠብቀው ሲቀርባቸው መጥተው ቤታችሁን እንደፈትሽ ማለታቸው አይቀርም›› አለ እስማኤል ጭንቅ እያለው።

# ምዕራፍፍ አሥራ አምስት

ጀንበር ጠልቃ ለአይን ያዝ አርግዋል፡፡ ከተማይቱን ሲያነፍራት የዋለውን ወበቅ ሊያባርር ቀዝቀዝ ያለ ንፋስ ሽውሽው ይላል፡፡ ከሌላው ጊዜ በተሻለ ፀጥታ ሰፍንዋል፡፡ አንድ ባለሽራ የወታደር መኪና ዝግ ብላ መጣችና እነ እስማኤል በር ላይ ቆመች፡፡ ጂዋ ወደ ቤት ገብቶ ከነበሪሁን ጋር ሰላምታ ከተለዋወጠ በኂላ፣ በቀጥታ ወደ ጉዋዳ አለፈ፡፡

‹‹ረሺድ›› አለ ኢስማኤል ሰውዬውን እየተመለከተና እየተጣደፈ፣

‹‹አሁን ያስጠራሁህ ለጥብቅ ጉዳይ ነው፡፡ የአንድ ጠላታችን ሬሳ እቤታችን ውስጥ አለ፡፡ ራቅ አለ ስፍራ ውሰድና ጣልልን፡፡ የምንደብቅበት ቦታ ልናገኝ አልቻልንም፡፡ ልንደብቀውም አልፈለግንም፡፡ በሬሳው በኩል የምናስተላልፈው መልእክት አለን፡፡ በዛሬው ሌሊት አሰሳ ይደረጋል ብለን ስለፈራን፣ ከዚያ በፊት ሬሣው ቦታ እንዳይገዘልን እንፈልጋለን››አለ፡፡

ረሺድ አይኖቹን በሰፊው ከፍቶ አፍንጫውን እያሻሸ፣

‹‹ቀደም ብለህ የሰጠኸኝን ግዳጅ በዛሬው ምሽት ለመፈጸም ተዘጋጅቼ ነበር፡፡ አሁን ደሞ ሌላ ግዳጅ ደረብክብኝ›› አለ ቅር እያለው፡፡

‹‹ይሄኮ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ግዳጅ አደለም፡፡ ሬሳውን ከወሰድክ በሁዋላ ያንኛውንም ግዳጅ ልትፈጽም ትችላለህ፡፡ ካልሆነም ያኛውን ለሌላ ቀን አስተላልፈው፡፡ ይሄ ጊዜ የሚሰጠው ችግር አደለም›› አለ በሪሁን ወገቡን በሁለት እጆቹ ይዞ፡፡

‹‹መልካም፣ እንዴት ነው የምንጭነው?›› አለ ወደ መኪናው

እየተመለከተ።

‹‹መኪናህን በሁዋላው ወደ በሩ ጠጋ አርገህ አቁመው። ሌላ ሰው እስመስለን በጆንያ እንጭነዋለን›› አለ አስግድ እየተጣደፈ።

‹‹የትነው የምጥለው?››

‹‹ወደ ጦር ሰፈራችሁ ጠጋ አርገህ ግመል ገበያ አካባቢ ትጥለዋለህ። በዚያ አካባቢ በምሽት ሰው አይበዛበትም። አካባቢውን የመረጥንበት ሌላ ምክንያት፣ ከሬሳው ጋር እንዲያያዝ ያዘጋጀነው ጽሑፍ ስላለ፣ ቀን ብዙ አንባቢ ያገኛል ብለን ስለ ገመትን ነው››

‹‹በሉ አዘጋጁ ›› አለ ረሺድ መኪናውን ሊያስተካክል እየወጣ።

እነበረሁን ሌሎች እቃዎችን እያወጡ መኪናው አጠገብ ሲያስቀምጡና ሲያነሱ፣ አካባቢውን ሲቃኙ ቆዩና ሬሳውን በጆንያ አምጥተው በፍጥነት መኪናው ውስጥ ከሁዋላ አጋደሙት።

በርይሁን መኪናው ውስጥ ገባና ሬሳው የተጠቀለለበትን ጆንያ ገፈ ሰፋ ባለ ወረቀት ላይ ያዘጋጁትን ጽሁፍ ሬሳው ደርባ ላይ በሲባጎ አስሮ ወረደ።

‹‹የህዝብ ጠላቶች አንድ በአንድ ይለቀማሉ። አፋኞችና ገዳዮች ይመነጠራሉ። ያለ አግባብ የተገደሉትን የዶፋን ጦር አባላት ደም በእጥፍ እንበቀላን›› ይላል ጽሁፉ። ይህ የተደረገበት ምክንያት በጦሩ መሃል ያለው አለመግባባት ይበልጥ እንዲከር ለማረግ ነው። ረሺድ ዋናው መንገድ እስኪገባ የመኪናውን መብራት ሳያበራ ሄደና ፍጥነቱን ጨምሮ ተሽከረከረ።

እነ እስማኤል ሰዓት እላፊው ከመድረሱ በፊት በራቸውን ዘግተውና መሳሪያዎቻቸውን ይዘው፣ ውጭ፣ ማድቤቱ ደርባ አደፈጡ። ይህን ያረጉት ሌሊቱን አፋኞች ወይም አሳሾች ይመጣሉ

በሚል ስጋት ነበር፡፡ ሰዓት እላፊው ትንሽ እንደቆየ፣ ከተማው መሃል የአውቶማቲክ ተኩስ ተሰማ፡፡ የወታደር መኪናዎች በከተማይቱ መንገድ ለይ ይሩዋሩጡ ጀመር፡፡ ሌሊቱ እየገፋ ሲሄድ ሁሉም ነገር ፀጥ ብሎ፣ የነ እስማኤል ስጋትና ፍርሃትም መለስ አለ፡፡ የፈሩት አፈና ወይም አሰሳ የለም፡፡ አደሩበት እንዳሉ የምስራቅ አድማስ ቀልቶ ሰማዩ የጋለ ብረት መሰለ፡፡ በየንጋቱ የሚያገሳው የዱርበን ድምጽ ግን አልተሰማም፡፡ መሳሪያዎቻቸውን ደበቁና ቤት ገቡ፡፡

ረፋዱ ላይ የወታደር መኪናዎች ከተማዪቱ ውስጥ እየተዘዋወሩ፣

‹‹ማንኛውም ሰው አሁኑኑ ለስብሰባ ወደ መውሊድ ሜዳ እንዲወጣ!!›› እያሉ ለፈፉ፡፡ ዋና ዋና መንገዶች በታጠቁ ወታደሮች ተሞሉ፡፡ ረፋዱ ላይ የከተማው ሕዝብ እንደ ታዘዘው በተወሰነለት ስፍራ ተሰበሰበ፡፡ ከላይ የጸሀይ፣ ከታች የአሸዋው ግለት ወበቁን አብሰውታል፡፡

‹‹ምን አርጉ ነው የሚሉን በዚህ ሙቀት?››

‹‹ምን አውቅላቸዋለሁ፣ እነሱ ሲሸነፉና አንድ ነገር ሲደርስባቸው፣ ውጭ ተደብድቦ ንዴቱን በሚስቱ ላይ ለመወጣት ወደ ቤቱ እንደ ሚሮጥ ባል ወደኛው ነው የሚያፈጡት፡፡››

‹‹ትናንት ማታ የሆነውን ሰምተሃል?››

‹‹አልሰማሁም፣ ምን ሆነ?››

‹‹የአፋኙ ጦር አባል የሆነ አንድ የሙቶ አለቃ ሞቶ ተገኘ፡፡ የጦሩ ምክትል አዛዥ ኮሎኔል ሳላህ ቢሪም ተገደለ፡፡››

‹‹ምን ገደላቸው?››

‹‹አፋኙን ሙቶ አለቃ የገደሉት የደፋኑ ጦር አባላት ናቸው፡፡ የኮሎኔሉ ገዳይ አልታወቀም››

‹‹አይ መከራችን፣ እንግዲህ ሲያምሱን ሊሰነብቱ ነው›› እየተባባለ የተሰበሰው ሕዝብ በሹክሹክታ ያወራል።

በህዝቡ ዙሪያ ያሉት ወታደሮች መሳሪያዎቻቸውን በተጠንቀቅ ይዘዋል። ከሜዳው በስተምእራብ ሲል አንድ አነስተተኛ ጠረጴዛና ሶስት መንበሮች የተደረጉበት መድረክ ይታያል። በመድረኩ ዙሪያ መትረየሶች የያዙ ጥቁር ለባሽ ወታደሮች የተቆጣ ነብር መስለው ቆመዋል።

የጦር መኰንኖች እየመጡ በመድረኩ ዙሪያ ቆሙ። ጥቂት እንደ ቆየ የጦሩ አዛዥ በመኰንኖች ታጅቦ ብቅ አለ። እንደ ንብ መንጋ ‹‹ "እምም ›› ይል የነበረው የሕዝቡ ድምጽ ቀስበቀስ ቀንሰና ጸጥታ ሆነ። አዛገዩ በተዘጋጀለት ስፍራ ተቀምጠ ከረዳቶቹ ጋር ሲነጋገር ቆየና ቆመ። በባትሪ ድንጋይ የሚሰራ የድምጽ ማጉያ በሌላ ሰው ተያዘለትና ረዘም ያለ ንግግር አረገ። የንግግሩ ይዘት አብዛኛው ሰው ከገመተው የራቀ አልነበረም።

‹‹ጠላቶቻችን የግንባሩ ጦርነት አልሆነላቸው ሲል ጊዜ፣ ወታደሮቻቸውን አስርገው መሃላችን በመስገባት አደጋ መጣል ጀምረዋል። የሠራጊዎቹ ተልእኮ መሐላችን ካሉት ደጋፊዎቻቸው ጋር የተቀነባበረ ነው። ውስጣችን ሆነው ሚስጢራችንን ለጠላት የሚያቀብሉ፣ አደጋ ጣዮችን በስውር የሚቀበሉና የሚሸኙ ሰዎች አሉ። ... እነዚህን ከዋናዎቹ ጠላቶቻችን ለይተን አናያቸውም። እንደውም አደገኛ ጠላቶቻችን እነሱ ናቸው። ... እስከ ዛሬ እራሱ ከመሃሉ መንጥሮ ያወጣቸዋል በማለት ሕዝቡን አምነን ነገሩን ችላ ብለነው ነበር። እምነታችን ግን ከንቱ ሆንዋል። ሌላ ትርጉምም ተሰጥቶታል። እንደ ደካሞችና ምንም እንደማናውቅ ተቆጥረናል። ግን

አይደለንም። እንዳልሆንም ከዛሬ ጀምረን እናሳያችሁዋለን›› እያለ ሲናገር ያንገቱ ስሮች ተገታተሩ። ስለተፈጸሙት ድርጊቶች ግን ምንም አልጠቀሰም። ንግግሩን ሲጨርስ፣ በዙሪያው ከነበሩት መኰንኖች ጭብጨባ ሌላ ድምጽ አልተሰማም።

አለባበሱን ካስተካከለና ላቡን ከጠራረገ በሁዋላ መለስ ብሎ፣

‹‹እምጡዋቸው እነዚያን ከሃዲዎች›› አለ። በፈጥኝ የታሰሩ አስር ሰዎች በወታደሮች እየተገፉ ብቅ አሉ። አፎቻቸው በነጭ ጨርቅ ተሸብበዋል። እነበሪሁን የሰዎቹን ማንነት ለማረጋገጥ ሰዉን እየገፉና እየተሹለከለኩ ወደፊት ተጠጉ።

‹‹ረጅሙ ሰውዬ ሼህ መሐመድ አህመድ ነው›› አለ እስማኤል አፉን በመዳፉ ከልሎ በሹክሹክታ

‹‹ሼህ መሐመድ የቱ?›› አለ በሪሁን አይኖቹን ሰዎቹ ላይ እንደተከለ።

‹‹ሼህ መሃመድን አጣኸው?›› ገላመጠው።

ሰዎቹን ለማየት ሕዝቡ የፈጠረው ትርምስ ገብ እንዳለ፣ አዛገፉ ወደታሰሩት ሰዎች እያመለከተ፦

‹‹እነዚህ ጉያችን ያሉ እባቦች ናቸው። እነሱንና እነሱን የመሳሰሉትን ጠላቶቻችንን ከመካከላችን ካላስወገድን የሰላም እንቅልፍ ልንተኛ አንችልም።›› አለና ወደ ወታደሮቹ ዞር ብሎ በጁ አንድ ምልክት አሳያቸው።

ወዲያው ጥቁር ለባሾቹ ወታደሮች ሰዎችን እየገፋፉ አቅራቢያው ወዳለ አሮጌ ቤት ግድግዳ አስጠጉዋቸውና በጉልበቶቻቸው እንዲንበረከኩ አረጉዋቸው። ስፍራው የነበረው ሰው የሚደረገውን ላለማየት አየኖቹን ጨፍኖ ‹‹ላኢላሃኢለላ!›› እያለ ያውካካ ጀመር።

‹‹ጠመንጃ ቀምተን. . .›› አለ አሰግድ በሁካታው መሃል ድምፁን ዝቅ አርጎ።

‹‹አይሆንም ህዝቡን ታስጨርሰዋለህ። እነ አብርሃም ደቦጭ የፈጸሙት ጀብድ ያስከተለውን እልቂት ለመገመት ባለመቻላቸው ነው አዲስ አበባ በደም የታጠበችው›› አለ በርይሁን ቆጣ ብሎ።

‹‹ተረረረረም!!›› የጥይት እሩምታ ተሰማ። የተንበረከኩት ሰዎች ድፍት እያሉ ግንባሮቻቸውን አሸዋው ላይ ተከሉ።

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

የነበሪሁን ስብሰባ እንደ ተለመደው አሊሃሽ ቤት ውስጥ በመካሄድ ላይ ነው። ተሰብሳቢዎቹ ቀደም ብለው ቦታቸውን ይዘዋል። የዚያን እለቱ ስብሰባ በወሳኝ ጊዜና በአስቸጋሪ ወቅት የሚደረግ ስለ ነበር፣ ከሌሎቹ ስብሰባዎች ሁሉ ለየት ይላል ። ስብሰባው ላይ ለመገኘት የመጡት ሰዎች ቁጥር ግን አነስ ያለ ነበር።

በሪሁንና አሰግድ እስማኤልን ቤት ትተውት ነው የመጡት። ከተማው ዙሪያ ያለው አደጋ ጣይ ቡድን መሪ ሐሚድ ጣሂር አለ። የሚጠበቁት ሃጂ ጎዳኒ ብቻ ነበሩ። ከተገመተው በላይ ስላመሹ አሊሃሽ ሊጠሩቸው ሄደና ብቻውን ተመለሰ። እንደገባም ያለ አንዳች ንግግር አቀርቅሮ ቁጭ አለ።

‹‹ምን ሆነሃል አሊሃሽ?፣ ሃጂ ደህና አይደሉም እንዴ?›› አለ ሐሚድ ጣሂር።

‹‹ስንነግራቸውና ስናስጠንቅቃቸው ችላ እያሉ ተገደሉ!›› አለ ሲቃ እያነቀው።

‹‹መቼ?›› አሉ ሁሉም ባንድነት።

‹‹ከግማሽ ሰዓት በፊት፣ አልያዝም እያሉ ሲታገሉ ገደሉና ሬሳቸውን ይዘውት ሄዱ አሉ›› አለ እነዳቀረቀረ።

ቤቱ በከባድ ዝምታ ተዋጠ። ሁሉም አቀረቀሩ።

‹‹የሆነው ሆንዋል፣ አሁን ውይይታችንን እንቀጥል። እኛንም

የሚጠብቀን እድል እሳቸው የገጠማቸውን የመሰለ ሊሆን ይችላል፡፡ ባለፈ ነገር መቆጨቱ፡ ፋይዳ የለውም፣ ቁም ነገሩ የሆነውን ላለመድገም መጠንቀቅ ነው›› አለ በርይሁን ምክር በሚመስል አነጋገር፡፡

ሁሉም ሃሳባቸውን ሰበሰቡና በበሪሁን መሪነት ውይይቱ ቀጠለ፡፡ ስብሰባው የድንጋጤና የስጋት ደመና አንዣበበበት፡፡ በተለመደው መሠረት መጀመሪያ አሊሻሽ ሪፖርቱን አሰማ፡፡

የየቡድኑ መሪዎች ስለ ስራቸው አፈጻጸም በየተራ ሪፖርት አቀረቡ፡፡››

‹‹ጥቆማ› ብቻ እንደተጨባጭ ማስረጃ በሚያገለግልበት በአሁኑ ጊዜ ብዙ መሥራት ይቻላል፡፡ ተጣጥሮ የባለስልጣን ወዳጅ መሆን ነው፡፡ የባለስልጣን ወዳጅ ባለሥልጣን ነው፡፡ ይታመናል፡፡ ቢዋሽ እንኳዋን ደፍሮ ‹ውሸታም› የሚለው የለም፡፡ የወደደውን መልአክ፣ የጠላውን መልአክ ሰይጣን ነው ብሎ ሊጠቅምም ሆነ ሊጎዳ ይችላል››አለ አሊሻሽ ትንሽ ፈገግ ብሎ፡፡

"የጠላት ጦር ምንም ቢረሽኑትና ቢያስገድዱት ወደ ፊት ለመግፋት አልቻለም፡፡ እንደውም የያዘውን ስፍራ እየለቀቀ ወደ ሁዋላ በማፈግፈግ ላይ መሆኑ ይወራል፡፡ የወገን ጦርም ሚሊሽያውን ጨምሮ፣ በዘመናዊ ትጥቅ በመደራጀት ላይ ስለሆነ በቅርብ ቀን ማጥቃት ይጀምራል የሚል የፍርሃት ሹክሹክታ በጠላት ጦር ሰፈር ይሰማል፡፡

"የጠላት ጦር ባለሥልጣናትንና አደገኛ ጠላቶቻችንን በመግደል፣ በመካከላቸው ጠላትነት እንዲፈጠር በማረግና በየጦር ሰፈራቸው አደጋ በመጣል...እስከ ዛሬ ብዙ ሰርተናል፡፡ ከዛሬ ጀምሮ የተወሰኑን ሰዎች በተለይም እኔና አለግድ ከእይታ መሰወር (ህቡዕ መግባት) አለብን፡፡

ለአሁኑ ሁኔታ ያለን አማራጭ ይህ ነው፡፡ አሊሻሽና እስማኤል አሰገዳጅ ሁኔታ እስከመጣ ድረስ አሁን ባሉበት ሁኔታ ይቀጥሉ፡፡ የኛ ህቡዕ መግባት እንቅስቃሴያችንን ለማፋጠን ይረዳናል፡፡ ለወደፊቱ እርስ በርሳችን የምንገናኝበትን አዲስ ስልትም መቀየስ አለብን... ›› አለ በርይሁን ቡድኑ የሚጠብቀውን ግዙፍ ሃላፊነት በሚያስገነዝብ አነጋገር፡፡

እኩለሌሊት ሆኖ የቡድኑ ስብሰባ ሊያበቃ ሲቃረብ፣ ራቅ ካለ ቦታ ተኩስ ተጀመረና እየቀረበ መጣ፡፡ የመኪናዎች እሩጫና ትርምስ በዛ፡፡ ትንሽ እንደቆዩ ቡድኑ ያለበት ቤት በር ተንኳኳ፡፡ ሁሉም ወደዚያ አፈጠጡ፡፡ በሪሁን ወደ አሰግድ ዞር አለና፣

‹‹ቦንቡን ይዘሃል?›› አለው፡፡

‹‹አልያዝኩም ሽጉጥ አለ›› አለ ጎኑን እየዳበሰ፡፡ በሩ አሁንም በሃይል ተመታ፡፡ ሃሚድ ጣሂር ከሸርጡ ውስጥ ሁለት ቦምቦች አውጥቶ አንዱን ለበሪሁን ሰጠውና ወደ አሊሻሽ ዞር ብሎ፣

"በጉዋሮ በር ወጥተን ውጭ እንቆይ፡፡ ዋናውን ቤት አልፈው ከመጡ አስፈላጊውን እናረጋለን›› አለ፡፡ የቤቱ ዙሪያው አጥር ነው፣ ባጥሩ ቢሾልኩ ወይም ቢዘሉ ሌላ አጥር ውስጥ ነው የሚገቡት፡፡

‹‹በሩን ሰብረው መግቦታቸው አይቀርም፡፡ ልክፈትላቸው፡፡ እንደ ምንም ብዬ በዘዴ መልሳቸዋለሁ እናንተ ገዝም ብላችሁ ተቀመጡ›› አለ አሊሻሽ ወደ በሩ እየሄደ፡፡

‹‹ቆይ! ሁላችንም አንድ ላይ እንሂድና አንተ በሩን ስትከፍት ድንገት አደጋ ጥለን ለማምለጥ እንሞክራለን፡፡ ካልተቻለም አብረናቸው እናልቃለን›› አለ አሰግድ የአሊሻሽን ክንድ ይዞ፡፡ ‹‹ግድ የላችሁም መብራቱን አጥፉና ተቀመጡ›› አለ አሊሻሽ አለባበሱን እያስተካከለ፡፡

ቤት ውስጥ የቀሩት ሁሉ መብራቱን አጥፍተው ወደጉዋሮ በመውጣት ከለላ እየያዙ ቆሙ፡፡

‹‹ሞተሃል እንዴ ይህን ያህል ስንጣራና በር ስንደበድብ?›› አለ አንድ ጐርናና ድምጽ ከውጭ፡፡

‹‹ከባድ እንቅልፍ ይዞኝ ነበር››

‹‹አሃሃሃሃ! ምነው ፈራህ እንዴ? አይዞህ!›› አለ ጎርናናው ድምጽ ወደ ውስጥ እየገባ፡፡ የባትሪ ብርሃን ጭለማው ቤት ውስጥ ብልጭ ድርግም ሲል ይታያል፡፡

‹‹እንዳንተ ያለ ወዳጅ እያለኝ ለምን ፈራለሁ›› አለ አሊሃሽ ድምጹን ከፍ አርጎ እየሳቀ፡፡ አሳሳቁ ለተደበቁት ጉዋደኞቹ ‹‹አይዝዋችሁ፣ሰላም ነው›› የሚል መልእክት ነበር፡፡ አሊሃሽና ባለ ጎርናናው ድምጽ ሰውዬ ጉዋዳ ገብተው በሹክሹክታ ሲነጋገሩ፡ ቆዩና፡-

‹‹ያለችኝ አንዲት ፓኬት ሲጋራ ብቻ ናት፡፡ ጫት አልገዛኩም!›› አለ አሊሃሽ ድምጹን ከፍ አርጎ፡፡

‹‹ግድ የለም!›› አለ ሰውዬው እየወጣ፡፡ እነበሪሁን ይህን ሲሰሙ እፎይ አሉና ወደቤት ተመለሱ፡፡

‹‹የመረጃ ክፍሉ አምሳ አለቃ ነው፣ ውጭ ተቶዋቸው ገባ እንጂ ብዙ ወታደሮች አስከትልዋል፡፡ ይህን ‹አስቀምጥልኝ›ብሎ ሰጠኝ፡፡ ሲዘርፉ ነው መሰለኝ ያመሹት›› አለ አሊሃሽ በሸርጥ የተጠቀለለ ነገር እያሳያቸው፡፡

‹‹ፍታው እስቲ›› አለ ሃሚድ ጣሂር ሸርጡን እያየ፡፡ ለማያዩዊ ቀለም የሚበዛው ዝጉርጉር ሸርጥ አልፎ አልፎ የደም ነጠብጣብ ይታይበታል፡፡ ሲፈታ በርከት ያለ ገንዘብና ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች ብቅ አሉ፡፡ ሁሉም በመደነቅ አፎቻቸውን በመዳፎቻቸው ከደኑ፡፡ አስግድ

ብድግ አለና ከብዙ ጌጦች መሃል አንዱን የወርቅ ቀለበት አንስቶ አየ። አይኖቹ ባንዴ እንባ አቀረሩ። ከንፈሩን ነከሶ ዞር አለና ለበሪሁን አሳየው። በሪሁን ቀለበቱን ተቀበለና መዳፉ ላይ ያነጥረው ጀመር። ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አለ።

‹‹ምንድ ነው እሱ?›› አለ ሃሚድ ጣሂር ቀለበቱ ላይ አፍጦ።

‹‹ኢስማኤልን ገለውታል›› አለ አሰግድ በተሰባበረ ድምጽ።

‹‹ቀለበቱም ሽርጡም የሱነው›› አለ በሪሁን ቀለበቱን ወደ ደረቱ ይዞ።

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

የደገሃቡር ሰማይ በስስ ጭጋግ ተሸፍንዋል፡፡ ንፋሱ አሸዋ እየዘገነ ከፊቱ በሚያገኘው ነገር ላይ ይበትነዋል፡፡ ጠንከር ብሎ ሲመጣ ደሞ ዛፎቹን እያስጎነበሰና ዘና ብሎ የሚያገኘውን ነገር ሁሉ እየነጠቀ ይጋልባል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደሞ ሁሉም ነገር ጸጥ ይልና ሙቀቱ ከሲኦል የሚርከፈከፍ ረመጥ ይመስል መድረሻ ያሳጣል፡፡ ከተማይቱን የሚያስጨንቃት ይህ ብቻ አልነበረም፡፡ ጦርነቱ ያስከተለባት ሰቆቃ እየባሰ መጥትዋል፡፡ ሞት ነግሶ በየእለቱ በእፍኙ ሙሉ እየዋጠ፣ ለሚቀጥለው እለት ምሱ ሌሎችን የሚያዘጋጅበት ወቅት ነው፡፡ አብዛኛዎቹ መኖሪያ ቤቶችና ሱቆች ተዘግተው እንዳደሩ እንደተዘጉ ይውላሉ፡፡ የታጠቁ የጠላት ወታደሮች አላፊ አግዳሚውን በግልምጫ ያሸቆጠቁጡታል፡፡

አንድ ከገጠር የመጣ ሰውዬ ሁለት ፍየሎች እየነዳ መሸጫ ወደ ተከለለው የገበያ ስፍራ ያመራል፡፡ አንድ ቢዮሌ (ውሃ እየቀዳ የሚሸጥ ልጅ) በርሜሉን በቀስታ ያንከባልላል፡፡ ፍየሎቹን ይነዳ የነበረው ሰውዬ ቢዩሌውን እንዳየ አቅጣጫውን ወደሱ አቀና፡፡ ፍየሎቹ ግን የሚንከባለለውን በርሜል ሲያዩ በርግገው ግራና ቀኝ ሸሹ፡፡ ሰውዬው ፍየሎቹን ለመመለስ እንደመሮጥ አለና ቢዩሌው በርሜል ስር በብጣሽ ጨርቅ የተቋጠረ ነገር ጣል አርጎ አለፈ፡፡ ቢዮሌ ቋጠሮውን በፍጥነት አነሳና በርሜሉን እየገፋ መንገዱን ቀጠለ፡፡

# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

የነ እስማኤልን አንገት የቀላ ካራ ለነሱም የተዘጋጀ ስመሆኑ እርግጠኞች የሆነት በሪሁንና አሰግድ የመስወሪያ ስፍራቸውን ከለወጡ ቀናት አልፈዋል። ስጊዜው ምቹ መሸሸጊያ የመሰላቸው የአሊሃሽ ቤት ነበር። እዚያ ሆነው ሰሞኑን ለሚጥሉዋቸው አደጋዎች እቅድ ሲያወጡና የቅስቀሳ ጽሁፎችን ሲያዘጋጁ ቆዩ።

‹‹በከተማው ዙሪያ ካለው አደጋ ጣይ ቡድናችን የደረሰኝ ሪፖርት በጣም ያበረታታል፣ ዛሬ ሌሊት ከተመይቱ ውስጥ አደጋ እንጥላለን ብለዋል›› አለ አሊሃሽ ብጣሽ ወረቀት እያነበበ፡-

‹‹... በእቅዳችን መሠረት እንቅስቃሴያችን በሶስቱም መንገዶች ላይ አትኩረዋል። በጅጅጋ መንገድ ሁለት አደጋዎች፣ በአዋሬ መንገድ አንድ አደጋ ጥለን ደህና ውጤት አግኝተናል። በርከት ያለ የጠላት አሳሽ ጦር ሁለት ጊዜ መጥቶብን ተቋዋቁመን መልሰነዋል። መሣሪያዎችና ስንቅም ማርከናል› ይላሉ" አለ አሊሃሽ ወረቀቱን እያጣጠፈ።

‹‹ደብዳቤው እንዴት ደረሰህ?›› አለ አሰግድ እየተገረመ።

‹‹በአዲሱ የግንኙነት መስመራችን፣ ቢዮሌው አባላችን ትጉህ ሠራተኛ ነው››

‹‹የአካባቢያችን ሁኔታ እንዴት ነው?››አለ በሪሁን የውይይቱን አቅጣጫ ለወጥ አርጎ።

‹‹ደህና ነው፣ አምሳ አለቃው ገንዘቡንና ጌጦቹን ለመውሰድ

ሰሞኑን መጥቶ ነበር። እሱ እንደሚለው በየግንባሩ ያለው ሁኔታ አስጊ ሆኖብናል። የኢትዮጵያ ጦር በአየር ኃይሉ እየተረዳ የማይበገር ሆንዋል፡፡ በቀሬ ግንባር ብዙ ሰውና ታንኮች አወደሙብን፡፡ በጀልዴሳና በፊዲስ ግንባሮችም ጦሪችን ከባድ ጥቃት ደርሶበታል፡፡ በመሆኑም ጦራችን ወደሁዋላ እየሸሸ አስቸገረን፡፡ ለዚህ ሁሉ ተጠያቂዎቹ ባለስልጣኖቻችን ናቸው፡፡ የነሱ አመራር ጉድለት ነው ይህን ሁሉ ያደረሰው ባይ ነው፡፡ ከግንባር ያፈገፈጉ ሁለት ከፍተኛ መኮንኖችና ጦራቸው ፊት በጥይት መደብደባቸውንም ነገረኝ፡፡ ሰሞኑን ይህን የሚመለከትና ጦሩን የሚያቃቅር ጽሁፍ ከአንድ የጦር ክፍል መበተኑንም ገልጾልኛል...››

‹‹ወረቀታችን ሰርትዋል፣ ማለትነው›› አለ በሪሁን፣ ሰስቱም ፈገግ አሉ። አሊሃሽ ፊት ላይ የነበረው ፈገግታ ግን ብዙ አልቆየ፡፡አቀርቅሮ በሰፊው ተነፈሰና፦

‹‹አንድ ያልነገርኩዋችሁ ነገር አለ፡፡ ረዳቴ፣ ነጋዴው አብዲ ኑር፣ ዛሬ ከማለዳው ጀምሮ ተሰውርዋል፡፡ የት እንደደረሰ አይታወቅም፡፡ ደጋግሜ ፈለግሁት፣ አላገኘሁትም›› አለ፡፡

‹‹ቀን በቀን ማፈን ጀመሩ እንዴ?›› አለ አስግድ፡፡

‹‹በፈቃደኝነትም ሊሄድ እንደሚችል መጠርጠር አለብን›› አለ በሪሁን ቅንድቦቹን ሰቅሎ፡፡

‹‹እንዲህ ከሆነማ ሌላ አደገኛ ሁኔታ ተፈጠር ማለትነው፡፡ ግን በፍቃደኝነት ከነሱ ጋር የሚቀላቀል ይመስልሃል?›› አለ አስግድ አሊሃሽን እያየ፡፡

‹‹አይመስለኝም፡፡ ለረጅም ጊዜ እንተዋወቃለን፡፡ በዚህ ቡድን ውስጥ ከተገናኘን ጀምሮም ብዙ ሚስጢራዊ ስራዎችን አብረን ሰርተናል፡፡

እንደውም አዲሱ የግንኙነት መስመራችን በሱ በኩል ነበር። አሁን ያነበብኩላችሁንም ደብዳቤ ትናንት ማታ ያመጣልኝ እሱ ነው። ኢሔ፣ ምናልባት ሃሳቡን ለውጦ እንደሆን አላውቅም። እንዲህ ባለ ቀውጢ ጊዜ እንኳንዋን ጉዋደኛን፣ ራስንም ማመን ያስቸግራል ›› አለና ራሱን አከከ።

‹‹እሱ ከታፈነ፣ ወይም አውቆ ከጠፋ ግንኙነቱ ተቋዋረጠ ማለት ነዋ›› አለ አሰግድ።

‹‹ አንተ ስለ ግንኙነቱ ታወራለህ፤ የድርጅታችንም ህልውና በከፍተኛ አደጋ ላይ ይወድቃል። ለማንኛውም፣ ሁኔታው እስኪለይ አንተ ቦር ብትል አይከፋም›› አለ በሪሁን አሊ ሃሽን እያየ። ‹‹ውነትህን ነው። ለዛሬ ተሸሽጌ ሁኔታውን እመለከታለሁ። ሁኔታውንና የናንተን ተልእኮ ውጤት አይቼ ፣ አብዲኑርም ማምሻውን ካልመጣ በነገው እለት ከተማውን ለቀን በአካባቢው ካለው ሌላ ቡድናችን ጋር መቀላቀል አለብኝ›› አለ አሊሃሽ።

መሽትሽት ብሎ ለአይን ያዝ ሲያረግ ሶስቱም ተራ በተራ ከቤት እየወጡ ራቅ ብለው በየአቅጣጫው መሸሻ ካለው አንድ ጨለማ ውስጥ ተከለሉ። ቦታው ያንድ ደጋፊያቸው ጉዋሮ ነበር። ጨለምለም ብሎ ለዓት እላፊው ሲቃረብ

‹‹እንግዲህ አንተ እዚሁ ቆይ። ሰላም ከሆነና እዚሁ ካለህ ይህን ጨርቅ አጥሩ ላይ ታንጠለጥለዋለህ፣ መለእክቱ ‹ሳላም› ነው ማለት ነው። ጨርቁ ከሌለ ግን መጥፎ ሁኔታ አጋጥሞህ ቦታ እንደ ለወጥህ እንረዳለን። እኛ ሌሊቱን ካልመጣን፣ ሲነጋጋ የምትገኝበትን ቦታ ለዚህ ቤት ባቤት ነግረህ ትሄዳለህ። እስከረፈፋዱ አለህበት ድረስ ካልመጣን፣ በእመቺህ አቅጣጫ አምልጥ ›› አለ በሪሁን አሊሃሽን እያየ፣ እሱና

አስግድ ሴሉቱን አደጋ ወደ ሚጥሉበ ቦታ ለመሄድ ሲነሱ። ቀደም ብለው ያስመጡትን የጠላት ወታደር የደንብ ልብስ ለበሱ፣ መሳሪያዎቻቸውን ያዙ፣ እና ጥቂት ካዳመጡ በሁዋላ ሮጥ ብለው ዋናው መንገድ ላይ ወጡ። ከርምጃቸው ኮራና ዝግ እያሉ ለምሽቱ ጥበቃ የተሰማሩ መደበኛ ወታደሮች በመምሰል አካባቢውን ይቃኙ ጀመር።

# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

መንገዱ ጭር ብሏል፡፡ ቤቶች በሙሉ ተዘግተዋል፡፡ ለትንፋሽ እንክዋን ጠፍቶ የዋለው ንፋስ እንደልቡ ይቦርቃል። አልፎ አልፎ የወታደር መኪናዎች በከፍተኛ ፍጥነት ያልፋሉ። እነበረሀን ዳሩን እየያዙ በዋናው መንገድ ይዘዋወሩ ጀመር፡፡ ባጠገባቸው በሚያልፉ መኪናዎች ውስጥ ያሉ የጠላት ወታደሮች እጆቻቸውን እያወዛወዙ «ነበድ(ሰላም)›› ይሉዋቸዋል፣ እነሱም አጸፋውን ይመልሳሉ፡፡ እንዳንዴም ከሌሎች ለጥበቃ ከተመደቡ እግረኛ ወታደሮች ጋር ሲገናኙ እንደተለመደው እጆቻቸውን በማወዛወዝ "ነበድ›› ይልዋቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ሲዘዋወሩ ቆዩና ዋናውን መንገድ ትተው መንደር ውስጥ እጥፍ በማለት ከለላ ያዙና አረፍ አሉ፡፡

«ትንሽ ቆይተን በቀጥታ ወደ ጦር ካምፑ እናዘግማለን፡፡ ወደዚያ የሚሄድ ተሽከርካሪ ካገኘንም እንዲወስደን እንለምናለን፡፡ ይሄ እንዲያውም ያለ አንዳች ጥርጣሬ ወደ ካምፑ ለመግባት ይረዳናል ›› አለ በሪሁን በሹክሹክታ፡፡

«ውሰዱንስንላቸው የጥበቃ ስራችሁን ትታችሁ የት ነው የምትሄዱት ቢሉንስ?››

«አንተ ታመህ ትወድቃለሃ፣ ወደ ክሊኒክ ነውኮ የምንሄደው›› አለ በሪሁን ሳቁን አፍኖ፡፡

‹ "ይሄ አይናችን እያየ አደጋ ውስጥ የመግባት ድርጊት ነው››

«እስካሁን አደጋ ውስጥ መኖርህን አታውቀውም? በሞት

የተከበበችው ሕይወታችን ሞትን ባትገድለውም አቁስላው ማለፍ አለባት ››

‹‹እሽሽሽ፣ የሰው ድምጽ ይሰማኛል›› አለ አሰግድ ጆሮውን ወደ አንድ አቅጣጫ ዘንበል አርጎ፡፡ አልፎ አልፎ ሽው ከሚለው ንፋስ በቀር ሌላ ድምጽ የለም፡፡ ዘግይታ የወጣችው ጨረቃ በጥቁር ደመና ተከባ ያዘነች ወየዘሮ መስላለች፡፡

‹‹ድው፣ ድው፣ ድው›› የሰው እርምጃ፡፡ ሁሉቱም መሳሪያዎቻቸውን በተጠንቀቅ ይዘው ጠበቁ፡፡ ጽምጹ ጸጥ አለ፡፡ ከሩቅ ይሰማ የነበረውም የሞተር ድምጽ ጠፋ ...ጨረቃም ጥቁር ደመና ተከናነበችና ጭለማ ባስፈሪ ግርማው ነገሰ፡፡

‹‹ድው፣ ሽክሽክ፣ ድው ድው፣ ሽክሽክ›› የሰው እርምጃ፡፡ የጠመንጃዎቻቸውን አፈሙዞች አስቀድመው እያደቡ ድምጹን ወደ ሰሙበት አቅጣጫ ሲያዘግሙ፣

‹‹ጭለማውን ተገን አርገን ጥግ ጥጉን እንሂድ›› የሚል የሹክሹክታ ንግግር ሰሙና ቆሙ፡፡ ተናጋሪዎቹን ሊያዩዋቸው አልቻሉም፡፡ ጨረቃይቱ አጭልጋ ታይ ይመስል ከአንድ ወገን ጠርዝዋን ብቅ አረገች፡፡ አሉበት ቁጢጥ ብለው በደብዛዛው ብርሃን ሲመለከቱ፣ የሁለቱ ሰዎች ቅርጽ  ታያቸው፡፡ አንደኛው የወታደር ልብስ ለብሰዋል፣ ሌላው ሸርጥ አገልድሞ ከላይ ረዘም ያለ ፎጣ መሳይ  የአንገት ልብስ አጣፍቷል፡፡ ባሉበት ሆነው ጎንበስ ቀና እያሉ  ወደ ዋናው መንገድ ሲመለከቱ ቆዩና፣ ጦር የተወረወረባቸው ይመስል አጎንብሰው ወደ ሁዋላ ሸሹ፡፡

‹‹ጆግ!፣ ጆግ! ፣ (ቁም! ፣ ቁም!)›› አሉ አሰግድና በሪሁን፡፡ ሰዎቹ ወደ ተለያየ አቅጣጫዎች ሮጡ፡፡ በሪሁን ወታደሩን፣ አሰግድ ሌላውን

ተከተሉዋቸው። አስግድ ተኰሰ። ሰውዬው ትንሽ ተራመደና ወደቀ። ሮጦ ሲደርበት ከጣር ጋር እየታገለ አንድ ነገር ወደ አፉ ሲያስገባ ሊታገል አየው። ቀልጠፍ ብሎ የሰውየውን ጉሮሮ ረገጠና በአፉ የያዘውን ወረቀት ነጠቀው። ግማሹ አፉ ውስጥ ቀረ።

«ለምን ተኰስክ? በል እሱን ተወውና እንሂድ!» አለ በሪሁን የአስግድን ክንድ ይዞ። በመንደሮች መሐል እየተሽለኰለኩ ሮጠው፣ ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ እያለ አንድ ስዋራ ቦታ ቆም እንዳሉ፣ ራቅ ያለ ስፍራ ተኩስ ተሰማ። እሩምታና ፈንጂ የተቀላቀለበት ተኩስ፣ ትንሽ ቆየና ጸጥ አለ። መኪናዎችና ወታደሮች ውር ውር ይሉ ጀመር።

እነ በሪሁንም በአጋጣሚው በመጠቀም ከወታደሮቹ ጋር ቀልቀል ብለው ተኩስ ወደ ተሰማበት ስፍራ ሮጡ። የውሃ ልማት ካምፕ እየተባለ ይጠራ በነበረበት አካባቢ ብዙ ወታደሮች ተከማችተዋል። መኪናዎች ቁስለኞችንና ሬሳዎች እየጫኑ ወደ ህክምና ጣቢያዎች ይከንፋሉ። አልፎ አልፎ ወታደሮች ሰብሰብ ብለው በመቆም፣ ምንም እንዳልተፈጸመ ሁሉ በግደሌሽነት ያወራሉ።

«ጅብ ካለፈ የውሻዎች መጮህ ፋይዳ የለውም» አለ ከወታደሮቹ አንዱ እየሳቀ። ሌሎቹም በሳቅ አጀቡት። እነበሪሁን በወታደሮቹ ሁኔታ እየተገረሙ በትርምሱ ውስጥ አልፈው ወደ መሃል ገቡ። በርከት ያሉ መኰንኖች አንዱን ወታደር ከበው በጥያቄ ያዋክቡታል። ወታደሩ በድንጋጤ ይንቀጠቀጣል።

«አሁን እኮ ነው! ሳናስበው ድንገት ነው የመጡብን! ወይኔ፣ ወይኔ፣ በላውንቸርና በመትረየስ ፈጁን። በዚህ በኩል ነው እስረኞቹን የወሰዱዋቸው. . .» ይላል በአመልካች ጣቱ እያመለከተ።

«ስንት ሰዎች ናችሁ የተረፋችሁት? ሌሎቹ የታሉ?» አለ

አንደኛው ኰሎኔል በቁጣ እየጮኸ፡፡

‹‹ሁላችንንም አልቀናል! የተረፈ ሰው የለም ጌታዬ!›› አለ እጆቹን እያርገበገበ፡፡

ማኰንኖቹ ወታደሩ ከድንጋጤው እንዳልነቃ ተገንዝበው፣ በጥብቅ እንዲታሰር ትእዛዝ ሰጡና፣-

‹‹ወንበዴዎቹን የሚከታተሉ ወታደሮች ሄዱ?›› አለ አንደኛው ከሁዋለው ወደ ነበሩት የበታች መኰንኖች ዞር ብሎ፡፡

‹‹በመዘጋጀት ላይ ናቸው፡፡ መኪናዎች እስኪመጡልን ነው የምንጠብቀው›› አለ መኰንኑ በወታደር አቋዋቋዋም እግሮቹን ሰብስቦ፡፡

‹‹ስምን በእግራችሁ አትሄዱም?!››

‹‹ወንበዴዎቹ ስለ ራቁ እንደርስባቸውም ብለን ነው››

‹‹ያሉትን ወታደሮች ይዘህ ወንበዴዎቹን ተከታተል! እኔም እመጣለሁ›› አለ ወደሌላ መኮንን ዞር ብሎ፡፡ በወታደራዊ ተጠንቀቅ ወደ ቆመው መኰንን ዞር አለና ደሞ፡-

‹‹ቆይ! ዋጋህን ታገኛለህ፣ ጥንቃቄ ባለማረግህ ይህ ሁኔታ ደረሰ፤ ደግሞ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ሲገባህ እዚህ ትልከሰከሳለህ ፡፡ ወንበዴዎቹ የማምለጫ ጊዜ እንዲያገኙ አውቀህ የምታረገው እንደሆን ይገባኛል! ውርደት ውስጥ እንደከተትከን ስጋህን ቆራርጬ ነው ለአሞራ የምሰጠው፣ እሰሩት!!›› አለና ጮኸ፡፡ በቅራቢያው ከነበሩት ወታደሮች አንዱ ቀልጣፍ አለና መኰንኑ ታጥቆት የነበረውን ሽጉጥ ከሰገባው አውጥቶ ያዘ፡፡ ሌላው መለዮውን ተቀበለውና ይዘውት ሄዱ፡፡

እነ በሪሁን ግርግሩ ውስጥ ተመሳስለው ሁኔታዎችን ሲመለከቱ፣ አንድ ጂፕ መኪና ስትብር ማጣትና ከፍተኛው መኰንን አጠገብ ቆመች

:: ነጂዋ ዘሎ በመውረድ ወታደራዊ ሰላምታ ከሰጠ በሁዋላ፣ መኮንኑን ያነጋግረው ጀመር::

‹‹የመረጃ ክፍሉ አምሳ አለቃ ነው›› አለ በረሁን በሹክሹክታ!

‹‹አገኘነዋ! በዚህ ግርግር እሱንም ሆነ አዛዡን ልንላቸው እንችላለን›› አለ አስግድ እየተቁነጠነጠ::

‹‹አይሆንም፣ አምሳ አለቃውን ለብቻው ካገኘነው. . .›› እያለ በረሁን ሲናገር፣ በተሰበሰቡት ወታደሮች አካባቢ አንድ ጥይት ተተኩሶና እንደገና ትርምስ ተፈጠረ::

‹‹ይህ አጋጣሚ ሊያመልጠን አይገባም!›› አለ አስግድ ተኩሱ ወደ ተሰማበት ቦታ በንዴት የሚራመዱትን ከፍተኛ መኮንንና የመረጃ ክፍሉን አምሳአለቃ እየተመለከተ::

‹‹መልካም እንግዲያው ጠንቀቅ በል ሙከራችን እንዳይከሽፍ››

‹‹በቦምብ ይሻላል:: ሁለታችንም ባንድ ላይ፣ ተዘጋጅ አሁን!!›› ከፍተኛ ብልጭታና የጆሮ ከበሮ የሚበሳ ድምጽ ተፈጠረ:: አካባቢው በጥቁር ጭስ ተጋረደ:: ማን ወዴት እንደሚተኩስ በማይታወቅበት ሁኔታ ተኩስ ተጀመረ:: እነበረሁንም በቅልጥፍና እየተዘዋወሩ የጠመንጃ ጥይቶቻቸውን በሰፈራው ባሉት ሁሉ ላይ ካርከፈከፉ በሁዋላ ከመሀል ወጡ:: ከወታደሮቹ የተረፉት ሲሸሹ የቆሰሉትና የሞቱት ሜዳው ላይ ተነጠፉ::

‹‹በፍጥነት ከዚህ ካልራቅን ጥቁር ለባሾችና አየር መቃወሚያዎች መጥተው ይፈጁናል›› አለ በፍርሀት ከሚተራመሱት ወታደሮች አንዱ ለጉዋደኛው::

‹‹እንሂድ! እንሂድ! ባንተ መኪና ወደ ካምፓችን እንሂድ›› አለ ሌላው የጉዋደኛውን ክንድ ይዞ እየሮጠ:: ወታደሮቹ ባለሽራ መኪናቸው

ውስጥ ገብተው ሞተር ሲያንቀሳቅሱ፣ ሌሎች ወታደሮች እየዘለሉ መከናይቱ ላይ ይወጡ ጀመር፡፡

‹‹እንሂድ፣ እኛም መኪናይቱ ላይ እንውጣ›› አለ በሪሁን ወደ መኪናይቱ እየሮጠ፡፡ እንደምንም ተንጠላጥለው ወጡ፡፡

‹‹ያ ጉረኛ ያየር መቃወሚያ ጦር አዛዥ አረፈው አይደል?›› አለ አንዱ ወታደር በመክነፍ ላይ ከነበረችው መኪና ላይ እንዳይወድቅ ዙሪያው ያሉትን ወታደሮች ይዞ፡፡

‹‹ሞትዋል ብለህ ነው? እሱኮ ሞት የጠላው ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ሶስት ጊዜ ቆስሎ ሞትዋል እየተባለ ተርፍዋል›› አለ ሌላው ድምጹን ከፍ አርጎ፡፡

‹‹ብጥስጥሱ ነው የወጣው፤ አጠበገቡ ነበርኩ እኔምኮ እግሬ ላይ በመጠኑ ቀምሻለሁ፡፡ ያሳዘነችን ያቺ ምስኪን አምሳ አለቃ ነች›› አለ የመጀመሪያው ወታደር እንደ ማቃሰት እያለ፡፡

‹‹ የመረጃ ክፍልዋ አምሳ አለቃ! የጦሩ ዋና አዛዥ እስዋ አይደለችም እንዴ? ምኑ ላይ ነው ምስኪንነትዋ? ስንቱን ከፍተኛ መኮንን ስታንቀጠቅጠው አላየህም? ደግሞስ. . . ብቻ ምን ያረጋል፣ እኛ አንናገርም፣ አላህ ፍርዱን ሰጠ!›› አለ ከዳር ያለው ሌላ ወታደር፡፡

አስግድና በሪሁን ‹‹እንኩዋን ደስ አለህ›› የሚል ምልክት ተጎነታተሉ፡፡ መኪናይቱ ወደ ሌላው ጦር ሰፈር እሚወስደው መንገድ መታጠፊያ ላይ ስትደርስ ቆመች፡፡

‹‹እስቲ እዚህ እንኩዋን ወረድ በሉ፣ በዚህ ሁኔታ ጭኜ ካዩኝ አለቆቼ እኔንም ይረሽኑኛል!›› አለ ሹፌሩ ድምጹን ከፍ አርጎ፡፡ በርከት ያሉ ወታደሮች ዱብ ብዱብ እያሉ ሲወርዱ፣ እነ በሪሁንም ቀልቀል አሉና ወረዱ፡፡

ጨሬቃ ደመናውን ገላልጣ ብቅ በማለት ሙሉ ብርሃን ለግላለች። ንፋሱ የተፈጠረውን ሽብር የፈራ ይመስል ጸጥ ብልዋል። የደገሐቡር ህዝብ ቤቱን ዘግቶና መብራቱን አጥፍቶ በየቤቱ ይጨነቃል፣ በስቃይ ከምትተራመሰው ከተማ ጋር ያቃስታል።

እነበራሁን በመጡበት ሁኔታ እየተሹለከለኩ አሊሃሽን ወደ ተውበት ስፍራ አመሩ። ቦታው ሲደርሱ አጥሩን ተመለከቱ፡ በምልክትነት እንዲሰቀል የተስማሙበት ጨርቅ አለ።

‹‹ሰላም ነው፣ ይሄኔ እንቅልፋን ይለጥጣል...››እያለ በራሁን ሲናገር፣

‹‹ቆይ!›› አለ አሰግድ አሊሃሽ ወደ ነበረበት አቅጣጫ አፍጦ። ወዲያው ለበርይሁን ምልክት አሳየውና ግራና ቀኝ ፈንጠር እያሉ በመንርከክ ጠመንጃዎቻቸውን ደገኑ። አንድ ደቂቃ፣ ሁለት፣ አምስት፣ አስር ደቂቃዎች አለፉ፤ ምንም የለም።

በራሁን ከነበረበት ብድግ ብሎ አሰግድ ጎን ቁጢጥ አለና፣ ‹ምን አይተህ ነው? ›› አለ በሹክሹክታ።

‹‹አንድ ነገር ውልብ ያለ መሰለኝ››

‹‹እርግጠኛ ነህ?››

‹‹አው››

‹‹እንግዲያው እንዲህ እናርግ። ወደ ሁዋላ እንመለስና በጆርባ ዞረን እንምጣ"

"የምታየውን ነገር በትክክል ሳትለይ እንዳትተኩስ››

እንደተባባሉት እያረጉ፣ አሊሃሽ እነበረበት ሄደው ቢፈልጉት የለም። እንደገና ወደ አጥሩ ቀርበው ተመለከቱ። የመኖሩ ምልክት የሆነው ጨርቅ አለ። ግራ በተጋባ ሁኔታ እየተያዩ ሲያስቡ፣

ከጭለማው ውስጥ በሹክሹክታ ‹‹ኡስማን ፣ ቤሩን›› የሚል ድምጽ ተሰማና፣ አሊሀሽ ብቅ አለ።

‹‹ለምን ታስደነግጠናለህ?›› አለ አስግድ ቆጣ ብሎ።

‹‹ቀደም ብሎ ሁለት ወታደሮች መጥተው፣ አናንተ መስላችሁኝ ተዝናንቼ ስጠብቅ ሊያዩኝ ነበር፣ አላህ ሰወረኝ። አጥሩ ጥግ በደረቴ ተኛሁ። መግቢያው ላይ ሆነው አካባቢውን በባትሪ ብርሀን ከቃኙ በሁዋላ ተመለሱ። ታዲያ አሁንም እናንተን በሩቁ ሳያችሁ፣ የቀድሞው ሁኔታ እንዳይደገም ብዬ ነው የተደበቅሁት››

ሶስቱም እልፍ ብለው ቁጭ እንዳሉ፣

‹‹ ወታሮች መጥተው ነበሩ›› አለ በሪሁን ጠመንጃውን ታፋው ላይ አጋድሞ።

‹‹አላህ ነው ያወጣኝ፣ ወላሂ ዛሬ ጉድ ሆኜ ነበር። እንዴት ነው ተሳካላችሁ? እነ ሃሚድ ጣሂርስ ቀናቸው? ተኩሱን ሰማሁ። ወታደሮችና ተሽከርካሪዎችም ይሩዋሩዋጡ ነበር››

‹‹እኛም ለእርዳታ ተሩዋሩጠን ነበር›› አለ አስግድ ፈገግ ብሎ።

‹‹ጦር ሰፈሩ ድረስ ሄዳችሁ?››

‹‹አዎ ሄደን ነበር። ውጤቱ በጣም አስደሳች ሆንዋል›› አለ በሪሁን ኰራ ብሎ።

‹‹ጦር ሰፈሩ ላይ ነው አደጋ የጣሉት እነ ሃሚድ?››

‹‹አደለም ትልቁ ወህኒ ቤት ውስጥ የነበሩትን እስረኞች በሙሉ ነጻ አወጡዋቸው›› አለ አስግድ።

‹‹በደህና አመለጡ?››

‹‹አው››

‹‹አላህምዲሊላሂ፣ ወዳጄ የአምሳ አለቃ ሞተ? ወይኔ ወዳጄ›› አለ

አሊሃሽ እየቀለደ።

‹‹አትንኩብኝ ብለህ ነበር›› አለ አሰግድ።

‹‹አዎ ብዬ ነበር። አሁንም እናንተ ስላላችሁ እንጂ፣ የእሱ መገደያ አሁን አልነበረም። መቆየቱ ይጠቅመን ነበር››

‹‹ቁርጥምጥም አርጎ ነበር የሚበላን። ባንተ ሃሳብ መሰረት ለጥቂት ጊዜ ተወት ልናረገው አስበን ነበር። የረዳትህ የአበዲኑር በትናንትናው እለት መሰወር ስጋታችንን ከፍ አረገውና የአምሳ አለቃ መገደል የማይታለፍ ጉዳይ ሆነ። አየህ አሊ፣ አብዲኑር በውድም ሆነ በግድ እጃቸው ቢገባ ምስጢር እንዲያወጣ እንደሚያስገድዱት የታወቀ ነው። በዚህ ሁኔታ ብንጋለጥ መጀመሪያ የሚበላን ይሄው ወዳጅህ ነበር። ለዚህ ነው ፈጣን እርምጃ ለመውሰድ የተገደድነው›› አለ በሪሁን።

‹‹ገባኝ፣ ካምፕ ውስጥ ገብታችሁ ነው ገደላችሁት? ›› አለ አሊሃሽ ለወሬው ጉዋግቶ። ያረጉትን ሁሉ እየዘረዘሩ ሲነግሩት አፉን በግማሽ ከፍቶሲያዳምጣቸው ቆየና፡-

‹‹ስለነዚያ መጀመሪያ አገኛቸው ስላላችሁዋቸው ወታደሮች፣ በተለይም ወረቀት ከእሱ ነጥቀነው ስላላችሁት ሰውዬ፣ አንደ ነገር ጠረጠርኩ›› አለ አሊሃሽ በጣም ቅር እያለው።

# ምዕራፍ ሃያ

እነበሪሁን ባለፈው ሌሊት የተፈፀመውን ሁኔታ በመገምገም በአሊሃሽ ላይ ይደርሳል ብለው የፈሩት ነገር ሊደርስ እንደማይችል ገመቱ። የጦሩ ጠቅላላ እንቅስቃሴ ያተኮረው፣ ሌሊቱን በተፈጠረው አደጋ ላይ ሆነ። እንዲያ ባይሆን ኑሮ የፈሩት ነገር ምናልባት ይደርስ ነበር። ያ ባለመሆኑ ደስ አላቸው። በተለይም ጥቁር ለባሾችን እየመራ ለአሰሳ የሚሰማራው የጦሩ የመረጃ ክፍል አምሳ አለቃ በመሞቱ ለጊዜውም ቢሆን ስጋታቸው መለስ አለ። ቢሆንም ካደሩበት ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ሊነጋጋ ሲል ቤታቸው ሰው ልከው ባለፈው ሌሊት ምንም የተፈጠረ ነገር አለመኖሩን አረጋገጡ።

በሪሁንና አሰግድ ሌሊቱን ያደሩበትን የደንብ ልብስ ለውጠው የዘወትር ልብሳቸውን ለበሱ። ጠመንጃዎቻቸውንም ፈታትተው በጨርቅ በመጠቅለል አቅራቢያው አለ ደጋፊያቸው ቤት ተዉና ወደ መኖሪያቸው አመሩ።

‹‹የኔ ጥርጣሬ ትክክል መሆን አለበት›› አለ አሊሃሽ ሶስቱም ቤት ደርሰው ሻይ ሲጠጡ።

‹‹ምን ነበር ጥርጣሬህ?››

‹‹ትላንትም የገደላችሁትና ወረቀት የቀማችሁት ሰውዬ እንዲያው. . .››

‹‹ትላንትም ስለዚህ ነገር አንድ ነገር ተሰማኝ ብለህ ነበር፣ ወረቀቱም ይሄውልህ። ልናነበው ብንሞክር አልገባችሁ አለን›› አለ

አሰግድ የያዘውን ብጣሽ ወረቀት ወደ አሊሃሽ እየዘረጋ።

‹‹እንደ መጣን አብዲኑር ቤት ሰው ልኬ ነበር፣ እስከአሁን አልመጣም። ቤተሰቦቹም በመጨነቅ ላይ ናቸው› አሉ። በቀደምለት ‹አንድ የማመጣው የጽሑፍ መረጃ አለ፣ በጣም ጠቃሚ ነው ብሎኝ ነበር እ. . .›› እያለ ወረቀቱን ከአሰግድ ተቀበለ። ግማሹ የተቀደደለት ይህ ወረቀት የአንድ አካባቢ ንድፍ ነው። ዙሪያው በቀስት እየተመለከተ በሱማሌኛ መግለጫ ተሰጥቶበታል።

አሊሃሽ ዝም ብሎ ወረቀቱን ሲያነብ ቆይቶ፣ ለአሰግድ መለሰለትና በሰፊው ተነፈሰ፡ቀይዳማ ፊቱ በአንዴ ጠቆረ።

እነ በሪሁን በሁኔታው ግራ ተጋብተው አኒዳች ነገር ይናገራል ብለው ሲጠብቁት፣ በራቸው ተንኳኳ። እነ በሪሁን ቦንቦቻቸውን ጨብጠው ወደበሩ አፈጠጡ። አሊሃሽ ብድግ ብሎ እያመነታ በሩን ከፈተ። አንዲት ሴት ልጅ አሊሃሽን እያየች ‹‹ሰው ይፈልግዎታል›› ብላ ተመለሰች። በሩን ከውጭ ዘጋና ተከተላት። እነበርይሁን ትንሽ ጠበቁና በነበሩበት እንዳሉ፣ ሀሳባቸውን በያዙት ወረቀት ላይ አረጉ።

‹‹የጦር ሰፈር ንድፍ ይመስላል። ወረቀቱን የያዘው ሰውዬ ለምንስሊውጠው ፈለገ?" አለ በሪሁን ከአሰግድ የተቀበለውን ወረቀት እየተመለከተ።

‹‹የጦሩ የመረጃ ሰራተኛ ይኖናላ››

አሊሃሽ ተመልሶ በሩን ከውስጥ ዘጋና፣

‹‹ልክ ነው እሱን ነው የገደላችሁት››አለ።

‹‹ማንን?›› ትኩር ብለው አዩት።

‹‹አብዲኑርን!››

‹‹በምን አወክ?›› አለ አሰግድ ፈጠን ብሎ።

‹‹ከሱ ቤት የመጣ ሰው ነው አሁን ያስጠራኝ፡፡ እሬሳው መንገድ ዳር ተገኘ፣ የአንድ ወታደር እሬሳም በአቅራቢያው ነበር ብሎ ነገረኝ››

በሪሁንና አሰግድ ተያዩና ወረቀቱን እንደገና እየተቀባበሉ ተመለከቱት

‹‹ያሳዝናል፣ ምንም እንኳ የዋን መረጃው በጣም ጠቃሚ ቢሆን፣ እንዲህ ያለ አደጋ ሊደርስ እንደሚችል መገመት ነበረበት፡፡ በኛም ባይሆን በጠላት እጅ ሊወድቅ ይችል ነበር›› አለ በሪሁን፡፡

‹‹የጦር ሰፈሩን አቀማመጥ የሚያስረዳ ንድፍ ነበር እንዴ?›› አለ አሰግድ ወረቀቱን ፊትለፊት ይዞ፡፡

‹‹ስነገሩማ የሚጠቁ የጦር ሰፈሮችን ለማጥናት ባቀድነው መሠረት የመጣ መረጃ ነበር›› አለ አሲሃሽ ራሱን እየነቀነቀ፡፡

‹‹ጠላቶቻችን የአብዲኑርንና የወታደሩን አሙዋሙዋት እንመርምር ይሉ ይሆን እንዴ?›› አለ አሰግድ፡፡

‹‹እንዲያ ማሰባቸውማ አይቀርም፡፡ ግን ‹ቤት የሚቃጠልበት ሰው የምትሸሽ አይጥ ቢያይ ሊገድላት አይሮጥም› እንደሚባለው፣ ካሉባቸው ከፍተኛ ውጥረቶች አንጻር፣ ለዚህ ነገር ትኩረት በሚሰጡበት ሁኔታ ላይ አይደሉም፡፡ ቢሆንም በዚህ ነገር ምክንያት የሚወስዱትን እርመጃ መከታተል አለብን፡፡ ከዚህ የሚበልጠው ነገር የተበጠሰው የግንኙነት ሰንሰለት የሚቀጠልበትን ዘዴ መፈለጉ ነው፡፡ አብዲኑር ከሞተ ከነሃሚድ ጋር ያለን ግንኙት ተቋዋረጠ ማለት ነው›› አለ በሪሁን፡፡ አሲሃሽ ቀበለ አረገና፡-

‹‹እርግጥ ነገሩ አሳሳቢ ነው፡፡ አደጋ ጣዩ ቡድናችን በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልቻልንም፡፡ ያቀድነው የሬድዮ ግንኙነት ስራውን ቢጀምር ይህ ሁሉ ችግር ይቃለል ነበር›› ብሎ ትንሽ እንደ ማሰብ አለና፣

«የራድዮው ግንኙነት እስኪጀመር፣ እኔ ያገኘሁትና ይሻላል ብዬ የመረጥኩት ዘዴ የግንኙነቱን መስመር በሃሊማ ሙሳ በኩል መዘርጋቱን ነው። ሴትዮይቱ በጣም ጠንካራ ናት። ወደ ቡድናችን ከተጠጋች ጀምሮ በጣም ጠቃሚ ረድታናለች። የሚሰጣትን ግዳጅ የለማመንታት ተቀብላ ባጥጋቢ ሁኔታ ትፈጽማለች። ምስጢር ጠባቂነትዋና ለቡድኑ ያላት ታማኝነት ጠንካራነው። እስከ ዛሬ ካገኘናቸው ጠቃሚ መረጃዎች ብዙዎቹ በስዋ በኩል የመጡ ናቸው። ባላት የተፈጥሮ ብልህነትና እኔ በምሰጣት መመሪያ ተጠቅማ የጠላት ጦር መኮንኖችን በዘዴ እያጠመደች በልቦቻቸውና በሚስጢር ካዝናዎቻቸው እየገባች የምትወጣ ናት። ባልዋ አቡበከር ሮመዳን ጠላት መጀመሪያ ከተማችንን በወረረበት እለት ከጦራችን ጎን ተሰልፈው በቆራጥነት ሲከላከሉ ከወደቁት ጀግኖች አንዱ ነው። መልከ ቀናና ልጅ እግር ስለ ሆነች በርከት ካሉ የጠላት መኮንኖች ጋር ትገናኛለች። ይህን እንከዋን እስዋ ፈልጋው ሳይሆን፣ ከላይ እንደገለጽኩት ከኔ የተሰጣት መመሪያ ነው። በስዋ በኩል እጅግ ጠቃሚ ስራዎች ተሰርተዋል። ወደ ፊትም ብዙ የምንሰራባት ሴት ናት።ከዛሬ ጀምሮ ግንኙነቱ በስዋ በኩል እንዲቀጥል ማረግ አለብኝ። ይመስላችሁም ?» አለ።

«በዚህ ሥራ የሚሻለውን ከኛ ይልቅ አንተ ነህ የምታውቀው። ያመንክበትን አርግ፤ ነገር ግን ከሴት መረጃ ሰራተኞች አንዳንዶቹ መረጃ ሊያመጡ ይሄዱና በፍቅር ተጠምደው የያዙትን ሚስጢር እያራገፉ የሚመለሱ ወይም በዚያው የሚቀሩ እንዳሉ አለመዘንጋት ነው» እያለ በሪሁን ሲናገር ኢሲሃቅ አቋዋረጠውና፡-

«ይገባኛል። ይህን ሁሉ አስቤበታለሁ፣ ግድ የለም። እንደውም

ጠንቃችን የሆነውን የዘመቻ መኮንን ሻለቃ አብዱላሂን ለማጥመድ ብቸኛዋ መንገድ እስዋ ናት...፡፡ በሉ ከውጭ ቆልፌባችሁ ሄዳለሁ፤ ገዛም ብላችሁ ተቀመጡ›› አለና ወጣ፡፡

‹‹የአብዲኑር አሙዋሙዋት እስከ አሁን ይገርመኛል፤ ምን አይነት አጋጣሚ ነው ባክህ?›› አለ አሰግድ በሹክሹክታ፡፡

‹‹ይሄ እንደዚህ ባለ የትንንቅ ወቅት ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ ምንም ለማረግ አንችልም ነበር፡፡ አንተ ግን ለምን ገደልከው?››

‹‹አንተስ ወታደሩን ለምን ገደልከው? እሱም እኮ ከአብዲኑር ጋር ከሄደ ደጋፊያችን ነበር፡፡››

‹‹ልይዘው ሞክሬ ነበር፣ ጠልፌ ጣልኩት፣ እተኛበት ሆኖ በምብ ሊወረውርብኝ ሲመቻች በሳንጃ ቀደምኩት፣... ሌላ አማራጭ አልነበረም››

‹‹እኔ ደሞ ያኔ ይህ ሁሉ አልታየኝም፣ ሰውዬው፣ ማለት አብዲኑር፣ በዚያ ቁመቱ ሲምዘገዘግ ልደርስበት አልቻልኩም፡፡ ከሚያመልጠኝ ብዬ ነው የመታሁት፡፡ ብደርስበትም አንተ የገደልከው ወታደር ያረገውን ማረጉ ስለማይቀር መሞቱ መሞት ነበር››

‹‹እስቲ የቅድሙን ወረቀት አምጣው፡፡ ለሰሞኑ ስራችን የሚጠቅሙን አንዳንድ ነገሮች እናገኝበት ይሆናል›› አለ በሪሁን፡፡ አሰግድ ወረቀቱን አውጥቶ ወለሉ ላይ ሲዘረጋው፤ ከአሊሃሽ በተረዱት መሰረት የንድፉን መስመሮች እየተከተሉ፣

‹‹በዚህ በኩል ዘበኛ አለ፣ ነዳጅ አለ፣ ይሄ የመሳሪያ ግምጃ ቤት ነው...›› እያሉ የጠላትን የጦር ሰፈር የማጥቂያ ስልቶች ይወያዩ ጀመር፡፡

‹‹እንዲህ ያለውን የጦር ካምፕ ለማጥቃት በርከት ያለ የሰው ኃይልና መሳሪያ ያስፈልጋል፡፡ እኛ ደሞ ሁለት ነን፡፡ ሰሞኑን ሊሂሻሽ ሰዎች ይጨመርላችሁ ቢል እምቢ አልክ፣ እንዴት አድርገን ነው ›› እያለ አስግድ ሲናገር አቋዋረጠውና፡-

‹‹ከተማ ውስጥ አደጋ ለመጣል፣ በተለይም እንደ ደገሃቡር ባለች ጠባብ ከተማ፣ ብዙ ሰው አያስፈልግም፡፡ ቆራጦችና የሰለጠኑ ጥቂት ሰዎች ይበቃሉ፡፡ የጦር ሰፈሮችን በመሳሰሉ ቦታዎች አደጋ ለመጣል ወይም ለመውረር ግን፣ እንዳልከው በተለያዩ ተልእኮዎች የሚካፈሉ ብዙ ሰዎች ያስፈልጋሉ፡፡ የአሁኑ ጥናታችን ብቻችንን ለምንፈጽመው ተግባር ሳይሆን፣ በከተማይቱ ዙሪያ ያለው የደፈጣ ተዋጊ ቡድናችን ለሚሰራውም ነው››አለ እየሳቀ፡፡

‹‹ጠላት በከፍተኛ ሁኔታ በተደናገጠበት በአሁኑ ጊዜ እየተከታተሉ መምታት ያስፈልጋል›› አለ አስግድ ቡጢውን ጨብጦና ጥርሶቹን ገጥሞ፡፡

‹‹መደናገጥ ብቻ ሳይሆን ተርበትብትዋል፡፡ ከፍተኛ ጉዳት ነው የደረሰበት፡፡ በቀደም በሬደዮ እንደሰማነው የወገን ጦር ከየጦረ ግንበሩ ጠላትን በማባረር ላይ ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ እዚህ ይደርስ ይሆናል›› አለ

ለጥቂት ጊዜ ዝም ተባባሉ፡፡ ከተዘጋባቸው ጎጆ ወጥተው በሃሳብ ፈረሶች በየአቅጣጫው ጋለቡ፡፡

በሪሁን ልጆቹና ሚስቱ ፊቱ ድቅን አሉበት. . .በተስፋ ስመመን ተዝዘ.. .የወገን ጦር ወደ ውስጥ የዘለቀውን የጠላት ጦር ድል እያረገ ሲመጣ፣ እሱም ተቀላቅሎ ጠላትን ሲነዳ፣...በድል ወደቤቱ ሲመለስ፣ ሰምሰም ጥልፍ የሃገር ልብስዋን ለብሳ ፣ ሾማ ጸጉርዋን በጀርባዋ

ቁልቁል ለቃ፣ ቀድሞ እንደምታረገው...ልጆቹ ከበው ሲንጠላጠሉበት...ታየው።

‹‹በህይወት ባገኛቸው አይደል" ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና ዞር ብሎ፣ "አስግድ!››አለ።

‹‹እ-እ- ወይ ም-ምነው?››

‹‹የት ሄድክ? ወደ ሂሩት?››

አስግድ አቀረቀረና ዝም አለ።

‹‹አይዞህ ሁሉም ሩቅ አደለም፣ ህይወት ካለ፣ ተስፋ አለ አስግድ። ተስፋ ባይኖር ህይወት አታንቀሳቅሰም። ተስፋችን እውን እንደሚሆን የፀና እምነት አለኝ፡ ይታየኛል፣ ያንተና የሂሩት ሠርግ። እንደ ከዋክብት ደምቃችሁ... ሽቶ እንደ ውሀ ሲረጭ...አዎ ይታየኛል። ሂሩት የሙሽራ ልብስዋን ለብሳ፣ ሻማ በያዙና አንድ ዓይነት ጌጠኛ ልብሶች በለበሱ ትንንሽ ልጆች ታጅባ፣ ነጭ የእጅ ሹራብ (ጉዋንት) ያረገ እጅዋን ከእጅህ አቆላልፋ፣ በሌላው አበባ እቅፉ ብቅ ስትል ይታኛለ...። የሰርጉ ስርአት አብቅቶ፣ ከሂሩት ጋሪ ወደ ጫጉላ ቤታችሁ ስትሄዱ... አይታይህም?›› አለ ጎንበስ ብሎ አይኖቹን እያየ።

በርይሁን የሚለው ሁሉ ያኔ የሆነ ፣ ሂሩትም ጎኑ ያለች፣ እየመሰለው አስግድ ፊቱ በደስታ ፈክቶ ሰውነቱ ሞቆ፣ ይበልጥ አሳበው።

‹‹አይ በርይሁን፣ ይሆናል ብለህ ነው?›› አለ ላቡን እየጠረገ። ወዲያው የበሩ ቁለፍ ከውጭ ተንኩዋኩዋ። ሁለቱም ሄዱበት የምኞትና፣ የተስፋ ዓለም፣ ወደእውኑ አለም፣ ወደ ተጨባጩ አለም ተመለሱና እጆቻቸውን ወደ ቦምቦቻቸው ልከው ወደ በሩ አፈጠጡ።

‹‹ኡ, የቤቱ ውስጥ ጭራሽ የእቶን ምድጃ ሆኖ የለም እንዴ?›› እያለ

አሊሃሽ ገባ። ምሳ ከበሉ ባሁዋላ አሊሃሽ ስለ ሄደበት ጉዳይ እየዘረዘረ ገለጸላቸው፣

«ቢዬሌውን በርሜል ሲገፋ አገኘሁትና ቀጠናችን ጽህፈት ቤት ትፈፈጋለህ ብዬ አመጣሁት። በሌላ አርእስት ብዙ ከተወያየን በሁዋላ ጉዳዩን ገለጽኩለት። መጀመሪያ አንገራግሮ ነበር። ያለውን ሁኔታ በዝርዝር ሳስረዳው ነገሩ ገባው። ‹ቀደም ብዬም የቡድናችን አባል እንደሆንክ ገምት ነበር› አለኝ። ከሱ ጋር ከተግባባን በሁዋላ ሃሊማን አስጠርቼ አገናኘሁዋቸው ። ነገሩ ተስተካክልዋል። ሃሊማ የሴቶች አስተባባሪ እየተባለች ወደ ቀጠና ጽህፈት ቤታችን ስለምትመላለስ ግንኙነቱ ያለ ጥርጥር ቀና ይሆናል›› አለ አሊሃሽ።

«ብዬሌው ከዚህ ቀደም የደረሰው መልእክት አልነበረም?›› አለ አሰግድ።

«ጠይቄው ነበር፣ ‹የደረሰኝ ነገር የለም፣ ምናልበት ከሰዓት በሁዋላ ይመጣ የሆናል ብዬ ጠብቃለሁ› ብሎ ነገረኝ››

«ሌላስ?›› አለ አሰግድ ላቡን እየጠረገ።

«የደፋን ጦር የሬድዮ መልእክት ሰራተኛ የሆነውን አባላችንን አግኝቼው ነበር። ከዚህ ቀደም እንደ ተነጋገርነው በአካባቢው ካለው አደጋ ጣይ ቡድናችን ጋር የሬድዮ ግንኙነታችንን በዛሬው ሌሊት እንሞክራለን ብሎኛል። ለነሃሚድ ጣሂር ተልኮ የነበረው ሬድዮ ትንሽ ጉድለት ስለነበረው ነው እስከዛሬረ የቆየው። በሁዋላ የላክነው የሬድዮ ሰራተኛ፣ ሁሉን አስተካክሎ ከኛ ነው ጥሪ የሚጠብቀው። ለሁለት መልእክት አስተላላፊዎችና ተቀባዮች ልዩ ልዩ የሚስጢር ኮድ (መገናኛ) አስጠንቶ መድቦልናል። አንደኛው ወደነሃሚድ ሄድዋል። ሁለተኛው በቀደም አነጋግሮኝ ነው የተመለሰው። ዛሬ ሌሊት እዚሁ

አድሮ የሬድዮ ግንኙነቱን ይጀምራል››

‹‹ይኼ ከተሙዋላማ ተገላገልን ማለት ነው›› አለ በሪሁን ፈገግ ብሎ፣

‹‹ይሙዋላል፣ ዛሬ የመጨረሻ ሙከራ ነው። ሰውየው የነገረኝ ሌላ ዜና በትናንትናው ሌሊት ወህኒ ቤቱ ላይ አደጋ የጣለው ቡድናችን ተልእኮው የተሳካ ቢሆንም ችግር ገጥሞት ነበር የሚል ነው›› አለ በስፊው ተንፍሶ።

‹‹ምንድነው ችግሩ?›› አለ በሪሁን አሊሃሽን እያየ።

‹‹ያስለቀቁዋቸውን እስረኞች ይዘው በሚኼዱበት ጊዜ የጠላጥ ጦር ተከትልዋቸው ነበር። ከሁዋላ ደርሶ ተኩስ ከፈተባቸውና ከሁለቱም ወገነን ሰዎች ሞቱ። በተለይ እስረኞች። ጦርነቱ ሲፋፋም የኛ ሰዎች ሁለት እስረኞችን ይዘው አመለጡ። ከነዚህ አንዱ ተማርኮ የነበረ የኢትዮጵያ ሚሊሽያ ጦር አባል ነው። ከናንተ ጋር ለመስራት ዛሬ ይመጣል፤ ተብያለሁ። የጠላት ጦር እጅግ ተበሳጭትዋል፣ ‹በጠምራ ጦር ነው የምንወጋው። አንዱ ጫፍ ፊተለፊት፣ ሌላው ደሞ ከጉያችን ቀስፊው ይዘውናል። ፋታ አሳጥተውናል› ይላሉ።ጥሩ ዜና ነገርከን፣ ሚሊሽያው ወገናችን ይበልጥ ያጠናክረናል›› አለ በርይሁን ፈገግ በሎ።

‹‹ከእስር ቤት ሲያመልጡ የተያዙትን አራት የወገን ጦር አባላት በህዝብ ፊት ነው ለመቀጣጫ የሚረሹንዋቸው›› አለ አሰግድ እንደማዘን ብሎ።

‹‹አይረሹንዋቸውም! የሚጠይቀውን ዋጋ ከፍለን...›› አለ በሪሁን ጥርሱን ነክሶ። አሰግድና አሊሃሽ በጥያቄ ተያዩ።

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

በማግስቱ ረፋዱ ላይ በሪሁንና አስግድ አንድ ቦታ ለመሄድ ሲዘገጃጁ አሊሃሽ መጣና፡-

‹‹ከሃሚድ ዘንድ መልእክት ደረሰኝ፣ ሚሊሺያውም መጣ›› እያለ ሲናገር፣ አንድ ረዘም ጠቆር ያለ ሰውዬ ተከትሎት ገባ፡፡ አሊሃሽ ወደ ሰውዬው እየተመለከተ ‹‹ይሄ›› ብሎ በያዘው ወረቀት ላይ የተጻፈውን ስም ለማንበብ እየተቸገረ ‹‹አ. . .አ. . .እኔ›› ሲል፣ ሰውዬው ጣልቃ ገባና፣

‹‹አኔቦ ላጸሬ ኢባላለው›› አለ በተሰባበረ አማርኛ፡፡

‹‹አው፣ እሱ ነው ትናንት የነገርኩዋችሁ ሚለሊሽያ፣ ሃሚድ ነው የላከው›› አለ ፈገግ እያለና አኔቦን እያየ፡፡

‹‹እንኳዋን ለዚህ በቃህ፡፡ እኔ በሪሁን፣ ይሄ አስግድ፣ እሱ አብሮህ የመጣው ደሞ አሊሃሽ እንባላለን፡፡ ወደፊት ከኛ ጋር ትሰራለህ፣ከፈለክ ነው፡፡ አይዞህ አትፍራ፣ ምንም ጥርጥር አይግባህ...›› እያለ በሪሁን ሲናገር አኔቦ ሶስቱንመ እያቀፈ ሳማቸው፡፡

‹‹ ሱማሊኛ ትችላለህ?›› አለ በሪሁን አኔቦን እያየ፡፡ ራሱን ነቅንቆ አለመቻሉን ገለጠ፡፡

‹‹እንግዲያው አሊሃሽ መናገር ትንሽ ያዳግተዋል እንጂ፣ አማርኛ ይሰማል፡፡ ማንኛውንም ነገር እሱ ያስረዳሃል፡፡ እኛ የምንፈጽመው ተልዕኮ ስለ አለን አሁን እንሄደለን›› አለ፡፡

‹‹እኔኮ አማርኛ ብዙ አልቲነጋጊሩም፣ ቢቻ ሳማል›› አለ አኔቦ ሳቅ ብሎ፡፡

‹‹ግድ የለም፣ የጋራ አላማና ፍላጎት ያገናኛችሁ ስለሆናችሁ ትግባባላችሁ›› አለ አሰግድ ፈገግ ብሎ፡፡

እንበርይሁን ወደ ግዳጃቸው ከሄዱ በሁዋላ፣ አሊሃሽ ከነበረበት ተነስቶ አኔቦ ጎን ተቀመጠና፡-

‹‹ሃዩ፣ እንዴትና አንቴ እዚ መጣ ? አስቲ ንገር›› አለ፡፡

መጀመሪያ አኔቦ አሊሃሽን በጣም ጠረጠረው፡፡ ያኔ በአካባቢው ከነበሩት የሱማሌ ብሄረሰብ አባላት መካከል በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑ፣ ይልቁንም ወራሪውን ጠላት ተቃውመው የትጥቅ ትግል እስከማረግ የሚደርሱ ይኖራሉ ብሎ ማመኑ ቸገረው፡፡ ይህን የተረዳው አሊሃሽ ብዙ ነገር አጫወተው፡፡ ስለነ በሪሁን፣ ስለ ቡድናቸውና ቀደም ብሎ ስለፈጸሙዋቸው ነገሮች አስረዳው፡-

‹‹ሲማ አኔቦ ቢዙ ሰዎች ‹ሶማል ሁሉ ከዳቲኛ ናቾ ፤ አገራቾ ሽጣል፣ ቶቢያዊነታቸው አያምኒም› ቲላል፡፡ ሲታት ኖ፡፡ ሶማል ሁሉ ኢንደዚ አዳሉም፡፡ ወላሂ አደሉም፡፡ ቢቻ ሶማል ዊስጥ ተጊድኖ፣ ተዊድኖ፣ ጠላት ጋራ ኢኛን ወጋ አላ፤ ከዳተኛ አላ፡፡ ጠላት ጋራ ጢቂም ተሳሰራ አላ፡፡ ሃይማኖቲና ጎሳ ፊቂር ተሳስራ አላ፡፡ ኢንደዚ ደሞ ሶማል ቢቻ አዳላም፡፡ ሌላ ቢዙ ሰዎች፣ በረሴብ? አላ፡፡ ደሞ ጡሩ ቶባዊ ሶማል አለ፡፡ ዱሮ ጠላት ጋር ጦሪናት ኖ ሞታ ሶማሎች ቡዙኖ፡፡ ጃጃማች ኡመር ሰመተር፣ ኢቶባው ሶማሎች ኖ፡፡ ዛሬ ደሞ ሶማሎች አላ፣ ኢቶባው ሶማሎች፡፡ ጠላት ሚዋጋ ሶማሎች፡፡ ጀግኖች ሶማሎች አላ፡፡ ወላሂ አላ፡፡ ውነተኛ ነጣናት ቢቻ ኒፈልጋል፡፡ ጠላት ብሮቦጋንዳ ቦቦቦ ኢላል፣ ኢኛ አቃል፡፡ ኢንዳጋና ባሪ መሆን ኢኛ አይፈሊጉም፡፡

ኢኛ መይም ሆኖ፣ ዘላን ሆኖ ፣ ዳንቆሮ አዳላም! ሞኝ አደሉም. . .››
አለው፡፡ ምላና ሻይ አቅርቦ እያሳሳቀና እየቀለደም ዘና እንዲል አረገው፡፡

ግንባሩ ላይ ችፍ ያለውን ላብ በቀኝ አመልካች ጣቱ ጥርግ አረገና፣

‹‹ኢኔ መጣ ከፋ ኪፍላጋር ክሎ ኮንታ አውራጃ ነው፡፡ ቶጫ ሚባል ቦታ ነው ተወልዴ፡፡ ገባሬና አባቱካ ገባሬኖ፡፡ ዱሮ ጀሚሮ ጨሰኛ ነበሬ፡፡ አቦት ማጣ ጊዜ ደስ አላ፡፡ መሬት ኢኛ ሆና፣ ነጣ ወጣ በሆላ ጠላቶች በዙ ጊዜ አገር ከለከላሎ፣ አቦት ጠበቃሎ ቢሲቼ ሰኔ ዋር ኢዘ ዘመታ፡፡ ጎዴ ዘመታ ጊዜ ፣ ጠላቱ ቢዙ ተታኮሳን፡፡ ቢዙ ቀን፡፡ ቢዙ ጠላት ወታደር ሞታ፡፡ ታንኩና መኪና ተቃጠላ፡፡ ያ ቃጠላ ጊዜ ሴላ መጣል፡፡ ያ ሞታ ጊዜ ሴላ መጣል፡፡ አቦ!!. . .›› ብሎ የተሳተፈባቸውን ጦርነቶች እያሰበ ራሱን ነቀነቀና፡-

‹‹ጦሪና ሂዝብ ወደ ሆላ ፈጋፈጋ ጊዜ፣ ኢኛ ቲኒሽ ሚሊሾች ጠላት ተከበባ፡፡ ጠላት ቢዙ ገደላና፣ ኢኛ ቢዙ ሞታና ሲሚንት ሶ ቢቻ መለጣ፡፡ አገር አናቁም፣ መንገድ አናቁም፣ በረሃ ውስጥ ከርተታ ጊዜ፣ መንገድ ላይ ቢዙ ጠላት ጦር ገኛ፡፡ ተደበቃና፣ ተኩሳና አለፋ፡፡ ቢዙ ወር ሆላ ኢቢ ደረሳ፡፡ ሶስት ሚሊሾች ጥይትካ፣ ራሃቢካ፣ ውሃ ጢሚካ ሞታ፡፡ ኢኛ አሚስቱ አንዱ ቀን በቢዙ ጠላት ከበባ፡ በቦንቢካ፣ በጥይቲካ ቢዙ ሰው ገደላ፣ መኪኖች ቃጠላ በሆላ ሶስት ሚሊሻ ሞታ፡፡ ኢኔካ ጎደኛ ጢት አላቃ ማረካ፡፡ ጎደኛ ጴጥሮስ ሻካ ነበሬ፡፡

"አንዲ ቃን ማታ ኢሲር ቤት ቀመጣ ጊዜ ኢኛ ሶው መጣና ጠላት ወታደሮች ገደላና ኢስረኞቹ ሁሉ ነጣ ወጣ፡፡ ማንጋድ ዳሞ ጠላት እንደገና ከበባና ጎደኛ ጴጥሮስ ቆሳላ ዳሞ ተማረካ፡፡ አቦ፣ አቦ፣ አይ፣...›› ከንፈሩን ነክሶ በግሩ መሬቱን ይተመትም ጀመር፡፡ በአይኖቹ እንባ ግጥም አለ፡፡

‹‹አይዞ፣ አተነደድ፣ መጣ ጊዳጅ ፈጠማ፣ ኢንደቻልክ ጀግኒናት ፈጠማ፣ ጠላት ተኒሽ አሸነፋ፣ አሁን ቂርብ ጊዜ ኢኛ ናሸኒፋል፣ ጣላት ናባሪራል። አይዞ አተናዲድ። ተማረካ ጎዳኛም ነጣ ወጣል ዘዴ ፈለጋል። አሁን ኢና ባሩን መጣ ጊዜ ጡሩ ወሬ ሰማል።›› አለ አሊሃሽ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ የአኔቦን ትከሻ መታ መታ እያረገ።

# ምዕራፍ ሃያ ሁለት

በሪሁንና አሰግድ አሊሃሸንና አኔቦን ቤት ትተው ሌሊቱን ወደ ሚፈጽሙት ግዳጅ ከተሰማሩ ቆይተዋል። የዘወትር ልብሳቸውን እንደለበሱ ከተማውን መሃል ለመሃል እያቋረጡ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አጠገብ ሲደርሱ፣

‹‹አይ ጊዮርጊስ በሌላ ስፍራ ያሉ ታቦታት በዛሬው እለት ከየ መቅደሶቻቸው ወጥተው በየጥምቀተ ባህሮቻቸው ሕዝበ ክርስቲያኑን ሲያስጨፍሩት ያድራሉ። አንተ ግን ንብ የተጸየፈው ቀፎ መስለሃል›› አለ በሪሁን አንጋጦ ቤተክርስቲያኑን እየተመለከተ።

‹‹ለካ ዛሬ ጥምቀት ነው!›› አለ አሰግድ

‹‹ጥምቀት አደለም፡ ከተራ ነው››

‹‹ምን አርጉ ብለው ነው አሁን የጠላት ወታደሮች የሙታንን መቃብር እንዲህ የሚያፈራርሱት?›› አለ አሰግድ ቤተክርስቲያኑ ዙሪያ ያሉት መቃብሮች ተነዳድለው፣ ቆርቆሮዎችና እንጨቶቻቸው ተነቃቅለው፣ በላያቸው ላይ የተተከሉት መስቀሎች ተሰባብበረው ስለ አየ እያዘነ።

‹‹ውሻ የአንበሳን እሬሳውንም ቢሆን አይቶ መጮሁ አየቀርም›› አለ በሪሁን እየሳቀ። ቤተክርስቲያኑ የመድሃኒት ማከመቻና አንዳንድ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በጦርነቱ ሲቆስሉ ለጊዜው ማሳረፊያ ሆንዋል። ይህ የተደረገበት ምክንያት የኢትዮጵያ የጦር አይሮኘላኖች ቢመጡም የአምልኮ ቦታዎችን እንደማይመቱ ስለታወቀ ነው።

ከተማይቱ ውስጥና ባካባቢው በተፈጠረው ውጥረት ምክንያት የሰዓት እላፊው ወደ ቀን አስራ ሁለት ሰዓት ተመልስዋል፡፡ ህዝቡ በጊዜ ወደ ቤቱ ለመግባት ይጣደፋል፡፡ የጠላት ወታደሮች ከተማይቱ ውስጥ የተበተኑትን ቁስለኛ ወታደሮቻቸውን በዱላ እየነዱ ወደ ማደሪያቸው ይወስድዋቸዋል፡፡

የሚድኸው፣ የሚያነክሰው፣ ፊቱ በሙሉ በፋሻ ተሸፍኖ በመሪ የሚሄደው፣ ሁሉ አለቃውን፣ እግዚአብሔርን፣ራሱን (እሱነቱን)፣ እየተሳደበና እየተራገመ በሁዋላው ካለው ዱላ ለመሸሽ ብቅ ጥልቅ ይላል፡፡ መትረየሶች በተጠመዱባቸው መኪናዎች ላይ የተቀመጡ ወታደሮች አካባቢውን እየገረመሙ ያልፋሉ፡፡

እነ በሪሁን ግዳጃቸው ስፍራ እንደደረሱ፣ ቦታው ላይ ይጠብቃቸው የነበረ ሰው በሚሰጣቸው ምልክት መሠረት በቅደም ተከተል አንድ አነስተኛ ቤት ውስጥ ገቡ፡፡ ቤትዋ እንደ አብዛኞዎቹ የአካባቢው ቤቶች ግድግዳዋ ጨፈቃ ፣ ጣሪዋ አሸዋ ነው፡፡ አንድ ሰው ከሁዋላቸው ገባና‹‹ወደ ውስጥ ግቡ›› እያለ ቀደማቸው፡፡

ጉዋዳ ገብተው አረፍ እንዳሉ ሻይ ቀረበላቸው፡፡ ትንሽ እንደቆዩ አስተናጋጃቸው ብድግ አለና፣

‹‹እኔ መሄዴ ነው፣ አብሮዋችሁ የሚቆይ ሰው አሁን ይመጣል››ብልዋቸው ወጣ፡፡

ቤቱ ጉዋዳ ውስጥ ሆኖ እንደገና ወደ ውስጥ የሚያስገባ ሌላ በር ይታያል፡፡ በሩ ባሮጌ ጨርቅ ተጋርድዋል፡፡ በሪሁንና አስግድ ሻያቸውን ፉት እያሉ መጋረጃውን በንቃት ሲመለከቱ፣ የሴት ድምጽ ሰሙ፣ ወዲያው መጋረጃው ተገለጠና አንድ መልከምልካም ሴት የበራ ፋኖስ ይዛ ብቅ አለች፡፡

‹‹አሰላም አሌይኩም፣ ነበድ?›› እያለች ፋኖሱን አጠገባቸው አኑራ፣ ቀናውን በር ከውስጥ ዘጋችና፣

‹‹ሃሊማ እባላለሁ። አላያችሁኝም እንጂ፣ ተከትያችሁ ነው የመጣሁት›› እያለች ተቀመጠች። ነጫጭ ጥርሶችዋ ለውበትዋ ድምቀት ሰጥውታል ። ራስዋ ላይ ሽብ ካረገችው ኻርጉርጉር ሻሽ ስር የሚታየው ሉጫ ጸጉርዋ ከረጅም አንገትዋ ጋር አይን ይስባል። የሽፋሎቻቸው ጠርዝ በኩል የተዳሰሰው አይኖችዋ ከጥርሶችዋ ጋር ይስቃሉ። ትኩር ብለው ሲመለከቱ የልብ ሚስጢር የሚያነቡ የመስላሉ።

‹‹እራት ሳምጣላችሁ›› ብላ ብድግ ስትል፣

‹‹ግድ የለም፣ በልተናል›› አለ በሪሁን በእጁ ጭምር እየተከላከለ።

‹‹ለናንተ የተዘጋጀውን እራት ማን ሊበላላችሁ ነው›› አለችና ድርያዋን (ረዥም ቀሚስ ) ከፊት ወደላይ ሰብሰብ አርጋ በመያዝ ወደ ጉዋዳ ገባች።       አሰግድ በሪሁንን እየውና

‹‹በርግጥ ለልዩ ሥራ የተቀመጠች ናት››

‹‹ሽቶዋ ስሜት ይኮረኩራል›› አለ አሰግድ ሳቅ እያለ።

‹‹በአሁኑ ጊዜ በሽቶ የሚኮረኩር ስሜት የለንም››

ሃሊማ ያዘጋጀችውን እራት አቀረበች። ከስጋ ጋር የተሰራውን ሩዝ ፣ ወተት፣ ዳቦ...እያመጣች ደረደረችና አጠገባቸው ተቀመጠች።

በሪሁንና አሰግድ ምንም እንኩዋን ካስከፊው ርሃብ ከተለያዩ ወራት ቢቆጠሩም፣ በጥንቃቄ የተዘጋጀ ጣፋጭ ምግብ ሲመገቡ የመጀመሪያቸው ነበር። ሩዙንም፣ ስጋውንም፣ ወደ ፊታቸው እየገፋች ወተቱንም እየቀዳችላቸው ደህና አርግው ተመገቡ።

ምግቡ አብቅቶ እቃውን አነሳስታ ስትሄድ፣

‹ሁለመናዋ የተሻገጎረጎረ ነገር›› አለ አሰግድ፡፡

‹‹በአሁኑ ጊዜ ውበትን የሚያደንቅ አይን የለንም›› አለ በሪሁን ወደሌላ እያየ፡፡ አሰግድ በጉዋደኛው ሁኔታ እየተገረመ ዝም አለ፡፡

‹‹አሁን ወደ ግዳጃችሁ ቦታ ወስዳችሁዋለሁ›› አለች ሃሊማ ሰአትዋን እየተመለከተች፡፡

‹‹ስለሁኔታው በአጭሩ ብትገልጪልን...›› አለ በሪሁን ባይኖቹ እየመረመካት፡፡ ድርያዋን ትንሽ ወደ ላይ ሰብሰብ አርጋ ፊታቸው ቁጢጥ አለችና ድምጽዋን ዝቅ አርጋ፣

‹‹አሊሃሽ አልነገራችሁም እንዴ?››አለች፡፡

‹‹ነግሮናል፣ ይበልጥ ካንቺ ለማወቅ ነው›› አለ በሪሁን ፈገግ ብሎ፡፡

‹‹አሁን የመኮንኖቹ መምጫ ሰዓት ነው፡፡ እናንተ እኔ ጉዋዳ ውስጥ ትደበቃላችሁ፡፡ መኮንኖቹ የሚመጡት በየተራ ስለሆነ፣ የምትፈልጉትን  መኮንን እኔ ሳጫውተው ልትይዙት ትችላላችሁ›› አለች ጣቶችዋን፣ አይኖችዋን፣ ከከንፈሮችዋን...እያንቀሳቀሰች፡፡

‹‹እኛ ለጊዜው የምንፈልገው የዘመቻ መኮንኑን ሻለቃ አብዱላሂን ነው፡፡ እሱ ከመጣ በሚገባ አጫውተሽ አዝናኚው›› አለ በሪሁን ፈገግ ብሎ፡፡

‹‹ይመጣል፣ ለማዝናናቱ ግዴለም፡፡ ብቻ ጥይት እንዳትተኩሱ፡፡ ካቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ ማለቴ ነው፡፡ ብቻቸውን ነው ባለስልጣኖቹ የሚመጡት፡፡ የራሳቸውን ወታደሮች አያምኑዋቸውም›› ብላ ፈገግ አለችና፣ ‹‹ከያዛችሁት በሁዋላ እንዴት ነው የምታረጉት?›› አለች፡፡

‹‹አልተነገረሽም እንዴ?›› አለ በሪሁን ፊቱን ቅጭም አርጎ፡፡

‹‹ተነግሮኛል፣ እናንተም በትክክል ተረድታችችሁ እንደሆን

ለማወቅ ነው። እሺ እንሂድ›› ብላ ቀደም አለች። ፋኖሱን ይዛ ከፊት እየመራች፣ እነሱ እየተከተሉ በባለመጋረጃው በር ወደ ውስጥ ገቡ። እንደገና ሌላ ክፍል አቋርጠው ጉዋሮ በር ላይ ሲደርሱ፡-

‹‹ያ የምታዩት የኔ ቤት መስኮት ነው። በዚያ ዘላችሁ ትገባላችሁ›› አለች ወደ መስኮቱ እያመለከተች። በባለ መስኮቱ ቤትና እነሱ ባሉበት ቤት መሐል ዙሪያው በቤቶች የተከበበ አነስተኛ ክፍት ቦታ አለ።

‹‹አንቺስ?›› አለ አሰግድ ሃሊማን እያየ።

‹‹እኔም በዚያው ነው የምገባው››ሳቅ አለችና ፋኖሱን አጥፍታ ስስቱም ወደ መስኮቱ ተጠጉ።

‹‹እኔ ልቅደም›› አለች ሃሊማ ፋኖሱን ለአሰግድ እየሰጠች። አሰግድ በአንደኛው እጁ ፋኖሱን ይዞ በሌላው ሊደግፋት እጁን ዘረጋ።

‹‹ግድ የለም አያስቸግረኝም ›› አለችና ቀሚስዋን ሰብሰብ አርጋ በመስኮቱ ሾልካ ገባች። በሪሁንና አሰግድ ተከተልዋት።

ፋኖሱን ለኩሳ መኝታ ክፍልዋ አስቀመጠችው። እነ በሪሁን ያሉበት ጉዋዳና መኝታ ቤትዋን የሚለየው ሳሳ ያለ ኘርንጉርጉር መጋረጃ ስለሆነ የፋኖሱ ውጋጋን እስካሉበት ይገባል።

‹‹እናንተ እዚሁ ትቀመጣላችሁ። አስጊ ነገር ከተፈጠረ በነዚህ ጀንያዎች መሃል መሽሽግ ወይም በገባችሁበት ዘላችሁ መውጣት ትችላላችሁ። ለምናልባቱ አንጂ ማንም ወዲህ አይገባም››

‹‹ተቀመጡ ቀዝቃዛ ውተት ላምጣላችሁ›› ብላ ከጉዋዳ ስትወጣ፡

‹‹ውሃ ይሻለናል›› አለ አሰግድ ላቡን እየጠረገ። ወዲያው ቤቱ ፊትለፊት በር ላይ የመኪና ድምጽ ተሰማ። ያመጣችውን ውሃ በጥድፊያ እየሰጠቻቸው፣

‹አንደኛው መኮንን መጣ መሰለኝ። እንግዲህ ድምጽ የለም›› ብላ

አንድ አጭር አውቶማቲክ ጠመንጃና ጥቅል ገመድ ሰጥታቸው ሄደች፡፡

በሩ በጣም ዝቅ ባለ ድምጽ ተንኳኳ፤ ተከፈተ፡፡

‹‹ነበድ›› አለ አንድ ጎርናና ድምጽ፡፡ በሩ ተዘጋ፡፡ ለአጭር ጊዜ ፀጥታ ሆነ፡፡ በሪሁን በቀስታ ወደ መጋረጃው ተጠግቶ ይመለከት ጀመር፡፡ የደንብ ልብሱን የለበሰ ረዥርም ሰውዬ መለዮውን እንደያዘ የሃሊማን ወገብ እቅፍ አርጐ ያያታል፡፡ እስዋ እጆችዋን ትከሻዎቹ ላይ ጣል አድጋ እንደሰው ታየዋለች፡፡ በቀስታ ተቀራረቡና ከንፈሮቻቸው ገጠሙ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ፤ ሃሊማ በመርፌ የተወጋች ይመስል፤ ወደ ሁዋላዋ ዘለለችና፤ ፊትዋን ወደሌላ ምልሳ ቆመች፡፡

‹‹ምነው የኔ ወርቅ?›› እያለ ትከሻዋን ያዝ ቢያረጋት እጁን ገፍታ አልፍ አለችና ቆመች፡፡ ሰውዬው ትንሽ እንደማሰብ አለና

‹‹የሰው ስሜት መግደል ልማድሽ ነው›› አለ ቆጣ ብሎ፡፡

‹‹ ለስሜትህ ማብረጃ ነው የምትፈልገኝ፤ አውቃለሁ፤ ለሌላውማ ሌሎች አሉልህ!›› አለች በውሸት እያለቀሰች፡፡

‹‹ምንድነው የምታወሪው? ሌሎቹ ደሞ ምንድንናቸው?››

‹‹እቁባቶችህና ሚስቶችህ ናቸዋ!፡፡ ያልሰማሁ መሰለህ? ሰሞኑን ከሞቃዲሾ ከሚመጣው የመዚቃ ጉዋድ ጋር ሁለቱ ሚስቶችህ እንዲመጡልህ መልእክት ማስተላለፍህን፤ አብረሃቸው ስትደንስ ልትከርም›› ዐይኖችዋን የጠራረገች፡፡

‹‹አሃሃሃ፤ ሃሃሃሃ፤ በቃ ይሄንኑ ስታስቢ ነው የሚትኖሪው?፡፡ ያልሽው ሁሉ ሃሰት ነው፡፡ወላሂ ቢላሂ ሃሊማ፤ ሃሰት ነው፡፡ ይሄን የነገረሽ ጠላታችን መሆን አለበት፡፡ ያልሽውን አላረኩም፡፡ እርግጥ ሴቶቻቸው እንዲመጡላቸው መልእክት ያስተላለፉ መኮንኖች አሉ፡፡ እኔ ግን አላረግሁም፡፡ ስንት ጊዜ ልንገርሽ ሃሊማ፡፡ ሕይወቴ ከጥይት

ብትተርፍ ያንቺ ናት፡፡ ምስክሬም አላህ ነው››

‹‹የሙዚቃ ጉዋዱ መቼ ነው የሚመጣው?›› አለች እደ ህጻን ራስዋን ደረቱ ላይ አስደግፋ፡፡

‹‹ባለፈው ሳምንት ነበር እዚህ ይገባል የተባለው ›› አለ ጉንጭዋን እየዳሰሰ፡፡

‹‹ታዲያስ?››

‹‹በሰሞኑ ውጥረት ምክንያት ፕሮግራሙ ሳይስረዝ አይቀርም››

‹‹በጣም ያሳዝናል››

‹‹እሱን ተይው፣ ይልቅ ምን የሚቸግርሽ ነገር አለ?››

‹‹ከኩዌት አስመጣልሻላሁ ያልከው ወርቅ የታለ?››

‹‹ሰሞኑን እዚህ ይደርሳል፡፡ ሌላም ስሙን አሁን የማልነግርሽ ዕቃ ይመጣልሻል፣ ቸኩላለ ሁ...›› አያለ ወደ መኝታዋ ሳባት፡፡

‹‹ልትሄድ?››

በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ፡፡

‹‹ውይ ያመኛልኮ፣ አልነገርኩህም?›› ብላ የኮቱን ቁልፎች እያስተጋከለች ‹‹ነገ ይሻላል›› አለች፡፡ የቁጣ እሳት የሚረጩ ዐይኖቹን አፈጠጠባት፡፡

‹‹አይሆንም አሁን ነው የምፈልገው››

‹‹እንግዲህ ችክ ትላለህ ፣ ስነግርህ ስማ!›› ብላ ቆጣ ስትልበት ጊዜ ፈገግ አለና በመለዮው ጉንጭዋን መታ አርግዋት ወጣ፡፡

‹‹ ሄደ?›› አለ አሰግድ በሪሁን ቆሞ ከሚመለከትበት ተመልሶ ጎኑ ሲጠመጥ፡፡

‹‹አዎ ሄደ›› አለ በሪሁን ባየው ሁኔታ እየተደነቀ፡፡ ሃሊማ በሩን ከውስጥ ዘግታ ወደ ነበ ሪሁን ገባችና፣

‹‹አንዱን ሸኘሁት፣ አወቃችሁት?፣ ኰሎኔል ሳሊም ይባላል፡፡ የጦሩ የስንቅና ትጥቅ ክፍል ሃላፊ ነው፡፡ እሱን የምትፈልጉት አልመሰለኝም›› አለች ፈገግ ብላ፡፡

‹‹ሰጊዜው አንፈልገውም። ችሎታሽን እናደንቃለን፡፡ ለቡድናችን የምታረጊውን የስንቅና የገንዘብ እርዳታ ሁሉ አሊሃሽ ነግሮናል ›› አለ አስግድ ፈገግ ብሎ፡፡

ሻይ ቀድታላቸው እየጠጡ ትንሽ እንዳወሩ በሩ እንደገና ተንኳኳ፡፡

‹‹የአሁኑ የምትፈልጉት ሻለቃ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ምልክት እስክሰጣችሁ እንዳትመጡ›› አለችና አፍዋን እየጠራረገች ወጣች፡፡

በሩ ተከፈተ፣ ተዘጋ፡፡

‹‹ ምነው የኔ ጌታ? ያሰወትሮህ አመሸህ ›› አለች ሃሊማ የሰውየውን እጅ ይዛ ወደ መኝታዋ እያመራች፡፡

‹‹ይሄ ነው ሻለቃው?›› አለ አስግድ ሁለቱም ወደ መጋረጃው ተጠግተው ሲመለከቱ፡፡

‹‹አዎ ዝምበል›› አለው፡፡

‹‹ዛሬ ደሞ ጥቁርቁር ብለሃል›› አለች ሃሊማ ጉንጩን እየዳሰሰች፡፡

‹‹ወደ ጫካ ሄጄ ነበር›› አለ ሻላቃው አልጋው ላይ ቁጭ እያለ፡፡

‹‹ለምን?››

‹‹ሰሞኑን በመህኒ ቤቱ ላይ አደጋ የጣሉት ወንበዴዎችና ወታደሮቻችን የተታኮሱበትን ቦታ ለማየት፡፡››

‹‹እነዚያ ማን ነበር ስማቸው? ‹የጣምራ ጦር› የሚባሉት ናቸው?››

‹‹ስማቸውን ደሞ ማን ነገረሽ?››

‹‹ውይ - ህዝቡ በሙሉ አደለም እንዴ የሚያወራው?››

‹‹እውነትም ጦር ፣ ውጋት!›› አለና በስፊው ተነፈሰ፡፡

‹‹በቃ እስረኞቹን እንደያዙ አመለጡ?››

‹‹ሌሊቱን የተከተላቸው ጦራችን ደርሶባቸው ነበር፡፡ ግን ምን ያረጋል፣ መንገድ አድፍጠው ኖሮ ሰዎችና ተሽከርካሪዎች ጎድብን"

‹‹በጣም ጉዱዋችሁ?››

‹‹ምን ይሄ እንከቶ ጦር በሄደበት እሳት እንደገባ ቅቤ ይቀልጣል፡፡ ወታደሮች ትእዛዝ አያከብሩ፣ የሚሰጣቸውን የጦር ስልት አይከተሉ፣ ውሃ ሊጠጣ እንደሚሄድ የግመል መንጋ እርስ በርሱ ሲጋፉ አንድ ፋይዳ ሳይሰራ እንዲሁ ያልቃል፣ ጦሩ››ብስጭት አለ፡፡

‹‹ወንበዴዎቹ የታባታቸው ይደርሳሉ ብለህነው?፣ ጦራችን ተጠናክሮ ቢነሳባቸው መድረሻ ነው የሚያሳጣቸው››

‹‹አይመስለኝም፣ ተቃራኒው ነው በመሆን ላይ ያለው››

‹‹እንኳዋን አንተ ተረፈክልኝ፣ የወደፊቱን አላህ ያውቃል"

ትነሽ እንዲያ እንደሆኑ፣ ከእቅፉ ወጥታ ቶሎ ቶሎ ትተነፍስ ጀመር፡፡ ጉንጮችዋ ቀልተው ከንፈሮችዋ አበጡ፡፡ ሻሽዋ ተፈቶ ሉጫ ፀጉርዋ በጀርባዋ ወረደ፡፡

ሻለቃው ሽጉጡን ወንበር ላይ አስቀምጦ ትጥቁን ሲፈታታ፣

‹‹ምነው? ፣ ትቸኩላለህ እንዴ?›› አለች ጸጉርዋን እየጎነጎነች፡፡

‹‹አዎ መኪናዬን እሩቅ ነው ትቻት የመጣሁት›› አንሶላውን ገልጣ መኝታውን አሳየችው፡፡ ልብሱን አወላልቆ መኝታው ውስጥ ሲገባ፣ ሀሊማ የተስማሙበትን የድምጽ ምልክት ለነበርይሁን አሰማቻቸውና ሽጉጡን አንስታ ወደ ሻለቃው ደገነች፡፡

‹‹እንካ ልብስህን ልበስና ተነስ! ›› አለ አስግድ የሻለቃውን ሱሪ እየወረወረለት፡፡ ሻለቃው እየተንቀጠቀጠ እንደምንም ሱሪውን አጥልቆ

አልጋው ጠርዝ ላይ ቁጭ አለ።

‹‹ኮቱን ስጠው!›› አለ በረሁን ጠመንጃ ውን ወደ ሻላቃው እንዳነጣጠረ።

‹‹ተንበርከክና እጆችህን ወደ ሁዋላ አርግ›› አለ አስግድ ሊያስረው ገመዱን እያዘጋጀ።በረሁንንና አስግድ ሰውዬውን የፊጥኝ ካሰሩትና አይኖቹን ከጨርቅ ሽብ ካደረጉ በሁወላ፣ በገቡበት መስኮት አሾልከው ከሃሊማ ቤት አወጡት።

# ምዕራፍ ሃያ ሦስት

ከፍተኛው የጠላት ጦር ሰፈር እንደተለመደው ግርግርና ትርምስ ይታይበታል። ከሁወላቸው ረጃጅም የሬድዮ መገናኛ ሽቦዎች የሰኩ የአዘገሮች ጅፕ መኪናዎች እየመጡ ጦሩ ምክትል አዛዥ ቢሮ አጠገብ ይቆማሉ። ከየመኪናዎቹ የሚወርዱት ከፍተኛ መኮንኖች እየተጣደፉ ወደ ምክትል አዛገሩ ቢሮ ይገባሉ።

የጦሩ ምክትል አዛዥ ቢሮው ውስጠ ተቀምጦ የአንገቱ ስሮች እስኪወጣጠሩ እየጮኸ በሬድዮ ስልክ ይነጋገራል። ትእዛዝ ይቀበላል። ትእዛዝ ይሰጣል። ቢሮው ውስጥ የሚገቡት መኮንኖች ከአለቆቻቸው አጸፋውን ባያገኙም ወታደራዊ ሰላምታ እየሰጡ ይቀመጣሉ።

ምክትል አዛገሩ በስልክ ሲነጋገር ቆየና ባለሃ ይሉ ጮሆ፡

‹‹እኔ ተናግሬያለሁ። ከዚህ ሌላ ምንም ላረግልህ አልችልም! ያለህን ጦር ይዘህ ባለህበት ተከላከል። ወደ ሁዋላ ብትመለስ የሚጠብቅህ ያው ሞት ነው!!›› አለና የስልኩን መነጋገሪያ ወረወረው። ከዚያ በክርናቹ ጠረጴዛ ላይ ተሞርኩዞ ክፍሉ ውስጥ የሉትን በዝምታ ቃኛቸው። መኮንኖቹ በወታደራዊ ስነ ስርዓት ጸጥ ብለው በመቀመጥ አዛገራቸው የሚለውን ለመስማት ዝግጁ መሆናቸውን አሳዩት። ከተቀደደ ፖስታ ጋር የተያያዙ ሁለት ገጽ ወረቀቶች ከጠረጴዛው ላይ እያነሳ በምጸት ፈገግ አለና፡

‹‹እኛ ጠመንጃችንን ደግነን ማዶ ማዶውን ስናይ ጠላቶቻችን ውስጣችን ገብተው እጆቻችንን ሊይዙን ነው›› ብሎ ተሰብሳቢዎቹን

ያቸው። በንግግሩ ግራ በወጋባት ተያዩ።

"አንድ ጦር በተሰማራበት ግዳጅ ላይ ለሚያገኘው ድልም ሆነ ለሚደርስበት ውድቀት መሪ መኮንኖች ከፍተኛውን ሚና ይጫወታሉ."ቀጠለ ምክትል አዛገ፣ "ጥሩ አመራር፣ የተሟላ ትጥቅና የውጊያ ሞራል ያለው ጦር በጠላቱ ላይ የበላይነትን ያገኛል። ጥሩ መሪ የሌለው ጦር ግን አውራ እንደሌለው ንብ የሚሄድበትን አያውቅም። የኛም ጦር ዛሬ ከድል ተገትቶ ከየጦሩ ግንባር ወደ ሁዋላ እንዲያፈገፍግ ካስገደዱት ምክንያቶች አንዱ፣ ብቃት ያላቸው መሪዎች ማጣቱ ነው። አንዳንድ ልፍስፍስ መኮንኖች ጦራቸውን እየጣሉ መፈርጠጣቸው ሲገርመን፣ እዚሁ ከፍተኛ አመራር ላይ ያሉትም ውድቀታችንን ያፋጥኑታል።.ይህ ዛሬ ማለዳ ከጠለቶቻችን የደረሰን ደብዳቤ ነው፣ አነበዋለሁ አዳምጡ ‹ እብሪተኛ ወራሪዎች፤ እንደምናችሁ። እየዘፈናችሁ እንደገባችሁ እያለቀሳችሁ መውጫችሁ ደርስዋል። ይህን እናንተም ሳትረዱት አልቀራችሁም። የደብዳቤያችን ዋና አላማ እንኳዋን ይህን ለማስገንዘብ አልነበረም። እግረመገዳችንን እንጥቀሰው ብለን ዕንጂ። በከተማይቱና በአካባቢዋ የምናረገውን እንቅስቃሴ ለመግታት የምታሳዩት መፍጨርጨር ምንም አልረዳችሁም። የምንታገላችሁ እናንተ እንደገመታችሁት ከሴላ ስፍራ ስርገን የገባን ሳንሆን እዚሁ የነበርንና ያለን ነን። ከአካባቢው ነዋሪዎች ጥቂቶቹን በሃሰተኛ ፕሮፓ ጋንዳችሁ በማወናበድና በጠመንጃ በማስገደድ ጊዜያዊ ድል አግኝታችሁ ነበር። ዛሬ ግን ሕዝቡ ሃቁን ተረድቶት ለነጻነቱ ተነስትዋል። ይዋጋችሁዋል። ከፊታችሁ የወገን ጦር ፣ ከሁዋላ እኛ አለን። በእብሪት የያዛችሁት መሬት መቀበሪያችሁ እንጂ መኖሪያችሁ አይሆንም!...

"አሁን ልንነግራችሁ የምንፈልገው ምናለባት በግልጽ ስላላወቃችሁት ምርከኛ ነው፡፡ መኮንኑ በእጃችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በታላቅ ክብር ይዘነዋል፡፡ ይህን እራሱ ይገልጽላችሁ ይሆናል፡፡ እናንተ ግን የማረካችሁዋቸውን አባሎቻችንን እንደምታሰቃዩዋቸው እናውቃለን፡፡ ቢሆንም የሚሰቃዩት ለትክክለኛ አላማ ስለሆነ የሚከፍሉት ክቡር መስዋእትነት ነው፡፡ ፍቃደኞች ከሆናችሁ እነዚህን አባሎቻችንን ልቀቁልንና ሻላቃችሁን እንልቀቅላችሁ፡፡ አይሆንም ካላችሁ ግን፣ በሻለቃችሁ ላይ ብቻ ሰይሆን በያንዳንዳችሁ ላይ እርምጃ የምንወስድ መሆናችንን በቅድሚያ እንገልጻለን... ›› አለና ቀና አለ፡፡

መኮንኖቹ አፎቻቸውን በከፊል ከፍተውና አይኖቻቸውን አፍጠው፣ ሲያዳምጡ ከቆዩ በሁዋላ የደረቁ ከንፈሮቻቸውን በምላሳቸው አረጣጠቡና በሰፊው ተነፈሱ፡፡ በደረሰው ነገር መደንገጥ ብቻ ሳይሆን እነሱም የሚጠብቃቸውን እድል ሲገነዘቡት ፍርሃት ከባድ አጁን ጫነባቸው፡፡

.‹‹ይሄ ደሞ የተማረከው የዘመቻ መኮንናችን የጻፍው ነው" አለ ምክትል አዛገፑ ንግግሩን ጫን በማረግ፡፡ ቀደም ብሎ ካነበበው ደብዳቤ ጀርባ ያለውን ወረቀት ከፍ አርጐ ለመኮንኖቹ አሳየና አነበበ፣ ‹‹እኔ ሻለቃ ያሲን አባስ በደህና ሁኔታ ላይ እገኛለሁ፡፡ እናንተ ከተባበራችሁዋቸውና የያዛችሁዋቸውን ምርኮኞች ከለቀቃችሁላቸው፣ እኔን በደህና እንደሚያሰናብቱኝ የያዙኝ ሰዎች ቃል ገብቱውልኛል፡፡ በምርኮኞቹ ላይም ሆነ፣ እኔን ለማስመለስ ሌላ እርምጃ ለመውሰድ ብትሞክሩ የከፋ ሁኔታ እንደሚመጣ ላረጋግጥላችሁ ወዳለሁ..." አለና ወረቀቱን ወደ ጎን ገፋ አርጎ፣

‹‹ተዲያስ ምን ትላላችሁ?›› አለር፡፡ በስተግራ የተቀመጠው ሽበቶ

መኰንን ከመቀመጫው ተመቻቸና፡-

‹‹የደረሰው ሁኔታ መቼም እጅግ አሳፋሪ ነው፡፡ አሁን ለምን ይሄ ደረሰ? ማነው ጥፋተኛው?፣ ብለን የምንነጋገርበት ጊዜ አይደለም፡፡ ወደ ባሰ ውርደት እንዳንገባ ሁኔታው የተሻለ መልክ የሚይዝበትን አፋጣኝ ዘዴ መሻት ነው ያለብን ›› አለ፡፡

‹‹ከመድረሱ በፊት መከለከሉ እንጂ፣ ከተዘፈቁበት በሁዋላ የውርደትን እድፍ ለማጠብ መሩዋሩዋጡ ጀግና አያሰኝም›› አለ ምክትል አዛገፉ ቆጣ ብሎ፡፡

‹‹ዘዴ የሌለው ጀግንነት ጅብደኛነት ነው፡፡ አየህ ጌታዬ ይህ ሁኔታ ከመድረሱ በፊት ለመከለከለ ብንችል መልከም ነበር፡፡ሞክረናል፡ አልሆነም፡፡ ችግሩ ወደ ባሰ ሁኔታ ሳይሸጋገር ባለበት እንዲቆም ለማረግ ብንችል ዘዴ የታከለበት ጀግንነት ስለሚሆን፣ እንደ ውርደት አይቆጠርም›› አለ ሸበቶው መኰንን ለስለስ ባለ አነጋገር፡፡

‹‹ምንድነው ወደ ባሰ ሁኔታ ከመሸጋገሩ በፊት የምትለው?›› አለ አዛገፉ እጆቹን እያወራጨ፡፡

‹‹ይህ ሁኔታ በኛም ላይ እንዲደርስ አያስፈልግም፡፡ ቢቻል አስጊውን ሁኔታ ማስወገድ፣ ካልተቻለ ደሞ ባለበት እንዲቆይ ማረግ፡፡ ምቹ ሁኔታ አግኝተን እስክናጠፋው ማለቴ ነው፡፡ በአጭሩ በጥያቄያችው መሠረት ምርኮኞቻቸውን ለቀን ሻለቃችንን ብናስመልስ ነገሩ በአጭሩ ይቀራል፡፡ አለዚያ. . .›› እያለ ሸበቶው መኰንን ሲናገር ምክትል አዛገፉ አቋረጠውና፡-

‹‹ አለዚያ ምን?›› ብሎ አፈጠጠበት፡፡ ሸበቶው መኰንን ትንሽ ፈርጠም አለና፡-

‹‹አለዚያማ ሻለቃችንን አሳልፈው ለዋናው የጠላት ጦር

ይሰጡታል፡፡ ይህ ከሆነ ደሞ ከፍተኛ ሚስጢራችን ባክነ ማለት ነው፡፡ ነገሩም ሁላችንን በኃላፊነት ያስጠይቀናል››አለ፡፡

‹‹እና የአንድን አደጋ ጣይ ወንበዴ ቡድን ህልውና ተቀብለን፣ ከዋናው ጦር ጋር ያላረግነውን ድርድር በማረግ ምርኮኞች እንለዋወጥ ነው የምትለው?›› አለ ቆሞ ጠርጴዛውን በብእሩ እየደበደበ፡፡

መሃል የተቀመጠው መፍራም ኰሎኔል ጉረሮውን ሞረደና፡-

‹‹የጸፋት ደብዳቤ መንፈስ እንደዚህ የሚል አይመስለኝም፡፡ ምርኰኞቻችንን ልቀቁልን እኛም ሻለቃችሁን እንለቅላችሁዋለን ነው ያሉት፡፡ እኛ የምንለቅላቸው ምርኰኞች ሲሄዱላቸው ሻለቃችንን ይለቁልናል ማለት ነው፡፡ ድርድርና ውይይት አልጠየቁም››አለ፡፡

ምክትል አዛገፉ ጎን የተቀመጠ ቀጭን ሻለቃ ፈገግ አለና፡-

‹‹ስለ ምርኰኞች መለዋወጥ የምታረጉት ውይይት ከንቱ መሰለኝ፡፡ ቀደም ብሎ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት አራቱን ምርኮናችና ሌሎች እሥራኞች በትላንትናው ሌሊት ረሽነናቸዋል›› አለ፡፡

‹‹መቼነው ይሄ ትእዛዝ የተሰጠው?›› አለ ምክትል አዛገፉ ሻለቃውን እያየ፡፡

‹‹ትናንትና ማታ›› አለ ሻለቃው በግዴለሽነት አነጋገር፡፡

‹‹ቃላቸውን ተቀብላችሁዋቸዋል?››አለ ምክትል አዛገፉ ጠረጴዛውን በብእሩ እየቆረቆረ፡፡

‹‹ሞክረን ነበር››

‹‹ታዲያስ?››

‹‹ምንም አንናገርም አሉ፣ ሚስጢራቸውን ልናስወጣቸው አልቻልንም››

ውይይቱ በዚህ ሁኔታ ቀጥሎ ብዙ ከተባለ በሁዋላ ምክትል

አዛገፑ ቆመና፣

‹‹ታዲያ ስለ ሻለቃችን ምን እናርግ ነው የምትሉት? የልክስክስና የወራዳ ሰው ፍጻሜ ይህ ነው›› አለ።

‹‹ይልቅስ ጊዜ ሳናባክን አንድ ፈፋጣኝ እርምጃ እንውሰድ። አፋኙ ቡድን ሻለቃችንን በከተማው ውስጥ አንድ ቦታ ደብቆ ለኛ ለላከው ጥያቄ መልስ በመጠበቅ ላይ ነው። ያለንን አጭር ጊዜ ተጠቅመን ሻላቃችንን ቢቻል ከነ ሕይወቱ፣ ያለዚያም አሬሳውን ማስመለስ አለብን›› አለ ቀጭኑ ሻለቃ ጠንከር ባለ አነጋገር።

‹‹እንዴት? የት? መቼ?›› አለ ሽበቶው ሹም ደረቅ ፈገግታ አያሳየ።

‹‹በአቅራቢያው ካለው ጦራችን ረዳት የሚሆን አንድ ሻለቃ ጦር እናስመጣ። በተጨማሪም በከተማይቱና በዙሪያው የተበታተነውን ጦራችንን አንድ ቦታ እንሰበስባለን። ከዚያ ከአንድ አቅጣጫ በመጀመር ከተማይቱን በደንብ እናስሳታለን። መጀመሪያ የምናረገው ግን፣ የሻለቃው ወዳጅ ነች የምትባውን ሴት ቤትና አካባቢውን በተጠናከረ ሃይል በሚገባ መፈተሽ ነው። ይህ ሳይዘገይ ዛሬ መከናወን ያለበት ተግባር ይመስለኛል›› አለ ቀጭኑ ሻለቃ።

‹‹ይህ ነው የተሻለው መንገድ፣ አሁኑኑ ትእዛዝ ሰጣለሁ። ምስጢሩ በሚገባ ይጠበቅ። ሁላችሁም አሰሳውን በማስተባበር ተግባር ስለ ምትረዱን እዚሁ ትቆያላችሁ›› አለ ምክትል አዛገፑ የሬዲዮ ስልኩን መነጋገሪያ እያነሳ።

# ምዕራፍ ሃያ አራት

አብዛኛዎቹ የደገሀቡር ከተማይቱ ቤቶች ዝግ ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ በየመንገዱ ላይ ይሚታዩ፣ የበሽተኛ ልብስ የለበሱ የጦር ሜዳ ቁስለኞች ብቻ ናቸው፡፡ በየጦር ሠፈሮቹ ያለው ትርምስና ግርግር ከውትሮው ለየት ይላል፡፡ ሁለት የወታደር ጂፕ መኪናዎች በከፍተኛ ፍጥነት እየበረሩ ከተማይቱን አቋርጠው ሄዱና በዚያው ፍጥነት ተመልሰው ወደ ዋናው የጦር ሠፈር አመሩ፡፡ ብዙም ሳይቆይ፣ ወታደሮች የጫኑ ካሚዮኖችና ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች ከጅጅጋ አቅጣጫ ወደ ከተማይቱ ገቡ፡፡

የመኪናዎቹን ድምጽ የሰሙ አንዳንድ የከተማይቱ ነዋሪዎች ራሶቻቸውን በመስኮት ብቅ እያረጉ አካባቢውን በስጋት ይቃኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደሞ ከጥቂት ጊዜ በኂላ የሚመጣውን አደጋ በመገመት ገርበብ ያሉ መስኮቶቻቸውንና በሮቻቸውን ጠበቅ እያደረጉ ዘጉ፡፡

መትረየስ የተጠመደባት ጂፕ ሁለት ካሚዮኖች ሙሉ ወታደሮች አስከትላ መጣችና መሃል ከተማ ስትደርስ፣ ወደቀኝ እጥፍ ብላ ቆመች፡፡ ካሚዮናቹ ላይ የነበሩት ወታደሮች እየወረዱ ተሰለፉ፡፡ ከጂፕዋ የወረደው የመቶ አለቃ ወደ ወታደሮቹ ጠጋ ብሎ ትንሽ አነጋገራቸውና በአመልካች ጣቱ ወደ አንደ መንደር ውስጥ እያመለከተ ትእዛዝ ሰጣቸው፡፡ ወታደሮቹ በሁለት ረድፎች ተሰልፍውና ጠመንጃዎቻቸውን በተጠንቀቅ ይዘው ሄዱና ሃሊማ ቤት አጠገብ ሲደርሱ ቆሙ፡፡ አንደኛው ረድፍ በአንድ የአምሣ አለቃ እየተመራ

ከቤቱ ጀረባ ዞረ። የተቀሩት ወታደሮች ደሞ ከፊት ለፊት የግማሽ ቀለበት ቅርጽ ሰርተውና ፊታቸውን ወደ ቤቱ ዙረው በተጠንቀቅ ቆሙ:: የሙቶ አለቃው የነበረባት ጂፕ የመትረየስዋን አፈሙዝ በሩ ላይ አነጣጥራ ሃሊማ ቤት ፊት ለፊት ቆመች:: የሙቶ አለቃው እየተዘዋወረ ወታደሮቹን የተሻለ ነው ብሎ በገመተበት አቅጣጫ እንዲቆሙ አረገ። የሃሊማ ቤት ብቻ ሳይሆን፣ የሰፈሩ ቤቶች በሙሉ ተዘግተዋል።

ትንሽ ቆይቶ መትረየስ የተጠመደባቸው ሁለት ተጨማሪ መኪናዎች መጡ:: ካአንደኛው መኪና ውስጥ የወጣው ሻምበል ወደ ሙቶ አለቃው ተጠጋና፡-

‹‹እህስ እንዴት ነው?›› አለው::

‹‹ቤቱን ከበነዋል፤ ከውስጥም ሆነ ከውጭ እስከ አሁን ምንም እንቅስቃሴ የለም›› አለ የሙቶ አለቃው ወደ ሀሊማ ቤት በር እየተመለከተ::

‹‹ቤቱ ከውስጥ አይደለም እንዴ የተዘጋው?››

‹‹አዎ፤ በሩም ሆነ መስኮቱ ከውስጥ ነው የተዘጉት››

‹‹ከጀርባ በደንብ አስከብበኸል?››

‹‹እዎ፣ ብቻ በዚያ በኩል መትረየስ የለንም››

‹‹እነዚህ ሁለቱም ጂፖች በጀርባ ይዙሩ›› አለ ሻምበሉ ራቅ ብለው ወደ ቆሙት መኪናዎች እያመለከተ:: ከዚያ ሻምበሉና የሙቶ አለቃው ቀስ እያሉ ወደ ሀሊማ መስኮት ተጠጉ:: ሙቶ አለቃው ደረቱን ከግድግዳው አዛምዶ አንድ እጁን ዘረጋና መስኮቱን አንኳኳኩዋ:: ከውስጥ ምንም መልስ የለም:: ደገመና አንኳወኩዋ:: መልስ የለም:: በሃይል ደበደበው:: ድምጽ የለም::

‹‹አውቀው ነው ያደፈጡት›› አለ ሻምበሉ በሹክሹክታ::

‹‹ታዲያ ምን ይሻላል?››

‹‹ብረት ለበስ መኪና ወይም ታንክ አስመጥተን በሩን እንገነጥለዋለን›› አለ ሻምበሉ አጎንብሶ ወደ ነበረበት እየተመለሰ። በሩ ፊትለፊት ሲደርስ፣ ቆም አለና አይኑን ጨፍኖ በቀዳዳ ወደ ውስጥ ተመለከተና፣ መቶ አለቃውን ሣብ አርጎ በቀዳዳው ወደ ውስጥ እንዲመለከት ጠቆመው። እሱም እንደ አለቃው ተመለከተና፣ ቀና ብሎ አይኖቹን እያሻሸ በጥያቄ አየው።

‹‹ምንድ ነው የምትሰሩት?፣ ድብብቆሽ ነው እንዴ የምትጫወቱት?›› አለ አንድ ጎርናና ድምጽ ከሁዋላቸው። ደንግጠው ዞር አሉ። አንድ ወፍራም ኮሎኔል ወገቡን በሁለት እጆቹ ይዞና እግሮቹን አንፈራጦ ቆምዋል። ሄደው ሰላምታ ሰጡት።

‹‹ከመጣችሁ ቆይታችሁዋል፣ እስከአሁን ምን ትሰራላችሁ? ትንኝ እንደሚፈልግ የወባ ማጥፊያ ሰራተኛ በየጥጉ የምታጎነብሱት ለምንድነው!" አለ በቁጣ።

‹‹ቤቱ ከውስጥ ተዘግትዋል። በሩንም ሆነ መስኮቱን ብናንኩዋኩዋ መልስ አጣን። በቀዳዳ ብንመለከት›› አለና ዞር ብሎ የመቶ አለቃውን አየው።

‹‹አ - ዎ በቀዳዳ ብንመለከት ሻለቃችን ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ አየነው›› አለ የመቶ አለቃው የደነገጠ ህጻን መስሎ።

ኮሎኔሉ አይኖቹን አፍጦና ጥርሶቹን ገጥሞ ሊያንቃቸው እየቃጣ፣

‹‹ታዲያ ምን ትጠብቃላችሁ!?›› አለ።

‹‹መስዋእትነቱን በማሳነስ የምናጠቃበትን ዘዴ በመመምረጥ ላይ ነን። ከበናቸዋል፤ የት እንዳይደርሱ ነው?›› xl መቶ አለቃው።

‹‹መከበባቸውን ሲያውቁ ሻለቃውን ቢገድሉትስ?›› አለ ኰሎኔሉ በርከክ ብሎ፡፡

‹‹ተቻኩለን በምንወስደው እርምጃ ምክንያት ተኩስ ቢከፈት ነው የሚገሉት፡፡ ሲገሉት ከፈለጉ እሱን ለማዳን የሚኖረን እድል በጣም ትንሽ፣ ነው፣ በእጃቸው እነጂ በእጃችን አይደለም፡፡›› አለ ሻምበሉ እጆቹን ደረቱ ላይ አያጣመረ፡፡

ኰሎኔሉ መለስ ብሎ ራቅ ብላ ወደ ቆችው መኪናው ሄደና፣ የሬድዮ መነጋገሪያውን ካነሣ፣ በኋላ ያሰበውን በመተው መልሶ ዘጋው፡፡ እንደገና ተመልሶ በፍጥነት እየተራመደ፣

‹‹ቤቱ ውስጥ ተቀምጥዋል አሳችሁኝ?› አለ

‹‹አዎ ሲያዩት ይችላሉ›› አለ ሻምበሉ ወደ ዛሲማ በር የሚያመራውን ኮሎኔል እየተከተለ፡፡

ኮሎሌሉ በጠባብዋ የበር ቀዳዳ ወደ ቤቱ ውስጥ ሲመለከት ቆየና ቀና አለ፡፡ እርምጃው እንዳይሰማ በጫማው ጫፍ እየተራመደ ወደ ነበረበት ተመለሰና፣

‹‹አየሁት፣ እራሱ ነው፡፡ የደንብ ልብሱን እንደለበሰ ነው ቁጭ ያለው፡፡ ምን ቢያስቡ ይሆን ይህን ያረጉት?›› አለ አይኖቹን ፊተለፊት ቡዝዝ አርጎ፡፡

‹‹እሱን አይተን በመቻኮል ወደ ቤቱ ለመግባት ስንሞክር አደጋ ሊጥሉብን አስበው ነው›› አለ የመቶ አለቃው ፈጠን ብሎ፡፡

‹‹ካገኙ ይውሰዱት በማለት ጥለውት ሄደው እንደሆነስ?›› አለ ኮሎኔሉ እያሰላሰለ፡፡

‹‹ቤቱኮ ከውስጥ ነው የተዘጋው፡፡ እነሱ ቤቱ ውስጥ ባይኖሩ፣ ሻለቃው ዝም ብሎ አይቀመጥም›› አለ ሻምበሉ ግራ በተጋባ አካሁዋን፡፡

ኮሎኔሉ ቶሎ ቶሎ እየተራመደ ወደ መኪናው ሄደና ሁኔታውን ለበላዮቹ በስልክ ገለጠ። ተጨማሪ ጦርና ብረት ለበስ ተሽከረከሪዎች እየተንጋጉ መጡና፣ አካባቢው በወታደር ተጥለቀለቀ። አዛገሮቹ ራቅ ብለው፣ ወታደሮቻቸው ወደ ቤቱ የሚገቡበትን ዘዴ ይወያዩ ጀመር። ያስጨነቃቸው ሻለቃቸውን ከነ ህይወቱ የማግኘቱ ነገር ብቻ አልነበረም። ለረጅም ጊዜ የጎን ውጋት የሆኑባቸውን የጣምራ ጦር ቡድን አባላት፣ ምናልባትም የቡድኑን መሪዎች እናገኛቸው ይሆናል ብለው ስለአመኑ፣ ቢቻል ከነ ህይወታቸው ካልሆነ ገድለው ሁሉንም ለማስቀረት ስለጉዋጉም ነበር።

ዝግጅቱና እቅዱ ሁሉ አበቃና በስፍራው የነበረው ጦር የጠመንጃውን አፈሙዝ ወደ ሃሊማ ቤት ደግኖ በደረቱ መሬት ያዘ። ሁለት ብረት ለበስ ተሽከሪካሪዎች ቀስ እያሉ ወደ ቤቱ ተጠጉ። አንደኛው ወደ መስኮቱ ተጠግቶ መትረየሱን ወደ ውስጥ አነጣጠረ። ሌላው በበሩ አቅጣጫ ቆመ።

የድምጽ ማጉያ የያዘ አንድ የመቶ አለቃ መስኮቱ አጠገብ ከቆመው ብረት ለበስ መኪና ውስጥ ብቅ በሎ፣

‹‹እዚህህ ቤት ውስጥ ያላችሁ ሰዎች ልታመልጡ በማትችሉበት ሁኔታ ተከባችሁዋልና እጆቻችሁን በሰላም ስጡ። እጁን በሰላም የሚሰጥ ሁሉ ምህረት ያገኛል›› አለና ጠበቀ። ምንም መልስ የለም።

‹‹አንድ ሰው ወጥቶ ያናግረኝ›› መልስ የለም። የመቶ አለቃው ሙከራው እንዳልሰራ ተረድቶ መኪናው ውስጥ ቁጭ ሲል፣ ከሁዋላው አንድ የሽጉጥ ተኩስ ተሰማ። የተኩስ ማስጀመሪያ ምልክት ነበር። መስኮቱ አጠገብ የቆመው ብረት ለበስ መኪና የመትረየስ ተኩሱን በመስኮቱ ወደ ውስጥ ያፈላው ጀመር። በበሩ ፊት ለፊት የቆመው

ብረት ለበስ መኪና ወደ ፊት ተንቀሣቀሰ፡፡ ጠመንጃዎቻቸውን የደገኑ ወታደሮች ግራና ቀኝ በአንድ ተራ ተሰልፈው መኪናውን ተከተሉ፡፡ መኪናው በሩን በአፍንጫው ገጨው፡፡ በሩ ከነመቃኑና ከነጉበኑ ተደርምሶ ወደ ውስጥ ወደቀ፡፡ ከመኪናው ግራና ቀኝ የተሰለፉት ወታደሮች ጥይት እእያርከፈከፉ ቤቱ ውስጥ ገቡ፡፡

ሁለት ወታደሮች በቀጥታ እየሮጡ ሄዱና ወንበር ላይ የተቀመጠውን ሻለቃ ግራና ቀኝ ይዘው ወደ ውጭ አወጡት፡፡ ውጭ ሆነው የሚጠባበቁት አለቆች እየተሽቀዳደሙ ተቀበሉዋቸው፡፡ ከሻለቃው ጀርባ አንድ ነገር መኖሩን ያረጋገጡት እየጎተቱ ከተኩሱ አካባቢ ትንሽ እልፍ ካሉ በሁዋላ ነው፡፡

‹‹ሻለቃውን ገድለው ከወንበር ጋር አስረውታል!›› አለ ሁኔታውን ከሁሉ ቀድሞ የተረዳ አንድ ወታደር፡፡

ተኩሱ ምንም አጸፋ ሲያጣ ቆመ፡፡ የቤቱ ውስጥና የአካባቢው በሚገባ ታሰሰ፡፡ ከውስጥም ሆነ በዙሪያው ህይወት ያለው ወይም የሞተ ፍጡር አለተገኘም፡፡ የግሊማ ቤት መስኮትና በሩ ተበርግደው ሲታይ፣ በወታደሮቹ መታሰል በአንድ አይኑ እያየ የሚስቅባቸው ይመስል ነበር፡፡

‹‹ደረት ኪሱ ውስጥ ወረቀት ይታየኛል!›› አለ ወፍራሙ ኮሎኔል ወንበር አዝሎ የተኛውን እሬሣ እየተመለከተ፡፡ አንድ ወታደር ወረቀቱን ከሬሣው ኪስ አውጥቶ ለኮሌኔሊ ሰጠው፡፡

‹‹የአባሎቻችንን ደም ገና በእጥፍ እንቀበላለን. . .›› ይላል ጽሁፉ፡፡

ስፍራው የነበሩት መኮንኖች ሰብሰብ ብለው ጥቂት ከተመካከሩ በሁዋላ፣ ቀደም ብሎ በወጣው እቅድ መሰረት ከዚያን ሰዓትና፣ ስፍራ ጀምሮ አሰሣው እንዲካሄድ ትእዛዝ ሰጡ፡፡

# ምዕራፍ ሃያ አምስት

በጊዜ የጀመረው አሰሳ ደገሃቡርን ያተራምሳታል፣ የተዘጉ ቤቶች በሰደፍና በርግጫ ይበረገዳሉ፣ እቃዎች ወደ ውጭ ይወረወራሉ፣ ተጠርጣሪ ሰዎች ህሊናቸውን እስኪስቱ እየተደበደቡ በመኪና ይጫናሉ። ህፃናት ይንጫጫሉ፣ እናቶች ዋይ ይላሉ፣ አባቶች ያቃስታሉ...።

እነ በሪሁን ይህን ተረድተው፣ አሰሳው እሉበት ከመድረሱ በፊት ከአካባቢው ለመራቅ ከተደበቁበት ወጡ።

‹‹እኔ እዚሁ ሆኜ የሚመጣውን ጠብቃሁ፣ እናንተ ለስራ የተሰማሩ ወታደሮች በመምሰል በተቻለ ፍጥነት ወደ አቡዋሬ መንገድ ተጠጉ። ሲመሽ በአካባቢው ያለው ቡድናችን መጥቶ ይቀበላችዋል። በደህና መድረሳችሁን ለማወቅና፣ እኔም ደህና መሆኔን ለመግለጥ ነገ የሬድዮ ጥሪ አረግላችሁዋለሁ›› አለ አሊሃሽ ሲሸኛቸው።

‹‹የዲዮ መገናኛውን በተለመደው ቦታ ደብቀው። አንተም ጠንቀቅ በል፣ በርህን ክፈትና ጠብቃቸው›› አለ በሪሁን ትጥረቁን እያስተካከለ።

‹‹ግድ የለህም፣ ሁሉም ቦታ ቦታውን ይዝዋል። አሰሳው ሳይቃረብ ሂዱ››

በሪሁን፣ አሰግድ፣ አኔቦና ሃሊማ የወታደር ልብሶቻቸውን ለብሰውና ጠመንጃዎቻቸውን አንግተው ወደ ዋናው ጎዳና ወጡ። በርይሁን ሀሊማን ለመጀመሪያ ጊዜ በወታደራዊ ትጥቅ ስላያት ፈገግ አለ። መሳሪያ አያያዝና ተኩስ በትንሹ ብትማርም፣ የወታደር ልብስ

ስትለብስ የመጀመሪያዋ ነው። መንገዱ ጭር ብልዋል፣ እልፍ ያሉት ሰፈሮች በአሳሹ ጦር ይተራመሳሉ። ጭር ባለው መንገድ ለይ መሳሪያዎቻቸውን የደገኑ ወታደሮች አለፍ አለፍ ብለው ቆመዋል።

እነበሪሁን በተን ሰብሰብ እያሉና አካባቢውን የሚቃኙ ወታደሮች እየመሰሉ ወደ አሰቡበት አቅጣጫ አመሩ። ምሽቱ ለአይን ያዝ አርግዋል፣ ከነበሩበት ራቅ እንዳሉ፣ ተከልሎ የቆመ አንድ ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ሃይለኛ መብራቱን አበራባቸው። የመደንገጥ ምልክት ሳያሳዩ፣ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

‹‹ጆግሶ!፣ ጆግሶ፣ (ቁም፣ ቁም!) ››አለ አንድ ድምጽ ከመኪናው ውስጥ፣

‹‹አሳሾች ነን!›› አለ በሪሁን ድምጹን ከፍ አርጎ

‹‹በያላችሁበት ቁሙ! እንዳትነቃነቁ!››። እነ በሪሁን እንደታዘዙት እንደቆሙ፣ ከግራና ከቀኝ ወታደሮች ሲከቡዋቸው አዩ። በሪሁን ‹‹ኦጽ›› ብሎ መሬት ሲወድቅ፣ ሌሎቹም እንደሱ አረጉ። በዙሪያቸው ጥይት ይፈላ ጀመር። እነሱም አጸፋ እየሰጡ ሲንከባለሉ፡ መኪናው መትረየሱን እየተኮሰ ተጠጋቸው። አሰግድና እኔቦ በምቦቻቸውን ጨብጠው እንደ እባብ በደረታቸው እየተሳቡ ወደ መኪናው ሄዱ። በሪሁን ‹‹ተመለሱ! ፣ ተመለሱ!›› እያለ ሲጮህ፣ የቦምብ ፍንዳታ ተሰማና፡ መኪናው እንደ ደመራ ይነድ ጀመር። ወታደሮቹ አሰግድና እኔቦ ላይ ጥይታቸውን አዘነቡባቸው። በርይሁንና ሃሊማ፣ የተኩስ ኢላማቸውን በነ አሰግድ ዙሪያ በማረግ የሚቀርቡዋቸውን ወታደሮች እየተከላከሉ ወደዚያው ሮጡ። ከነ ሰግድ ጋር ተቀላቅለው ትንሽ እንደተታኮሱ፣ ሃሊማ ድምጽዋን ከፍ አርጋ፣

‹‹ አሰግድ ተመታ!›› አለች። ተኩሱ ይበልጥ ተፋፋመ፣ የጠላት

ወታደሮች አስግድን ለመማረክ ይሽቀዳደሙ ጀመር። እነ በርይሁን መሳሪያዎቻቸው እስኪግሉ ቢተኩሱም ሊያስጥሉት አልቻሉም።

ከፊታቸው ያለውን መሬት የሚያርሰው ጥይት እንኳዋን ወደ ፊት ሊያራምዳቸው ፣ አይኖቻቸውንም ሊያስገልጥ አለ። የሚከባቸው ጦር ብዛትም እየጨመረ መጣ። ይህን የተመለከተው አኔቦ ከደረቱ ቀና አለና እያከታተለ ሁለት ቦምቦች ጣለ። አካባቢው በአሸወዋ አቡዋራ ሲጋረድና የጠላት ወታደሮች የተኩስ ሲዘበራረቅ፡-

‹‹በስተግራ በኩል ወደ ሁዋላ!›› አለ በሪሁን የሃሊማን ትከሻ ይዞ እየጎተተ፣ ከባዶ ጠመንጃዋ ጋር ትታገል ነበር። ከተኩሱ መሀል ወጥተው ትንሽ ከሮጡ ቡዋላ አንድ ሰዋራ ስፍራ ቆሙ።

‹‹ወሰዱት አይደል አስግድን?! ወይ ወንድሜ!፣ ወይ አሰግድ! አይ ሰው፣ ለህይቴ ሳሳሁና ትቼህ መጣሁ...›› አለ በሪሁን ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለና እንባ እየተናነቀው። ሀሊማ እንባዋን በሸሚዝዋ እጅጌ እየጠረገች ቁጭ አለች። አተነፋፈሳቸው እስኪስተካከል በዝምታ ተለጉመው ሰስቱም አረፍ አሉ።

"ማዛን ሚን ሰራል? ጠላቱ በቀላ ኢሱ ዳም በቀላል ናው ጡሩ..."አለ አኔቦ በዝምታው መሃል። በርይሁን ትኩር ብሎ አየውና ብድግ አለ። ሰበርባራውን መሬት እየመረጡ ቶሎቶሎ በመራመድ ላይ እያሉ፣

‹‹ሰዎቹ እርስ በርሳቸው ተላለቁ›› አለች ሃሊማ ከሁዋላ ወደ ሚሰማው ተኩስ ጆሮዋን አቅንታ። እነሱ ከተኩሱ መሃል ቢወጡም ዙሪያ ቀለበት የሰራው የጠላት ጦር እነሱ በማያውቁት ምክንያት እርስ በርሱ በመተጋተግ ላይ ነበር። ከአንድ ሰዓት ጉዞ በሁዋላ ጥቂት ለማረፍ አንድ ቁጥቋጦ ስር ቁጭ አሉ። ደካማው የጨረቃ ብርሀን በጭለማ ተሸነፈና ቅርብ ያለ ነገርን እንኳን ለማየት የማይቻል ሆነ።

‹‹ይቀበላችሁዋል የተባለው ቡድን የታል?፣ ይህን ያህል ርቀን ስንጉዋዝ ልናገኘው ይገባ ነበር››አለ በሪሁን በሰፊው ተንፍሶ።

‹‹ገና ወደ አካባቢው አልመጣ ይሆናል ፤ ወይም ራቅ ብሎ ይሆናል የሚጠብቁን፣ ምናልባትም ሌላ ሁኔታ አጋጥሞት ቀርቶ ይሆናል›› አለች ሃሊማ በድካም የዛሉ እግሮችዋን እጥፍ ዘርጋ እያረገች።

‹‹እንደሱ ከሆነማ፣ ከደፈጣ ተዋጊ ጦራችን ጋር ለመገናኘት የምናረገው ጥረት እጅግ አድካሚ ይሆናል››

‹‹ግድ የለም፣ እናገኛቸዋለን›› አለች ሃሊማ።

‹‹ አንቺ ኅበዝ ወታደር ኖ ፣ ኢንዳዚ ኢኔ አላወቃም ፤ በጣም ገረማ ኖ›› አለ አኔቦ ሃሊማን እያየ። ያለው ስለ አልገባት ወደ በሪሁን ዞር አለች። የተናገረውን ተረጎመላት።

‹‹በችግርና በጭንቅ ጊዜ ቀድሞ የሌለ ብርታትና ሃይል ይምጣል፣ እኔ እራሴም ገርሞኛል። ጠላት ከተማችንን ሊይዛት በተቃረበ ሰሞን ባለቤቴ ሴሲት መሳሪያውን ሲፈታና ሲገጥም እመለከት ነበር። በመጨረሻው እለት ህዝቡና ጦሩ የጠላትን ወረራ ሲከላከል፣ ባለቤቴ ከጎኔ እስከ ወደቀ ድረስ አብሬው ነበርኩ። የሱን መሞት ሳይ ራሴን መቆጣጠር አቅቶኝ እኔም ወደቅሁ"

በርይሁን ባስግድ መማረክ ምክንያት እጅግ ስላዘነ ማውራት አልፈለገም። እነ አኔቦ ዝም ቢሉት፣ ስቅስቅ ብሎ ቢያለቅስ፣ ብቻውን ቢሆን...ነበር ምርጫው፣ እየዩ ሲዳላ ነው እንደሚባለው ሆነበት እንጂ።

እንዲህ ባለው አስቸጋሪ ሁኔታና ጊዜ ውስጥ ሆነው ምን ማረግ እንደሚገባቸው በሚያሰላስሉበት ጊዜ ነው፣ ከሁዋላቸው የሰዎች እርምጃ የሰሙት። ብድግ ብለው ቢመለከቱ ተከበዋል፣ ምንም የማረግ

እድል ሰያገኙ ሰዎቹ ተረባረቡና ያዙዋቸው። የያዙዋቸው ሰዎች እጆቻቸውን እየጠመዘዙ የፍጥኝ አሰሩዋቸው፣ አይኖቻቸውንም በጨርቅ ሸብ አረጉዋቸው።

‹‹እንግዲህ ያለ ምንም መንፈራገጥ ወደ ምንወስዳችሁ ስፍራ መሄድ ነው›› አለ ከአሳሪዎቹ አንዱ። እንደ አይነስውር እየተመሩ ወደ ማያውቁት አቅጣጫ ተጉዋዙ።

‹‹ወይኔ በሪሁን! ለዚሁ ነው ከጉዋደኛዬ ተለይቼ ከሞት የሸሸሁት? አብሬው በወደቅሁ›› አለ በሃሳቡ፣ በደሊላ ተንከል አይኖቹን እንደጣው ለምሳን ለአንድ አፍታ እንዳች ተአምራዊ ሃይል እየተመኘ።

ትንሽ ከተጉዋዙ በሁዋላ ማራኪዎቻቸው አቆሙዋቸው፣

‹‹አይናቸውን ግለጥላቸው!›› አለ አንድ ድምጽ በትእዛዝ።

የታሰረው ጨርቅ ተፈታ። የደበዘዘ የባትሪ ብርሃን ይታል።

‹‹ኡስማን! (በሪሁን)፣ በጣም ይገርማል!፣ አናንተ ናችሁ እንዴ?፤ እጆቻቸውን ፍቱላቸው›› አለ የገጠር አደጋ ጣይ ቡድን መሪ፣ ሃሚድ ጣሂር ገፅ ባለ ድምጽ።

"አባሎቻችን ናቸው›› አለ በሪሁን፣ ሃሚድ እነ አኔቦን አይቶ ግራ መጋባቱን በመገንዘብ።

‹‹ከተወሰነው ሰዓት በጣም ዘገያችሁ። አለባበሳችሁ ደሞ እንዲህ እንደሚሆን አልተነገረንም። የጠላት ወታደር ነው የምትመስሉት። ሰዎቻችን ጠንቃቆች ባይሆኑ ኑሮ ትሞቱ ነበር። ›› አለ ሃሚድ አረማመዱን እያፈጠነ።

የሃሚድ አለባበስ እንደ ነበሪሁን አልነበረም። ቁምጣ ታጥቆ ከታች የወታደር ጫማ አርግዋል። ከላይ የለበሰው፣ እጀጉርድና አንገተ ክፍት አሮጌ ሹራብ ነው። ጥይት ሙሉ ጀበርናውን(ዝናሩን) ወገቡ ላይ ሸብ

አርጎና በርከት ያሉ ቦምቦች ጀበርናው ላይ አንጠልጥሎ ካደገ ጂሙ ጋር ሲታይ ያስፈራል።

የተከታዮች አለባበስ ግን፣ የተዘበራረቀ ነው። በባዶ እግራቸው ያሉ፣ ጫማ ያረገ፣ ሱሪ የለበሰ፣ ሽርጥ ያገለደሙ... ናቸው። ከጠላት የተማረኩ ጠመንጃዎች ይዘዋል።

"ከተማው ውስጥ የነበረው አሰሳ ከምንጊዜውም የከፋ ነበር። ሌላ የማምለጫ ዘዴ ስናጣ ጊዜ የወታደር ልብስ ለብሰንና ተመሳስለን ለመሹለክ ነበር ሃሳባችን፣ ምን ያረጋል?" አለ በሪሁን የአሰግድ በጠላት እጅ መግባት እያሳዘነው።

"ታዲያ፣ ጠላት አጋጠማችሁ?"

‹‹አው አጋጠመንና...ተኩስ አልሰማችሁም?"

"ላንድ አፍታ ሞቅ ብሎ የበረደ ተኩስ ሰምተናል፣ እናንተ ነበራችሁ እንዴ? እንኩዋን አላህ አተረፋችሁ! ከዚያ ያላነሰ ነገር ከኛም ይደርስባችሁ ነበር፣ የጠላት ወታደር እንደመሰላችሁን ብንተኩስባችሁ ኑሮ..."

እንዲህ ዲእየወሩ ተመለሱና ከተማው ዳር አለ ደጋፊቸው ጎጆ ገብተው አረፍ አሉ። ባለቤቱ ቤት ያፈራውን ሲያረግላቸው ይጣደፍ ጀመር።

‹‹አንቺ ደሞ ከየት መጣሽ? ምን ታረጊያለሽ?›› አለ ሃሚድ ሀሊማን እያየ። የብረት ባርኔጣዋን ስታወልቅ ነው የወቃት።

‹‹አንተ የምታረገውን አረጋለሁ›› ፈገግ አለች።

"አሊሃሽና ዩኑስ(ሰግድ) ደህና ናቸው?" አለ ሃሚድ በርይሁንን እያየ።

‹‹አሊሃሽ ደህና ነው›› አለ በሰፊው ተንፍሶ።

‹‹የኑስስ?››

‹‹ሞተ››

‹‹መቼ እባክህ ፣ ከናንተ ጋር እንደሚመጣ ነበር የተነገረኝ››

‹‹አ-ዎ ፣ ከኛ ጋር ጉዞ ጀምሮ ነበር። መንገድ ላይ የጠላት ጦር ከበበንና ገደለው›› ከንፈሩን በቁጭት ነከሰ።

‹‹ዛሬ?››

‹‹አ-ዎ፣ ማምሻውን››

በሪሁንና ሃሊማ ያጋጠማቸውን ሁኔታና የአሰግድን አሙዋሙዋት አስረዱት።

‹‹በጣም ያሳዝናል፣ ግን መሞቱን በምን አረጋገጣችሁ? ቆስሎም ሊተርፍ ይችላልኮ›› አለ ሃሚድ።

‹‹አሄሄ? ፣ ያ ሁሉ ጥይት ዘንቦበት የሚተርፍ አይመስለኝም" አለ በሪሁን አይኖቹን ቡዝዝ አርጎ።

‹‹እናንተ እንዴት ተረፋችሁ? ከጥይት መሃል አይደለም የወጣችሁት?››

‹‹ባክህ ቆስሎም ቢማርኩት ይገሉታል...›› አለች ሃሊማ፣ እዝን ብላ።

‹‹ምን ይደረገግ?›› አለ ሃሚድ አቀርቅሮ። ለጥቂት ጊዜ ሁሉም ዝም አሉ።

‹‹የወገን ጦር ወዲህ በመገስገስ ላይ ነው ይባላል›› አለ ሃሚድ ካቀረቀረበት ቀና ብሎ።

‹‹አዎ፣ ጠላት አቅም አጥትዋል። በየቀኑ ከየግንባሩ የሚመጣው ቁስለኛ ብዙ ነው። ከግንበር ሸሻችሁ እየተባሉ ብዙ መካንኖችና ወታደሮች በየጊዜው ይረሸናሉ። የወገን የጦር አይሮኘላኖች ፋታ

ነስተዋቸዋል፡፡ ከሁኔታው እንደ ተረደሁት፣ የጠላት ጦር የመፈርጠጥ ዝግጅት በማረግ ላይ ነው››አለ በሪሁን

‹‹የማጥቂያ ጊዜያችን ከእንግዲህ ነው ፡፡ በየአሸዋው ቀልጠው ይቀሩዋታል እንጂ አያመልጡንም›› አለች ሀሊማ ታፋዋን በጥፊ እየመታች፡፡

ከዚያም በሚቀጥለው ቀን ስለ ሚፈጽሙት ስራ ከተወያዩና ጥቂት እረፍት ካረጉ በሁዋላ፣ ሌሊቱን ተጉዘው ወደ ጅጅጋ በሚወስደው መንገድ ላይ ካደፈጠው ቡደናቸው ጋር ተቀላቀሉ፡፡ ረፋዱ ላይ የሬድዮ መልዕክት ሰራተኛው ከአሊሃሽ የተላለፈ መልእክት የያዘች አንዲት ወረቀት አምጥቶ ለሃሚድ ሰጠው፡፡ በሪሁን ፣ ሃሊማና አኔቦ መልእክቱን ለማወቅ በመጉዋጉዋት ወደ ሃሚድ ጠጋ አሉ፡፡ ሃሚድ ንበቡን ሳይጨርስ ቀና ብሎ እነ በሪሁንን በፈገግታ አስያቸውና፡-

‹‹ዩነስ አልሞተም›› አለ፡፡

‹‹እ? እ? ምን አልክ? ›› አሉ ሃሊማና በሪሁን ባንድ ላይ፡፡

‹‹ አልሞተም፣ ‹ቆስሎ ተማርከዋል› ነው የሚለው አሊሃሽ›› አለ ሃሚድ በእጁ የያዘውን ወረቀት እንደ ማራገብ እያለ፡፡ አኔቦ በበሪሁንና በሃሊማ ሁኔታ ግራ ተጋባ፡፡ የሚያስደስት ወይም የሚያስደነግጥ ነገር እንደ ሰሙ ተረድቶ ነገሩ እንዲገልጡለት በአይኖቹ ይማጠናቸው ጀመር፡፡ በሪሁን ሁኔታውን ሲነግረው፡፡ ራሱን ነቀነቀና፣

‹‹ ሚኒም ሊዩናት ኤሌም፣ ኢንደ ሞታ ቆጠራል፡፡ ኢናሱ ከነፍስ ያዛ ሆና ኢንኩዋን ገዲላል›› አለ፡፡

‹‹ግድ የለም እንኳን በህይወት መኖሩ ተረጋገጠ፡፡ ከእንግዲህ አይገሉትም!›› አለ በሪሁን እጆቹን ጨብጦ፡፡

‹‹. . .የከተማው አሰሳ ብዙ ሰዎችን ካሰቃየና እስር ቤት ካጎረ

በሁዋላ አብቅተዋል፡፡ እኔና ሌሎቹ አጋሮቻችን እስከ አሁን ደህና ነን፡፡ በነገው እለት ከፍተኛ ኮንቮይ ከቀብሪደሃር ይመጣልና አስቡበት› ይላል መልእክቱ›› አለ ሃሚድ የአሊሃሽን ደብዳቤ የመጨረሻ መስመር እያነበበ፡፡

ጥቂት ከተመካከሩ በሁዋላ፣ አሊሃሽ የአሰግድን ሁኔታ እየተከታተለ በየጊዜው እንዲገልጥላቸው መልእክት አስተላለፉ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ከፍተኛ ኮንቮይ ይመጣል ስለተባለ፣ ቀደም ብለው ያወጡትን እቅድ ለጊዜው በመተው፣ በኮንቮዩ ላይ አደጋ ወደ መጣሉ አሳብ አዘነበሉ፡፡ በዚሁ መሰረት አደጋ ጣዩ ቡድን በሁለት ተከፈለና፣ አንዱ በሃሚድ፣ ሁለተኛው ደሞ በበሪሁን እንዲመራ ተወሰነ፡፡

ሃሚድ ጣሂር የራሱን ቡድን ይዞ ሌሊቱን በመገስገስ ቀብሪደሃር መንገድ ላይ አድፍጦ አደጋ እንዲጥል፣ በሪሁን ደሞ ቡድኑን ወደ ከተማው አስጠግቶ፣ የአሰግድን ታእንዲከታተልናከአሊሃሽ በሚደርሰው መረጃ መሰረት አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን እርምጃ እንዲወስድ ተወሰነ፡፡

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

አሰግድ ቆስሎ በጠላት ጦር በተማረከ ጊዜ የቆሰለው ትከሻው ላይ ነበር:: ማራኪዎቹ ጉዳቱ ከባድ ስለ አልመሰላቸው መጠነኛ ህክምና ርገውለት ዋናው ጦር ሰፈር ውስጥ ወደ ሚገኘው እስር ቤት ተወሰደ:: ከሱ የሚፈልጉት ጠቃሚ መረጃ ስላለ ነው እንዲህ የደከሙለት:: ትከሻው ላይ ያለው ቁስል ከአንገቱ ጀምሮ በፋሻ ተጠቅሎለት፣ ብረት ለበስ መኪና ውስጥ ሆኖና ሁለት ካሚዮኖች ሙሉ ወታደሮች አጅበውት ነው እስር ቤት የደረሰው::

ሁለት እጆቹ በካቴና እንደ ታሰሩ አንዲት ጠባብ እስር ቤት ውስጥ አስገብተው ዘጉበት:: ክፍልዋ ስትዘጋ ፍጹም ጭለማ ዋጠው:: ቆሞ አይኖቹን ጭፍን ክፍት ሲያረግ ቆየ:: ዐይኖቹ ጭለማውን ሲለምዱለት አንዳንድ ነገሮች ድብዝዝ ብለው ይታዩት ጀመር:: ዞር ሲል እግሮቹን ኩርትም አድርጎ የተቀመጠ አንድ ሰውዬ አየ:: የሰውዬው እጆች እንደሱው በካቴና ታስረዋል:: ትከሻው ላይ ያሉት የማእረግ ማረጊያ ጥብጣቦች የተቀረጡበት ሙሉ የወታደር ልብስ ለብሰዋል::

‹‹ቁጭ በል፤ የሞት ጉዋደኛዬ እንኩዋን ደህና መጣህ›› አለ ሰውዬው አንጋጦ እያየው:: አሰግድ እልፍ ብሎ ተቀመጠና ሰውዬውን ትኩር ብሎ አየው::

‹‹ከየት ነህ አንተ ደሞ? ›› አለ ሰውዬው አገጩን ጉልበቱ ላይ

አስደግፎ።

«ክዚሁ»

«የትነው የቆሰልከው?»

«እዚሁ»

ሰውዬው ትንሽ ቆጣ ብሎ፣

«ወንድሜ እኔ አደለሁም ሞት የፈረድኩብህ። ምናልባት እንደኔው የሞት መንገደኛ ከሆንክ ላጫውትህ ብዬ ነው። ሰዓቱ ደርሶ ሞት እስኪረከበን ከአሁኑ ለምን እንጨነቃለን ? በፈገግታ እንጠብቀው ብዬ ነው...» አለና ህይወት ሊለበት ፈገግታ እያሳየው።

አሰግድ ሊያናግረው እንዳልፈለገ ሲረዳ፣ ጣራውን ይመለከት ጀመር። አሰግድ ሲያየው ቆየና፣

«እ - እርስዎ ከየት ነው የመጡት» አለ።

«እ? እኔን ነው? አዎ እኔ እዚሁ ነበርኩ »

«ለምን ታሰሩ?»

«ያዘዝከው ኮንቮይ አደጋ ደርሶበታል፣ አውቀህ ነው ያን ያረከው ተብዬ »

«የምን አደጋ?»

«ሰሞኑን ጥይትና ስንቅ የጫኑ ብዙ ተሽከርካሪዎች ከቀብሪደሐር ሲመጡ መንገድ ላይ አደጋ ደረሰባቸው። ካደጋ ጣዮቹ ጋር ተሻርከህ ነው ይህ እንዲሆን ያረግከው አሉኝ»

« በዚህ ጉዳይ ነው የታሠሩት?»

«አ-ዎ በዚህ ጉዳይ ነው። አንበሣ ጠቦት በነጠቀ ቁጥር የሚቀጣው እረኛ ነው። አለቆቻችን ባጠፉና በተሣሣቱ ቁጥር፣ ወይም የጠላት ጦር አይሎ ባጠቃን ቁጥር፣ የምንቀጣው እኛ ነን። የስህተታቸው እድፍ በኛ

ደም ይታጠብ ይመስል፣ በቀላቸውን በእኛ ላይ ተወጥተው ብእጥፊያቸ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ ወስደናል › በማለት ለበላዮቻቸው ሪፖርት ያቀርባሉ። በኛ ጦርና ህብረተሰብ ውስጥ ያለው አሠራር ይህን ይመስላል። ፍርዱንና በቀሉን ለታሪክ መተው ነው›› አለና ከንፈሮቹን ገጥሞ ጥርሱን አኘከ።

‹‹እርስዎ በሀሰተኞች ተንኮል ከጠፉ በሁዋላ በታሪክ ‹እደ እከሌ ሃቀኛ ነበር በግፍ ነው የጠፋው › ቢባልልዎ ምን ይጠቅምዎታል?››

‹‹እውነትህን ነው ከግለሰብ ጥቅም አንጻር ሲታይ ፋይዳ የለውም። ለዚህም ነው በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ህሊናቸውንና ወኔያቸውን ለጊዜያዊ ጥቅም ሸጠው ሻከራ ንፋስ በነፈስ ቁጥር አቅጣጫቸውን የሚለዋውጡት። ጠንከር ያለ ክንድ ሲጨብጣቸው ቀደም ብለው ያመኑበትን ፋይዳ ለመካድ አያመነቱም። እንዲህ ያሉ ሰዎች እውነትን ሸጠው ጊዜያዊ ጥቅም ያገኙ ይሆናል፤ ዋይታቸው ግን እሩቅ አይደለም። ይጋለጣሉ፣ በታሪክም በታሪክም በክፉ ስራቸው ሲታወሱ ይኖራሉ››

‹‹ታሪክ ጸሀፊዎችም ቢሆኑ በራሣቸው አመለካከትና በጥቀማቸው አንጻር ነው የሚጽፉት። ማለቴ፣ እነሱ በደለኞች የሚሉዋቸውና አንደ ወንጀለኞች የሚቆጥሩዋቸው ሰዎች ሃቀኞች ፤ እነሱ እውነተኞች የሚሉዋቸው ፣ ግፈኞችና የግል ጥቅማቸውን አሣዳጆች ሊሆኑ ይችላሉ››

‹‹አይ አንተ ልጅ፤ ታሪክ ጸሀፊዎች እኮ እራሣቸው ታሪክ ሰሪዎች አይደሉም። ታሪክ ሰሪው ሰራተኛው ህዝቡ ነው። እውነተኛ ታሪክን የማንም ብእር ቀብሮ ሊያስቀረው አይችልም። እውነትን ማንም አያጠፋት። ታሪክ ሰሪው ህዝብ ወቅቱን ጠብቆ እውነቱን ያወጣዋል። አሃሃሃ ››

በዚህ ሁኔታ ሲወያዩ ሰውዬው እንዳለው ሣይታወቃቸው ብዙ

ሰዓታት አለፉ፤ ምሽቱም እየገፋ ሄደ፡፡ አሰግድና ሰውዬው ውይይታቸውን አቋርጠው በየራሳቸው አሳብ ሲንሳፈፉ፣ ከውጭ የሰዎች እርምጃ ሰሙ፡፡ የአሰግድ ልብ በአፉ ሊወጣ የደረሰ መሰለ፡፡ እተነፋፈስ ፈጠነ፡፡ ከውጭ በሩ አካባቢ ሹክሹክታ ተሰማና ዝምታ ሆነ፡፡ ከአሰግድ ጋር ያለው ሰውዬ ድምጹን ከፍ አድርጎ፦

‹‹ግቡና የምታረጉትን እርጉ እንጂ! ምን ታንሾክሹካላችሁ ? እኛ ማንፈራ እናንተ ፈራችሁ እንዴ?!›› አለ ፡፡ በሩ ተከፈተ፡፡ አንድ ሰውዬ በሩ ላይ ቆሞ የያዘውን የባትሪ ብርሃን ወደ ውስጥ አበራና ‹‹ሀበሽ ካሌ! (አበሻ ና!)›› አለ ድምጹን ዝቅ አርጎ፡፡

አሰግድ እንደ ነጠረ ኳስ ብድግ አለና ወደ ተጠራበት ሄደ፡፡ ሃይለኛው የባትሪ ብርሃን ዐይኖቹን እንደልቡ አላስገልጥ አለው፡፡ ምንም ማያይ ዐይኖቹ በጨርቅ ታስረው፣ ግራና ቀኝ ክንዶቹ ተይዘው ተወሰደ፡፡ ከጥቂት እርምጃዎች በሁዋላ በር ተከፈተና አንድ ቤት ውስጥ ገብቶ እንዲቆም ተደረገ፡፡

‹‹ግለጠው!›› አለ አንድ ሰላላ ድምጽ፡፡ የአሰግድን አይኖች የሸፈናቸው ጨርቅ ተፈታ፡፡

‹‹ጠጋ በል ወዲህ!›› አለ ያው ድምጽ፡፡ ከሁዋላው የቆሙት ወታደሮች እየገፉ ወደ ፊት አስጠጉት፡፡ ዐይኖቹን ጭፍን ክፍት ሲያረጋቸው ቆየና ከፊት ለፊቱ ጠረጴዛውን ተደግፎ የቆመ አንድ ከነፈረ ለምጣም ሻምባል አየ፡፡ ከሻምበሉ ግራና ቀኝ እልፍ ብለው ዳለቻ ቱታዎች የለበሱ ሁለት ሰዎች ቆመዋል፡፡ በስተግራ ያለው የኤሌክትሪክና የቃጫ ገመድ ፣ በስተቀኝ ያለው ደሞ አኮርባጅና ኳስ የሚመስል ትንሽ ነገር ይዘዋል፡፡

ሻምበሉ ለምጣም ከንፈሩን እየነካከሰና ጠረጴዛውን በቡጢ

እየመታ፡-

‹‹እውነተኛውን ነገር ግለጥልን ብንልህ እምቢ አልክ አይደል? እስከ አሁን ቁስለኛ ነህ ብለን አዘነንልህል። ከእንግዲህ ስጋህን ነው የምንዘለዝለው›› አለና ጮኸ።

አሰግድ ፈገግ ብሎ ሻምበሉን ፊት ለፊት እያየ፡-

‹‹በየጊዜው የነገርኩዋችሁ ሁሉ ትክክለኛ ነው። ከዚያ የተለየ ነገር የለኝም! ስጋዬን የመዘልዘል ፍላጎት ካላችሁ ግን ቀጥሉ›› አለ።

‹‹ጦራችሁ ወደኛ አስርጎ ያስገባችሁ ሰዎች በትክክል ስንት ትሆናላችሁ?›› አለ ከሻምበሉ በስተቀኝ የቆመው ሰውዬ በያዘው አኮርባጅ የገዛ ታፋውን መታ መታ እያረገ።

‹‹አስርጋችሁ የምትልኩት እናንተ ናችሁ እንጂ የኛ ጦር አይደለም። በመስፋፋት ምኞት ሰክራችሁ፣ ሌላውንም አስክራችሁ የሰው መሬት ለመያዝ፣ የሌላውን ነጻነትና ህልውና ለመድፈር የምትሰርጉትና የምታሰርጉት እናንተ ናችሁ። እኛ መሬታችንን ላለማስወሰድ የምንዋጋ ተከላካዮች እንጂ ሰራጊዎች አደለንም››

ሻምበሉ ፈገግ አለና፣

‹‹ለዚህ ነው እኛም በመደበኛ ጦር ምርኮኛነት የምንንከባከብህ። ትክክለኛውን ነገር ብትገልጥልን ደሞ ከዚህ የተሻለ ክብካቤ ወደ ሚደረግልህ ቦታ ትዛወራለህ›› አለ እያሾፈ።

‹‹ነገርኩህ፣ እኛ ወደዚህ በመገስገስ ላይ የለው ነጻ አውጪ ጦራችን አካል ነን። በሙቶ የሚቆጠሩ ነጻነትና አገር ወዳድ የአካባቢው ነዋሪዎች ጎናችን አሰልፈናል። የተግባራችንን ምንነት በካባቢያችሁ በምናረገው እንቅስቃሴ የተረዳችሁት ስለሆነ፣ ልገልጽላችሁ አልፈልግም። አልገባችሁ እንደሆን ወደ ፊት ይበልጥ ትረዱታላችሁ። ትክክለኛው

ሁኔታ ይህ ነው»

ሻምበሉ በእስግድ ንግግር ስለተናደደ በጥፊ መታው፣ ሲንገዳገድ በስተቀኝ የቆመው ሰውዬ በእኮርባጅ ጀርባው ላይ ደገመው::

«ውሰዱት! ይሄ ሁሉ ለአንድ ወንበዴ የማይገባ ክብር ነው!» አለ ሻምበሉ ጮሆ:: እስግድን ያጀቡት ወታደሮች እየገፋፉት ወስደው ክፍሉ ውስጥ ወረወሩት:: በሩ ከውጭ ተቆልፎበት ጥቂት እንደቆየ ቀና አለና አዳመጠ:: ክፈሉ ውስጥ ድምጽ የለም::

«ሌላ ክፍል ውስጥ ነው እንዴ ያስገቡኝ?» አለ ለራሱ:: ቁጭ አለና ጥቁሩ ጥለማ ላይ አፍጦ:

«አንተ ሰውዬ፣ ተኝ እንዴ?» አለ ቀደም ብሎ ክፍሉ ውስጥ አብሮት የነበረውን ሰውዬ በመፈለግ:: መልስ አጣ:: በመቀመጫው እየተንፏቀቀ በእግሮቹ አካባቢውን ዳሰሰና ጠባብዋ ክፍል ውስጥ ከሱ ሌላ ህይወት ያለው ፍጡር እንደሌለ አረጋገጠ::

ቀደም ብሎ ከሱ ጋር የነበረው ሰውዬ ይወሰድ፣ ወይም እሱ ሌላ ክፍል ውስጥ ይግባ መለየት አቃተው:: ያም ሆነ ይህ ከጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ አንዳች ነገር እንደሚደርስበት እርግጠኛ ሆንዋል::

ከውጭ የመኪናዎች እንቅስቃሴ ይሰማል:: በጣም ራቅ ብሎ ደሞ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጅራፍ የሚንጣጣ፣ አንዳንዴ ደሞ እንደሚቆላ ማሽላ የሚንጣጣ የጥይት ድምጽ ይሰማዋል::

በደንብ ሣይድን በፋሻ ብቻ የተጠቀለለው ቁስሉ እየቆጠቆጠውና ወበቁ እየቀቀለው፣ ከውጭ የሰዎች እርምጃ በሰማ ቁጥር ካሁን አሁን አውጥተው ገደሉኝ እያለ ሲጨነቅ አደረ::

በማግስቱ ሌላ ክፍል ወሰዱት:: ክፍሉ ሰፋ ያለ ቢሆንም በእስረኞች ብዛት ተጨናንቅዋል:: የላቡ፣ የሽንቱ፣ የቁስሉ...ሽታ ክፍሉን የመከራ

ዋሻ አስመስሎታል። ያመጡት ዘቦች እንደ ምንም ገፋፍተው ካስገቡት በሁዋላ በሩን ከውጭ ቆለፉት። የተዘጋውን በር ከውስጥ ተደግፎ እንደቆመ እስረኞቹን አያቸው። አብዛኛናዋቹ ፋሻ የጠመጠሙ፣ ልብሶቻቸው ደም የደረቀበቸው ፣ ፊቶቻቸውና አይኖቻቸው ያበጡባቸው፣ የመረቀዙ እግሮቻቸውን እግድግዳ ላይ ሰቅለው የሚያቃስቱ...ናቸው።

‹‹ና- እንደምን ተጋፋና እዚህ ቁጭ በል!›› አለ አንድ ጺማም እስረኛ አሰግድን እያየ። ሌሎቹ እስረኞች እልፍ እያሉ ቦታ ለቀቁለት።

‹‹ከየት ነህ አንተ ደሞ ?›› አለ ጺማሙ እስረኛ በካቴና በታሰሩ እጆቹ ጺሙን እየቋዋጨ።

‹‹ከዚሁ ነው›› አለ በአፉ የሞላውን ምራቅ የሚተፋበት ቦታ እየፈለገ።

‹‹ከየት?፣ ከቀበሪደሃር ነህ?›› አለ ግራ አይኖቹ በእብጠት የተዘጉበት ሌላ እስረኛ።

‹‹አደለም፣ ከሌላ ቦታ ነው፣ እናንተ ከዚያ ናችሁ?›› አለ አሰግድ በዙሪያው ያሉትን እያየ።

‹‹እዚህ ካለነው ግማሽ የምንሆነው ከዚያ ነን›› አለ ጺማሙ እስረኛ በሰፊው ተንፍሶ።

‹‹ምን አረጋችሁ ብለው ነው ያሰሩዋችሁ?››

‹‹ለምን ህይወታችሁ ተረፈ ብለው ›› አለ አይኑ አባጣው እስረኛ ጥርሶቹን ገጥሞ።

‹‹ወይኔ ደሃዋ እናቴ፣ ልጆቼ፣ ሚስቴ›› ይላል ሌላ እሰስረኛ።

‹‹ለነሱ ሰፊ መሬት ፍለጋ መጥተህ ነው ፣ የእሣት እራት የሆንከው...›› አለ ሌላው።

ቀኑን በዚህ ሁኔታ አሣልፈው፣ ጸሀይ ጠልቃ ቸለማ በጥቁር ብርድ ልብሱ አካባቢውን ሲያለብስ፣ እስረኛው ሁሉ በጭንቀት ያቃስት ጀመር። እያንዳንዱ ሰው የራሱን ልብ ምት የሚያዳምጥ መሰለ። በዚህ ጸጥታ መሃል አንድ መኪና መጥቶ እስር ቤቱ ፊት ለፊት ቆመና ሞተሩን አጠፋ።

አሰግድ ጎን የተቀመጠ አንድ እስረኛ ሙትት ባለ ድምጽ፣

‹‹ሊወስዱን መጡ?›› አለ

‹‹የት ነው የሚወስዱን?›› አለ አሰግድ እሱም ድምፁን ዝቅ አርጎ። አፉን ደም ደም አለው፣ መላ ሰውነቱ ጋለ። በጀርባው የሚወርደው ትኩስ ላብ የበረዶ ውሀ ሆነበት።

‹‹ሊገድሉን ነው፤ ትናንትም በዚህ ሰዓት መጥተው ነው ብዙ ሰዎች የወሰዱት›› ከውጭ ሰዎች በችኮላ ሲራመዱ፣ በትእዛዝና በጭቅጭቅ ሲነታረኩ ይሰማ ጀመር። ሞት ከውጭ ጉድጉድ ሲስልና፣ ካራውን ሲስል፣ እስረኞች ከውስጥ ሲያቃስቱ ሰዓታት አለፉ።

እኩለ ሌሊት ሲቃረብ የእስር ቤቱ በር ተከፈተ። ሁለት የእጅ ባትሪዎች ሃይለኛ ብርሃናቸውን ወደ ውስጥ ሰደዱ። ሁለት እስረኞች ስማቸው ሲጠራ ብድግ እያሉ ወጡ። ሶስተኛው በድነጋጤ መንቀሳቀስም፣ መናገርም ስለ አቃተው ወታደሮች ጎትተው አወጡት። በአራተኛነት አሰግድ ተጠራ። ብድግ ብሎ በሩ ላይ ሲደርስ ሁለት ሰዎች ተቀበሉና አይኖቹን በጨርቅ አሰሩዋቸው። አምስተኛ እስረኛ ተጠራና አነስተኛ ካሚዮን ላይ ጫኑዋቸው። ካሚዮኑ ላይ ከወጡት እስረኞች አንዳንዶቹ፣ ‹‹አሸሃዱ አላህ፣ አሸሃዱ አላህ...›› እያሉ ሲያቃስቱ፣ አንገት አንገታቸውን በካራቴ ስለተመቱ ጸጥ አሉ።

መኪናይቱ ተንቀሳቅሣ በመካከለኛ ፍጥነት በረረች።ጥቂት

ከተጉዋዘች በሁዋላ ምቹውን መንገድ ትታ ወጣ ገባ ወደ ሆነው ገባችና፣ እንደ መቆምም እንደ መሄድም እያለች ስታመነታ፣ ከአካባቢው የእሩምታ ተኩስ ተሰማ፡፡ አስግድ ፈጠን አለና መኪናይቱ ወለል ላይ በደረቱ ተኛ፡፡ መኪናይቱ ቆመች፡፡ የእስረኞቹ አጃቢ ወታደሮች እየዘለሉ ወረዱ፡፡ ተኩሱ እየበዛና እየቀረበ መጣ፡፡ ወታደሮቹ አድፍጦ ከቆያቸው ያልታወቀ ሃይል ጋር ለሩብ ሰአት ያህል ሲታኮሱ ቆይተው ካሚዩኒቱንና እስረኞቹን እየተው ሸሹ፡፡

በተኩሱ መሀል ያልታወቁ ሰዎች መኪናይቱ ላይ እየወጡ እስረኖቹን አወረዱዋቸው፣ አስግድን ከተሸከሙት ሁለት ሰዎች አንዱ :-

‹‹አይዞህ አስግድ ፣ እኛ ነን›› አለው፣ የበሪሁን ድምጽ ነበር፡፡

# ምዕራፍ ሃያ ሰባት

አሰግድ ከሞት መንጋጋ ተነጥቆ እነ በሪሁን እጅ ከገባ በሁዋላ ለጥቂት ቀናት በድብቅ ሲታከም ቆይቶ አገገመ፡፡ አደጋ ጣይ ቡድኑ በየጊዜው ከጠላት የሚሰነዘርበትን ጥቃት ሲቋቋቋቋምና ሲያጠቃ ቆየ፡፡ በነዚሀ ጊዜያት በርከት ያሉ ድሎች የመቀዳጃቱን ያህል፣ ከባድ መስዋእትነቶችንም ከፍልዋል፡፡ በርከት ያሉ አባሎቹ ሀይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በገጠር ይካሄድ የነበረውን የደፈጣ ውጊያ የሚመራው ሃሚድ ጣሂር ቀብሪደሃር መንገድ ላይ ቡድኑ አደጋ በጣለበት እለት በፅኑ ቆስሎ ከሁለት ቀን በሁዋላ ሞተ፡፡

ቢሆንም የጠላት ጦር ባካባቢው የነበረውን የበላይነት እያጣ በመሄዱ፣ አደጋ ጣይ ቡድኑ ያለ ሃይሉን አሰባስቦ በአዲስ ስልት የማጥቃት ተግባሩን ለመጀመር ተዘጋጀ፡፡ ደገሃቡር ከተማና ባካባቢዋ ያሉት የጠላት ወታደሮች የተሰፋ መቁረጥና የመሸነፍ ስሜት ይታይባቸዋል፡፡ በመወናበድና በመታለል ጠላት ጎን ተሰልፈው ከነበሩት የአካባቢው ቤሄረሰብ አባላት አብዛኛዎቹ ሃቁን እየተረዱ የጠመንጃዎቻቸውን አፈሙዝ ወደጦሩ ማዞር ጀመሩ፡፡ ከጭፍጨፋውና ከአፈናው የተረፉት የከተማይቱ ነዋሪዎች በድል አድራጊነት ወደነሱ የሚገሰግሰውን የወገን ጦር ዜና እየተከታተሉ አይናቸውንና ልባቸውን ከፍተው ይጠብቁታል፡፡

አሊሃሽ ከተማው ውስጥ ሆኖ ለቡድኑ ለመስራት ከማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ፣ አብረውት ከሚሰሩት ሰዎች ጥቂቶቹን በማስከተል ከነበሪሁን ጋር ተቀላቀለ፡፡ የቡድኑም ተዋጊ ሃይል መከፋፈሉ ቀርቶ ባንድ ላይ እንዲጠቃለልና የሚሸሸውን የጠላት ጦር በከተማው ውስጥና በቀብረደሃር መንገድ ላይ እያደፈጠ እንዲያጠቃ ተወሰነ፡፡

በአዲሱ መዋቅር መሠረት በሪሁን የቡድኑ አስተባባሪና መሪ ሆኖ እንደገና ተመረጠ፡፡ በተጨማሪም ከከተማ ውጭ የሚካሄደውን የደፈጣ ውጊያ እሱና አሰግድ እንዲመሩ፣ አሊሃሽና አኔቦ ደግሞ አስር ራሳቸን ሆነው፣ ከተማው ውስጥ እየገባ አደጋ የሚጥለውን ቡድን እንደመሩ ተወሰነና እንቅስቃሴው ቀጠለ፡፡

‹‹በዛሬው ሌሊት የሚሸሽ የጠላት ጦር ስለአለ፣ ከፍተኛ ስራ ይጠብቀናል፡፡ አሊሃሽና አኔቦ ሰዎቻችሁን ይዛችሁ ጭለማን ተገን በማረግ ከተማው ውስጥ ትገቡና፣ የጠላት ጦር ለመንቀሳቀስ ዝግጅት በሚያረግበት ጊዜ ባመቻችሁ መንገድ አደጋ ትጥላላችሁ፡፡ እኛ ደግሞ መንገድ ላይ ጠብቀን ከናንተ የሚተርፈውን ጦር እናጠቃዋልን››አለ በሪሁን ሰዎቹን ሰብስቦ፡፡ አሰግድ ቀጠል አረገና፣

‹‹ጠላት ይዞ ከሚሸሸው ንብረት አባዛኛው ከአካባቢው የተዘረፈ ስለሆነ፣ ካስጣልን በሁዋላ ባግባቡ እንዲጠበቅ እናርግ›› አለ፡፡

ከዚያም በአሊሃሽ ቀዳሚነት አኔቦ፣ ሃሊማ፣ ቢዬሌው አብደላና ሌሎች እየተከታተሉ ወደምሽቱ ግዳጃቸው አመሩ፡፡

ቀደም ብላ የወጣችሁ ግማሽ ጨረቃ በከዋክብት ታጅባ ሰማያዊውን ሰማይ አስውባዋለች፡፡ ቁጥቋጦዎችን እያሰገደ የሚጋልበው ንፋስ አካባቢውን ያመሰቃቅለዋል፡፡

በራሁን የሚመራው ቡድን ምቹ የማጥቂያ ስፍራ ይዞ፣ የሚመጣለትን ሲሳይ ወይም ሞት ነቅቶ ይጠባበቃል። አኩሶ ሌሊትሲቃረብ ራቅ ካለ ስፍራ የመብረት ብልጭታ ታየ። ተከታትለው የሚጉዋዙ ተሽከርካሪዎች መብራት ነበር። አጎንብሶ እየሮጠ አስግድ ወደ ነበረበት ሄደና ፣

«የጠላት ኮንቮይ መጥቷል፣ ሙሉ በሙሉ በደፈጣ ክልሳችን እንደገባና የፈንጂ ድምጽ እንደተሰማ አንተ ከዚህ ሳትነቃነቅ መትረየስህን መተኮስ ነው። ምናልባት ጨበጣ የምንሰነዝር ከሆነ ምልክት አሳይሀለሁ፣ ያኔ ተኩስህን ታቆማለህ» አለው።

«ኮንቮይ በሌሊት አይንቀሳቀስም እያልክ ስከራከርህ ረታኸኝ» አለ አስግድ እየሳቀ።

«የምትሸሽ ነፍስ፣ ጊዜና አቅጣጫ አትመርጥም» ብሎ ትከሻውን መታመታ አረገውና ተመሳሳይ መመሪያ ለመስጠት ወደ ሌሎቹ ሄደ።

አስግድ የመትረየሱን ሰደፍ እትከሻው ላይ ደገነና ገመምተኛ ሰውነቱን እያመቻቸ፣ አንድ እጁን መትረየሱ ላይ ጣል አድርጎ፣ በሌላው እጁ አመልካች ጣት የመትረየሱን ምላጭ ይዞ፣ ፊት ለፊት ባለው ገላጣ መንገድ ላይ አነጣጠረ።

የመኪናዎች ድምጽ የንፋሱን ፉጨት እየጣሰ ከሩቅ እንደሚተም የንብ መንጋ«እምምም» ይላል። እየቀረቡ የሚመጡት መኪናዎች መብራት የጨረቃይቱን ብርሃን እያሸነፈ መጣ። የመጀመሪው መኪና አደጋ መጣው ክልል ውስጥ ገባ፣ ሁለተኛው ለጠቀ። ሌሎቹም እየተጣደፉ ተከታተሉ። መኪናዎቹ የሚያነሱት አቡዋራ ከመብራታቸው ጋር የአሸዋ ደመና ሠራ።

ብዙም ሳይቆይ መንገዱ ላይ የተቀበረው ፈንጂ በመኪና ተረጠና

ፈነዳ። ታላቅ ብልጭታ፣ የእሳት ነበልባል፣ ጥቁር ደመና...።
የመኪናውና የሰው አካል ፍንጣሪ ከላይ ዘነበ...። በሁዋለኞቹ
መኪናዎች ላይ ነበሩት ወታደሮች እየዘለሉ ሲወርዱ፣ ያደፈጠው ጦር
የእሩምታ ተኩስ ያዘንብባቸው ጀመር። ከነህይወቱ መሬት
የሚረግጠው ወታደር በጣም ጥቂት ነበር።

አደጋ ጣዩ ቡድን ከሞት የተረፈውን የጠላት ጦር እያባረረ
ሲመታ፣ ከሁዋላ ብዙ የጠላት ተሽከርካሪዎች እየመጡ ይቆሙ
ጀመር። በዚህ ጊዜ በሪሁን በድምጹም ፣ በእጁም ‹‹ ወደሁዋላ
አፈግፍጉ›› እያለ ለቡድኑ ትእዛዝ ሰጠ። ይህን ያረገው፣ ከሁዋላ
ከመጡት ተሽከርካሪዎች ላይ የሚወርዱት የጠላት ወታደሮች ብዙ
ስለሆነና ከራሱም ጦር ብዙ ሰዎች ስለ ወደቁበት ነው። ከሁዋላ
የደረሰው የጠላት ጦር የደረሰውን አደጋ በሩቅ አይቶና ተዘጋጅቶ ነበር።

በሪሁን የተረፉ አባላቱን ይዞ በአቋራጭ እየገሰሰ ከነ አሊሃሽ ጋር
እተቃጠሩበት ስፍራ ደረሰ። ከተማው ውስጥ አደጋ እንዲጥል
የተሰማራው የአሊሃሽ ቡድን ቀድሞ ጠበቃቸው። አባላቱ
ተዳክመዋል። አኔቦ ሃሊማና ቢዬሌው አብደላ ጎን ለጎን ተቀምጠው
ይተክዛሉ።

‹‹ውጤት እንዴት ነው? ፣ የታለ አሊሃሽ?›› አለ በሪሁን ወደ አኔቦ
ጠጋ ብሎ። ቢዮሌው አብደላ ቀና ብሎ በሪሁንን አየና ስቅስቅ ብሎ
ያለቅስ ጀመር። ሃሊማ የበሪሁንን አንገት አቅፋ፣

‹‹ሞተ፣ አሊሃሽ ሞተ!›› አለች ።

‹‹የት ነው የሞተው!›› አለ አስግድ አይኖቹን ወደ አኔቦ አፍጦ።

‹‹ከተማ ዉስጥ ተኩሳ ጊዜ በምቢ መታ። ኢኛ ጠላቱ ላይ ዲንጋት
ደራሳና አደጋ ጠላ፣ ጠላት ሸሻ፣ እኛ አባራራ፣ ኢንዳጋት ሌላ ጠላት

ማጣና ብዙ ተኩሳና ቢዙ ሰው ገደላ ሆላ አሊአሺና ሁለት ሳው እኛ ጋ ሞተ ››

‹‹ብዙ የጠላት ጦር ከቦን መውጫ አጥተን ነበር፣ በአኔቦ ብርታትና ትግል ነው ሌሎቻችን የተረፍ ነው፡፡ ያን በሽሽት ላይ የነበረ ጦር ምናልባት እናንተም አግኝታችሁት ይሆናል›› አለች ሃሊማ አይኖችዋን እየጠረገች፡፡

‹‹አዎ ፣ እኛ ገጥመነው የነበረ ጦር ነው፡፡ እጅግ ብዙ ነው፣ እኛም ገድለንና አቃጥለን ልንጨርሰው ስለአልቻልን ትተነው መጣን፡፡ ሲነጋጋ ወደ ሌላ ግዳጅ እንሰማራ ይሆናል፤ ትንሽ አረፍ ብላችሁ እህል ቃማምሱ›› አለ በሪሁን የሃሊማን ትከሻ መታ መታ እያረገ፡፡

በሪሁን ጉዋደኞቹ ሃዘን እንዳይከብዳቸውና ተስፋ እንደይቆርጡ ክስተር፣ ፈገግ ይበል እንጂ፣ ውስጡ እጅግ አዝንዋል። አሊሃሽን የመሰለ ብልህ፣ ቆራጥና ታማኝ ጉዋደኛ ማጣት፣ ሃሚድን ከመሰለ ጀግና፣ ደፋርና ሃገር ወዳድ መለየት ቀላል ጉዳት አይደለም፡፡ በጭንቅ ጊዜ ታማኝ ጉዋደኛ፣ ለአንድ አላማ አብሮ የቆመ ጉዋደኛ ሲሞት እጅግ ያሳዝናል፤ ያስደነግጣልም፡፡ የተስፋ መቁረጥ ስሜትም ያመጣል፡፡ በርይሁን እነዚህን ስሜቶች ውስጡ ቀበራቸው፣ ዋጣቸው፡፡ እነዚህ ስሜቶች ለቆራጥ አላማ መሰናክሎች መሆናቸውን አውቆ በሌሎቹ ጉዋደኞቹ ዘንድ እንዳይኖሩ ተከላከለ፡፡ የደፈጣ ተዋጊው ቡድን በጦርነቱ ብዙ አባሎቹን አጥትዋል፡፡ ሃሚድ ጣሂርንና አሊሃሽን የመሰሉ መሪዎች በዚያ ወቅት ማጣቱ ግን ከሁሉም በላይ ጎዳው፡፡ የመሪነቱ ሃላፊነት ተጠቃሎ በሱ፣ በአሰግድና በአኔቦ ጫንቃ ላይ ወደቀ፡፡

ከሰዓታት እረፍት በሁዋላ፣ ሲነጋጋ የተረፈው የደፈጣ ተዋጊ ጦር

ተሰባሰበ። ከቆሰሉት ውስጥ ሊዋጋ የሚችለው ከተመረጠና፣ የተጉዋደለውም ትጥቅ በመጠኑ ከተሙዋላ በሁዋላ በሪሁን ብድግ ብሎ፣

‹‹ወንድሞቼ፣ ከአብሪተኛው ወራሪ ጦር ጋር በስውርና በግልጽ ስንዋጋ እዚህ ደርሰናል። በዚህ ከባድና አስቸጋሪ ትንንቅ ወቅት በጠላት ላይ ያደረስነው ጉዳት በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ነፃ አውጪው ጦራችን ከግንባር ጠላትን ሲያርበደብድ፣ እኛ ደሞ ለጠላት የጉያ ውጋት ሆነን ፋታ ስንነሳው ቆይተናል። በዚህ የትግል ወቅት በርከት ያሉ ወንድሞቻችን መስዋዕት ሆነዋል። የነሱ መስዋእትነት ለትክክለኛ አላማ ስለሆነ የሚያኮራ ሞት ነው። የወደቁት ሃገርንና አብዮትን ሲከላከሉ ስለሆነ፣ በታሪክ ይኖራሉ። የነሱን አርማ አንስተን ከዚህ ቀደም ስናረግ እንደቆየነው፣ የውርደት ማቅ ለብሶ የሚሸሸውን የጠላት ጦር እየተከታተልን መምታት አለብን። ነፃ አውጪው ጦራችን ስሞኑን፣ እዚህ ይደርሳል ብለን ስለ ምንጠብቅ፣ ከሱ ጋር ሆነን ጠላትን እንደ ግመል መንጋ እንነዳዋለን። እስከዚያ የጠላትን ሽሽት ለማዘግየት የተቻለንን ሁሉ እናረጋለን›› እያለ ሲናገር ለዙሪያ ጥበቃ ዘብ ከቆሙት ሰዎች አንዱ እየሮጠ መጣ።

‹‹ምነው?›› አለ በሪሁን ዞር ብሎ።

‹‹ብዙ ተሽከርካሪዎች በመምጣት ላይ ናቸው፣ አቡዋራ ይታየኛል››

ቡድኑ በፍጥነት ሁለት ላይ ተከፍሎ፣ አንዱን ቡድን አኔቦ እየመራ በሌላ አቅዋራጭ እንዲቀድም ሲደረግ፣ በሪሁንና አስግድ ደሞ ሌላውን ቡድን ይዘው በገዞ ላይ ወዳለው የጠላት ጦር ገሰገሱ።

ጸሃይ ወደ መሬት የቀረበች ይመስል፣ ገና በማለዳ ሙቀቱ መድረሻ

ያሳጣል፡፡ ሌሊቱን ሲቦርቅ ያደረው ንፋስ ጸጥ ብሎ ፍጡር ሁሉ የሚተነፍሰው አየር ፍለጋ ይቃትታል፡፡ በሪሁን የሚመራው አደጋ ጣይ ቡድን በመለስተኛ ሩጫ ገስገሰና ባለፈው ሌሊት እንዳረገው፣ የሚሸሸውን ጦር ለመምታት ተዘጋጀ፡፡

ከሁዋላ የሚከተለውን ሞት የሚሸሸው የጠላት ጦር፣ በካሚዮኖች፣ በብረት ለበስ ተሽከርካሪዎችና ታንኮች ተጭኖ መጣ፡፡ አደጋ ጣዩ ቡድን፣ የጠላት ጦር በተጠበቀበት ክልል ሲገባለት ተኩስ ከፈተ፡፡ እሳት የሚተፉ ላውንቸሮች እየበረሩ ካሚዮኖቹን እንደሳር ጉጆ አጋዮዋቸው፣ ብረት ለበስ ተሽከርካሪዎች እንደ ጡዋፍ ነደዱ፣ ታንኮች የሃዲዳቸው ሰንሰለት እየበጠሰ ተገትረው ይጋዮ ጀመር፡፡ ከዚያ ተርፎ ወደ ፊት የሚሸሸውን እነ አኔቦ ያስቀሩታል፡፡ የጠላት ጦር፣ ያለ ሃይሉን በማሰባሰብ የሞት ሽረቱን ይከላከል ጀመር፡፡ አንድ ጊዜ አደጋ ጣዩ ቡድን ሲያጠቃና ሲገፋ፣ በሌላ ጊዜ ደሞ የጠላት ጦር ሲገፋና ሲያጠቃ ቆዩ፡፡

አኔቦ ወደ በሪሁን ሰው ልኮ፣

‹‹ሃይላችንን በአንድ አጠናክረን ብናጠቃና ብንከለከል ይሻላል፣ የጠላት ሃይል እያየለ መጥትዋል›› አለ፡፡

በዚሁ መሰረት ሁለቱ ቡድኖች ተቀላቅለው፣ የጠላትን ጦር ያዋክቡት ጀመር፡፡ የጠላት ጦር አይሎ አውራ ጎዳናውን ሲቆጣጠር፣ ከአደጋ የተረፉ ወታደሮቹንና ጥቂት ተሽከርካሪዎችን ያሳልፋል፡፡ አደጋ ጣዩ ቡድን ሲያይልበት ደሞ፣ ወደ መከላከሉ ይመለሳል፡፡

በሪሁን ጥቂት ሰዎች ይዞ በጎን በማሳበር ወደ ፊት በመጠጋት አላራምድ ብሎ ያስቸገራቸውን የጠላት ላውንቸር ተኩዋሽ ከገደለ በሁዋላ፣ ቁጥቁዋጦውን እየጣሰና መትረየሱን እያንተከተከ

ወደሚገሰግሰው ታንክ ሲሮጥ፣ አንዳች ብልጭታ በራበትና ወደቀ፡፡ ከላይ የሚዘንበው አፈር ግማሽ ሰውነቱን ቀበረው፣ በዙሪያው የሚያየው ነገር ሁሉ በራሱ የሚሮጥ መሰው፡፡ ግራና ቀኝ ክንዱን ተይዞ ሲጎትቱት፣ የተኮረኮረ ይመስል ይስቅ ነበር፡፡

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት

‹‹አሰግድ ፣ አሰግድ›› አለ በሪሁን ድክመው ባለ ድምጽ:: በጉደኖቹ ሽክም ከጦርነቱ አካባቢ ራቅ ወዳለ ስፍራ ከተወሰደ አንድ ሰአት በሁዋላ ገና ድምጹን ማስመቱ ነው:: እነ ሰግድ አንደበቱ ለአንድ ሰአት ያህል አንደበቱ በሞት ተለጉሞ የነበረ ዋደኞቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ድምጹን በማስማቱ፣ ተያዩና ፈገግ አሉ:: አሰብድ ካንገቱ ቀና አረገው::

‹‹እኔን ከሞት ለማትረፍ አትድከሙ፣ ኔ ነገር አብቅትዋል:: ሂዱ፣ በድል አድራጊነት ከሚመጣው ሰራዊታችን ጋር ሆናችሁ የመጨረሻው የጠላት ወታደር ከድንበራችን እስኪወጣ ድረስ ለማባረር ተዘጋጁ:: እኔ ለዚህ አልታደልኩም...›› አለና ትንፋሽ ስለአጠረው ዝም አለ::አሰግድ ከንፈሩን ነከሰ፣ እንባው እንደዝናብ ወረደ::

በሪሁን በሣምባው ሙሉ አየር ሣበና፣

‹‹ አሰግድ...ምናልባት፣ ምናልባት እህ..፤ ለምለምንና ልጆቼን በሕይወት ካገኘሃቸው አደራ በምትችለው ሁሉ ተንከባከባቸው:: እህ. . .በአለም ካሉ አሣዛኝ ፍጡራን ሁሉ አንጄቱን የሚበሉት፣ የምትወደውን ባል ያጣች ሴትና፣ አባት የሌለቸው ልጆች ናቸው:: እህ. . .ከማንኛውሰው ይልቅ አጽናኝና ረዳት ይፈልጋሉ:: አይዞዋችሁ በላቸው::. . . እህ በሪሁን የሞተው እናንተ በነጻነት ጃንጥላ ስር ሆናችሁ እኩልነትና ሰላም የሰፈነበት ሕይወት እንድትኖሩ ነው በላቸው:: በሪሁን የሞተው የጭቁኖች መድህን የሆነውን አብዮት

ከቅልበሣ ሲያድን፣ አገሩን ከወራሪዎች ሲከለከል ነው። እናንተም ለብሄራዊ አንድነታችንና ለጭቁኖች አሸናፊነት ታገሉ ብልዋል በሳቸው።

"በተለይ ለለምለም እነዲህ በላት፣ ባሌ ሞትዋል ብለሽ አትዘኚ፣ የጀግና ሚስት በመሆንሽ ኩሪ እንጂ። የጀግና ሚስት እንደሆንሽ ሁሉ የጀግኖች እናት እንድትሆኚ ልጆችሽን በስርዓት አሣድጊያቸው። የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ለችግር አጋልጦ እንደ ማይተዋችሁ እርግጠኛ ነኝ በላት። . . . .እህ . . .ለልጆቼም ንገራቸው። በየጊዜው ንገራቸው። . . . አባታችን ሞተ ብላችሁ አትዘኑ። የጀግና ልጆች በመሆናችሁ ኩራት ይሰማችሁ። ለናት ሐገራችሁና ለአብዮታችሁ ጠቃሚ ዜጎች ሁኑ... ብልዋል እያልክ ንገራቸው። ሰው ጥቃትን አሜን ብሎ ከኖረ፣ ነጻነቱን ይሸጣል ባላቸው... ›› አለና ዝም አለ።የሐሊማ እንባ እንደጐርፍ ይመርዳል፣ አኔቦ አይኖቹን ቡዝዝ አርጎ ይተክዛል።

ለስለስ ያለ ንፋስ ሽው ማለት ጀምርዋል። ሐሩሩ እንደ ወትሮው አያስጨንቅም። የደገሐቡር ነዋሪዎች በመሸሽ ላይ ያለው የጠላት ጦር በተስፋ መቁረጥ የሚያደርስባቸውን ገሃድ ጭፍጨፋ በመፍራት ቤቶጫቸውን እየዘጉ ከተሰወሩበት አልወጡም። በርግጥም የተወረረች ሆናለች፣ ከተማይቱ። ጠላት ጥልዋት የሸሸ፣ የወገን ጦር ያልገባበት ባዶ ከተማ። እነ አሰግድ የጠላት ጦር ከከባቢው ጥርግርግ ብሎ መፈርጠጡን ካረጋገጡ በኂላ በሪሁንን ወደ ከተማው ዳር አስጠግተው በሚችሉት ሁሉ የሕክምና እርዳታ ሊያረጉለት በመጣር ላይ ናቸው። የበሪሁን ቁስል ግን እንከዋን በነሱ፣ በከፍተኛ ህክምናም የሚድን አይመስልም። ደከመባቸው፣ መናገር አቃተው።

በሁለተኛው ቀን፣ በርይሁን እተኛበት በረንዳ ላይ ሰብሰብ ብለው

ማረግ ስለሚገባቸው ነገር ሲመካከሩ፣ ሐሊማ ድንገት ብድግ አለች። ሁሉም ወደስዋ አፈጠጡ። አፍዋን በከፊል ከፍታ አሩቅ ስትመለከት ቆየችና፣ እጆችዋን እያረገበገበች እልልታዋን አቀለጠችው። አስግድ ፣ ቢዬሌው አብደላና አኔቦ ብድግ ብለው የሐሊማ አይኖች ወደ አፈጠጡበት አቅጣጫ ተመለከቱ። የኢትዮጵያ ሰንደቅ አላማና ቀይ ባንዲራ ከግራና ከቀኝ የምታውለበልብ ብረት ለበስ ተሽከርካሪ መሐል መንገዱን ይዛ ወደነሱ ትሽከረከራለች፣ ታንኮች በተሰባጠረ ሰልፍ አጅበዋታል። አግሬቭ ወታደሮች የብረት ቆቦቻቸውን ደፍተውና ጠመንጃዎቻቸውን ደግነው ታንኮቹ በሚያነሱት የአብዋራ ጭጋግ ውስጥ ያሰመስማሉ። ጦሩ እየቀረበ ሲመጣ፣ የሐሊማ እልልታም ይጎላ ጀመር። አስግድና አኔቦ ግራ እጆቻቸውን ጨብጠው ወደ ላይ በማንሣት ‹‹አሸንፈናል! ድል አርገናል !›› የሚል ምልክት ያሣያሉ።

ብረት ለበስዋ መኪና ፍጥነትዋን እየቀነሰች መጣችና እነሱ ከነበሩበት አሥር እርምጃ ያህል ሲቀራት ቆመች። ከፊት የተቀመጠ አንድ ሰው እጁን በድግ አርጎ እያወዛወዘ በሩቅ ሰላምታ ሰጣቸው። ሐሊማ ‹‹እልልል››እያለች ወደሰውየው ሮጠች አኔቦና አብደላ ተከተሉዋት። ሰውዬው ከመኪናይቱ ወርዶ የብረት ቆቡን ያዘና ቆመ። ሃሊማ እንደሮጠች ሄዳ አንገቱ ላይ ተጠመጠመች፣ አኔቦ በተጠንቀቅ ቆሞ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጠው።

በሪሁን ድንገት ዐይኖቹን ከፍቶ ካንገቱ ቀና ለማለት እየሞከረ ሲያቅተው ስግድ አየ። በርከክ ብሎ፦

‹‹ሰራዊታችን መጣ!›› አለ በሹክሹክታ።

‹‹እህ፣ ቀ-ቀና አርገኝ ልየው... ›› ቀስ ብሎ ቀና አረገው።

‹‹አ-አል-አልሞትኩም... ሰንደቅ አላማዬን አየሁ...አ-የሁ-.አ-የ-

ሁ›› አለና ዝም አለ።

ከመኪናዎች የወረዱት አዛዦችና ወታሮች ከነ ሐሊማ ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ወደነ አሰግድ መጡ። አኤቦ ረዘም ላለው የጦር አዛዥ ስለ ማንነታቸው ነገረው። አሰግድ ብድግ ብሎ ተገቢውን ወታደራዊ ሰላምታ ሰጣቸው።

‹‹ሃ ጋ!፣ ሃ ጋ (ይሄ ነው ይሄው)›› አለች ሐሊማ በሪሁን ወደ ተኛበት እያመለከተች። በሪሁን በጀርባው እንደተኛ ጥርሶቹ ፈልቀቅ ብለውና፣ አይኖቹ ገርበብ ብለው በህልም አለም የሚስቅ ይመስላል።

አዛዡ መኮንን በርከክ ብሎ፣ የበርይሁንን የእጅና የአንገት ደም ስሮች ጨባበጣቸው፣ ዐይኖቹንም እየገለጠ አያቸውና በብርድ ልበስ ሸፈን አርግዋቸው ተነሳና፣ ከበታች መኮንኖቹ አንዱን ጠርቶ፣

‹‹እዚሁ እንዲቀበር አርግ›› ብሎ ትእዛዝ ሰጠ። ሐሊማ ጬኸትዋን በመዳፍዋ አፈነችው። እንባዋ ግን እንደ ጐርፍ ወረደ።

‹‹አንተም ቆስለሃል እንዴ?›› አለ አዛዡ ወደ አሰግድ ዞር ብሎ፣ ከአንገቱ ስር ብቅ ያለውን ነጭ ፋሻ እያየ።

‹‹አዎ ›› አለ በእንባ ጭጋግ የተጋረዱ ዐይኖቹን በሪሁን እሬሣ ላይ እንደተከለ።

‹‹ይሄ ወደ ሐረር ይወሰድና ይታከም!›› አለ አዛዡ የአሰግድን ትከሻ መታ መታ እያረገ ። ወደ አኤቦ ዞር አለና ደሞ፣

‹‹ አንተ ወደ እናት ክፍልህ እስከትላክ እዚህ ከሚቆየው ጦር ጋር ትሆናለህ። አንቺ ደሞ የኔ እህት" አለ ሀሊማን እያየ፣ "አንቺ ደሞ፣ ከጦራችን ጋር ወግነው ላገራቸው ነጻነት ዋጋ ከከፈሉ ሰዎች ጋር ተገቢውን ነገር መንግስት ያረግልሻል..." እያለ ሲናገር ሰግድ ጣልቃ ገባና፣

‹‹እኔ ከናንተ ጋር ወደፊት ሄዳለሁ ›› አለ ጥርሱን ነክሶ ከሣግ ጋር እየታገለ፡፡

‹‹የሕክምና እርዳታና እረፍት ስለሚስፈልግህ ወደኋላ ተመልሰህ መታከም አለብህ ›› አለ መኮንኑ በትእዛዝ አነጋገር፡፡

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

አስግድ ከኢተየጵያ ሰራዊት ጋር ወደ ፊት ለመሄድ ያረገው ልመና ስላልተሳካለት በሪሁንን ቀብሮ ወደ ሐረር ሄደ።

ሐረር የሚገኘው የፖሊስ ሆስፒታል እንደ ሌሎቹ ሆስፒበሎች በጦር ሜዳ ቁስለኞች ብዛት ተጨንቅዋል። መደበኛ ክፍሎች፣ በረንዳዎችና መተለለፊያዎች ሁሉ ሞልተው ቦታ አልበቃ ስለአለ፣ ድንኩዋንኖች ተተክለዋል።

ሆስፒታል ተኝቶ ምርመራ ተደረገለትና ትከሻው ውስጥ ጥይት ስለአለ፣ ቀዶ ጥገና እንደ ሚደረግለት ተነገረው። ሆስፒታል በገባ በማግስቱ የበሽተኛ ቢጃማውን ለብሶ፣ ግቢው ውስጥ ሲዘዋወር አረፈደ። ከሱ ቀደም ብለው እሆስፒታሉ ውስጥ ከነበሩት ቁስለኞች መካከልም ሆነ ከሆስፒታሉ ሰራተኞች የሚያውቀው አንድም ሰው አልነበረም።

ከምሣ በሁዋላ ድንኩዋናቸው አጠገብ ሰብሰብ ብለው ወደ ተቀመጡ ቁስለኞች ጠጋ ብሎ ቁጭ አለ። ብዙዎቹ ኦጋዴን ውስጥ በተደረገው ጦርነት ተካፍለው የቆሰሉ ስለሆኑ፣ ወሬያቸው ስለጦርነቱ ነበር።

አስግድ፣ ሰዎቹ ኦጋዴን የነበረው የፖሊስ ፈጥኖ ደራሽ ሃይል አባላት የነበሩ መሆናቸውን ከውይይታቸው ስለተረዳ ፣ ቀደም ብለው የጀመሩት ሞቅ ያለ ውይይደት ጋብ ሲል ጉሮሮውን ሣለና፡-

‹‹ጉዋዶች ከናንተ ውስጥ በሪሁንን የሚያውቀው ሰው አለ?››

አለ።

‹‹በሪሁን፣ በሪሁን?›› አለ ግራ እግሩ ከታፋው ጀምሮ በደረቀ ኖራ (ጄሶ) የተጠገነ ቁስለኛ።

‹‹በሪሁን በጋሻው። ቀደም ሲል ደገቡር፣ በሁዋላ ደሞ ቀብሪደሃር የነበረው ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አባል›› አለ ቁስለሃቹን በየተራ እያየ።

‹‹ኦ በሪሁን ሼኮሽ የነበረው? የመቼህን እሱ እዚያ ከነበሩት አባሎች ጋር ተደምስዋል››አለ ምርኩዝ የተደገፈ አንድ በሽተኛ።

‹‹ቤተሰቡን፣ ሚስቱን ፣ ለምለምን ታውቃታለህ?›› አለ በጉግት እያየው።

‹‹እኔ እንኩዋን በቅርብ አላውቀቻውም። የኔም የበሪሁንም ጉዋደኛ የሆነ ሰው ነው ስለ ሁኔታው ያጫወተኝ ››

‹‹ምን አለህ? ደህና ናቸው? የትናቸው አለህ?›› አለ ሰውዬውን በሁለት እጆቹ ይዞ።

‹የሻሬ ሰባት ወራት ገደማ ቀብሪደሐር ከተማ በጠላት ስትያዝ፣ ከህዝቡ ጋር በመሸሽ ከብዙ ስቃይና መከራ በሁዋላ ሐረር ገቡ። ትንሹ ልጅዋ ረሃብና ውሀ ጥሙን ስለአልቻለው መንገድ ላየ ሞተባት ብሎ ነገረኝ"

‹‹ለምለም እዚሁ ሐረር ነው ያለችው አለህ?››

‹‹አይደለችም ወዲያውኑ ዘመዶችዋ ዘንድ አደስ አበባ ላክናት። በባልዋና በልጅዋ ሞት በጣም አዝናለች፣ ሰውም አትሆን ብሎ ነገረኝ››

ሌሎቹ ቁስለኞች በውይይቱ መሀል እየገቡ፣ በበርይሁን ቤተሰብና በብዙ ሺህ ሰዎች ላይ የደረሰውን ችግር እያነሱ ሲወያዩ ቆዩ።

‹‹በጊዜ አካባቢውን ልቀቂና ሂጂ እያልን ስንለምናት እምቢ ብላ በበረሃ ተንከራተች። በሪሁን እንደኔ ተርፎ በህይወት ብታየው ኖሮ

ምንኛ ደስ ባላት? ምናለበት እንደ ሂሩትዬ እድለኛ ብትሆን? ሂሩት የኔን በህይወት መኖር ሰምታ ስትደሰት፣ ለምለም ደሞ እንደስዋ እድለኛ ባለመሆንዋ ስታለቅስ ማየት እጅግ ያሣዝናል። ሂሩትዬስ የኔን በህይወት መኖር ዜና ስትሰማ እንዴት ትሆን ይሆን? መቼም ድንገተኛ ደስታ እንደ እብድ ነው የሚያረጋት። ከነቃል ኪዳናችን ብትኖር አይደል፣ ማን ያውቃል? ሞተ ተብሎ ሲነገራት፣እንደ ማንኛውም የሙት ቀለበት ቀለበቴን ቶሎ አውልቃ ሌላ ተክታበት እንደሆነስ?...ብቻ በህወት ትኑር » እያለ ሲያሰላስል ቆየ።

ከዚያም ከበሽተኞቹ በመለየት ወረቀትና ፖስታ አስገዝቶ ለሂሩት ደብዳቤ ይጽፍ ጀመር፣

«ሂሩትዬ እንደምን አለሽልኝ። ይህ ደብዳቤ ሲደርስሽ ምን ተሰማሽ? ድንጋጤ? ደስታ? ወይስ ሃዘን?። አዎ እነዚህ ሁሉ ይፍራረቁብሽ ይሆናሉ። ህይወት የብዙ ድርጊቶች መፈራረቂያ ናት። ሂሩትዬ ምናልባት ከዚህ ቀደም አሰግድ ሞትዋል ብለሽ እርምሽን አውጥተሽ ይሆናል። በእርግጥም ከሞት ጋር ሰንበቼ ነው የመጣሁት። ሲታገለኝ ስታገለው፣ ሲጥለኝ ስጥለው፣ እዚህ ደርሻለሁ። ‹እንዴት› የሚለውን ወደ ፊት ስንገናኝ በሰፊው አወራልሻለሁ። ለዚህ በመብቃቴ ደስ ይበልሽ። አሁን ያለሁት ሐረር ከተማ በሚገኘው ፖሊስ ሆስፒታል ውስጥ ነው።ትከሻዬ ላይ ትንሽ ቆስዬ ስለነበርና ጥይተዋም ስጋዬ ውስጥ ቀርታ ስለነበር እናወጣልሃለን ተኛ ብለውኝ ነው ሆስፒታል የገባሁት። እኔ እኮዋን አንድ ጊዜ አንቺንና ለምለምን ላያችሁ ጉዋጉቼ ነበር።

"አሁንም ቢሆን ቁስሉ በጣም ቀላል ለስለሆነ ቀዶ ጥገናው ከተደረገልኝ በሁዋላ ሮጥ ብዬ አያችሁዋለሁ። ካልሆነ ግን ወደ ጦር

ግንባር መመለሴ ነው። እየሽ ሂሩትዬ አንቺ እራስሽ አዘውትረሽ እንደምትናገሪው ያለ ሃገርና ያለ ነጻነት ፍቅርም ሆነ ትዳር ሊኖር አይችልም። ቀዳሚው ነገር አገርን ከወራሪ፣ አበዮትን ከቅልበሣ በማዳኑ ነው። ብቻ ይህ ደብዳቤ እንደ ደረሰሽ ባስቸከይ ጻፊልኝ። ምንም ቢሆን መጣለሁ ብለሽ እንዳትሞከሪ። ያለሽበት የመሀል አገር ትግል ቀላል እንዳልሆነ አውቃለሁ።

በስልክ ሳገኝሽ የምችልበትን አድረሻ ብትገልጭልኝ ደውልልሻለሁ። አንቺም ከቻልሽ ሐረር ፖሊስ ሆስፒታል ደውይልኝ።

"ሂሩትዬ እስከ አሁን ‹‹እኔ›› እያልኩ ስጽፍልሽ አንድ ነገር ሣይሰማሽ አልቀረም። ‹በሪሁንስ ምን ሆነ?› ብለሽ ትጠይቂ ይሆናል። በሪሁን ሞትዋል። እናንተ እንደተረዳችሁት ከዛሬ ሰባት ወራት በፊት አደለም የሞተው። ብዙ ጀብድ ሰርቶ፣ ለጠላቶቹ የጎን ውጋት ሆኖ ፣ በወረሩት ሀገር ተደላድለው እንዳይኖሩ ፣ የሰላም እንቅልፍ እንደይተኙ አርጎ ነው። እንኩዋን የወገን፣ የጠላትም ታሪክ የማይረሣው ጀግንነት ፈጽሞ ወድቅዋል።ከሁለት ቀናት በፊት ደገሐቡር የተቀበረ። የበርይሁን ሞት የኛ ህይወት ነው፣ ለነጻነት ና ለአብዮታችን ህልውና የተከፈለ መስዋእት። አቃለሁ ሂሩትዬ፣ ለምለም በምትወደው ባልዋ መሞት በጣም ታዝናለች። በተለይ እርግጠኛ ሞቱን ስትሰማ። አንዳንቺ እድለኛ ሆና የምትወደውን ባልዋን፣ የልጆችዋን አባት ብታገኘው እንዴት ደስ ባላት? ምን ያረጋል የህይወት እድልዎኛ ናት። ብቻ አጽናኛት፣ ባለን አቅም ሁሉ ልንረዳት ይገባል።

በዚህ ዳብዳቤዬ ብዙ ልጽፍልሽ አልቻልኩም፣ ደብዳቤሽን ወይም የስልክ ጥሪሽን በጉጉት ጠባበቃለሁ።. . ያንቺው አስግድ አለሙ››

# ምዕራፍ ሠላሳ

አሰግድ ከቀዶ ጥገናው በሁዋላ ተሽሎት አልጋው ላይ ጋደም ብልዋል። የሆስፒታል ጉዋደኞቹ አጠገቡ ተቀምጠው ያጫውቱታል።

‹‹ቀና በልና አጫውተን ይህቺ ቀዶ ህክምና ሆነችና ነው የምትተኛላት? እሾህ የወጣልህ ያህል ቁጠራት። እኛ ቂራ እንደገባ ፍሪዳ ተተልትለን እንዳንተ አልተዳከምንም። ቀናበል" አለ ሰለሞን የተባለ ቁስለኛ የአሰግድን ጀርባ መታ መታ እያረገ። አሰግድ ጋደም ያለው፣ በሽታው ጸንቶበት ሣይሆን፣ ከአስር ቀን በፊት ለሂሩት ለጻፈላት ደብዳቤ መልስ ባለማግኘቱ፣ የይሆን ይሆናል ግምቶጭ እየደረደረ ያሰለስል ስለነበር ነው። ጉዋደኞቹ ሊያጫውቱት መጥተው ዝም ማለቱ ተገቢ አለመሆኑን በመረዳት ቁጭ አለና፡-

‹‹ይቅርታ፣ ትንሽ ደክሞኛ ነው። ፈይሣ ድኖ ወጣ አላችሁ?›› አለ አይኖቹን እያሻሸ። ያንለት ከሆስፒታል የወጣውን ቁስለኛ ጉዋደኛውን አስታውሶ።

‹‹አው ወጣ፣ ከህክምና መሰናበቱ ሣይሆን፣ ወደማገገሚያ ነው የተዛወረው ››አለ ሌላው ቁስለኛ።

‹‹ብዙ ቆይትዋል እንዴ ሆስፒታል ውስጥ?››

‹‹አ-ዎ፣ መጀመሪያ የአጋዴን ፖለስ ቢያዎች መጠቃት ሲጀምሩ ነው ሰገግ ላይ የቆሳለው። ቀደም ብሎ እንደውም ከወገቡ በታች አይንቀሳቀስም ነበር። አሁን ግን በምርኩዝ እየተረዳ ይራመዳል››

‹‹እንደ ሌሎቹ የጠረፍ ጠባቂ ጦር አባሎች የመጀመሪያው

የጦርነት ገፈት ቀማሽ ነዋ። በኦጋዴን የድንበር ጣቢያዎች ባነስተኛ መጠንና ትጥቅ ተበታትነው፣ እስከ አፍንጫው ታጥቆ ከመጣ ኃይል ጋር ሲተናነቁ የወደቁ ጀግኖች ምንጊዜም ከህሊናዬ አይጠፉም። በኢሚ፣ በደናን፣ በፌርፌር፣ በኤልቆረን፣ በበቆርቆርዮን፣ በሰረረወይን፣ በዱዱብ ፣ በምሥራቅ ጋሻሞ በገላዲን፣ በአዋሬ፣ በኢነጎሃ፣ በደበጎሬያሌ፣ በድሁን፣ በተፈሪ በር፣ በቶጎ ው ጫሌ፣ በሽላቦ ፣ በሺኮሽና በሌሎቹም ካቢያዎች የነበሩ የፈጥኖ ደረሽ ፖሊስ አባላት፣ ጉዶ የነበረው ሰጋው የሚሊሺያ ጦራችንና ሌሎችም፣ የፈጸሙት ጀግንነት የሚረሣ አይደለም›› አለ አሰግድ ኦጋዴን ውስጥ የነበረው የጦርነት ሁኔታ ለአንድ አፍታ በሃሣቡ ብልጭ ብሎበት።

‹‹የጠቀስካቸው ጣቢያዎች ሁሉ ሰሞኑን በወገን ጦር በመያዝ ላይ ናቸው። ጀግኖች አባቶቻችን በደምና አጽማቸው ያጸኑት ድንበር ተከብርዋል...›› እያለ ኪዳኔ ሲናገር፣

‹‹አሰግድ አለሙ! አሰግድ አለሙ!›› የሚል ድምጽ ተሰማ። አንደኛው ቁስለኛ ብድግ ብሎ፣ ‹‹እዚህ ነው ያለው!›› እያለ ከድንኩዋን ወጣና፣ ፖስታ ይዞ፣

‹‹አሰግድ፣ እጮኛህ ጻፈችልህ! እንኩዋን ደስ አለህ! ምን ታረግልኛለህ?...››እያለ ተመለሰ። አሰግድ ቆሞ አይኖቹን ፖስታው ላይ አፈጠጠ።

‹‹ምን ታረግልኛለህ?" አለ ፖስታውን ወደ ሁዋላው እየሸሸገ።

‹‹የፈለግከውን፣ የፈለግከውን አረግልሀለሁ›› አለ አሰግድ ሁለት እጆቹን በልመና እካሁዋን ዘርግቶ። የልቡ ምት ፈጠነ፣ አሳበው።

ፖስታውን ተቀብሎ ወደደረቱ አስጠጋና፣

"ለብቻዬ ላንብበው፣ ባካችሁ ከዚህ ሂዱልኝ..." አለ አጠገቡ

ያሉትን በዐይኖቹ እየተለማመጠ፡፡ እጆቹ ተንቀጠቀጡ፡፡ የፖስታውን ጠርዝ ተከትሎ በትክክል ለመቅደድ የወሰደበት ጊዜ አመት መሰለው፡፡ ሂሩት ከፖስታው ውስጥ ብቅ የምትልለት ይመስል ጓጓ፡፡

‹‹ውድ ወንድሜ አሰግድ አለሙ...›› ብሎ ነው ደብዳቤው የሚጀምረው፡፡ የልቡ ምት እንደገና ፈጠነ፡፡ ፖስታውን ገልበጥ አርጎ የላኪውን ስም ተመለከተ፣ ከ"ለምለም ጋሻው" ይላል፡፡ ዐይኖቹ ላይ ሽረሪት ያደራባቸው ይመስል አጥርቶ ማየት አቃተው፣ ትንፍሹ አጠረ፣ ወረቀት የያዘበት መዳፉ ላብ ያመነጭ ጀመር፡፡

‹‹እንዴት ከሂሩት ቀድማ ለምለም ጻፈችልኝ? ሂሩት ለምን አልጻፈችልኝም?›› የሚሉትና ሌሎችም ጥያቄዎች እራሱ ውስጥ ተንጫጩበት፡፡ ምራቁን እየዋጠና ለመረጋጋት እየሞከረ ደብዳበእን እንደገና ገለጠው፣

‹‹ውድ ወንድሜ አሰግድ አለሙ፡፡ ከሁሉ አስቀድሜ እንኩዋን ከዚያ ሁሉ መአት ተረፍክ እልሀለሁ፡፡ የቀበሌያችን ፖስተኛ ለሂሩት የጻፍከውን ደብዳቤ አምጥቶ ‹ለእህትሽ የተጻፈ ነው› ብሎ ሰጠኝ፡፡ ገልበጥ አርጌ የላኪውን አድራሻ ስመለከት ደነገጥኩ፡፡ ነገሩ ህልም ይሁን እውን መለየቱ አቅቶኝ ነበር፡፡ ደብዳቤውን እስከ መጨረሻው ካነበብኩ በሁዋላ ተገረምኩ፡፡ ደስታና ሃዘን ተፈራረቁብኝ፡፡ ከሰባት ወራት በፊት የሞተ ዘመድ ከመቃብር አለም ሲመለስ ያስደነግጣል? ያስደስታል? አንተው ፍረድ፡፡

"በደብዳቤህ እንዳልከው ‹ተፈጥሮ አድልዎኛ ናት› የህይወት ባህርም ሁሉን እኩል አያንሳፍፍም፡፡ የገሚሱን ጀልባ ማእበል ሲያስጥመው፣ ገሚሱን ሲንጠው፣ ሌላውን ደሞ ጻጥ ብሎ ያንሳፍፈዋል፡፡ የዛሬ ሰባት ወር ገደማ፣ እናንተ የነበራችሁበት የሼኮሽ

ጢቢያ እንደተደመሰሰ፣ ከሌሎቹ አባሎች ጋር ሞተዋል ብለን እርማችንን አውጥተን ነበር። አሁን በደብዳቤህ እንደገለጽከው ደሞ ታሪኩ ሌላ ሆነ። ምንም እንኩዋን ተፈጥሮ አድልታብኝ ባሌን ለማግኘት እድለኛ ባልሆንም ፣ በሪሁን፣ የኔ በሪሁን፣ የኔ ጀግና፣ የበለጠ ጀብዱ ሰርቶ መሞቱን ስሰማ ደስታው ሀዘኔን ቀንሶታል። የተፈጥሮ እዳ ነው፣ ማንም በምንም ምክንያት ይሞታል። የኔ በርይሁን የሞተው ግን የነጻነት ዋጋ ሆኖ ነው።

"ትንሹን ልጃችንን ታጠቅን የአጋዴን በረሃ በላብኝ። ሃዘን አባሮኝ ስመጣ ሀዘን ድንኩዋን ውስጥ ገባሁ። አጽናኝ ስሻ፣ ሃዘን ከሰበራቸው ሰዎች ጋር ተቀላቀልኩ። ከላይ ልጅ የሞተባት እናትና ከታች አባቱን ያጣ ልጅ ይዞና የራስንም ባል በሞት ተነጥቆ ለመጽናናት ምን ያህል አዳጋች መሆኑን አስብ። አጽናኝስ ቢሆን ችግሩ የደረሰበትን ሰው ውስጣዊ ቁስል መች ይፈውሰዋል?። ለመጽናናት የሚቻለው በራስ ብርታት መሆኑን ተማርኩ። ቻልኩት። ተጽናናሁ። ዋናው መጽናኛዬ ጀግናው ባሌ እንደለው ‹ድላችን› ነው።

"ልጃችን፣ አለም በሪሁን፣ ከሌሎች የጀግኖች ልጆች ጋር ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ሲላክ ታጠቅ ጦር ሰፈር ገብትዋል። በማንኛውም ነገሩ አባቱን እንደሚመስል ከአወጣጡ ያስታውቃል።

"አሰግድዬ ተፈጥሮ አድልዎኛ የሆነችው በኔ ላይ ብቻ አይደለም። ሂሩት በህይወት ኖራ ይህን ደብዳቤህን ለማየት ብትታደል ኖሮ አጋጣሚው ምንኛ በሰመረ፣ግን አልሆነም። በቀበሌያችን ውስጥ በነበራት አብዩታዊ ተሣትፎ ምክንያት በጸረ አብዩተኞች ጥይት ወድቃ እኔ እዚህ ከመድረሴ አንድ ቀን ቀደም ብላ ተቀበረች። እና፣ እኔ ባሌን ለማግኘት እንዳልቻልኩ ሁሉ፣ አንተም አበባዋን ሂሩትን

አጥተሃታል፡፡ በአብዮቱና በአንተ ውስጥ አብባ ፍሬዋን ሣትሰጥ ከስማለች፡፡ ተጽናና፡፡ የማጽናናትህ እንደሌሉቱ ሆኜ ሣይሆን፣ ባሌን ፣ ልጄን ፣ እህቴን አጥቼ እንዳንተው እየተሰማኝ ነው፡፡ ተጽናና መፅናኛችን ‹ድላችን› ነው..." ይላል ደብዳቤው፡፡

የአሰግድ እንባ ፊቱ በተዘረጋው ደብዳቤ ላይ ዱብ ዱብ አለ፡፡ አይኖቹንና አፍንጫውን እየጠራገገ ደብዳቤውን ወደ ደረቱ ይዞ በዝምታ አነባ ፡

‹‹ተጽናና ! መጽናኛችን ድላችን ነው!›› የሚለው የለምለም ማጽናኛ በጆሮው አስተጋባ፡፡

በጠላት ጥይት የቆሰለ ጓደኛው "ግደለኝ፡- ጨርሰኝ..."
እያለ የሚያስቸግረው ሰው፡- ዙሪያው በጠላት ተከቦ ማምለጫ
መንገድ ያጣ ወታደር ምን ያደርጋል?

በጠላት መድፍ እተደበደበች ከተማ ውስጥ የነበሩት ቤተሰቦቹ
በህይወት መኖራቸውን፡- ካሉም የደረሱበትን የማያውቅ ሰው
ምን ያደርጋል?

በብዙ ኪሎ ሜትሮች እርቀት ላይ ካለው የወገን ጦር ጋር ለመገናኘት
ሳይችል ቀርቶ፡- ውሀ ጥሙና ርሀቡ እያሰቃየውና በጠላት እየታደነ
በረሀ ለበረሀ የሚንከራተት ወታደርስ?

ዋጋ ብር 41.00

እታሚ አፍሮ ማተሚያ ድርጅት ስልክ 0114-197446/47